# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 179 የካቲት 29 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## ልዩ እትም

በኢፕድ ሴት ጋዜጠኞች የተዘጋጀ

እንኳን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ113ኛ በሀገራችን ለ48ኛ ጊዜ

ለሚከበረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን አደረሳችሁ፡፡

## “ሴቶችን እናብቃ፤ ልማትና ሠላምን እናረጋግጥ”



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

# ቀይ መለዮ ለባሾቹ

# - የአየር መከታዎች

**አስቴር ኤልያስ**

**ዜና ሐተታ**

በኮማንዶና አየር ወለድ ዕዝ የአየር ወለድ ማሠልጠኛ ማዕከል ቅጥር ግቢ ውስጥ ተገኝተናል፡፡ በግቢው የተገኘነው ቀትር ላይ እንደመሆኑ አንድ ዓይነት የደንብ ልብስ የለበሱ አካላዊ ብቃታቸውና ጽናታቸው ፊታቸው ላይ የሚነበብ ቆፍጣና ኮማንዶዎች ለምሳ ወዲህ ወዲያ ሲሉ ይስተዋላሉ፡፡ አራት እንስት ኮማንዶዎች ደግሞ ለአንድ ዓይነት ተልዕኮ በሚመስል መልኩ ወደ አንድ አቅጣጫ ሊያቀኑ ከእግራቸው ፈጠን ሲሉ ይታያሉ፡፡ እኛም ከእርምጃቸው ገታ አድርገን እዛው በቆሙበት የሴቶች ቀንን ምክንያት በማድረግ ልንጠይቃቸው ወድደን፡፡

እነዚህ ፈጥኖ ደራሽ አየር ቀዛፊዎች፤ መቶ አለቃ አይዳ አላሮ፣ ሻምበል ትቅደም ወርቁ፣ ሻምበል ማዕረግነሽ መንግሥቱ እና ሻምበል የሩቅነሽ ጌታነህ ለጥያቄያችን ምላሽ ለመስጠት አላንገራገሩም፡፡ የእንኳን አደረሰን መልዕክታቸውን ያስቀደሙት አራቱ ኮማንዶዎች የመለዮ ፍቅር እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ ዋና ዓላማቸውም ሴትነት ሳያግዳቸው ሀገራቸውን በጽናት ማገልገል እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ቀይ መለዮ ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል



ፎቶ፡- ሃዲስ አብርሃ

ኮሚሽነር ብሌን ገብረመድህን

## በምክክሩ ሴቶችን ማሳተፍ ዘላቂ ሠላምና እኩልነት የሰፈነባት ሀገር ለመገንባት እንደሚያስችል ተገለጸ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሀገራዊ ምክክሩ ሴቶችን ማሳተፍ ዘላቂ ሠላምና እኩልነት የሰፈነባት ሀገር ለመገንባት እንደሚያስችል የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ብሌን ገብረመድህን ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር

በምክክሩ ሴቶችን ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል



ብርጋዲየር ጄኔራል ሁሉአገርሽ ድረስ

## የሴቶች ሀገራዊ ተሳትፎን በማረጋገጥ ሠላም ማስፈን ይገባል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የሴቶች ሀገራዊ ተሳትፎ እና እኩልነት በማረጋገጥ ዘላቂ ሰላም ማስፈን እንደሚገባ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የሴቶች ሀገራዊ ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል







# የኢነርጂና የአቪዬሽን አቅምን በብልሀት ስመጠቀም ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የኢነርጂና የአቪዬሽን እምቅ አቅምን በብልሀት ለመጠቀም የሚያስችል ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ እያደረገች መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሳምንታዊ መግለጫውን በትናንትናው ዕለት ሰጥቷል፡፡

መግለጫውን የሰጡት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ በቀጣናው በኢነርጂና በአቪዬሽን ዲፕሎማሲ መስክ ትብብርና ቀጣናዊ ትስስር እንዲኖር አበክራ እየሠራች ትገኛለች፡፡

የከርሰ ምድር፣ የፀሐይና የንፋስ ኃይል ለማመንጨት የሚያስችል እምቅ አቅም መኖሩን የጠቀሱት ቃል አቀባዩ፤ የህዳሴውን ግድብ ጨምሮ ከተለያዩ ወንዞች ኃይል በማመንጨት ከኢትዮጵያ አልፎ ለጎረቤት ሀገራት እንዲተርፉ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ ጋር በኢነርጂና በአቪዬሽን ዲፕሎማሲ መስክ ለመተባበር የሚያስችል አቅምና እምቅ ብቃት አላት ያሉት አምባሳደር መለስ፤ ይህን በሚገባ በብልሀትና በዘዴ ለመጠቀም የሚያስችል ዲፕሎማሲያዊ ሥራ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ጎረቤት ሀገሮች ያለባቸውን የኢነርጂ ውስንነት ለመፍታት የኢትዮጵያን ገበያ እንደሚፈልጉ ጠቅሰው፤ ይህን እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ ለመሥራት በመንግሥት በኩል ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ከኬንያ ጋር የ25 ዓመት የኤሌክትሪክ ግዥ ስምምነት በመፈራረም ወደ ሥራ ከተገባ መቆየቱን ያነሱት ቃል አቀባዩ፤ ከሌሎች ጎረቤት ሀገራት ጋር ሰፊ የኤሌክትሪክ ሽያጭ እንቅስቃሴ ሲደረግ መቆየቱን አንስተዋል፡፡

ከኬንያ ጋር ያለው የኤሌክትሪክ ትስስር ኢትዮጵያ ከሌሎች የምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ ሀገሮች ጋር ለሚኖራት የኢነርጂ ትስስር ትልቅ ትርጉም ያለው መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

እንደ አምባሳደር መለስ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በኢነርጂና አቪዬሽን ሰፊ አቅም አላት፡፡ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በኬንያና ታንዛኒያ ጉብኝት ያደረጉትም ጎረቤት ሀገራት ይህን አቅም እንዲጠቀሙና አካባቢያዊ ትስስር እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ወደ ሰሜን አፍሪካ የምትወስደው ኤሌክትሪክ ትስስር ሱዳን ደርሷል ያሉት ቃል አቀባዩ፤ በረጅም ጊዜ እቅድ እስከ እስፔን ሊሄድ የሚችል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሀገሪቱ ያላትን ሰፊና እምቅ የኢነርጂ አቅም በሚገባ መጠቀም መጀመሯን በመግለጽም፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በታንዛኒያ በነበራቸው ጉብኝት በግብርና፣ ኢነርጂ፣ አየር መንገድና በረራ ዙሪያ ስምምነቶችን ተፈርመዋል ብለዋል፡፡ ይህም የአቪየሽንና ኢነርጂ ዲፕሎማሲን የሚያጠናክር ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እንደ አምባሳደር መለስ ማብራሪያ፤ በቀጣይ ከታንዛኒያ ባሻገር እስከ ደቡብ አፍሪካ ሀገሮች ሁለት ሺህ ሜጋ ዋት ለመሸጥ እቅድ ተይዟል፡፡ ከታንዛኒያ ጋር 400 ኪሎ ቮልት በሽያጭ መልክ ለማቅረብ ከስምምነት ተደርሷል፡፡ ይህም ኢትዮጵያንና ታንዛኒያ በሁሉም መስክ ጠንካራ ትስስር እንዲፈጥሩ ያስችላል፡፡

በአቪየሽን በኩል ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር ተብብሮ መሥራት የሚፈልጉ ብዙ አየር መንገዶች አሉ ያሉት አምባሳደሩ፤ በአቪየሽን መስክ ከታንዛኒያ ጋር የቆየ ግንኙነት መኖሩን ጠቅሰዋል፡፡ ከሀገሪቷ እስካሁን 75 ፓይለቶችና 25 ቴክኒሻኖች በኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጠና መውሰዳቸውን ገልጸዋል፡፡

# ቀይ መለዮ ለባሾቹ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከአውሮፕላን ላይ በፓራሹት 37 ጊዜ ያለምንም እንከን የዘለለችው የአየር ወለድ ማሠልጠኛ የዲስፓቸር ባለሙያዋ መቶ አለቃ አይዳ አላሮ ይህን ታላቅ ወኔና ድፍረት ከአያቶቿና አባቶቿ እንደወሰደችው ትናገራለች፡፡ በልጅነቷ የተቀላቀለችው የሀገር መከላከያ ሠራዊት በውስጡ ያገኘችው የሀገር ፍቅር ስሜት እና ሙያው የሚያላብሰው ቁርጠኝነት ለ18 ዓመት በውትድርናው ዓለም እንድትቆይበት አድርጓታል፡፡

እርሷ እንደምትለው፤ ኢትዮጵያ ላይ ምንም አይነት ችግር እንዲመጣ አትሻም፡፡ የትኛውም የሚመጣ ችግር ቀድሞ ሊያጠቃ የሚችለው ሴቶችን ነውና ለሠላም መከበር ሁሌም ዝግጁ ናት፡፡ "ብዙ ሰው ሀገሩን እንደሚወድ ይናገራል፡፡ ነገር ግን ድርጊት ከቃል ይበልጣል፡፡ በንግግሬ የፈለገውን ያህል ባሳምራትም ተግባር ከሌለ ግን አይሆንም፡" የምትለዋ የአየር ቀዛፊዋ ንግሥት፤ ሁላችንም ከሚያጣሉን ታሪኮቻችን ይልቅ የሚያስማሙን ይበልጣሉና ስለሠላም እናብር ስትል ትገልጻለች፡፡ እያንዳንዱም ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያ ላይ ለሚሆነው ነገር ኃላፊነት እንዳለበት ታመለክታለች፡፡

እንደ እርሷ አባባል፤ ሁሉም ለሠላም መስፈን ቆም ብሎ ማሰብ አለበት፡፡ ሠላም የሚፈልቀው ከውስጥ ነው፡፡ ወደሌላ ሰው እና ማኅበረሰብ የሚጋባው ከውስጥ የሚፈልቀው ሠላም ነው፡፡ ሁሉም የሚኮራባትን ሀገረ ኢትዮጵያ ለማግኘት ቁርጠኛ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ይንንም ለሀገሩ፣ ለእናቱ፣ ለልጁ ብሎም ለትዳር አጋሩ ሲል ሊያደርግ ይገባዋል፡፡

ከአውሮፕላን ላይ በፓራሹት አምስት ጊዜ የዘለለ ኮማንዶና አየር ወለድ ማሠልጠኛ ማዕከል የሴቶች ጉዳይ አመራር ሻምበል ትቅደም ወርቁ በበኩሏ፤ ሀገሬ ሠላሟ ተጠብቆና ኢኮኖሚዋ ጠንክሮ ታላቅ ደረጃ ላይ ደርሳ ማየት ምኞቴ ነው ትላለች፤ ምኞት ብቻ ሳይሆን ኃላፊነቴን ለመወጣት ዝግጁ ነኝ ስትል ታስረዳለች፡፡

እርሷ፣ የሀገሬ አፈር ተቆርሶ የሚበላ፤ አየሯም ተቀድቶ የሚጠጣ ነው ስትል ትናገራለች፡፡ ትርፍ ሀገር የለኝም፤ እንዲኖረኝም አልሻም፡፡ በፊት ልጅ እያለሁ ሰዎች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዘው ሲያለቅሱ የሚያስመስሉ እንጂ እውነት አይመስለኝም ነበር፡፡ አሁን አሁን ሳይ የሀገሬ አፈር ጠረኑ ራሱ ለእኔ መድኃኒቴ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ ያለኝ አንድ ሀገር ነው፡፡ ሌላ የትም መሄጃ የለኝምና ሀገሬን አከብራለሁ ስትል ትናገራለች፡፡

እንደ እርሷ አባባል፤ እኛ የሚያምርብን ኅብረትና አንድነት ሲኖረን ነው፡፡ ሴቶች ደግሞ ከመቼውም በላይ በዚህ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ አንዳችን ለሌላችን እናስፈልጋለን፡፡ የሚያምርብን መስማማት ነውና ፍቅር ነው፡፡ ስለዚህ ተባብረንና ተግባብተን ሀገራችንን ትልቅ ደረጃ ላይ እናድርስ፤ ሀገራችን ትልቅ ደረጃ ላይ ደረሰች ማለት እኛም ትልቅ ደረጃ ላይ መድረስ እንችላለን፡፡ ሴቶችም ሆነን ትውልዱ ከዚህ አንጻር ተጠቃሚ መሆን ይችላል ትላለች፡፡

ሴት መምራት፣ አገር መጠበቅ፣ ማከም፣ ማስተማርም ሆነ ሌላ ሌላውንም ተግባር ማከናወን ትችላለች የምትለዋ ደግሞ የልዩ ኃይሎች ማሠልጠኛ ማዕከል በደረጃ ሁለት ሆስፒታል ሎጂስቲክ ኃላፊ ሻምበል ማዕረግነሽ መንግሥቱ ናት፡፡ ከአውሮፕላን ላይ በፓራሹት ስድስት ጊዜ የዘለለችው ሻምበል ማዕረግነሽ፣ ሴት በየትኛውም የሥራ መስክ ብትሰማራ ማከናወን ትችላለች፡፡ እንዲያውም ሴቶች በሚያልፉበት ፈተና ውስጥ ወንዶች ቢገቡ እንደሴት ይወጡታል የሚል እምነት የላትም፡፡ ተፈጥሮ ራሱ ሴትን የሚያግዝ ነው ባይ ናት፡፡

በሌላ በኩል ሴቶች በሠላም መስፈን ሒደት ውስጥ ያላቸው ሚና ቀላል አይደለም ትላለች፡፡ ለየትኛውም ነገር ሴቶች መሠረት ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ በዚህ ሳምንት የተከበረው የዓድዋ ድል ላይ ሴት ትልቁን ሚና ተጫውታለች፡፡ ስለዚህ ሴት ሀገር ናት፡፡ ሴት እናት፣ እህት፣ የትዳር አጋር ናት፡፡ ሴት የሌለችበት ነገር ስኬታማነቱ አያስተማምንም ማለት ያስደፍራል፡፡ ሴት በአግባቡ የተካፈለችበት የትኛው መልካም የሆነ ሥራ የተሻለ መሆን የሚችል ነው የሚል እምነት አላት፡፡

እርሷ፣ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ለዚህች አገር የሚከፍሉት መስዋዕትነት እኩል ነው ባይ ናት፡፡ ሁሉም ደግሞ የሚጠበቅበትን ድርሻ ከተወጣ ነገ የተሻለችዋን ኢትዮጵያ ማየት እንችላለን ትላለች፡፡ ነገ የተሻለችዋን ኢትዮጵያ ለማየት ደግሞ ዛሬ ላይ መካበበር፣ አንድነትና መተሳሰብ የግድ ይለናል፡፡ ሁሉም ለብሔሩ ሳይሆን ለሀገሩ የሚያደላ መሆን አለበት፡፡ ብሔርተኝነት የሌለበት፣ የወንድማማቾች ጥላቻ የጠፋበት ኢትዮጵያን ማየት እናፍቃለሁ ስትልም ታመለክታለች፡፡

«እኛ ሴቶች በተፈጥሯችን ፈጣሪያችን የሰጠን ክህሎት አለን፤ እሱን በመጠቀም ወንዶች የሠሯቸውን ጀብዶች ሁሉ እንሠራለን፤ ማርገዝ መውለድ ወደኋላ አያስቀረንም፤ አላስቀረንምም» ስትል የምትናገረው ሻምበል የሩቅነሽ ጌታነህ ናት፡፡ ከአውሮፕላን ላይ በፓራሹት አምስት ጊዜ ዘላለች፡፡

እርሷ፣ ከምንም ነገር በላይ አገር ይቀድማል ትላለች፡፡ ስለዚህም ሁሌም በተጠንቀቅ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህኛው እንጂ ያኛው ሥራ አይመቸኝም ማለት በእርሷ ዘንድ አይቻልም፡፡ ሻምበል የሩቅነሽ ለሴቶች መልዕክት አለኝ ትላለች፡፡ ሴት ሆኖ መፈጠር ከምንም አይነት ሥራ አያግድም ባይ ናት፡፡ ወንዶች የዋሉበት መስክ ሴትም መዋል ትችላለች፡፡ ዋናው ፍላጎቱ እንጂ ሴትነት ከየትኛውም ስፍራ የሚያስቀር አይደለም፡፡ ወኔና ድፍረቱ እስካለ ድረስ የሚያቅት ምንም ነገር እንደማይኖርም ታስረዳለች፡፡

ሻምበል የሩቅነሽን፣ "ሀገሬ ሠላም ነግሶባት ማየትን እሻለሁ፡፡ " ስትል ጠቅሳ፤ ዜጎቿ እርስ በእርስ ተዋድደው ማየትን እንደምትፈልግ ታስረዳለች፡፡ ወገኔ በሠላም ወጥቶ ጉዳዩን ፈጽሞ በሠላም እንዲገባም ምኞቴ ነው፡፡ የእርስ በእርስ መገፋፋት ቀርቶ አንዱ የሌላው ጠባቂና ወዳጅ ሆኖ ማየት እሻለሁ፡፡ የእርስ በእርስ መተሳሰብ እንዲኖርም ከመፈለግ በዘለለ፤ ለዚህ መልካም እሴት ሁሉም የየበኩሉን እንዲያደርግ እፈልጋለሁ፡፡ በተለይ ሀገሬ ከችግር፣ ከድህነትና ከፀረ ሠላም ኃይሎች ተላቅቃ ማየት ያስደስተኛል ትላለች፡፡

አራቱም ኢትዮጵያን ለማገልገል ከመቼው ጊዜ በላይ ቁርጠኞች ነን ይላሉ፡፡ ለሠላም ሲባል የሚጠበቅባቸውን መስዋዕትነት ለመክፈልም ዝግጁዎች ናቸው፡፡ የሠላም አለመስፈን በተለይ ለሴቶችና ሕጻናት ይባሱኑ አሳሳቢ እንደሆነም ጠቅሰው፤ ሁሉም በነፃነት ወጥቶ ይገባ ዘንድ ለሠላም እኩል መታገል አለበት ይላሉ፡፡

# በምክክሩ ሴቶችን ማሳተፍ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ብሌን ገብረመድህን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሴቶች በሀገራዊ ምክክሩ መሳተፋቸው ዘላቂ ሠላምና እኩልነት የሰፈነባት ሀገር ለመገንባት ያስችላል። በመሆኑም ሴቶች በሀገራዊ ምክክሩ በንቃት በመሳተፍ ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ሀገረ መንግሥት ለመገንባት በሚደረገው ጥረት አሻራቸውን ሊያሳርፉ ይገባል።

ሀገራዊ ችግሮችን እንደሚፈታ ታምኖበት ወደሥራ በገባው የሀገራዊ ምክክር ላይ ሴቶች ከኮሚሽነርነት ጀምሮ በተለያዩ ደረጃዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ መደረጉ ዘላቂ ሠላምና እኩልነት የሰፈነባት ሀገር ለመገንባት ያስችላል ብለዋል። በዚህ ረገድም በሀገሪቱ ለዘመናት ሲንከባለሉ የቆዩ ልዩነቶችንና አለመግባባቶችን በመፍታት ሀገራዊ አንድነትና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን የሚረዳ አካታች ሀገራዊ ምክክር ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

ሴቶች በተለያየ ጊዜና ቦታ በሚፈጠሩ ችግሮች ቀዳሚ ተጎጂዎች ናቸው ያሉት ኮሚሽነሯ፤ በሀገሪቱ ካለው የሕዝብ ብዛት ግማሽ የሚሆኑት ሴቶች በመሆናቸው በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ነፃና ገለልተኛ ሆነው እንዲሳተፉ በማድረግ ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ሀገረ መንግሥት ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ማሳካት እንደሚገባ ገልጸዋል።

በሀገራዊ ምክክሩ የሴቶች ተሳትፎ ሰፊ ድርሻ እንዳለው ገልጸው፤ በዚህም ሀገራዊ ምክክሩን በሥራ አስፈጻሚነትና ኮሚሽነርነት ከመምራት ጀምሮ በማወያየት፣ አጀንዳ በማሰባሰብ፣ አጀንዳ በመቅረጽ፣ ተሳታፊና ተባባሪ አካላትን በመለየት፣ በምክክር ሂደቱና በሌሎች ሥራዎች ላይ ሊሳተፉ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

ለዘመናት ሲንከባለሉ የቆዩ ልዩነቶችንና አለመግባባቶችን በመፍታት ሀገራዊ አንድነትና ዘላቂ ሠላም ማስፈን መዳረሻ ግብ ያደረገው ሀገራዊ ምክክር ስኬታማ እንዲሆን ሴቶች ግንባር ቀደም ሚና መጫወት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

እንደ ኮሚሽነር ብሌን ገለጻ፣ ሴቶች በሀገሪቱ ዘላቂ ሠላም እንዲሰፍን በቤታቸው፣ በመሥሪያ ቤታቸውና በተለያዩ መድረኮች ላይ ያወራሉ። በርካታ ሀገራዊ ጉዳዮችን ባካተተው የምክክር ሂደት ላይ መሳተፋቸው ደግሞ በውጭ ሆነው ስለሚያወሩለት ሠላም ዘላቂ የመፍትሔ ሀሳቦችን በተግባር ለማቅረብ ዕድል ይፈጥርላቸዋል።

በሀገራዊ ምክክሩ ሴቶች እንደ አንድ የኅብረተሰብ ክፍል ተሳታፊ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከመምህራን ማኅበር፣ ከዕድሮች፣ ከወረዳ አስተዳደር፣ ከአርሶ አደር፣ ከሲቪክ ማኅበራትና፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥም ሴቶች ስላሉ በሁሉም ተሳታፊ መሆን እንደሚችሉ አመልክተዋል።

ምክክሩ ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ሀገረ መንግሥት ለመገንባት፣ ዘላቂ ሠላም ለማስፈን፣ ሀገራዊ መግባባትንና አንድነትን ለማጠናከር ጉልህ ሚና ያለው በመሆኑ ሴቶች በንቃት በመሳተፍ የራሳቸውን አሻራ በማሳረፍ ለተተኪው ትውልድ የምትመች ኢትዮጵያን ሊያስረክቡ እንደሚገባ ተናግረዋል።

«ሴቶችን በአመራርነትና በሌሎች ሥራዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ኮታ ሳይሆን ችሎታ ነው» ያሉት ኮሚሽነር ብሌን፤ ለሀገር አንድነት፣ እድገት፣ ብልጽግና እና ሌሎች ሥራዎች ላይ እቅድ ሲወጣ፣ ውሳኔ ሲወሰን፣ ሰነድ ሲዘጋጅና ተግባራዊ ሲደረግ የሁለቱንም ፆታ ያማከለ መሆን እንዳለበት ገልጸዋል።

ሴቶች የሀገራዊ ምክክሩን ጨምሮ በትላላቅ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ የጾታ እኩልነቱን በማረጋገጥ የምንመኛትን ኢትዮጵያ እውን ማድረግ ይጠበቅብናል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ዘላቂ ሠላሟ ተጠብቆ ሁለተናዊ እድገት እንድታስመዘግብ ሴቶች በየደረጃው ባለው የሀገራዊ ምክክር ሂደት በንቃት በመሳተፍ ለስኬታማነቱ ሊሠሩ እንደሚገባ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# የሴቶች ሀገራዊ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የመከላከያ ሚኒስቴር የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ዳይሬክተር ብርጋዲየር ጄኔራል ሁሉአገርሽ ድረስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአንድ ሀገር ዘላቂ ሠላም የሚረጋገጠው በጠንካራ ሴቶች ወሳኝ ተሳትፎ ነው። በመሆኑም ሴቶችን በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ከማሳተፍ ጀምሮ እስከ አመራርነት ማብቃት ይገባል።

ሴቶችን ማብቃት ማኅበረሰብን ማብቃት እንደሆነ ገልፀው፤ በሠላም ማስከበር ሥራውም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሴቶችን በማሳተፍ ብሎም ከወንዶች ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የስምሪት የመስጠት ሥራም እየተሠራ ነው ብለዋል።

በዚህም ኢትዮጵያ የሴቶችን በማሳተፍ በዓለም ካሉ ውጤታማ ሀገራት ተርታ እንደምትሰለፍ ብርጋዲየር ጄኔራል ሁሉአገርሽ ገልጸዋል።

በሚኒስቴሩ የሴቶች ቀን ሲከበር በሴቶች ተጋድሎ ሠላምን እናረጋግጣለን፤ እኩልነትን እናሰፍናን በሚል ሀሳብ ሲሆን በሠላም ማስከበር ግንባር የተሠማሩና ከወንዱ እኩል ብሎም በበለጠ በጀግንነት ታሪክ የሠሩ ሴቶችን በማሳተፍና መስዋዕት የሆኑ ጀግኖች ጓዶችን በማሰብ መሆኑንም አንስተዋል።

ብርጋዲየር ጄኔራሏ እንደገለጹት፤ የአንድ ሀገር ሠራዊት ማለት ለሀገር የቆመ ዘብ ማለት ነው። ሴት የሠራዊት አባላትም የራሳቸውን ሕይወት ለሀገራቸው መስዋዕት ለማድረግ በቁርጠኝነትና በልበሙሉነት የተሞሉ ጠንካራ አባላቶች ናቸው። በመሆኑም ሴቶችን ብቁ እና የበለጠ ተሳታፊ ለማድረግ በሥልጠና እና በትምህርት እራሳቸውን በማዳበር ግንባር ቀደም ተፅዕኖ ፈጣሪ በመሆን አለባቸው። የሀገር ሠላም በተረጋገጠ ቁጥር እንደተቋምም በተለይም ሴት ሠራዊቶች ራሳቸውን ከማብቃት እና እንደሀገር ዘመናዊ ሠራዊት ከመገንባት አንጻር ትልቅ ጥቅም አለው። የዘንድሮ መሪ ቃልም የዚህ ሀሳብ ማሳያ ነው።

ለሀገር ሉዓላዊነትና ሠላምን በማረጋገጥ ሕዝቦች በሠላም ወጥተው እንዲገቡ እየተከፈለ ያለው መስዋዕትነት እና ኃላፊነትንም ከወንድ አባላቶች ጋር በመሆን እየተወጡ መሆኑንም ብርጋዲየር ጄኔራል ሁሉአገርሽ ተናግረዋል።

ሴቶች ልጅ ከማሳደግ ጀምሮ ብዙ ጫናዎች ያለባቸው መሆኑን አስታውሰው፤ በመሆኑም ሴቶች በይቻላል መንፈስ እርስ በርስ በመደጋገፍ ጠንክሮ በመሥራት ያመኑበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይቻላል ብለዋል።

አክለውም «ሴቶች አንድ ስንሆን ትልቅ አቅም አለን፤ ያለንን አቅም የበለጠ እንዲጨምር የሴቶች የበለጠ ተሳትፎ ወሳኝ ነው።ለዚህም የኢትዮጵያ ሴቶች አንድ በመሆን ለሠላምና ለልማት መነሳት አለባቸው» ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# የሴቶችን ጤና መጠበቅ ጤናማ ትውልድን ለማፍራት ያስችላል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- የሴቶችን ጤና መጠበቅ ጤናማ ትውልድን ለማፍራት ያስችላል ሲሉ በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ዳይሬክተር ወይዘሮ ሔለን አዱኛ ገለጹ፡፡

ዳይሬክተሯ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ሴት ልጅ የቤተሰቧ ዋነኛ ምሰሶ ናት፡፡ የእርሷ ጤና መሆን ለቤተሰቧም ሆነ ላለችበት ማኅበረሰብ ጤናማነት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

በቤት ውስጥ ቤተሰቧን የምታስተዳድር ሴት፣ የልጆቿን ድህነትን ከማረጋገጥና ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓት እንዲኖራቸውም ከማድረግ አንጻር ሰፊ ድርሻ አላት ያሉት ዳይሬክተሯ፣ ይህንን ሚናዋን በአግባቡ መወጣት እንዲቻላት በቅድሚያ የራሷ ጤንነት መጠበቅ አለበት ብለዋል፡፡

ዳይሬክተሯ እንደተናገሩት፣ ጤንነቱ የተሟላ ቤተሰብን ከመምራት አንጻር የሴት ልጅ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ለሴቶችና እናቶች ጤና መጠበቅ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

የሴቶችን ጤና ከመጠበቅ አንጻር፣ ሴቶችና እናቶች የጤና ተቋማትን በአካባቢያቸው እንዲያገኙ ከማድረግ ጀምሮ የጤና አገልገሎቶችን እንዲያገኙ የማድረግ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው፡፡

አንዲት እናት ከራሷ አልፋ የቤተሰቧን ጤና የመጠበቅና የመከታተል አቅምና ብቃት ያላት ሴት እንድትሆን በጤና ተቋማት በቋሚነትና በተለያዩ ጊዜያት ደግሞ በዘመቻ መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሠሩ እንዳሉም አስታውቀዋል፡፡ በተለይም፣ ከቅድመ መከላከል አንጻር የጡት ካንሰርና የማኅጸን ካንሰር ምርመራዎች እየተሰጡ ሲሆን፣ የበሽታዎቹን ስርጭት ለመቀነስና የእናቶችን ጤና ለመጠበቅ ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩም ይገኛሉ ብለዋል፡፡

ከቅድመ ወሊድና ድረ ወሊድ የጤና ክትትል ጋር በተያያዘም የእናቶችና ሕጻናትን ሞት ለመቀነስ በሚሠሩ ሥራዎች ከጤና ተቋማት በተጨማሪ የቤት ለቤት አገልግሎቶችም እንደሚሰጡም ተናግረዋል፡፡

ሴቶች ጤናቸውን እንዲጠበቅ ከማድረግ አንጻር የሚሠሩ ሥራዎች ከሴት ሕጻናት ጀምሮ የሚጀምር መሆን አለበት ያሉት ዳይሬክተሯ፣ ከታችኛው የትምህርት ደረጃ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ ጤናማ ትውልድን ለማፍራት የሴቶችን ጤና መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መሠራት እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

ዳይሬክተሯ፣ ሴቶች ራሳቸውን ለማብቃት በሚያደርጉት ጥረት ምቹ ያልሆኑ ሁኔታዎችን በመቀየር ረገድ በተለይም ተቋማት ትኩረት ሰጥተው መሥራት አለባቸው ብለዋል፡፡ እናቶች በተሠማሩበት የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሚናቸውን መወጣት እንዲችሉ ልጆቻቸውን በጤና እና በንጽሕና ማቆየት የሚያስችሏቸው የሕጻናት ማቆያዎችን እንዲያመቻቹም ጠይቀዋል፡፡

# ሴት ሠዓሊያንን ማብቃት ላይ ያተኮረ ፕሮጀክት በይፋ ተጀመረ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ግራር፣ የጠቢባን መናኸሪያ ከተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) አሸበርግ ፕሮግራም ጋር በመተባበር ሠዓሊትን ፍሊጋ የተሰኘ ሴት ሠዓሊያንን ማብቃት ላይ ያተኮረ ፕሮጀክት ትናንት በይፋ አስጀምሯል፡፡

የግራር፣ የጠቢባን መናኸሪያ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሴሚናስ ሀደራ እንደገለፁት፤ "ማንኛውም የሥነ ጥበብ ሙያተኛ በዚህ የዲጂታል ዘመን ያሉትን እድሎች መገንዘብ እና መጠቅም ይገባቸዋል። በተለይም ሠዓሊትን ፍሊጋ ፕሮጀክት ሴት ሠዓሊያን ያላቸውን የፈጠራና ተሰጥዖ ተገቢውን እውቅና እንዲያገኙ የሚያስችል ፕሮጀክት ነው፡፡

በዋና ሥራ አስኪያጁ ንግግር መሠረት፤ ፕሮጀክቱ የዲጂታል ክህሎት ሥልጠናን በመስጠት፣ የዲጂታል ስብዕና መገንቢያ አሠራሮችን በማልማት እና በመተግበር የሴት ሠዓሊያንን በዲጂታል ሥርዓት ውስጥ ያለውን የሥርዓተ ፆታ ኢ-ፍትሐዊነት ያጠባል፡፡ እንዲሁም አካታች እና ፍትሐዊ የጥበብ እና ፈጠራ ሥነ ምሕዳር እንዲጎለብት በመሥራት ሴት ሠዓሊያኑ በዘመናዊው የዲጂታል ዓለም ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዲኖራቸው ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

ዋና ሥራ አስኪያጁ፣ ሠዓሊትን ፍሊጋ ፈጠራን በመደገፍ፣ አካታችነትን በማበረታታት እና የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለይቶ በመፍታት የሴት ሠዓሊያንን በማብቃት ዘላቂ ተፅዕኖ ማሳደር የሚያስችል መሠረት የሚጥል ነው ብለዋል። ፕሮጀክቱ ሚዛናዊ የባሕል ምርቶችና አገልግሎቶች ስርጭት ማሻሻል፣ የአርቲስቶች እና የባሕል ሙያተኞች ተንቀሳቅሶ የመሥራት ዕድሎችን ያጎለብታል፡፡ እንዲሁም በሥነ ጥበብ ውስጥ የሥርዓተ ፆታ እኩልነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ ድጋፍ ያደርጋልም ብለዋል።

በዚህ ፕሮጀክት ከ20 ሴት ሠዓሊያን ጋር በቅርበት የሚሠሩ እና ድጋፍ የሚያደርጉ በብራንዲንግ፣ በማኅበራዊ ሚዲያ አመራር፣ ድረ ገጽ አጠቃቀም፣ የይዘት ዝግጅት እና የገበያ ልማት ስልቶች ላይ ያተኮሩ ሥልጠናዎች እንዲያገኙ ይደረጋል። ይህም ሠዓሊያኑ ሥራዎቻቸውን ለታዳሚ ለማቅረብ፣ አዳዲስ የገበያ ዕድሎችን ለመጠቅም ያስችላቸዋል።

ለሰፊው የጥበብ አፍቃሪው ማኅበረሰብ ተደራሽ ለመሆን እና በዓለም አቀፍ የዲጂታል ሥነ ምሕዳር ውስጥ ያሉ ፕሮጀክቱ በፈጣን እድገት ላይ የዲጂታል ሽግግርና የስብዕና ግንባታ ያለውን ሚና በመገንዘብ የሴት የጥበብ ሙያተኞችን ተሰሚነት ያጎለብታል፡፡

ፕሮጀክቱ የገበያ ትስስር ለመፍጥር፣ የ20 ሴት ሠዓሊያንን የሥነ ጥበብ ሥራዎች በዓውደ ርዕይ ይዘት ይቀርባል። በተጨማሪም ሠዓሊትን ፍሊጋ ለ100 በጥበብ እና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ወጣቶች የሥራ ዕድሎች የሚፈጥር ነው።



# የጥበበኞቹን ሕይወት የቀየረው ማዕከል

**ዳግማዊት አበበ**

ዜና ሐተታ

ልጅ በማሳደግ የዛለ እጅ አላቸው:: የበረታው የሕይወት ትግል ቢደቁስም አልጣላቸውም:: ቢደክሙም ለሥራ አልቦዘኑም:: በጭቃ የተዳደፉ ጣቶች ባለቤት ናቸው:: ውብ የጥበብ ሥራ ይከውናሉ:: ከቤተሰብ አልፎ ለሀገር ካስማ የሆነ ጥበብ ::

አፈር አልመው ከውሃ አዋሕደው ያቦካሉ:: የተሰናዱ የሸክላ መገልገያዎችን ማበጃጀቱን ተክነውበታል:: ልክ በእሳት ፈትነው እንደሚያሳምሩት ሸክላ ናቸው:: እነሱም ተፈትነው ችግሩን አልፈውታል::

ተቋሙ እንሥራ የሸክላ ማዕከል ይባላል:: ባለ ብርቱ እጆቹ ሴቶች ይነግሡበታል:: በማዕከሉ እልፎች ሕይወታቸውን ቀይረዋል:: ከነዚህ መሐል አንዷ ወይዘሮ የሺብርኄጥ አየለ ይባላሉ:: እትብታቸው በሰሜን ሸዋ ዞን ልዩ ስሙ ጊደም ማርያም አካባቢ ተቀብሯል:: አራት ወንድና ሁለት ሴት ልጆች ከማሕፀናቸው ተገኝተዋል:: ገና በለጋነታቸው ልጅህን ለልጄ ተብሎ ባሕል በየነባቸው:: ከማያውቁት መዳር ተፈረደባቸው:: በአስር ዓመታቸው ከትዳር ተዋወቁ::

በመሮጫ እድሜያቸው ትዳር ያዙ:: በለጋ እድሜያቸው ቤተሰብ ማስተዳደር ከበዳቸው:: ለዚህም መላ ዘየዱ:: ከባለቤታቸው ዘመዶች ጠጋ ብለው የሸክላን ሥራ ተማሩ::

የሸክላ ሥራን በ1977 ዓ.ም "ሀ" አሉ:: ጉልቻ፣ ምጣድ እንዲሁም ትናንሽ ድስቶችን በመሥራት ጀመሩ:: ሥራቸውን አስርና ሃያ ሳንቲም ይሸጡታል:: የሚያገኙት ሳንቲም የቤተሰቡን ጉሮሮ ለመድፈን አግዟቸዋል::

በሂደትም ተወልደው ያደጉበትን ስፍራ ለቆ መሄድ ግዴታ ሆነ:: ወደ አዲስ አበባ ከተሙ:: ሕይወት በመዲናይቱ አልጋ በአልጋ አልነበረም:: የቦታ ችግር ትልቁን ስፍራ ይይዛል:: ሥራውን ለሁለት ዓመታት ሠሩ:: ከዚያም ቀጨኔ አካባቢ ወደሚገኝ የሸክላ ድርጅት ገቡ:: ለረጅም ዓመታት በዛው ቆዩ::

ከአራት ዓመት በፊት ነገሮች መልካቸውን ቀየሩ:: መንግሥት የሸክላ ሠሪ ማኅበራትን በአንድ ላይ አመጣ:: እንሥራ የሸክላ ማዕከልንም ገነባ:: እሳቸውም ከማዕከሉ ተቀላቀሉ:: በዛ በነፃነት እየሠሩ መሆኑን ይገልፃሉ:: በዚያ የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸዋል:: ያመረቱትን ምርት ያለምንም ድካም በማዕከሉ ይሸጣሉ:: በዚሁ ቤተሰባቸውን ያስተዳድራሉ::

ያኔ ለእለት ጉርሳቸው ብለው መማር የጀመሩት የሸክላ ሥራ ዛሬ ክሷቸዋል:: ለቤተሰባቸውን ዋነኛ የገቢ ምንጭ ከመሆን አልፏል:: ማዕከሉ በሥራ ትጋታቸው የዋንጫ ተሸላሚም አድርጓቸዋል::

ሌላኛዋ ጥበበኛ ከበቡሽ ጌጡ ትባላለች:: የአንድ ልጅ እናት ናት:: የሕይወቷ 15 ዓመታት በሸክላ ሥራ ላይ አልፈዋል:: እናትና እህቷን የሸክላ ሥራ እየሠራች ታስተዳድራለች::

ሙያውን ከእናቷ ነው የወረሰችው:: እናትም የሸክላ ሥራ ለብዙ ዓመታት መሥራታቸውን ታስታውሳለች:: በወቅቱ ማኅበረሰቡ እናቷ የሚሠሩትን ውብ የሸክላ ጥበብ ሥራ ይወደው ነበር:: ቢሆንም እርሳቸውን ያገል ነበር:: እነሱንም የሸክላ ሠሪ ልጅ እያሉ ያንቋሽሻል:: ዛሬ የማኅበረሰቡ አስተሳሰብ እየተቀየረ መጥቷል:: በሥራዬ እኔም ልጄም ኮርተን እየኖርን ነው ትላለች ::

የእንሥራ ማዕከል ከተመሠረተ እዛው ናት:: በዚህም ምርቶችን በመሸጥ ኑሮዋን እየደጎመች ናት:: ከማዕከሉ መቋቋም አስቀድሞ ሥራው ከባድ መሆኑን አንስታለች:: ምርት ማዘጋጃ ኩሽናና ጭቃውን ማድረቂያ ቦታ ማግኘቱ ስለመከበዱ አስታውሳለች::

እንሥራ ማዕከል የኔን ብቻ ሳይሆን የብዙ እናቶችን የቦታ ችግር የቀረፈ ነው ትላለች:: ወደ ማዕከሉ ከተቀላቀለች ጀምሮ የገበያና የቦታ ችግሮች ተቀርፈዋል:: ሙያዋም እያደገ መጥቷል:: የምታመርታቸውን ምርቶች ቶሎ ቶሎ እየተሸጠላት ስለመገኘቱም አንስታለች::

ወይዘሮ ገነት አሰፋ ይባላሉ:: የማኅበሩ ሰብሳቢ ናቸው:: እሳቸውም የሸክላ ሥራ ላይ ተሠማርተዋል:: እንሥራ ሲመሠረት 257 አባላት እንደነበሩት አንስተዋል:: በአሁኑ ጊዜም አባላቱን 302 በማድረስ ለተጨማሪ 128 ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል ይላሉ።

መንግሥት ሃሳብ ከማመንጨት አልፎ ሥራዎችን ከውኗል:: በማዕከሉ በርካታ እናቶች ገቢያቸው መሻሻሉን ጠቅሰዋል:: ማኅበረሰቡ ለሸክላ ሙያተኞች ያለውን አመለካከት የቀየረ መሆኑንም ነው የገለጹት::

ማዕከሉ ተጨማሪ መሥሪያ ቦታ ቢመቻችለት መልካም ነው ይላሉ:: አባላቱን በማሳደግ አሁን ካለው በበለጠ የሸክላ ዕደጥበብ ውጤቶችን የሚያመርት ትልቅ ተቋም መሆን ይችላል ሲሉ ያክላሉ ።

ለማዕከሉ ትልቅ ችግር እየሆነ የመጣውን ጉዳይ አንስተዋል:: ይህም የሸክላ ምርት እንዲጠነክር የሚረዳው የማቃጠያ ቦታው ጥበት ነው:: አሠራሩ ባሕላዊ መሆኑን ጠቅሰዋል:: ከችግሩ በዘላቂነት ለመላቀቅም የኤሌክትሪክ ማቃጠያ እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ። ማዕከሉ ይህ ችግር ከተቀረፈለት የሴራሚክ ምርቶችን ለማምረት እቅድ እንዳለውም ይናገራሉ ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሴቶችን ሁሉን አቀፍ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማላቅ ይገባል

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ113ኛ፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ48ኛ ጊዜ የሚከበረው የዘንድሮው የሴቶች ቀን፣ መሪ ሐሳቡ "ሴቶችን እናብቃ! ልማትንና ሠላምን እናረጋግጥ!" የሚል ነው። መሪ ሐሳቡ እንደሚያመለክተው ደግሞ፣ ልማት እና ሠላምን ለማረጋገጥ ሴቶችን ማብቃት እጅጉን የሚያስፈልግ መሆኑን ነው። ዛሬ ላይ ዓለማችን በሠላም እጦት ውስጥ ለመኖሯ አንዱ ምክንያትም ይሄው ሴቶችን አብቅቶ ያለማሳተፍ ስለመሆኑም በርካታ አመክንዮዎችን መጥቀስ ይቻላል።

እርግጥ ነው በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛውን ቁጥር የያዙ ሴቶች ዛሬም ገና አልበቁም። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መረጃ እንደሚያሳየውም፣ እ.ኤ.አ. በ2023 በዓለም ላይ የሴቶች ቁጥር አራት ቢሊዮን ይገመታል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ ከዓለም ሕዝብ 49 ነጥብ 75 ይሆናል። በእርግጥ በዓለማችን ላይ ላለፉት 22 ዓመታት በተከታታይ ወንዶች ከሴቶች ይልቅ በቁጥራቸው ብልጫውን ይዘው ዘልቀው እንደነበር ይታወቃል። ዛሬ ዛሬ ግን የሴቶች ቁጥር ከወንዶች ጋር እኩል በሚያስብል ሁኔታ በመምጣት ላይ ይገኛል።

ይህ ግን ከቁጥር አንጻር ያለውን መረጃ የሚያሳይ እንጂ፣ ሴቶች በቁጥራቸው ልክ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፉ ላይ ያላቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነት በዛው ልክ የሄደ አይደለም። ይሄ ሁኔታ ደግሞ ሴቶች ከእነዚህ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከውሳኔ ሰጪነት ሚናቸውም ጭምር እንዲርቁ እያደረጋቸው ስለሚገኝ ይሄንን አካሄድ መቀየር የተገባ ነው።

በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ ወዲህ በመጡ መሻሻሎች የሴቶች ተሳትፎን በሁሉም መልኩ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መልካም ጅምሮች ታይተዋል። ለምሳሌ፣ በሀገራችን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያለው የሴቶች ውክልና ከፍ ብሏል። ይህም የሴቶች ቁጥር ከወንዶች አንጻር በመቶኛ ሲሰላ 42 ነጥብ አምስት መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መረጃ ያሳያል። ይህ ከፍ ያለው የሴቶች ቁጥር መታየቱ ይበል የሚያሰኝ ነው።

ከዚህ በተጓዳኝ በካቢኔ አባልነት(ሚኒስትርነት) ደረጃ ያለው የሴቶች ተሳትፎ እስከ 50 በመቶ የደረሰበት አጋጣሚ ነበር። አሁንም ቢሆን ድርሻቸው ከፍ ያለ ነው። ኢትዮጵያ በፕሬዚዳንቷ፣ አዲስ አበባም በከንቲባዋ ሴቶችን ከፊት ማስቀደሟም የዚህ ሌላው አብነት ነው።

ነገር ግን ይሄን መሰሉ ሁነት በየደረጃ ሲታይ ከላይ ያለው ዓይነት አካሄድ በተዋረድ ሲወርድ አይታይም። በአንዳንድ ተቋማት ደግሞ የሴቶች ተሳትፎ ብርቅ የሚሆንበት ሁኔታ በሰፊው ይታያል። ሆኖም እውነታው የሴቷን ተሳትፎ በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካው ዘርፍ ይበልጥ በማጎልበቱ ረገድ የላይኛውን ዓይነት የውሳኔ ሰጪነት ቦታው እንዲኖራቸው ማድረጉ ለልማቱም ለሠላሙም ሚናው የጎላ መሆኑን ተገንዝቦ መሥራትን ይጠይቃል።

እንደ መሪ ሀሳቡ ሁሉ ሴቶች የቁጥራቸውን ያህል የውሳኔ ሰጪነቱን ስፍራ ይዘው ቢሆን፣ ሀገራችን ዛሬ እየደረሰባት ያለው የሠላም ችግር ይሄን ያህል ገፍቶ ላይወጣ ይችል ነበር። እናም ሴቶችን ከወንዶች ባልተናነሰ ተሳትፏቸውን ለማጎልበት ዛሬም ቢሆን አይረፍድም፣ አልረፈደምም። ተሳትፏቸውን ወደላቀ ደረጃ ለማሳደግ የሚጠየቀው ቀናነት ብቻ ነው። ሴቶች የሚሳተፉበት የልማትም የሠላምም ሒደት ጤናማነት የተረጋገጠ ስለሚሆን ከዚህ አንጻር ሴቶችን ወደውሳኔ ሰጪነት ቦታው ማምጣቱ አዋጭ ነው።

ምንም እንኳ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ካሉ አምስት ሀገራት መካከል ለሴቶች የተሻለ ውክልና በመስጠቱ የምትጠቀስ ብትሆንም፣ ይህ ብቻ በራሱ በቂ ነው ለማለት አያስደፍርም። ዛሬም ቢሆን ውሳኔ ሰጪ የሆኑ ናቸው የሚባሉ ተቋማት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በተፈለገው ልክ አይታይም። ሴቶችን በፖለቲካው ዘርፍ ከወንዶች እኩል ለማሳተፍ የሚደረግ ጥረት በአገራችን መሪ ዘንድ ቢኖርም ገና ብዙ የሚቀረን ነገር መኖሩ ሊዘነጋ አይገባም።

የዘንድሮው መሪ ሐሳብ፣ "ሴቶችን እናብቃ! ልማትንና ሠላምን እናረጋግጥ!" የሚል እንደመሆኑም፣ ሴቶችን ማብቃት የግድ ነው። ሴቶችን አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ከአመራር ሰጪነት ቦታ መግፋት አግባብነት የሌለው አካሄድ ነው። ደግሞም ሴቶች ተገቢ የሆነ ውክልና ሊኖራቸው ይገባል ሲባል እንዲያው ለይስሙላ መሆን የለበትም። በመንግሥት ካቢኔ ውስጥም ሆነ በሌሎች ቦታዎች የሴቶች ተሳትፎ ከፍ ሊል ይገባል ሲባልም ለተሳትፎ ብቻ መሆን የለበትም።

ምክንያቱም ሴት ወደ አመራርነት እና ውሳኔ ሰጪነት መጣች ማለት፣ ሙስናን ከመሠረቱ ለማጥፋት መንገዱ ተጀመረ ማለት ነው። የሠላም መስፈን የመጀመሪያ ተጠቃሚ የሚያደርጋት እርሷን በመሆኑም፣ ሴት ወደ ውሳኔ ሰጪነት ስትመጣ ስለሠላም ቅድሚያ ሰጥታ ትሠራለች። በሀገራችን ሠላም ሰፈነ ማለት ደግሞ ልማት በሚፈለገው ልክ ይሳለጣል።

ሴቶች፣ ተገቢውን ስፍራ ሲይዙ ለሠላም መስፈንም ሆነ ለልማት መሳለጥ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል የሚባለውም እውነት ስለሆነ ነው። ከዚህ አኳያ ሴቶችን ማብቃት ማለት ማኅበረሰቡን ካለበት ውጣ ውረድ ማላቀቅ ነው። ሀገርን ከድህነት አረንቋ ማውጣት ነው። ወጣቱ በሠላም እጦት ሥራ ፈት ሆኖ ተስፋ እንዳይቆርጥ ሥራ እንዲፈጠርለት ማስቻል ነው።

ሴቶች ወደ አመራርነት እና ውሳኔ ሰጪነት ይምጡ ሲባል፣ ሴቶችን ተሳታፊም ተጠቃሚም የሚያደርጉ ሥራዎች ይከናወኑ ማለት ነው። ለዚህ ደግሞ ሴቶችን ዛሬም ቢሆን እየደረሰባቸው ካለው ጥቃት መታደግና መከላከል የመንግሥት ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ነው። ሴቶችም በራሳቸው የውሳኔ ሰጭነት ሚናቸውን ለማሳደግ በየተሠማሩበት አቅማቸውን ማሳየት ይኖርባቸዋል። በዚህ መልኩም ለሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማደግ ሁሉን አቀፍ ትብብርና ሥራ ይጠይቃል።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የሀገር ካስማ... ሴት

መክሊት ወንድወሰን

ሴትነትን ስናነሳ እህት፣ ልጅ፣ ሚስት ከሚለው በላይ እናትነት በብዙኃኑ ልብ ላይ ገዝፎ ይታያል። በምድር ላይ እናቱን የማይወድ ፍጡር አለ ቢባል የመልካም ልብ ባለቤት አልያም ሰዋዊ ስሜትን የተላበሰ ነው ለማለት ያስቸግራል። እናላችሁ የምድር ሚዛን ጠባቂ የሆነችው ሴት ዓለም ካላት ሃብት እኩል ተጠቃሚ እንድትሆን አለማድረጉ ንፉግነት አይመስላችሁም?

የሃገር ካስማ ሴት ሆና ሳለች ስለሃገር ወጥታ ስትናገር አድማጭ የምታጣበት እና ተዓማኒ የማትሆንበት ጉዳይ አሁንም ለምን የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው። ዘመናዊ የተባሉት የዓለም ክፍሎች ላይ ሳይቀር እስካሁን የሴትን ልጅ እኩል ተጠቃሚነት ሙሉ በሙሉ ሳያረጋግጡ ቆይተዋል። ለውሳኔ ሰጪነት እሷን ወደ ኋላ ከማስቀረት ይልቅ ለእሷ የታያት በቂ ነው ብሎ መቀበሉስ ምኑ ላይ ነው ክፋቱ ብዬ እጠይቃለሁ። ሴት ቢያውቅ... በወንድ ያልቅ የሚለው የሀገራችን ብሂል ሴቶች ለብቻቸው አይወስኑም አይችሉም ወደሚል አንድምታ ሲወስዱት ይታያል። ዓለምም በዚሁ መርሕ እየተመራች ስለመሆኗ በተደረጉ የተለያዩ ጥናቶች የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እስካሁን በየትኛውም ሀገር ሙሉ በሙሉ ማረጋገጥ አለመቻሉ ታላቅ ማሳያ ነው።

እስከዛሬ በሴቶች እኩል ተጠቃሚነት ዙሪያ በተሠሩ ሥራዎች የተነሳ ጉልህ ለውጦች አሉ። ዓለምም በወንዶች ብቻ የነበረውን ሥርዓቷን ቀይራ ሴቶች ያላቸውን አቅም እና ሰብዓዊ መብታቸውን እንዲያረጋግጡ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል ። ነገር ግን አሁንም ድረስ ሙሉ በሙሉ የፆታ እኩልነትን ለማስመዝገብ ታላቅ ትግል የሚጠይቅ ጉዳይ ሆኖ በመቀጠል ላይ ነው። ሴቶች ውሳኔ ሰጪነትን በሚጠይቁ ቦታዎች ላይ የመቀመጣቸው ነገር የማይዋጥላቸው ሰዎች አሉ። ይህንንም የሚያያይዙት ባላት ሩህሩህ የሆነው ተፈጥሯዊ ባሕሪዋ ነው። ነገር ግን ደግሞ በተለያየ ኃላፊነት ላይ የተቀመጡ ሴቶች ደግሞ ሥራቸውን እጅግ በቁርጠኝነት እና ችላ ባለማለት ጥንቅቅ አድርገው የተሰጣቸውን ሥራ ኃላፊነት እንደሚወጡ ደግሞ ብዙዎች የሚመሰክሩት ጉዳይ ጭምር ነው ።

አሁንም ድረስ ግን ሴቶች በመሪነት የተቀመጡባቸው ቦታዎች ላይ በተለያዩ የዓለም ሀገራት መድልዎ፣ ጥቃት፣ የትምህርትና የጤና አጠባበቅ ተደራሽነት ውስንነት እንዲሁም የኢኮኖሚ ልዩነቶች ይደርስባቸዋል። የዚህን ችግር መጠን ለማሳየት በተለያዩ ዓለማቀፍ ጥናቶች የተደገፉ አኃዛዊ መረጃዎችን እንመልከት።

በሴቶች እና በወንዶች ያለውን የኢኮኖሚ ልዩነት ስንመለከት፣ ሴቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ በአማካይ ከወንዶች በ23 በመቶ ያነሰ ገቢ ያገኛሉ ይህ በጉልበት ሥራ ላይ የተሰማሩ እና በጉልበታቸው ብቻ በሚመዘኑ የሥራ መስኮች ላይ ብቻ ሳይሆን እኩል የትምህርት ዝግጅት ያላቸው እና እኩል የመመረቂያ ነጥብ ይዘው በተመሳሳይ የሥራ ዘርፍ ላይ ያሉ ሲሆን ነገር ግን የሚከፈላቸው ክፍያ ከወንድ የሥራ ባልደረቦቻቸው ያነሰ መሆኑ ነው። ሴቶች በአመራር ቦታዎች ላይ ያላቸው ውክልና ፣ ተሳታፊነት ሲታይም ዝቅተኛ ነው። በፓርላማ ውስጥም መቀመጫ ማግኘት የቻሉት 24 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች ብቻ ናቸው።

በትምህርት ላይም የልጃገረዶች የትምህርት ተደራሽነት የተሻሻለ ቢሆንም በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች የተለያዩ ፈተናዎች እየገጠሟቸው ይገኛል። ከነዚህም ውስጥ እንደ ያለ አቻ ጋብቻ እና ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ያሉ የተለያዩ ባሕሎች ምክንያት ሴቶች የመማር እድላቸው ላይ መሰናክል ሆኖባቸዋል። እነኝህን በመሳሰሉ ችግሮችም በዓለም ዙሪያ በግምት ከ130 ሚሊዮን በላይ ልጃገረዶች ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሦስት ሴቶች አንዷ በሕይወት ዘመኗ አካላዊ ወይም ፆታዊ ጥቃት ይደርስባታል። በሴት ልጅ ግርዛት እና ያለአቻ ጋብቻ ባሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አሁንም በዓለም ዙሪያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ልጃገረዶች ይጎዳሉ። ይህም በትምህርት እራሳቸውን ከፍ አድርገው እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ጉዞ በአጭሩ የሚያስቀር ነው።

አሁን ላይ በየሀገራቱ የሴቶችን ተሳትፎ ለመጨመር በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ቢሆንም ችግሩን ከስሩ ለመንቀልና የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማሳደግ በዋናነት የተለያዩ የሕግ ማሻሻያዎች ሊደረጉ ይገባል። መንግሥታት የፆታ እኩልነትን የሚያረጋግጡ እና የሴቶችን መብት የሚያስጠብቁ ሕጎችን አውጥተው ማስተግበርም ይገባቸዋል። በሕጎችም ሴቶች እንደ ወንዶች ሁሉ ለሚሠሯቸው ተመሳሳይ ሥራዎች እኩል ክፍያ እንዲያገኙ የሚያስገድድ፣ ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች እና በሁሉም ዘርፍ የሚደርሱ አድሎዓዊ ጉዳዮችን መፍታት የሚችል መሆንም አለበት ።

የሴቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ፆታ ተኮር የሆኑ ፖሊሲዎች መተግበር አለባቸው፤ ከእነዚህም መካከል ሴቶች እኩል ክፍያ፣ ብድር የማግኘት ዕድል እና የሥራ ፈጠራ ድጋፎችን እንዲሁ ሊያገኙ ይገባል። የግል ሴክተሩም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እንዲያበረታታ እና አድሎዓዊ ድርጊቶችን እንዲያስወግድ ማበረታታት አስፈላጊ ነው ።

በጤና እና ደህንነት ዘርፉም መንግሥታት እና ድርጅቶች ለሴቶች ጤና ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ማረጋገጥ እንዲሁ ሊሠራበት የሚገባ ዘርፍ ነው። በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለመፍታት መሥራትም አለባቸው። ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ለመቅረፍም ለሴቶች የተለያዩ የድጋፍ አገልግሎቶችን መስጠት፣ አካባቢዎች ደህንነታቸው የተጠበቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና የሕግ ጥበቃን እና ከለላን መስጠት ወሳኝ ነው። ሴቶች በሚደርስባቸው ጥቃቶች በሕግ የተደነገጉ ውሳኔዎች አለማክበር ከተጠቂዎች እና ጉዳዩ ላይ ትኩረት ሰጥተው የሚሠሩ አካላት በተደጋጋሚ የሚቀርብ አቤቱታ በመሆኑ በወረቀት ላይ ተጽፈው የሚገኙ ሕጎችን ከማስፈጸም ባሻገር፣ ሴቶች የሚደርሰውን ጥቃት ለመቀነስም ሆነ ለማስቀረት ጥብቅ የሆኑ ሕጎችን ማስቀመጥ ያስፈልጋል። በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ሴቶች በሥራ ቦታቸውም ሆነ በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች ደህንነት እንዳይሰማቸው የሚያደርግ በመሆኑ ሕጎች ተግባራዊ መደረጋቸው ስጋት የተሞላበትን እንቅስቃሴ የማስቀረት አስተዋፅዖ አለው። በተለያዩ ጊዜያት ጥቃት ደርሶባቸው ጥቃት አድራሹ አካል ውሳኔ ቢሰጠውም እንኳን ውሳኔው በተገቢው መንገድ አለመተግበር፣ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊትም ሆነ በኋላ ባጠቃቸው አካል ተደጋጋሚ የሆነ ጥቃት የሚደርስባቸው በመሆኑ ጥቃት የደረሰባው ሴቶች ሪፖርት ከማድረግ እንዲቆጠቡ እና በስጋት እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል በመሆኑም ጥቃት ላደረሰው አካል ሳይሆን ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ከለላ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው ።

በዓለም አቀፍ ትብብር በኩልም እንዲሁ በመንግሥታት፣ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና በሲቪል ማኅበረሰብ መካከል ያለው ትብብር የዓለም አቀፍ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው። ሴቶችን ብቁ በማድረግ እና እድል በመስጠት ፣ ሴቶች ላይ ለሚደርሱ ጥቃቶች ተገቢውን ቅጣት የሚሰጡ እና መሰል ፆታዊ ጥቃቶች እንዳይስፋፉ የሚሠሩ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎችን እና ግብዓቶችን መጋራት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እድገትን ለማፋጠን ሚናው የላቀ ነው።

ለሴቶች ተጠቃሚነት ሌሎች አካላትን ከመጠበቅ ይልቅም እራሳቸው የጉዳዩ ባለቤቶች ሴቶች ወደፊት የሚወጡበትን ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ራሳቸውን በኢኮኖሚም ሆነ በእውቀት እኩል ተወዳዳሪ ለማድረግ ተግተው መሥራት ይኖርባቸዋል። ለዓለም በርካታ ነገሮችን የሚሰጡት ሴቶች ከሰጪነት አልፎ ራሳቸውን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚተጉ መሆን ይገባቸዋል። በተጨማሪም ዕድሉን አግኝተው በተለየ ኃላፊነት ላይ ያሉ ሴት መሪዎችም ሴቶች ያላቸውን አቅምም ሆነ ችግር ለመረዳት የሚችሉ በመሆናቸው በተሰጣቸው ኃላፊነት ሕጉን በተከተለ መልኩ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚሠሩ እና ዕድል ላላገኙ እና በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች ድምፅ መሆን ይገባቸዋል። ሴት እናት፣ ሚስት፣ እህት፣ በአጠቃላይ የዓለም ሚዛን ጠባቂ የሆኑት ሴቶች የመሪነት ሚናቸውን ለመወጣት ዓለም ባላት ተፈጥሮ እኩል ተጠቃሚ ለመሆን የራሳቸውም ሆነ የሌሎች ኃላፊነት በጉልህ እንደሚጠበቅ ልብ ያለው ልብ ይበል ብዬ አበቃሁ።

ልዩ ዕትም

# ‹‹ዓለም በዕልህ እና በጦርነት የምትታመሠው ሴት ባለመደመጧ ነው››



- ወ/ሮ እየሩሳሌም ሹምዬ፣ በአፍሪካ ሕብረት የጥናት ትንተና ክፍል ዋና ሃላፊ አማካሪ

ምሕረት ሞገስ

ወልቃይት ፀገዴ ማይአይኒ በምትባል መንደር ውስጥ የተወለደችው እየሩሳሌም ሹምዬ፤ ገና በጨቅላነቷ ከሞት ጋር ታግላለች። ከቤተሰቦቿ ጋር ከአውሮፕላን የሚዘንበውን ቦንብ ሸሽታ በዋሻ ለቀናት ውላለች። ጊዜው 1980 ዎቹ አካባቢ በመሆኑ መንደራቸው የነበረው ጦርነት ቤተሰቦቿን እንዳያሳጣት በብዙ ስጋት ውስጥ አልፋለች።

ጦርነትም ቢኖር ሕይወት ይቀጥላል፤ በአካባቢው ትምህርት ቤት ስላልነበር ቀራቀር ከተማ አያቷ ቤት ሔደች። ትምህርት ቤት ስትገባ ባለምጡቅ ዓዕምሮነት ታዋቂነትን አተረፈች። ለእዚህ የበቃችው አባቷ አቶ ሹምዬ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የጤና መኮንን ስለነበሩ ለአካባቢው ሕብረተሰብ የህክምና አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ ልጆችን ሰብስበው ያስተምሩ ነበርና በእንግሊዘኛም ሆነ በአማርኛ ፊደል ለይቶ ከማወቅ ጀምራ ማንበብ እና መፃፍ እንዲሁም አንዳንድ መሰረታዊ የዕውቀት መነሻዎችን ከአባቷ በመማሯ ነበር።

ቀራቀር ገብታ በ1985 ዓ.ም ስትፈተን የአንደኛ ክፍል ትምህርትን ብቻ ሳይሆን የሁለተኛ ክፍል ፈተናንም በማለፏ በአንድ ጊዜ ለአንድ የግማሽ ዓመት መንፈቀ ትምህርት የ2ኛ ክፍል ትምህርቷን፤ በ2ኛው መንፈቅ ዓመት የ3ኛ ክፍል ትምህርቷን አልፋ 4ተኛ ክፍል ደረሰች። በ1986 ዓ.ም የእየሩሳሌም አባት አቶ ሹምዬ በሥራ ምክንያት ወደ ሽሬ እንዳስላሴ ሔዱ። በዚህ ምክንያት እርሷም ሽሬ ገብታ ፀሐዬ ትምህርት ቤት ለአንድ ዓመት ከተማረች በኋላ የ5ኛ ክፍል ትምህርቷ ደግሞ እምባ ዳንሶ በሚባል ትምህርት ቤት እስከ 8ኛ ክፍል ተምራ እዛው ሽሬ ከ9ኛ ክፍል መማር ጀመረች። ሆኖም የ10ኛ ክፍል ትምህርቷን ከመጀመሯ በፊት በ17 ዓመቷ ተዳረች።

ትዳር የመሰረተችው ባለቤቷን አውቃው ሳይሆን የእርሷ እና የባለቤቷ ቤተሰቦች ተነጋግረው በመስማማታቸው ነው። ባለቤቷ ከአዲስ አበባ ወደ ሽሬ ሔዶ አርብ ቀን ዓይታው እሁድ አገባት። አዲስ አበባ ይዟት መጣ። ሽመልስ ሃብቴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብታ መማሯን ቀጠለች። ምንም እንኳ ልጅ ብትሆንም ትዳር ይዛለችና ቤቷን ለመምራት ስትል የማታ ለመማር ተገደደች። ከተማው ለእርሷ ሰፊ በመሆኑ ተወዳዳሪ ለመሆን ያዳግተኛል የሚል ስጋት አደረባት። ትዳሯ ብቻዋን ከአጋሯ ጋር ሆና የምትመራው ሳይሆን የባለቤቷ ቤተሰቦች ቤት አንድ ላይ ብዙ ሆነው ስለሚኖሩ ተደራራቢ የሥራ ጫናዎችን መጋፈጥ ግድ ሆነባት።

በቤቱ ውስጥ እንደሰራተኛም እንደባለቤትም ሆና የ11ኛ ክፍል ትምህርቷን ስትከታተል እርግዝና ተከሰተ። በተጨማሪ 12ኛ ክፍል ስትደርስ ወንድ ልጅ ወለደች። ባለቤቷ የከተማ ሰው ሆኖ እርሷ የገጠር ሰው ሆና በዛ ላይ ልጅነት ተጨምሮበት ከባለቤቷ ጋር መግባባት አስቸጋሪ ሆነ። ያም ቢሆን በአራስነቷ የ12ኛ ክፍል የማጠቃለያ ፈተናን ወሰደች። ዩኒቨርሲቲ የሚያስገባ ውጤት አላመጣችም። ስለዚህ ኮሌጅ ለመግባት ተገደደች። ልጇን እያሳደገች ለመማር አድማስ ኮሌጅ ገብታ የቀን ትምህርት ጀመረች። በጥሩ ውጤት አጠናቀቀች። ነገር ግን በቀን ትምህርቷን መቀጠል አልቻለችም። አንደኛው ምክንያት የኮሌጁን ክፍያ መሸፈን አለመቻሏ ሲሆን፤ ሌላው በቤት ውስጥ በሥራ የሚረዳት ባለመኖሩ እና ልጇን ለማሳደግም በመቸገሯ ትምህርቷን ወደ ማታ አዘዋውራ ሥራ መፈለግ ጀመረች።

በጣም ጎበዝ መሆኗን የተረዱ የኮሌጁ መምህራን መስክረውላት ተወዳድራ አልፋ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመማሯ የላብራቶሪ እረዳት ሆና ተቀጠረች። አድማስ እየሠራች አድማስ እየተማረች ሌላ የመንግስት መስሪያት ቤት ደግሞ አመለከተች። በተወዳደረችበት የመንግስት መሥሪያ ቤት ለመቀጠር በቃች። ከዛ ሕይወት ቀለል ማለት ጀመረ። ከትዳር አጋር ጋር ቤት ተከራይተው ራሳቸውን ችለው መኖር ጀመሩ። ወ/ሮ እየሩሳሌም ሹምዬ ዛሬ አድማስ ኮሌጅ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዲግሪ ከመያዝ አልፋ፤ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሰላም እና ደህንነት ተቋም፤ በአፍሪካ ሰላምን በማስተዳደር ዙሪያ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቷን አጠናቅቃለች። በተጨማሪ ተቋምን በመምራት እና በማስተዳደር (ኦርጋናይዜሽናል ሊደር ሽፕ) የሁለተኛ ዲግሪዋን ተምራለች።

አሁን በአፍሪካ ሕብረት የጥናት ትንተና ክፍል ዋና ሃላፊ አማካሪ ሆና በማገልገል ላይ ትገኛለች። የሁለት ልጆች እናት ሆና ብዙ ውጣ ውረዶችን ብታልፍም የራሷን ተሞክሮዎች እና ሌሎችም የምታምንባቸውን የሕይወት ፍልስፍናዎችን አካታ «ራስን የመሆን ሚስጥር » የተሰኘ መፅሃፍ ፅፋ ሰሞኑን አስመርቃለች። ከዛሬዋ ከሴቶች ቀን እንግዳችን እየሩሳሌም ሹምዬ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እነሆ ብለናል። መልካም ንባብ፡-

> “ሴት በሃይል የተሞላውን የወንድን ጥንካሬ የማርገብ አቅም አላት። ነገር ግን ዓለም የሰጣት ሥርዓት ያ አይደለም። ዓለም በጦርነት እና በዕልህ የተሞላው ሴት ባለመደመጧ ነው።"

**አዲስ ዘመን፡- ትምህርት፣ ሴትነት፣ የቤተሰብ ሃላፊነት እንደገና የሥራ ሕይወት ይሔ ሁሉ አብሮ የሚሔደው እንዴት ነው?**

**ወ/ሮ እየሩስ፡-** የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሬ በተደጋጋሚ ከራሴ ጋር አወራ ነበር። ስራዬን ጥንቅቅ አድርጌ እሰራለሁ። ቤቴን በአግባቡ እመራለሁ። ዲግሪዬንም ከጨረስኩ በኋላ ቋንቋን ጨምሮ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስልጠናዎችን በመሳተፍ ሰርተፍኬት እሰበስብ ነበር። ጎን ለጎን አርት ስኩል እማር ነበር። ከባለቤቴ ጋር ልጆቻችንን ስናሳድግ ለብዙ ጊዜ ሰራተኛ አልነበረኝም። የማታ ስማር ምሽት ሶስት ሰዓት ቤቴ ደርሼ የምሳ ዕቃ እና ሌሎችም ለምግብ ማብሰያ እና መስሪያ አገልግሎት ሥራ ላይ የዋሉ ዕቃዎችን አጥባለሁ። በማግስቱ ቤተሰቤ የሚመገበውን ምግብ አስቀድሜ ምሽት ላይ አበስላለሁ። የምሳ ዕቃ ጠረጴዛ ላይ ደርድሬ ስጨርስ ገላዬን እታጠባለሁ። ከዛ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ማጥናት ያለብኝን አጠናለሁ። ለትምህርቴ የሚያግዙ መፅሃፎችን አነባለሁ።

በማግስቱ 11 ከአርባ እነሳለሁ። ቁርስ አቅርቤ የሚታሠረውን ምሳ አስሬ ልጆቼን ካዘጋጀሁ በኋላ የሚፀዳውን አፀዳድቼ ከቤቴ እወጣለሁ። በዛ ሰዓት እኔ ትልቅ ጉዳት የምለው ትምህርቴን ለማቆም ካስገደዱኝ ብቻ ነበር። ትምህርት ማቆም የሕይወቴ መጨረሻ ይሆናል ብዬ አምን ነበር። በትምህርቴ አልደራደርም ነበር። ከዛ ውጪ በምንም ነገር ላይ ታግሼ ኖሬያለሁ። እንደእኔ በልጅነታቸው ተድረው አዲስ አበባ የገቡ ሴቶችን ሕይወት አያለሁ። ያንን ሕይወት በፍፁም አልመኘውም ነበር። ስለዚህ ያ እንዳይሆን በፕሮግራም እየተመራሁ ራሴን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት አደርግ ነበር።

እኔ ላይ የነበረው ችግር ምንም ዓይነት ማህበራዊ ኑሮ ተሳትፎ አልነበረኝም። ሰርግም ሆነ ልደት ምርቃትም ሆነ ማንኛውም ጥሪ አልሔድም ነበር። ከሰኞ እስከ ዓርብ ቀን እየሠራሁ ማታ ማታ እማራለሁ። እሁድ እና ቅዳሜ ማጥናትን ጨምሮ ቤት ማፅዳት እና ልብስ አጠባን የመሳሰሉ ሌሎች ሥራዎች የሚከናወኑበት ቀናቶች ነበሩ። ከሰዎች ጋር የማወራበት ሰዓት አልነበረኝም። ነገር ግን ሰዓት ሳገኝ ከራሴ ጋር አወራ ነበር። ከዛም ቅዳሜ እና እሁድ ትምህርት ላይ መውሰድ ያለብኝ ስልጠና መኖሩን ካረጋገጥኩ ስልጠናዎችን እወስድ ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ከልጆች እና ከባለቤት ጋር ሰዓት ማሳለፍ ያስፈልጋል። ከቤተሰብ ጋር ሰዓት ነበረሽ?**

**ወ/ሮ እየሩስ፡-** መጀመሪያ አንድ ልጅ ብቻ ስለነበረችኝ ብዙ አልቸገርም ነበር። ልጄ የቤት ሥራዋን ሠርታ ያቃታትን ይዛ ትጠብቀኛለች። ከደከማት ትተኛለች። ከባለለቤቴ ጋር ወጥ አሙቄ ራት ከበላን በኋላ ደብተሯን አያለሁ። ከአባቷ ጋር በዛ ሰዓት እናወራለን። ቅዳሜ እና እሁድ ደግሞ የቤቱን ሥራ እየሠራሁ ከእርሷ ጋር ጊዜ አሳልፍ ነበር። ማራሚያዋት ብዙም አስቸጋሪ አልነበረችም። ሁለተኛው ልጅ አማኑኤል ሲወለድ ግን ከፍ ያለ እንክብካቤ ይፈልግ ነበር። ስለዚህ መደበኛውን የማታ ትምህርት እስከ ዲግሪ ተምሬ በማጠናቀቄ በቅርበት እርሱን የምንከባከብበት ጊዜ አላጣሁም። ትምህርቱንም በደንብ እከታተለው ነበር።

ምንም እንኳ ከዕለት ወደ ዕለት ደምወዜ እያደገ ሕይወቴ እየተሻሻለ ቢሔድም ደስተኛ አልነበርኩም። የምፈልገውን ሕይወት እየገፋሁ እንዳልሆነ ይሰማኝ ነበር። ምክንያቱም እኔ ውስጤ ነፃ ነው። ይህንን አድርጊ ይህንን አታድርጊ ተብዬ መኖር አልፈልግም። ሃሳቤን ጠረጴዛ ላይ አቅርቤ የሌላው ሰው ሃሳብም በጠረጴዛ ዙሪያ ቀርቦ ተማምኖ ተነጋግሮ መቀጠል እንጂ ሁሉ ነገር ተጭኖብኝ ሁኚ፣ ስጪ፣ አምጪ እየተባልኩ መኖር አልፈልግም። ደስተኛ ሳልሆን ሕይወቴ እንዲያልፍ አልፈልግም። በራሴ ዙሪያ የምፈልገውን አድርጌ መኖር እፈልጋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- እና ልጆች ተወልደዋል። ብዙ ሰው ስልጆቹ ሲል የማይፈልገውን ሕይወት እየመራ ሕይወቱ ያልፋል። አንቺ ምን አደረግሽ?**

**ወ/ሮ እየሩስ፡-** የእኔ ሕይወት ትንሽ ይለያል። መጀመሪያም ትዳር መሰረትኩ ይባል እንጂ የራሴ የምለው የትዳር ሕይወት አልነበረኝም። ከላይ እንደገለፅኩት አገባሁ፤ የገባሁት ግን የባለቤቴ ቤተሰቦች ቤት ነው። ሥራ መሥራቱ ይህን አድርጊ ሲባል ከመታዘዝ አልፎ፤ ፈጣሪ የሚሰጠውን የምወልደውን ልጅ እንኳን እኔ ፆታውን እንደፈለግኩ መወሰን እንደምችል አድርጎ ቅሬታ የማቅረብ ሁኔታ ነበር። ትዳሩ የተመሠረተው ፍቅር ላይ አልነበረም። ጭራሽ መተዋወቁም አልነበረም። ገና ከመጀመሪያው ትዳሩ ተዋውቆ፣ ተግባብቶ ተፋቅሮ ኑሮን ለማጣጣም ሳይሆን ትዳር የሚባል ካምፓኒ እንዲመሠረት እና ልጅ እንዲወለድ ብቻ ታስቦ ነው።

የነበርኩበት ሁኔታም ከትዳር በኋላ ፍቅር ለመመስረት የሚመች አልነበረም። በብዙ አስተሳሰብ ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች የሚኖርበት ቤተሰብ ሲሆን፤ ባለትዳር የሆነው እና ያልሆነው፤ በቤት ውስጥ ለመስራት የተቀጠረው

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ‹‹ዓለም በዕልህ እና...

ከገጽ 6 የዞረ

እና ያልተቀጠረው አይነሳም ነበር። ብዙ የሥራ ጫናም ነበር። ወጥ እሰራለሁ፤ እንጀራ እጋግራለሁ። ከዛ አልፎ ያለ አቅሜ ብርድ ልብስ እና ጋቢ ከማጠብ ጀምሮ ከበድ ያሉ ሥራዎችን እንድሰራ እገደድ ነበር። ያ ደግሞ በትዳሬ ላይ ተስፋ እንድቆርጥ አድርጎኛል። ቤተሰቦቹ ከፈለግሽ ኑሪ ካልፈለግሽ መሔድ ትቺያለሽ አይነት አስተያየት ነበራቸው።

ልጅ ይዤ ወደ ሽሬ ብሔድ ካለው ሕይወት የባሰ ጉስቁልና እንደሚያጋጥመኝ በማመን ታገስኩኝ። ከዛ ሕይወት የሚያወጣኝ ትምህርት መሆኑን በማመን ከትምህርቴ ጋር ተጣበቅኩኝ። በአብዛኛው እኔ የምፈልጋቸውን ዕውቀቶች ልቀስምባቸው የምችልባቸው መፅሐፎች የተፃፉት በእንግሊዘኛ ነው። እንግሊዘኛውን መፅሐፍ አንብቦ መረዳት ከባድ ሆነብኝ። ስለዚህ የቋንቋ ትምህርት ቤት መግባት እና ገንዘብ ሲገኝ ደግሞ የግል የቋንቋ አስተማሪ መቅጠር የግድ ሆነ። ስለዚህ እንደሌላው ሰው ገንዘብ ሳገኝ ልብስ እና የቤት ዕቃ ከመግዛት ይልቅ ወደ ፊት ለመሔድ ባለኝ መንገድም ሆነ ገንዘብ በሙሉ እጠቀም ነበር።

እቁብ እገባ እና ሲደርሰኝ የማውለው ለትምህርት ነበር። ባለቤቴም በተደጋጋሚ ትምህርት ቤት እንዳልሔድ መማሬን እንዳቆም ይገፋኝ ነበር። ለምሳሌ ቀን የሚያደክም ሥራ ሠርቼ። ማታ ተምሬ። በታክሲ ተጋፍቼ ቤቴ ስደርስ ሥራ ይጠብቀኛል። ገንዘብ ሳገኝ ሰራተኛ ብቀጥርም የሆነ ሰበብ እየፈለገ ሠራተኛዋ እንድትባረር ያደርጋል። እንደውም ድጋፍ እየተደረገልኝ እንዳልሆነ እንደውም ለማደናቀፍ ጥረት እየተደረገ መሆኑን እየተረዳሁ፤ እንዳላየ አልፋለሁ። የሆነ ቀን ላይ በቃ ምንም ድጋፍ አልፈልግም። እራሴን ራሴ ከደገፍኩ በቂዬ ነው ብዬ መደምደሚያ ላይ ደርሻለሁ።

በጣም ያለቀስኩባቸው ጊዜያቶች አሉ። ማንም ምን ሆነሽ ነው ብሎ ሳይጠይቀኝ ሲቀር፤ ለራሴ ያለሁት ራሴ ብቻ ነኝ ከማለት አልፌ በምንም ነገር እደራደራለሁ በትምህርቴ ላይ ግን አልደራደርም ብዬ ቀይ መስመር አሠመርኩ። ሰራተኛ አይኖርም ስባል ችግር የለም ብዬ ቀጥያለሁ። ትምህርት ቤት አትሔጂም ስባል ግን በምንም መልኩ አልሰማም አልኩ። በሌላ በኩል በየቀኑ ሥራ ከመያዝ ጀምሮ የማገኘው ውጤት የደመወዝ እድገቱ እና ሌላ ሌላውም እኔን የበለጠ እያስደሰተኝ ሃይል እየሰጠኝ ቀጠለ። ሌሎች ሰዎች ያላቸው እይታ እየተሻሻለ መጣ።

በአግባቡ ትልልቅ መፅሃፎችን አንብቤ ለመረዳት ሞከርኩኝ፤ ተሳካልኝ። በየቀኑ የቋንቋ ችግርም እየተቃለለልኝ መጣ። ከንባቤ በኋላ የተረዳሁት ሰዎች ዝቅ አድርገው ያዩኝ የነበረው እኔ ፈቅጄላቸው እንጂ እኔ ባልፈቅድላቸው ያ አይሆንም። አንዱ ለአንዱ እንዳልተፈጠረ ሁሉም ለየራሱ እንደተፈጠረ አንዱ ከሌላው ጋር በመልካም ፍቃዱ ተባብሮ መኖር እንዳለበት ተረዳሁ። ብቁ እና በቂ ከሆኑ ማንም ማንንም ምንም ማድረግ እንደማይችል አንብቤ አወቅሁ።

የሚጠቅመኝን እና የማይጠቅመኝን ለይቼ በማወቄ፣ አተኩሬ ራሴ ላይ በመስራቴ እና ጊዜዬን ምን ላይ ማባከን እንዳለብኝ በጊዜ ገባኝ። ስለዚህ ምንም ዓይነት ደቂቃ የሆነ ቦታ አላባክንም። ምክንያቱም እያንዳንዱ ደቂቃ ለእኔ ዋጋ አለው። የመስሪያ ቤት ምሳ ሰዓት ላይ እንኳን ከጓደኞቼ ጋር ሰዓቱን አላሳልፍም። የምበላው በላፕ ቶፕ እያነበብኩ ስለሆነ በእጄ አልበላም። በማንኪያ እየበላሁ አነባለሁ። የትኛውንም ደቂቃ በማይረባ ጉዳይ ማሳለፍ አልፈልግም።

**አዲስ ዘመን፡- የመንግስት መስሪያ ቤት ሆነሽ እንዴት ነበር?**

**ወ/ሮ እየሩስ፡-** የነበርኩበትን ተቋም በዝርዝር በሁለተኛው መፅሐፌ ላይ እገልፀዋለሁ። እንደውም ሁለተኛው መፅሐፌ በዚሁ የመንግስት ተቋም ላይ ያተኮረ ነው። የገባሁበት ተቋም ትልቅ የተባለ ትልልቅ ባለስልጣናት የሚሰሩበት እና የሚገኙበት ተቋም ነው። እኔ በዕውቀት ይበልጡኛል ብዬ ስላሰብኩኝ አብሬያቸው ለመነጋገር እንኳን በጣም እሰጋ ነበር። ጠረጴዛ ላይ ለእነርሱ የሚመጥን ሃሳብ ይዤ ለመቅረብ ከራሴ ጋር ተነጋግሬ ሙሉ ሆኜ ለመቅረብ ማንበብ ጀመርኩኝ።

ስለኢኮኖሚ፣ ስለፖለቲካ፣ ስለ ማህበራዊ ጉዳይ እና ስለሌሎችም በስፋት ሳነብ፤ እነርሱ የሚቀርቡት ሃሳብ አንሶ ታየኝ። እንደውም አንዳንዴ ሲሳሳቱ እስከማረም ደረስኩኝ። እኔ በየቀኑ ሳነብ በየቀኑ በራሴ ላይ መሻሻሎችን ማየት ጀመርኩ። ክፍተቴን ካወቅኩኝ ክፍተቴን ሳልሞላ ማደር አልችልም። ብዙ ሰዓት በጣም አነባለሁ። አንዳንድ ቀን ምሳዬን ራሱ በፌስታል ይዤ በማንኪያ በልቼ ፌስታሉን ቅርጫት ውስጥ ከትቼ ማንበቤን እቀጥላለሁ። አንዳንዴ ለምሳዬ ቆሎ ገዝቼ በሶፍት ላይ ቆሎዬን ዘርግፌ እየበላሁ አነባለሁ። ሻይ መጠጣት ቡና መጠጣት አቆምኩ። ውሃ እጠጣለሁ።

**አዲስ ዘመን፡-ሃሳብን የማስተሳሰፍ ችግር አላጋጠመሽም?**

**ወ/ሮ እየሩስ፡-** መጀመሪያ ከላይ እንደገለፅኩት ለጠረጴዛ የሚመጥን ሃሳብ አይኖረኝም ብዬ ምንም አልናገርም ነበር። ለሶስት ዓመት አካባቢ ማዳመጥ ብቻ ነበር። በሰርቪስ ከስራ ባልደረቦቼ ጋር ስሔድ በታብሌት መፅሃፍ አነባለሁ። መውረጃዬ ሲደርስ ሰው ይነግረኛል እንጂ፤ አንዳንዴ የት እንዳለሁ አላውቀውም ነበር። ምክንያቱም የምፈልገው ማንበብ ብቻ ነው። ሳነብ ደግሞ የማነበው ከልቤ ነው። መንገድ ላይም የምሔደው ያነበብኩትን እያሰላሰልኩ ነው። ሥራ ስሠራም ዩቲዩብ ከፍቼ ጥቁር አሜሪካን ሴቶች እንዴት ሕይወታቸውን እንደተጋፈጡ እሰማ ነበር።

ከዛ በኋላ ግን ተሰማም አልተሰማ፤ ለውጥ አመጣም አላመጣ የእኔ የምለውን ሃሳብ ማስተላለፍ ጀመርኩ። ባገኘሁት አጋጣሚ ባገኘሁት መድረኮች ላይ ሁሉ ዝም አልልም፤ እናገራለሁ። ለምን እንዲህ ሆነ እያልኩኝ መጠየቅ ጀመርኩ። ምክንያቱም እንደአገርም፣ ሃላፊነት እንደሚሰማው ሰውም ሆነ እንደአንዲት ሴት ስህተቶችን ማየት ጀመርኩ። እዛ ላይም ግን ራሴን የተሻለች ለማድረግ እሞክራለሁ። ሁል ጊዜ አልተኛም። ሁሌ አነባለሁ፤ ያገኘሁትን እውቀት አደንቃለሁ። ከዛ ከትንሽ ጊዜ በኋላ የማውቀውን ለማካፈል መሞከር ጀመርኩ። በተለይ እንደእኔ ዓይነት ከሆኑ ሴቶች ጋር ከወጣት ወንዶች ጋር እናወራለን። አንዳንዴ የማስበውን እፅፈዋለሁ። አሁን የታተመው መፅሐፍ የዛን ጊዜ መፅሐፍ ይሆናል ብዬ ባላስብም ስፅፍ የነበረው ተጠረቃቅሞ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከመንግስት ሠራተኝነት እንዴት ወጣሽ?**

**ወ/ሮ እየሩስ፡-** ማደግ መለወጥ የሚፈልግ ሰው ሁል ጊዜም የሚለውጠውን መንገድ ይፈልጋል። በመንግስት ሠራተኝነት የማመጣው ለውጥም ትንሽ እንደሆነ፤ ከግለሰብ አንፃር የሚኖረኝ መሻሻልም ጥቂት ሊሆን እንደሚችል ተገነዘብኩ። ስለዚህ ለአገሬም ለልጆቼም ሆነ ለራሴ የተሻልኩ ሆኜ ለመገኘት ራሴ ላይ እየሠራሁ መጣሁ። ከዛ በኋላ አጋጣሚዎችን መፈለግ እና እድሎችን ማማተር ጀመርኩ። ከሁለት ዓመት በላይ ስፈልግ ለትንሽ ደመወዝ ጭማሪ ሳይሆን ለመሠረታዊ ለውጥ በመትጋቴ አጋጣሚውም ወደ እኔ መጣ። በመጀመሪያ በአፍሪካ ሕብረት ሥራ መኖሩን ስሰማ ካለፍኩኝ ልሞክር ብዬ መስሪያ ቤቴን ጠየቅኩኝ፤ ፈቃድ ያስፈልግ ነበር። የበለጠ ለመማርም ራሴን የተሻለ ቦታ ላይ ለመድረስ በ2010 ዓ.ም ‹‹ተቋሙን እንድለቅ ፈቀዱልኝ። ›› አልኩ ተፈቀደልኝ።

**አዲስ ዘመን፡- የአፍሪካ ሕብረት ተወዳድሮ መቀጠር ብዙዎች ለማሰብ ራሱ አይሞክሩትም አልፋለሁ ብሎ ማሰብስ ከባድ አይደለም?**

**ወ/ሮ እየሩስ፡-** ትክክል ነሽ ቀላል አይደለም። ሌሎችም እንዲህ እንደሚያስቡ አውቃለሁ። እኔም እንደተወዳደርኩ አልፌ በአንድ ጊዜ አልተቀጠርኩም። ቅጥር መውጣቱን ስሰማ እንደማላልፍ ልቦናዬ እያወቀ ቢያንስ ፈተናውን ልየው ብዬ ተፈተንኩ። እናም እንደገመትኩት ወደቅኩ። ውጤቱ ገና ሳይገለፅ እንደምወድቅ አውቄያለሁ፤ ምክንያቱም ለምጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ እየሰጠሁ አልነበረም። አንደኛ አንዳንዶቹ ጥያቄዎች እንደውም አልገቡኝም ነበር። ነገር ግን ተፈትኜ ስወጣ እንደምወድቅ ባውቅም በቀጣይ የጎደለኝን አሟልቼ ተወዳድሬ እንደምቀጠር እርግጠኛ ነበርኩ።

በአጋጣሚ አንድ ኖርዌ የኖረ ዘመዴ ቤቴ መጥቶ ሲያጣኝ የፈለገችውን ታድርግበት ብሎ ገንዘብ አስቀምጦልኝ ሔደ። ብዙ ሰዎች እንደሚያደርጉት ልብስ ወይም የቤት ቁስ አልገዛሁም። በግሌ የእንግሊዘኛ ቋንቋ አስተማሪ ቀጥሬ ተማርኩ። ቋንቋውን የማወቂያ ቴክኒክ ላይ ትኩረት በማድረግ ከሁለት ዓመት በኋላ ዕድሉ በድጋሚ ሲመጣ፤ እንደማልፍ እርግጠኛ ነበርኩ። እንደገመትኩት አልፌ ሥራ ጀመርኩኝ።

**አዲስ ዘመን፡- አፍሪካ ህብረት ውስጥ መሥራት እንዴት ነው?**

**ወ/ሮ እየሩስ፡-** ለስድስት ወር ያህል ልምምድ አድርጌያለሁ። ሁሉም የአንድ አገር ሰው አይደለም። ከተለያየ የአፍሪካ አገራት የመጡ ሰዎች ናቸው። የተለያየ የቋንቋ የተለያየ የሥራ ልምድ እና ባህል ያላቸው ናቸው። እርሱን መልመድ እና ለስራ በሚመች መልኩ መዋሃድ ያስፈልጋል። እኔ የዋና ሃላፊው አማካሪ በመሆኔ እና ዋና ሃላፊውም በተደጋጋሚ ለሥራ ከሀገር ስለሚወጣ በተከታታይ እንግዶችን አዘጋጃለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በዓለም ዙሪያ የሴቶችን ፈተና እንዴት ታይዋለሽ?**

**ወ/ሮ እየሩስ፡-** በእርግጥ ዓለም ለሴቶች ምቹ አይደለችም እንላለን። ዓለም እየተሠራችበት የመጣችበት ሂደት ለሴቶች ምቹ አይደለም። ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ቻይና ውስጥ እንደውም ሴት እንደዕቃ ትታይ ነበር። ባል ሚስቱን ከቤቱ እንደ አንድ ዕቃ ይቆጥራት ነበር። ስለዚህ አንድ ቻይናዊ ሚስቱን የመምታት አልፎ ተርፎ የመግደል መብት ነበረው። ሂደቱ በጣም ረዥም ነው። ሴት ብቁ እንዳልሆነች፤ ነፍሷ እንኳ የእርሷ እንዳልሆነ ይታሰብ ነበር።

ተፈጥሮ ወንዶችን ጠንካራ ሴቶችን ለስላሳ አድርጎ ሚዛኑን ጠብቆ ቢፈጥረንም፤ ዓለም የወንዶችን ጥንካሬ ወደ ሃይል ሲወስድ፤ የሴቶችን ልስላሴ ግን እንደስንፍና አትችልም ለማለት ዝቅ ለማድረግ ተጠቀመበት። ስለዚህ እርሷን እና ሃሳቧንም ዝቅ ማድረግ መጣ። ነገር ግን ሴት ተፈጥሮን የማስቀጠል ምንጭ ናት። ከሁለቱም የወጣ ዘር ተዋህዶ ሰው ሆኖ የሚወለደው ከሴት ነው። የተሻለ ትውልድ እንዲፈጠር ዋናውን ድርሻ የምትይዘው ሴት ናት። የዓለም ስርዓት ግን ሴቶችን በተሳሳተ መንገድ አስቀመጠ።

ሴት በሃይል የተሞላውን የወንድን ጥንካሬ የማርገብ አቅም አላት። ነገር ግን ዓለም የሰጣት ሥርዓት ያ አይደለም። ዓለም በጦርነት እና በዕልህ የተሞላው ሴት ባለመደመጧ ነው። ሃይማኖቶች የተለያየ አስተምሮ አላቸው። ወደ ታች እየወረደ ሲመጣ የሴት ድርሻ ምግብ ማብሰል ላይ ብቻ እንደሆነ ይታሰባል። ይህ ፍፁም የተሳሳተ ሃሳብ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ።**

**ወ/ሮ እየሩስ፡-** እኔም አክብራችሁ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።



# ‹‹በምድር ላይ ትልቁ ደስታ ያለው ለሰው በማካፈል ውስጥ ነው››

- ዶክተር መክሊት ፊሊጶስ
የጉድ ሰመሪታን ፋሚሊ ሰፖርት ኦርጋናይዜሽን መስራችና ሥራ አስኪያጅ

**ማህሌት አብዱል**

ተወልደው ያደጉት በሃዋሳ ከተማ ውስጥ ነው። በሐዋሳ ዩኒቨርስቲ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንዲሁም በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን የማስተርስ ዲግሪያቸውን ሰርተዋል። በተጨማሪም በፈረንሳይ ከሚገኘው አሴንሺያ ቢዝነስ ስኩል ከሚባል ተቋም በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። በተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት በሙያቸው ተቀጥረው ለዓመታት አገልግለዋል። ይሁንና ከልጅነታቸው ጀምሮ ችግረኞችን የመርዳት ፅኑ ፍላጎት የነበራቸው በመሆኑና በተለይም በአስቸጋሪ ህይወት ያሉ ሴቶችን ህይወት የመታደግ ራዕይ ስለነበራቸው የመንግስት ሥራቸውን በመተው ጉድ ሰመሪታን ፋሚሊ ሰፖርት ኦርጋናይዜሽን የተባለ የበጎ አድራጎት ማዕከል መስርተዋል።

በዚህ ማዕከል በዋናነት ኑሮ ግድ ብሏቸው በወሲብ ንግድ ውስጥ የገቡ ሴቶችንና በተለያየ ምክንያት ወደጎዳና የወጡ ህፃናት ድጋፍ ያደርጉላቸዋል። በርካታ ሴቶች ስልጠና እና ድጋፍ በመስጠት ራሳቸውን እንዲችሉ በማድረግ፤ እንዲሁም በሺዎች የሚቆጠሩ ህፃናት ከቤተሰባቸው ጋር የማቀላቀልና የነገው ሃገር ተረካቢ ትውልድ እንዲሆኑ የማብቃት ሥራ በመስራት ለሃገር እድገት አወንታዊ ሚና እየተጫወቱ ያሉ ሴት ናቸው። እኛም ዶክተር መክሊት ፊሊጶስን ለዛሬው የሴቶች ቀን ልዩ እትም እንግዳችን አድርገን ስናቀርብ፣ በሕይወት ተሞክሯቸውና በሥራቸው ዙሪያ ልምዳቸውን ለማካፈል በማሰብ ነው። መልካም ንባብ!

**አዲስ ዘመን፡-** **ወደ በጎአድራጎት ሥራ የገቡበትን አጋጣሚ ያስታውሱንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**ዶክተር መክሊት፡-** ወደዚህ ስራ ከመምጣቴ በፊት በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የመስራት እድል አግኝቻለሁ። ከእነዚህም መካከል ገቢዎችና ጉምሩክ፣ ኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ ጥራትና ደረጃ ኤጀንሲና ገንዘብ ሚኒስቴር የመሳሰሉ ተቋማት ተጠቃሽ ናቸው። በሐዋሳ ዩኒቨርስቲ በምማርበት ጊዜ ጥሩ ውጤት ያላቸውን ተማሪዎች እየመለመሉ የተለያዩ መስሪያ ቤቶች እንዲቀጠሩ ይመቻችላቸው ስለነበር ነው እኔም በእነዚህ ተቋማት የመስራት እድሉን ያገኘሁት። ወደዚህ ሥራ ልገባ የቻልኩት ከልጅነቴ ጀምሮ በአካባቢያችን የእኛን እርዳታ የሚሹ በርካታ ሰዎችን እያየሁ በማደጌ የተቸገሩትን ሁሉ የመርዳትና የማገዝ ፍላጎት ስለነበረኝ ነው። የሰው ልጅ ሲኖር ከራሱ አልፎ ለሌላው መኖር አለበት የሚል አቋም አለኝ።

አንድን የተቸገረ ሰው በምን መልኩ መርዳት እችላለሁ? የሚለው ጥያቄ ከልጅነቱ ጀምሮ ይመላለስ ነበር። ልጅ ሆኜ እንኳን እኔን ብለው የሚመጡ ብዙ የተቸገሩ ሰዎች ነበሩ። የቤተሰቡን ልብስ ሁሉ እያወጣሁ በመስጠት እታወቃለሁ። እናም ሰውን የመርዳት ፍላጎት ከልጅነት ያለ ህልሜ ነው። ምንም ባይኖረኝ እንኳን ሰዎችን ለማገዝ ወደምችልበት መፍትሔ ከመፈለግ አልቦዝንም ነበር። ምክንያቱም ደግሞ ሰውን የምንረዳው ስላለን ብቻ አይደለም፤ ወይም በገንዘብ ብቻ አይደለም ሰውን የምንረዳው። የሰውን ችግር ማዳመጥ ራሱ መርዳት ነው፤ ለአንድ ሰው ጊዜ መስጠት ራሱን ሰውን መርዳት ነው። ምክር መስጠት አልያም መርዳት ከሚችል ሰው ጋር ማገናኘትም ሰውን መርዳት ነው። እኔ ምንም ገንዘብ ባልነበረኝና ተማሪ በነበርኩበት ሰዓት ብዙ የማግዛቸው ሰዎች ነበሩ። ጊዜ በመስጠት፤ በተለይ የአዕምሮ በሽተኞችን ቤታቸው ድረስ በመሄድ በመንከባከብ፣ ምግብ በመስራትና ቤታቸውን በማፅዳት የበኩሌን ድጋፍ አደርግላቸው ነበር። እናም ከዚያ የጀመረ ነው የበጎ አድራጎት ሥራዬ።

**አዲስ ዘመን፡-** **በልጅነትዎ ለተቸገሩ ሰዎች ያደርጉት በነበረው ድጋፍ የቤተሰቦችዎ ምላሽ ምን ነበር?**

**ዶክተር መክሊት፡-** ትልቁ ነገር ይህ ራዕይ በውስጤ ያለ ነው። እግዚአብሔር በውስጤ ያስቀመጠው ሸክም ስለሆነ ውስጤ ያመነበትን ነበር የማደርገው። በእርግጥ በጣም ጥሩ በሆነ ቤተሰብ ውስጥ ነው ያደኩት። ቤተሰቦቼ በጣም የስራ ሰዎች ናቸው ፤ የጤና ባለሙያዎች ስለነበሩም የሰውን ችግር ይረዳሉ። ደግሞም በመንፈሳዊ ህይወታቸው ጠንካራ ስለነበሩ እኛንም ሲያሳድጉንም በጣም በጥንቃቄ ነበር። ከዚያም አልፎ ደግሞ በተለያየ በጎ አድራጎት ሥራዎች ይሳተፋሉ። በነገራችን ላይ እኛ ቤት በጣም ብዙ ሰው ተምሮ ፤ ተመርቆ ጥሩ ደረጃ ላይ መድረስ ችሏል። ለትምህርት በጣም ትኩረት ይሰጥ ስለነበርም እዚያ ቤት ያደገ ሰው በትንሹ ማስተርስ የሌለው የለም። ማንም ሰው መጥቶ፤ ተምሮ፤ ተለውጦ የሚወጣበት ቤት ነው። እኔ ደግሞ እንዳልኩሽ ሰውን የመርዳት ነገር በውስጤ የነበረ ሸክም ነው።

ትዳር ከያዝኩም በኋላ ይኸው የበጎ-አድራጎት ሥራዬ አልቆመም። በምችለው አቅም ሁሉ ችግረኞችን ማገዝ እንዳለብኝ አስባለሁ። ግን ደግሞ እንደመደበኛ ሥራዬ አድርጌ የያዝኩበት አጋጣሚ አንድ ቀን መንገድ ላይ አንዲት ልትወልድ የደረሰች ነፍሰጡር ሴት ያገኘሁት ሁኔታ ነው። ይህች ሴት ተደፍራ አርግዛ፤ መውደቂያና ማረፊያ ስለሌላት ወደ ጎዳና ወጣች። ቀኗ ደርሶ ልትወልድ ስትልም የሚያስጠጋት ባለመሆኑ ጎዳና ላይ እንዴት ትሆናለች የሚለው ነገር ሃሳብ ስለሆነብኝ መኖሪያ ቤቴ አመጣኋትና አንድ ክፍል ውስጥ አስቀመጥኳት። በዚህ ጊዜ በጣም ብዙ ሰው ‹‹እንዴት እንዲህ አይነት አደገኛ እርምጃ



ፎቶ-ሐዲስ አብረሃ

“አብዛኛው ህፃን ቤተሰብ ያለውና በግጭት ምክንያት ነው ከቤት የሚወጣው። ኢኮኖሚ ችግርና በአቻ ግፊት የወጡም አሉ። በመሆኑም እያንዳንዱ ልጅ ታሪክ ለማጥናት ይሞከራል፤ በመቀጠልም የስነ-አዕምሮ ሃኪሞች፤ የጤና መኮንኖችና ነርሶች አማካኝነት በአካልም በስነ-ልቦናም ጤናማ እንዲሆኑ ይሰራል።"

ትውስጃለሽ? የማታውቂያትና ልትወልድ የደረሰች ሴት አንድ ነገር ብትሆንብሽ ተጠያቂ ትሆኛለች›› ይሉኝ ነበር። ግን ኃላፊነቱን ወስጄ አስፈላጊውን ድጋፍ አደረኩላት፤ የፈጣሪ እርዳታ ታክለበትና በሰላም ወለደች፤ እስካሁን ትጠይቀኛለች፤ ልጇ አሁን አስር ዓመቱ ነው፤ ጥሩ ሥራ ትሰራለች፤ ሌላ ትዳርም ይዛለች። እናም በዚያ ነው የተጀመረው።

ከእርጉዟ ሴት ተጀምሮ ብዙ ለማህበራዊ ችግር የተጋለጡ ሰዎችን ከባለቤቴ ጋር በመሆን ለማገዝ ሞክረናል። በነገራችን ላይ ባለቤቴም ለዚህ ሥራ ልቡ ክፍት ነው። የእሱም ራዕይ ተመሳሳይ ነው። እናም ከባለቤቴ ጋር በመሆን በመጀመሪያ አስር ጎዳና ላይ የነበሩ፤ በተለይ ደግሞ የአዕምሮ ህመም የነበራቸውን ሰዎች በመንከባከብ በማስተማር ፤ የእነሱን ለውጥ በማየት መኖር የመጀመርነው። እነዚያ ሰዎች ከእኛ ጋር በቤታችን ውስጥ ነበር ይኖሩ የነበሩት። ብዙ ጊዜዬንም እነሱን በመንከባከብ ነው የማሳልፍ የነበረው። ያ ደግሞ ከፍተኛ እርካታ ይሰጠኛል። ምክንያቱም በምድር ላይ ትልቁ ደስታ ያለው ለሰው በማካፈል ውስጥ ነው። የሰው ችግር ተፈቶ ስመለከት በጣም እደሰታለሁ። ከትንሽ ነገር ተነስቶ ቁምነገር ላይ ሲደርሱ ፤ ችግራቸው ተፈቶላቸው ማየትን የመሰለ ደስታ የሚሰጠኝ ነገር የለም። ደግሞም የበለጠ ለመስራት ያበረታታኛል።

ከዚህ በመነሳት ይሄን የድጋፍ ሥራ እንዴት ነው ወደተቋም መቀየር የሚለውን በማሰብ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ስም ፈቃድ አውጥቼ መስራት ጀመርኩኝ። ይህ ሲሆን ደግሞ ባለሙያ ከመቅጠር ባለፈ ፤ ገቢ ማግኘት የሚቻለበት ሁኔታ በመፍጠር ራሱን ችሎ እንዲቆም ጥረት ስናደርግ ቆይተናል። አሁን እንደተቋም ከተቋቋመ ስድስት ዓመቱ ነው። ከተቋቋመ በኋላ በርካታ ሥራዎችን ሰርተናል። በሴቶችና ህፃናት ላይ ትኩረት አድርገን እንዲሁም የተለያዩ ለማህበራዊ ችግር የተጋለጡ ሰዎች ላይ ትኩረት በማድረግ በርካታ ሥራዎችን ሰርተናል። ከእነዚህ ውስጥ ከ300 በላይ ከጎዳና እና ህይወት አስገድዷቸው በወሲብ ንግድ ከሚተዳደሩ ሴቶችን ህይወት መለወጥ ችለናል። ከሰባት እስከ ስምንት ወር ማዕከላችን ላይ እንዲቆዩ በማድረግ ስልጠናዎችን ሰጥተን ራሳቸውን እንዲገኙ በማድረግ ፤ ሙያ እንዲኖራቸው ተደርጎ፤ ተፈትነው ብቃት ማረጋገጫ ይዘው ብቁ ሆነው ወደ ሥራ እንዲቀጠሩ አድርገናል። ከዚያም ባለፈ ትናንሽ ስራዎችን በራሳቸው እያስጀመርን ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ችለናል። አሁን ላይ በማዕከላችን ውስጥ 320 የሚሆኑ ሴቶች አሉ።

ይህ የሚያሳየው ሰውን መርዳት ከትንሽ ነገር መጀመር እንደምንችል ነው። ይህ ውጤት የመጣው በትጋት ቀን ከሌሊት ስለምንሰራ ነው። ከእኔ ጋር ያሉ ባልደረቦቼም በትጋት ነው የሚሰሩት። ምክንያቱም ደግሞ በሰው ህይወት ላይ መስራት በጣም ከባድ ነው። ከ1ሺ 74 በላይ ከጎዳና ላይ ተነስተዋል። እነኚህ ከጎዳና ላይ የተነሱ ህፃናት በተለያዩ ሱስ ውስጥ የነበሩ፤ ትምህርት የማይማሩ፤ በተለያየ የስነ-ልቦና ቀውስ ውስጥ የነበሩ ፤ ለብዙ ጥቃት የተጋለጡ ነበሩ። በተለይ በዚህ ዘመን ማንኛውም ህፃን ልጅ መማር አለበት። ምክንያቱም ያልተማረ ልጅ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ አይከብድም።

ብዙ ህፃናት መንገድ ላይ የምናገኛቸው ብርድና ራቡን ለመቋቋም ሲሉ ማስትሽና ቤኒዚን እየሳቡ ነው። ለተለያየ ሱስ ተጋላጭ ሆነው ለጤና ቀውስ ተጋልጠውም ነው የሚገኙት። የምግብ ማጣት ብቻ ሳይሆን ፍቅር የማያገኙና በቤተሰብ ናፍቆት የተጎዱ ስለነበሩ እነዚህን ልጆች ከገቡበት ሁኔታ ለማውጣት መጀመሪያ እንዲያገግሙ ነው የሚደረገው። ራሳቸውን እንዲያገኙና የተመጣጠነ ምግብ ተመግበው እንዲጠነክሩ ይደረጋል። በመቀጠልም መሰረታዊ ትምህርት እንዲያገኙ በኋላ ቤተሰብ ነው የምናፈላልግላቸው። አብዛኛው ህፃን ቤተሰብ ያለውና በግጭት ምክንያት ነው ከቤት የሚወጣው። ኢኮኖሚ ችግርና በአቻ ግፊት የወጡም አሉ። በመሆኑም እያንዳንዱ ልጅ ታሪክ ለማጥናት ይሞከራል፤ በመቀጠልም የስነ-አዕምሮ ሃኪሞች፤ የጤና መኮንኖችና ነርሶች አማካኝነት በአካልም በስነ-ልቦናም ጤናማ እንዲሆኑ ይሰራል። በመጨረሻ ቤተሰቡን አፈላልገን የማስታረቅና የማገናኘት ሥራ ነው የምንሰራው።

ወላጅ የሌለው ደግሞ የቅርብ ዘመዶቹን አፈላልገን ፈቃደኛ ከሆኑ እነሱን የማሳደግ አቅም ያላቸው መሆኑን ስናረጋግጥ ለእነሱ እንሰጣቸዋለን። ምንም ቤተሰብ የሌለው ደግሞ አሳዳጊ ወላጅ እንፈልግለታለን። ምንም ደግሞ ላልተገኘለት ህፃን ልጅ ተቋማችን ውስጥ በዘለቄታዊነት የሚኖርበትንና የሚማርበትን ሁኔታ እናመቻቻለን። ቤተሰብ ጋር ስናቀላቅል ግን ዋናው ነገር ትምህርት በመሆኑ ትምህርታቸውን እንዲማሩ አስፈላጊውን ድጋፍ እናደርግላቸዋል። ማንም ልጅ ከትምህርት ገበታ እንዳይቀር እስከ ትምህርት ቢሮ ድረስ በመዝለቅ በጋራ እንከታተላለን። እንዲሁም ከሴቶችና ህፃናት ቢሮ እንዲሁም ፍትሕ ቢሮ ጋር ትስስር ፈጥረን እነዚያ ልጆች ዳግሞ ወደ ጎዳና እንዳይመለሱ እየሰራን ነው። በነገራችን ላይ ከትምህርት ሲቀሩ ከትምህርት ቢሮ ወዲያውኑ ነው ሪፖርት የሚደረግልን። እነዚህ ህፃናት ብቻቸውን እንዳይንቀሳቀሱ ብዙ የንቅናቄ መድረኮችን አዘጋጅተናል።

በተለይም ከወላይታ በርካታ የህፃናት ፍልሰት አለ፤ አዲስ አበባ ላይ ከሚታዩት ከ60 በመቶ በላይ የሚሆኑት ህፃናት ከወላይታ ዞን የሚመጡ ናቸው። ስለዚህ ወላይታ ላይ ያሉ የመንግስት

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# ‹‹በምድር ላይ ትልቁ ደስታ...

ከገጽ 8 የዞረ

ባለድርሻ አካላትን ሰብስበን ብዙ የግንዛቤ ማስጨበጫያ ስራ ሰርተናል። በነገራችን ላይ ከየክልሉ የመጡትን ብቻ ሳይሆን ፍልሰቱን ለማቆም በፈጠርነው ትስስር አማካኝነት በማንም ልጅ ያለ ወላጅ በመናኸሪያዎች ውስጥ እንዳይንቀሳቀስ የቁጥጥር ስራ በጋራ እየተሰራ ነው። በተጨማሪም በገጠር ያሉ ሴቶችን የማብቃት ሥራ እንሰራለን። ስለቤተሰብ ምጣኔ በማስተማርና የወሊድ መከላከያ በመስጠትም የበኩላችንን ሚና እየተወጣን እንገኛለን።

ከዚህ ባሻገር የንፁህ ውሃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የሴቶችን ድካም ለማቅለል ጥረት እናደርጋለን። በተጨማሪም ውሃ ፍለጋ ከስድስትና ሰባት ሰዓት ያላነሰ የሚጓዙበት ሁኔታ አለ፤ ይህም ደግሞ ከጥቃት ጀምሮ እስከሞት አደጋ ድረስ ያጋልጣቸዋል። በመሆኑም የውሃ ተጠቃሚ ያደረግናቸው አካባቢዎች ላይ በተለይ የሴቶችን ድካም ማቅለል ብቻ ሳይሆን ከጥቃትም የመታደግ ሚናም አለው።

የምገባ ማዕከልም ሰርተናል፤ መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟላት የማይችሉ የማህበረሰብ ክፍሎች እንዲመገቡ፤ ከዚያም አልፎ ሁልጊዜ ተረጂ ሆነው መቀጠል ስለሌለባቸው ስልጠና ወስደው ደግሞ ራሳቸውን የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል። እነሱ ደግሞ ራሳቸውን ሲችሉ ሌሎችን እንዲደግፉ ነው የሚደረገው። በነገራችን ላይ የተቋማችን መርሆ እዚህ የሚረዱ ሰዎች በቋሚነት ተረጂ እንዲሆኑ ሳይሆን እየበቁ እንዲወጡ ማድረግ ነው። በተለይ ሴቶችን አብቅተን ከማህበረሰቡ ጋር መቀላቀል ነው ዋናው አላማችን።

**አዲስ ዘመን፡- ሥራውን ስትጀምሩ በተለይ የአዕምሮ እክል የነበረባቸውን ሰዎች ቤት አስገብቶ ማኖር ፈታኝ አልነበረም?**

**ዶክተር መክሲት፡-** ልክ ነው፤ የአዕምሮ ህሙማን ቤቴ ውስጥ በማኖርበት ወቅት አብዛኛው የአካበቢ ማህበረሰብ እኔን ራሱ እንደጤነኛ አይቆጥረኝም ነበር። በወቅቱ ታዲያ ሁለተኛ ልጄን ነፍሰጡር ነበርኩ፤ የመጀመሪያ ልጄ ደግሞ ገና ሁለት ዓመት እንኳን አልሞላትም ነበር። በእንዲህ ሁኔታ እያለው ህሙማኑን አምጥቼ ሳኖር ብዙ ሰዎች ግር ይሰኙ ነበር። ግን ደግሞ ባለቤቴም በጣም ይደግፈኛል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ይህንን የማደርገው ከውስጤ ሰዎችን የመርዳት ፅኑ ፍላጎት ስለነበረኝ፤ ያለው ሁኔታ አያሳስበኝም ነበር። በዚያ ውስጥ እያለፍኩኝ ቢሆን በምሰራው ሥራ እርካታ ነበረኝ። ለውጣቸው፤ ውጤታቸውን ስመለከት ደግሞ የበለጠ እያበረታታኝ እንድሰራ ያደርገኝ ነበር።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ብዙ ገጠመኞች አሉኝ፤ ቤት ውስጥ የአዕምሮ ህሙማን በምናኖርበት ጊዜ ልክ ስንተኛ ጠብቃ ‹‹መስታወት እሰብራለሁ!›› ብላ የምትጮህና የምትረብሽ ሴት ነበረች፤ መኪናም ካየች ካልሰበርኩኝ ብላ ስትበጠብጥ ባለቤቴ በሌሊት ተነስቶ መኪናውን ይዞ የሚወጣበት ጊዜ ነበር። በሌላ አጋጣሚ ደግሞ ሁልጊዜም የራሳቸውን ንፅህና እንዲጠብቁ እናደርጋቸው ነበር፤ አንድ ቀን አንዲት ህመምተኛ ታጠቢ ብዬ መታጠቢያ ክፍል የሚያስፈልጋትን ሰጥቼ አስገባኋትና ወጣሁ፤ እናም ለረጅም ሰዓታት ብጠብቃት ከመታጠቢያ ክፍሉ አልወጣ አለችኝ። የሆነ ነገር ሆናለች ብዬ ደንግጬ ላያት ስገባ ልብሷን ሳታወልቅ በላይዋ ላይ ውሃው እየወረደ ቆማ ነው ያገኘኋት።

አንዳንዶቹ ደግሞ በአጥር ወጥተው ይጠፉብኝና እነሱን ፍለጋ ከተማ ውስጥ የምዞርበት አጋጣሚም ብዙ ነው። አንድ ጊዜ አንዲት የአዕምሮ ህመምተኛ በምሽት ከግቢ አምልጣ ወጣችና ስፈልጋት አስፋልት መሃል ላይ ራቆቷን ቆማ እንደትራፊክ መኪኖቹን ስታስተናብር ነው ያገኘኋት። ሰው ሁሉ ፈርቷት በርቀት ተሰብስቦ ያያታል፤ ላረጋጋት ስቀርባት ሰው ሁሉ ‹‹ትመታሻለች! ይቅርብሽ!›› ይሉኝ ነበር፤ እሷ ግን ተጠግቼ ሥጠራት አይታኝ አለቀሰች፤ ወዲያ ወደ አዕምሮዋ ተመልሳ ቤቱ ጠፍቶባት እንደሆነ ነገረችኝ። በዚያ ሁኔታ ሳገኛት እግሯን ብርጭቆ ወግቷት በጣም ተጎድታ ነበር፤ ግን ምንም አልታወቃትም ነበር። ወዲያው ህክምና እንድታገኝ አደረግናት። እናም እንዲህ አይነቱ ሰብአዊ ድጋፍ ከፍተኛ ሃሴት ነው የሚሰጠኝ።

እንዳልሽው የምንከባከባቸው ሴቶች የአዕምሮ ህሙማን ስለነበሩ ማህረሰቡን በድምፅ የመረበሽና ብዙ ሁከት ይፈጠር ስለነበር ብዙ ተቋውሞ ይደርስብኝ ነበር፤ በዚያ ልክ ግን ለውጣቸውን ሲያዩ እየተረዱኝ የመጡና የሚያግዙኝ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ነው የመጣው። እንዳልሽው ከቤተሰቤ ጀምሮ በጣም ግር ይላቸው ነበር፤ ‹‹ህፃናት ባሉበት ቤት እንዴት እንዲህ አይነቱን ሃላፊነት ትወስጃለሽ›› የሚሉኝ ነበሩ። በመሆኑም እንዲህ አይነቱን ቅሬታ ለማስወገድ ህጋዊ ፍቃድ ማውጣት እንዳለብኝ ወሰንኩኝ። ምንም አይነት ችግር ከመፈጠሩ በፊት ህጋዊ መሆን የግድ ይል ስለነበረ ነው። በመሰረቱ ሥራ ለመስራት ስትነሺ አላማሽ መልካም ከሆነ ፈጣሪም ይረዳሻል። ከዚያ በኋላ ብዙ ነገሮች ተመቻቹና በደንብ የተደራጀ ተቋም መፍጠር ቻልን። ብዙ ባለሙያዎች ድጋፍ የሚያድርጉበትና ትንሿ ኢትዮጵያ በሚባል ደረጃ ከሁሉም አካባቢ የመጡና የተለያየ እምነት የሚከተሉ ዜጎች የሚረዱበትና በቅተው የሚወጡበት ተቋም ሆኗል። ያ ሊሆን የቻለው የልቤ መሻት መልካም በመሆኑ ፈጣሪ ስላገዘኝ ነው።

> **በድምሩ ከ1ሺ 64 በላይ ከጎዳና አንስተን ከቤተሰብ የማቀላቀል ሥራ ሰርተናል። አሁን ላይ ወደ 120 ህፃናት በማዕከላችን ይገኛሉ። ቤተሰብ ማቀላቀል ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚ ጎዳና የወጣ ልጅ ዳግም ሲቸግረው ወደጎዳና እንዳይመለስ ቤተሰቡን በፋይናንስ እንደግፋለን።"**



**አዲስ ዘመን፡- በተመሳሳይ በወሲብ ንግድ የተሰማሩ ሴቶችን ካሉበት ህይወት የማውጣቱ ሥራ ላይ የሚያጋጥማቹ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?**

**ዶክተር መክሲት፡-** በነገራችን ላይ የሴተኛ አዳሪዎች ህይወት እንዲሁ በቀላሉ የሚነገር አይደለም፤ በጣም ከባድ ነው። በዚህ ስራ ከአምስት ዓመት በላይ እንደመቆየቴ ብዙ ተግዳሮቶች አጋጥሞኝ ነበር። አሁንም እየሰራን ያለነው ስጋት እንደተጋረጠብን ነው። በቅርብ ጊዜ እንኳን አዲስ አበባ ውስጥ እስከመደብደብ ድረስ ጥቃት ደርሶብናል። ምክንያቱም ደግሞ በእነሱ የሚጠቀሙ ብዙ ሰዎች አሉ። ከክፍለ ሃገር ሲያመጧቸው ለመስተንግዶና ለሌላ አይነት ሥራ ብለው ነው፤ ግን ልክ እንደመጡ መታወቂያቸውን ይቀበሏቸውና ግሮሰሪዎች ውስጥ ይቀጥሯቸዋል፤ ሆን ብለው መጠጥ አጉድለው ይሰጧቸውና ገንዘብ እንዲጎልባቸው ያደርጓቸዋል፤ ገንዘቡ ሲጎድልባቸው ወዲያውኑ እንዲከፍሉ ይነግሯቸዋል። አለበለዚያ ‹‹ከወንድ ጋር አድረሽ ዕዳሽን ክፈይ ፤ ራስሽንም ተጠቃሚ ሁኚ›› ብለው ጫና ያሳድሩባቸዋል። ስለዚህ የምትከፍለው ስለሌላት ሳትወድ በግዷ ወደ ወሲብ ንግድ ትገባለች። ግን ደግሞ ከወንድ ጋር ባደረች ቁጥር ግማሹን ለአሰሪዎቿ የመስጠት ግዴታ አለባት። እናም ሁሌም እዳ እንዲኖርባቸው ስለሚፈለግ ቅጣት ይጣልባቸዋል። ሳያስፈቅዱ ሱቅ ከሄዱ ይቀጣሉ፤ ማታ ከወንድ ጋር አድረው፤ ጠዋት 12፡00 ሰዓት ተነስተው ቡና መጠጣት ግዴታቸው ነው፤ ይህንንም ካላደረጉ 600 ብር ይቀጣሉ። እዳቸው እንዲጨምር በማድረግ ከዚያ ህይወት እንዳይወጡ ይደረጋል።

እናም ሴተኛ አዳሪ በሚበዙበት እንደቺቺኒያ አካባቢ በምንሄድበት ጊዜ በባለሃብቶች እስከመደብደብ ድረስ ጥቃት ደርሶብኛል። ያም ቢሆን ግን ተገደው ወደዚህ ህይወት የገቡ ሴቶችን መታደግ እንዳለብኝ ስለማምን በዛቻውም ሆነ በድብደባው ወደኋላ አላልኩም። አሁንም ከከተማ አስተዳደሩ ታችኛው መዋቅር ድረስ ተሳስረን በትጋት እየሰራን ነው ያለነው። ሴቶችን በግዳች ወደ ወሲብ ንግድ የሚያስገቡ ሰዎች በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ እየሰራን ነው። የሰው ልጅ በጣም ካልተቸገረ በስተቀር ራሱን አይሸጥም!። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሴተኛ አዳሪዎችን በማውጣት ሂደት ላይ በቅርቡ ያገኘኋት ህፃን ልጅ እናቷ በስራዋ ምክንያት በቂ እንክብካቤ ስላላደረገችላት የሁለት ዓመት ልጅ ብትሆንም ስድስት ኪሎ ብቻ ነበረች፤ ምክንያቱም እናቷ ገላዋን ሸጣ፤ በቀን 60 ብር ካገኘች ምግብ ታበላታለች፤ ካላገኘች ግን ሳትበላ ትውል ስለነበር ነው። በዚህ ምክንያት ለምግብ እጥረት በሽታ ተጋልጣ ነበር፤ የፀጉሯና የቆዳዋ ከለል ራሱ ተለውጦ ነበር። ይህችን ህፃን እንዳገኘኋት ነበር ወደ ሆስፒታል የወሰድኳት። በአፍንጫ ተጨማሪ ምግብ እንድታገኝ ተደርጎ አሁን ላይ በጥሩ ጤንነት ላይ ነው ያለችው፤ መራመድም፤ መጫወትም ችላለች።

እናም እንደዚህ አይነት ብዙ ችግሮችን በየቀኑ እናስተናግዳለን፤ ብዙዎቹ ሴተኛ አዳሪዎች ወልደው ሳይታረሱ ገና በ15 ቀናቸው ልጃቸውን ባዶ ቤት አስቀምጠው ተመልሰው ወደ ሴተኛ አዳሪ ህይወት ይመለሳሉ። በዚያ ሁኔታ ጥለዋቸው ሲሄዱ በሻማ ተቃጥለው የሚሞቱ አሉ፤ ታፍነው የሚሞቱም አጋጥመውናል። በተለይ ልጆች ስድስት ወር ሲሆኑና መገላበጥ ሲጀምሩ ከአልጋ የሚወድቁበትና ታፍነው የሚሞቱበት ሁኔታ ብዙ ነው። ይህ አይነቱ አሳዛኝ ገጠመኝ ሁልጊዜ የሚስተዋል ነው። ጎዳና ላይ የሚወለዱ ህፃናት ደግሞ ሃይለኛ ብርድና ንፋስ ስለሚመታቸው ወዲያውኑ ለሳንባ ምች ይጠቃሉ። ስለዚህ የችግሩን ስፋት ሲታይ እኔ ዋጋ ከፈልኩኝ ብዬ ለማውራት ይከብደኛል። ለዚህ ችግር መፍትሔ መሆን በራሱ መታደል ነው። የሚገርምሽ ብዙ ሌሊቶችን ውጪ ነው የማሳልፈው። ምክንያቱም በየቀኑ የማየው ነገር የበለጠ እንድተጋ የሚያነሳሳኝ በመሆኑ ነው። እነዚያ ሰዎች ተለውጠው ቁምነገር ደረጃ ላይ ሲደርሱ ስመለከት ትልቅ ደስታ ይሰጠኛል።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ ሰዎች ከተለያዩ ሱሶችና ልምምዶች የመጡ እንደመሆናቸው ተመልሰው ወደዚያ ህይወት እንዳይገቡ ምን አይነት ሥራዎች ነው የምትሰሩት?**

**ዶክተር መክሲት፡-** እንዳልሽው በወሲብ ንግድ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ላይ መስራት በጣም ከባድና አድካሚ ነው። ብዙ ዋጋ ከተከፈለባቸውና ከተለፋባቸው በኋላ ወደኋላ የመመለስ ነገር ይኖራል። ነገር ግን መላው የማዕከላችን ሰራተኛ ሌት ተቀን በትጋት የሚሰራ በመሆኑ እስካሁን እንዲህ አይነቱ እምብዛም አላጋጠመንም። ግን ይህንን ለማምጣት ብዙ መድከምና ያለመታከት መስራት ጠይቆን ነበር። እነዚህ ሰዎች ወደማዕከሉ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ለሶስት ሳምንታት ያህል ሱሱ ስለሚያስቸግራቸው ከጠዋት እስከማታ በስራ እንዲወጠሩ እናደርጋለን። በሱሶቹ ፋንታ እንደቸኮሌትና ማስቲካ በመስጠት ቀስ በቀስ እንዲላቀቁ እናደርጋለን። ስፖርት እንዲሰሩ፤ በጋራ እንዲጫወቱ፤ አልጋቸውን እንዲያነጥፉና የተለያዩ ሥራዎችን በመስራት ማህበራዊ ህይወትን እንዲለማመዱም ይደረጋል። ከእኛ አቅም በላይ የሆኑት ደግሞ ከጤና ማዕከላት ጋር ትስስር ፈጥረን ወደዚያ የምንልካቸውም አሉ። ግን 95 በመቶ የሚሆኑት በሁለት ሳምንታቸው ከሱስ ነፃ ይሆናሉ።

በመቀጠልም ኮሌጅ ልከን የሙያ ትምህርት እንዲማሩ እናድርጋቸዋለን። ባለራዕይና ተስፋ ያላቸው እንዲሆኑ ተጨማሪ የስነ-ልቦና እንዲሁም ሥራ ፈጣሪ የሚያደርጋቸውንና የገንዘብ አያያዝ የሚችሉበትን ስልጠና ይሰጣቸዋል። ትልቁ ሥራ ያለው ከማዕከሉ ከወጡ በኋላ ነው፤ ወጡ ብለን አንተዋቸውም፤ ትስስር ፈጥረን፤ የስራ እድል እንዲያገኙ፤ ራሳቸውን እንዲለውጡ ይደረጋል። በቅርቡ በርካታ ሴቶች ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በምግብ ዝግጅት ሰልጥነው ትልልቅ ሆቴሎችና ተቋማት መቀጠር ችለዋል። እንዲሁም የራሳቸውን ስራ ፈጥረው የተቀየሩ አሉ። ከወጡም በኋላ በየጊዜው ክትትል የምናደርግላቸው በመሆኑ ብዙ ወደነበሩበት ህይወት የሚመለሱበት አጋጣሚ የለም። በነገራችን ላይ ይህንን ሥራ የሚሰራው ከውስጥ የሆነ መነሳሳትና ፅናት ሲኖር ነው። መልሰው ወደዚያ ህይወት የሚገቡ ከሆነ ልፋታችን ከንቱ ስለሚሆን እያንዳንዱ ሰው በትጋት ነው የሚሰራው፤ ያም ነው ውጤታማ ያደረገን። ከዚህ ባሻገር የህክምና ድጋፍ ያገኛሉ። በነገራችን ላይ ወደማዕከሉ የሚገቡ አብዛኞቹ ሴቶች ከኤች አይ ቪ ጋር የሚኖሩ ናቸው፤ በቅርቡ በተደረገው ምርመራም 60 በመቶ የሚሆኑት የመጀመሪያ ደረጃ የማህፀን ካንሰር እንዳለባቸው ታውቋል። በመሆኑም በርካታ መልካም ፈቃደኞች ጋር በመተባበር የህክምና ድጋፍ እንዲያገኙ እየተደረጉ ነው ያሉት።

**አዲስ ዘመን፡- በማዕከሉ የሚረዱ ህፃናት ወላጅ ጋር ከማገናኘቱ ሥራ ጎን ለጎን በዘላቂነት ትምህርት አግኝተው የነገ ሃገር ተረካቢ ትውልድ እንዲሆኑ ምን ያህል ጥረት ታደርጋላቹ?**

**ዶክተር መክሲት፡-** እስከአሁኑ በድምሩ ከ1ሺ 64 በላይ ከጎዳና አንስተን ከቤተሰብ የማቀላቀል ሥራ ሰርተናል። አሁን ላይ ወደ 120 ህፃናት በማዕከላችን ይገኛሉ። ቤተሰብ ማቀላቀል ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚ ጎዳና የወጣ ልጅ ዳግም ሲቸግረው ወደጎዳና እንዳይመለስ ቤተሰቡን በፋይናስ እንደግፋለን። ሥራ እንዲፈጥሩም እናቋቁማቸዋለን። ለብዙ እናቶች ላም ገዝተን ሰጥተናቸዋል፤ አሁን ወተት ሸጠው ኑሯቸውን ይደጉማሉ። ይህንን የምናደርገው ደግሞ ምስክር ባለበት ነው፤ ሴቶችና ህፃናት ቢሮ፤ የፍትሕ አካላት እንዲታዘቡ እናድርጋለን፤ ምክንያቱም ደግሞ እኛ ሁልጊዜ ከእነሱ ጋር መሆን ስለማንችል ነው። እንዳልሽው ተቋማችን ትምህርት ላይ ትኩረት የሚያደርገው የነገ ሃገር ተረካቢ ትውልድ እንዲሆኑ በማሰብ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የምገባ ማዕከሉ ተጠቃሚ የሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች እነማን ናቸው? ለዚህ ሥራ ድጋፍ የሚያደርግላችሁስ አካል አለ?**

**ዶክተር መክሲት፡-** የምገባ ማዕከሉ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር ነው የምንሰራው። እዛው ተቋም ውስጥ ነው ያለው። ችግረኛ የሆኑ ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍሎች በቀን ሶስት ጊዜ በማዕከሉ ይመገባሉ። ግን ደግሞ ሁልጊዜ ተመጋቢና እርዳታ ጠባቂ መሆን ስለሌለባቸው የማቋቋምና የማደራጀት ሥራ ይሰራል። ሥራ መጀመሪያ ገንዘብ እንሰጣቸዋለን፤ መንግስትም የመስሪያ ቦታ ይሰጣቸውና ራሳቸውን እንዲችሉ፤ ከእርዳታ እንዲወጡ ይደረጋል። መስራት የማይችሉ ናቸው በዘላቂነት የሚመገቡት።

**አዲስ ዘመን፡- እናትና ሴት መሆን በራሱ ፈታኝ በሆነበት ሁኔታ እንዲህ አይነቱን ሥራ መስራት በራሱ ከባድ አልነበረም?**

**ዶክተር መክሲት፡-** እናት ለልጇ የመጀመሪያ አስተማሪ ናት፤ እናት ልጇን በትክክል ቀርፃ ካሳደገች ነገ መልካም ትውልድ ይኖራል። እናት ለባሏ ጥሩ አማካሪ ናት። ሴትን ልጅ ማስተማርና ማብቃት ማለት ትውልድ ላይ ኢንቨስት ማድረግ ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ደግሞ ሴቶች በሃገራችን እንደ ሁለተኛ ዜጋ የሚቆጠሩበት ሁኔታ አለ። በተለይ በገጠሩ አካባቢ ሴቶች ከወንዶች እኩል የትምህርት እድል አያገኙም፤ ሴት ልጅ ከወንድ እኩል ሃላፊነት መሸከም አትችልም ተብሎ ይታሰባል፤ ሴት ልጅ ለብዙ ጥቃት ትጋለጣለች። አሁንም ድረስ ያልተቀረፈ ችግር በመሆኑ ሴቶች ላይ መስራት ይገባል ብዬ ስለማምን ነው፤ ብዙ ዋጋ ቢያስከፍለኝም በዚህ ሥራ ላይ የዘለቅሁት። ሴት ልጅ እናት ናት፤ እህት ናት ፤ ልጅ ናት በአጠቃላይ ሁሉም ነገር ናት። በመሆኑም ትንሽ ድጋፍ ቢደረግላት ከወንዶች እኩል መስራት ትችላለች ብዬ ስለማምን የምከፍለው ዋጋ ብዙም አያሳስበኝም። ደግሞም ሁላችንም የምንችለውን ልናደርግ ይገባል። አስቀድሜ እንዳልኩት ሰውን ለመርዳት ብዙ ገንዘብ ላያስፈልገን ይችላል፤ እንደውም ብዙ ገንዘብ ያላቸው ሲረዱ አላየንም፤ ይልቁንም ያለንን በማካፈልና የመፍትሔ አካል በመሆን ሁላችንም የየአቅማችን ማዋጣት አለብን የሚል መልዕክት ማስተላለፍ እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር መክሲት፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ልዩ ዕትም

# የቀይ ቦኔቱ ፍቅር
# የሰንደቅ ዓላማው አደራ

**አስቴር ኤልያስ**

ገና የ9ኛ ክፍል ተማሪ ሳለች አስተውላው የማታውቀው ነገር በሃሳቧ ይከሰታል። ዕለቱ ትምህርት ቤታቸው የወላጆች ቀን የሚያከብርበት ጊዜ ነበርና በትምህርት ቤቷ ቅጥር ጊቢ ተገኝታለች። በዕለቱ ከአካባቢያቸው ጩንቻ ከተማ፣ መከላከያ ሠራዊትን የተቀላቀለ አንድ ሰው ድንገት በትምህርት ቤታቸው ተከሰተ። ይህ ባለቀይ ቦኔቱ ወታደር የአካል ጉዳት ስለደረሰበት ቦርድ ወጥቷል ።

ወታደሩ በትምህርት ቤታቸው በሚከበረው የወላጆች ቀን ላይ የተገኘው ግን ባዶ እጁን አልነበረም። ሲዋደቅላት የነበረውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዞ እንጂ። ቀይ ቦኔት ለባሹ፣ ከሰንደቅ ዓላማው ጋር ለረጅም ሰዓት አልተቀመጠም፤ ይልቁኑ ሰንደቁን በእጁ እንደያዘ ተማሪዎች ፊት ወጣ በማለት «ማነው ይህን ሰንደቅ ዓላማ የሚረከበኝ? ማን ነው እኔን የሚተካኝ? አስኪ ኢትዮጵያዊ የሆነ ማን ነው? እኔ ለሀገሬ ያበረከትኩት ይኸው አካሌን ነው።» እያለ የተጎዳውን አካሉን ለተማሪዎች በማሳየት የሚተካውን ሰው ፍለጋ አይኑን ከአንዱ ጥግ ወደሌላው ጥግ ይወረውራል።

የሚቀበለውን አንድ ባለወኔ እስኪያገኝም ከንግግሩ አልታቀበም። «ይህን ሰንደቅ ዓላማ የሚቀበለኝ ማን ነው?» ማለቱን ቀጠለ። «ይህን ሰንደቅ ዓላማ ላወርሰው የምችለውን ሰው እፈልጋለሁ። » መናገሩን ያዘ ።

ትውልዷ ጋሞ ጎፋ ዞን፣ ጩንቻ ወረዳ አርባ ምንጭ ዙሪያ መሆኑን የሴቶችን ቀንን አስመልክቶ ልዩ እትም ላዘጋጀው ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ የተናገረችው የዚያኔዋ ተማሪ፤ የአሁኗ ሻምበል የሩቅነሽ ጌታነህ፣ ከመዋዕለ ህጻናት እስከ አስረኛ ክፍል የተማረችው ጩንቻ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲሆን፣ ተወልዳ ያደገችውም ሆነ ትምህርቷን ያጠናቀቀችው እዛው ጩንቻ ከተማ ውስጥ ነው። በወቅቱ የባለ ቀይ ቦኔቱ ወታደር ውትወታ አቅሏን አስቷታል። ሳታውቀውም እስከዛሬ ድረስ ለራሷም ግርም የሚላት ነገር ተከሰተ። ውስጧን አንዳች ስሜት ውርር ሲያደርጋት ተሰማት።

ወታደሩ፣ «ማንን ላውርስ? ማን ነው ደፋሩ? ማንስ ነው ከኢትዮጵያ ጎን መቆም የሚሻው?» እያለ የልመና ያህል ጥያቄውን ያዥጎደጉድ ገባ። «ማን ነው ታዲያ የሚቀበለኝ?!» እያለ ተማሪውን ማነሳሳቱን ቀጠለ። ይህን ሁሉ ጥያቄ ሲያቀርብ ተንበርክኮና ሰንደቅ ዓላማውን በክብር ይዞ ነበርና የትናንቷ ታዳጊ የ9ኛ ክፍል ተማሪዋ የሩቅነሽ ሳታስበው ብግድ ትላለች። መነሳቷን በአግባቡ ሳትረዳ ባለቀይ ቦኔቱ ወታደር ዘንድ መድረሷን አወቀች።

አጠገቡ ስትደርስ ያለምንም ማቅማማት ከፊቱ በርከክ ትልና ከተንበረከከው ባለቀይ ቦኔቱ ወታደር ዘንድ የሀገሯን ሰንደቅ ዓላማ ሁለት ትንንሽዬ እጆቿን ዘርግታ በአክብሮት ተቀበለች።

እርሷ ከዛ በፊት ስለውትድርና ብዙ ግንዛቤ የላትም። በዕለቱም ቢሆን ከወታደሩ እጅ ሰንደቅ ዓላማውን ለመቀበል የዚያን ያህል ዝግጁ አልነበረችም። ወደ ትድርናው ዓለምም እገባለሁ ብላ አላሰበችም። እርሷ ሃሳቧ ውስጥ ያለው ትምህርቷን ጨርሳ ያስተማሯትን ቤተሰቦች መርዳት ነበር።

ሻምበል የሩቅነሽ፣ በዕለቱ ከቀይ ቦኔት ለባሹ ሰንደቅ ዓላማውን የተቀበለችበት አግባብ ለየት ያለ ስሜት የታከለበት እንደነበር በቅርብ የሚያውቋት አስታውሰዋታል። አቀባበሏን ያዩ አዋቂዎችም «አንቺ የምትሆኚው ወታደር ነው» ይሏት እንደነበርም ትናገራለች። እርሷም ከዚያን ጊዜ ወዲህ ስለውትድርና በውስጧ ታስብ፣ ታብሰለስል ያዘች።

"የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን አጠናቀቅኩ። ውጤት እስኪመጣም ታገስኩ። ልክ ውጤት እንደመጣ በውትድርናው ዘርፍ ማስታወቂያ ወጥቶ ነበርና ወዲያው የውትድርናውን ሕይወት ተቀላቀልኩ» ትላለች ሻምበል የሩቅነሽ። በወቅቱ ውትድርናን ለመቀላቀል ባለበች ጊዜ ውሳኔዋ በእርሷ ዘንድ የተቀረጠ ቢሆንም፤ እናቷ ግን እንዳትሄድባቸው በብዙ ለምነዋት እንደነበር አትረሳም።



ሻምበል የሩቅነሽ ጌታነህ

«እናቴ 'እባክሽ ልጄ አትሒጂ' እያለችና እያለቀሰች ስትከተለኝ ዞሬ አላየኋትም" የምትለዋ ሻምበል የሩቅነሽ፣ «እኔም እምባ እየተናነቀኝ፤ ያኔ የተቀበለኩትን የሰንደቅ ዓላማ አደራ በተግባር ለመተርጎም የመጀመሪያውን ርምጃ አንድ ለማለት ወሰንኩ።" ትላለች።

የእኔ ነገር ለራሴም እስካሁን ድረስ ይገርመኛል። ልክ አባቶች ለልጆች በአደራ መልክ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የሚያስረክቡትን አይነት ይመስለኛል። በወቅቱ እኔን የተሰማኝ ስሜት ከባድ ነበር። ያን አይነቱን ስሜት ተቋቁሞ መቀመጥ የሚታሰብ አልነበረም። ይህን መሰሉን ድርጊት ዛሬ ላይ ሆኜ ሳየው ያኔ ከዓመታት በፊት እኔ የተሰማኝን አይነት ስሜት ውል ይለኛል ትላለች።

ሻምበል የሩቅነሽ እንደምትለው፤ ውትድርና ራስን ለሀገር ሉዓላዊነት መስዋዕት ለማድረግ የሚገቡበት ክቡር ሙያ ነው፤ ይህ ደግሞ መንገዱ አልጋ በአልጋ እንዳልሆነ እሙን ነው። እናም ውትድርና ሴቱንም ሆነ ወንዱንም ፈታኝ ነው። ሥልጠናው እጅግ ፈታኝ ነው። ሴት ሲኮን ደግሞ ትንሽ ጠንከር ይላል።

እርሷ በመጀመሪያ እግረኛ ስትሆን ከዚያም ወደኮማንዶው ተቀላቀለች። መሠረታዊ ውትድርናውን ስድስት ወር ሠልጠና እንደጨረሰች ለኮማንዶው ተምልመላ ነበር። ምልመላው ሴቱንም ወንዱንም ያካተተ ስለነበር «አጋጣሚ ፍላጎቱም ስለነበረኝ እድሉን አገኘሁ» ትላለች። «የቀይ ቦኔት ፍቅር አለብኝ» የምትለው ሻምበል የሩቅነሽ፣ ያኔ የ9ኛ ክፍል ተማሪ ሳለች እጅጌውን ከፍ አድርጎ የጠቀለለውን፣ አካሉ የተጎዳ ቦርድ የወጣውን

> ወታደር በሥልጠና ዘመኑም ሆነ ሀገሩን በማገልገል ላይ እያለ የሚተያየው እንደ አንድ የእናት ልጅ ነው። የሚያስገርመው በስድስት ወራት ሥልጠና ውስጥ የሚፈጠረው መግባባት እጅግ ጠንካራ የሆነ ቤተሰባዊ መሆንን ነው።

ከባለቀይ ቦኔቱ ወታደር የተቀበለችው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ብቻ ሳይሆን የተማረከችበት ሙሉ ወታደራዊ አለባበሱንም ጭምር ነበር።

በውስጧ ያለው የወታደሩ የተስተካከለ ቁመና ስለነበር በየትኛውም የሥልጠና መንገድ ለማለፍ ብዙ አልተቸገረችም። ልክ የእግረኛውን ሥልጠና አጠናቀው እንደተመረቁ እርሷ ወደኮማንዶ ተቀላቀለች። የኮማንዶ ሥልጠናውን ደግሞ ስምንት ወር ሰለጠነች።

ሻምበል፣ «ዋናው የአካል ብቃት ሥልጠና ነው፤ የአካል ብቃት ከሌለ ተራራ መውጣት መውረድ አይቻልም፤ ትጥቅ እና መሣሪያ መያዝ ስላለ የአካል ብቃት የግድ ነው» ትላለች። መሣሪያ መያዝ ብቻ ሳይሆን ጠላትን አልሞ መምታት የሚጠበቅ በመሆኑ ሥልጠናው ዘርፈ ብዙ ነው» ስትል እንዲህ በመሆኑም ሴት በመሆኗ ብቻ ከመሻቷ አላስቀራትም።

ሻምበል የሩቅነሽ እንደምትለው፤ የኮማንዶው ሥልጠና ዋናው ዓላማ በአጭር ጊዜ፣ ፈጣን በሆነ ስልትና በአነስተኛ ኪሳራ ብቻ ጠላትን መምታት ነው። አሊያም ደግሞ ወደተፈለገው ቦታ በአጭር ጊዜ ውስጥ መድረስ ነው። በብዛት እነርሱ ተፈላጊ የሚሆኑት እንደ ኮማንዶ ሥልጠና ያልወሰደው እግረኛ ጦር በሚዳከምበት ጊዜና የወታደር ኃይል በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ድጋፍ ለመስጠት ነው። እግረኛው መሣሪያ ሊያልቅበት ይችላል። ከዛ አንጻርም ጠላትን ፊት ለፊት በመግጠም በሳንጃም እጅ ለእጅም በመግጠም ያንን ጠላት ድባቅ ለመምታት ነው ስትል ታስረዳለች።

ሻምበል የሩቅነሽ፣ ኮማንዶ እንደመሆኗ በፓራሹት ዘላለች። በፓራሹት አምስት ጊዜ ከዘለለች በኋላ የገባችው ወደማሠልጠኑ ነው። ጥቂት ጊዜም በዚሁ ዘርፍ አሠልጥናለች። ከዚሁ ጎን ለጎን የልዩ ኃይል ሥልጠናም ወስዳለች። ኮማንዶ እያሠለጠነች ሳለ ለሌላ ግዳጅ ትፈለግ ስለነበር ወደብላቴ አቀናች። እርሷ የመሠረታዊ ውትድርና፣ የአየር ወለድ፣ የኮማንዶ እና የልዩ ኃይል ሥልጠናዎችን ወስዳለች።

ሻምበል የሩቅነሽ፣ በውትድርናው ዘርፍ ሀገርን ማገልገል ቤተሰብ እንዳትመሠርት አላገዳትም። ትዳር ይዛ የልጅ እናት ሆናለች። ይሁንና ውትድርና፣ ከትዳርና ልጅ ጋር ሲሆን በተወሰነ ደረጃ ከበድ እንደሚል አትሸሽግም «እኔ የልጅ እናት ነኝና ይህ ይከብደኛል፤ ያኛውም ይቀትኛል ብሎ ነገር የለም» የምትለው ሻምበል የሩቅነሽ፣ «ይህን ከግንዛቤ የምናስገባው ወደውትድርናው ዓለም ስንገባ ነው» በማለት ታስረዳለች።

«እኛ ሴቶች በተፈጥሯችን ፈጣሪያችን የሰጠን ክህሎት አለን፤ እሱን በመጠቀም ወንዶች የሠሯቸውን ጀብዶች ሁሉ እንሠራለን፤ ማርገዝ መውለድ ወደኋላ አያስቀረንም፤ አላስቀረንምም» እርግጥ ነው ማርገዙ፣ መውለዱና ማሳደጉ የራሱ የሆነ የጊዜና የጉልበት መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ነው። ይህም ውትድርናን ከባድ ያደርገዋል። ነገር ግን ለውትድርና ያላቸው ፍቅር ሁኔታውን እንዲያጣጥሙት ጉልበት እንደሚሆናቸው ታስረዳለች።

እርሷ፣ «ከሁሉም ሀገር ይቀድማል» በሚል እያገለገለች ያለው የአስር ዓመት ልጇን እናቷ ዘንድ አስቀምጣ ነው። ትናንት ብላቴ፤ ዛሬ ደግሞ ቢሾፍቱ ላይ ናት፤ ነገ ደግሞ እዚህ ቦታ፣ በዚህ አይነት ግዳጅ ታስፈልጊያለሽ ከተባለች ለመሄድ ዝግጁ ትሆናለች። ሻምበል ሁሌም በተጠንቀቅ ትገኛለች። «ይህኛው እንጂ ያኛው ሥራ አይመቸኝም» ማለት አይቻላትም።

ሻምበል የሩቅነሽ «ለሴቶች መልዕክት አለኝ» ትላለች። ሴት ሆኖ መፈጠር ከምንም አይነት ሥራ አያግድም። ወንዶች የዋሉበት መስክ ሴትም መዋል ትችላለች። ዋናው ፍላጎቱ እንጂ ሴትነት ከየትኛውም ሥፍራ የሚያስቀር አይደለም። ወኔና ድፍረቱ እስካለ ድረስ የሚያቅት ምንም ጉዳይ እንደማይኖር ታስረዳለች። እንዲያውም በአየር ወለድ ሥልጠናቸው ወቅት ትዝ የሚላት በፓራሹት በሚዘለለው ዝላይ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ቀዳሚ እንደሆኑ ነው።

በወቅቱ የምታስታውሰው ‹ሴቷ ዘልላ እንዴት እኔ እቀራለሁ› በሚል ወንዶች ተነቃቅተው እንደሚዘሉም ጭምር ነው።

እንዲያውም አንድ የምታስታውሰው ነገር ሴቶች የዘለሉትን ወንዶቹ ይቅርብን ብለው ወደኋላ የተመለሱበትንም አጋጣሚ ጭምር ነው። ስለሆነም ሴት መሆን ሀገርን ከማገልገል፣ ቤተሰብን ከማስተዳደር እና መሰል ከሆኑ ሥራዎች የሚያስተጓጉል አይደለም ትላለች። ሴት ቆራጥ እንደሆነችም ትገልጻለች።

በውትድርና ሕይወት ያጋጠሙኝ ትውስታዎች በርካታ ናቸው። የመጀመሪያው ውትድርና ቤተሰባዊነትን የሚጎላበት ነው። ከተለያየ ብሔር የተውጣጣው ወታደር በሥልጠና ዘመኑም ሆነ ሀገሩን በማገልገል ላይ እያለ የሚተያየው እንደ አንድ የእናት ልጅ ነው። የሚያስገርመው በስድስት ወራት ሥልጠና ውስጥ የሚፈጠረው መግባባት እጅግ ጠንካራ የሆነ ቤተሰባዊ መሆንን ነው።

«ከእነዚህ ጊዜያት በአንዱ ወቅት የማልረሳው ነገር አለ» ትላለች ሻምበል የሩቅነሽ፣ «የዛሬ ሶስት ዓመት አካባቢ በሰላም አስከባሪ ግዳጅ ላይ ነበርኩ፤ በአጋጣሚ ከፓትሮል ላይ ወድቅኩ። መትረፍ የቻልኩት የወሰድኳቸው ሥልጠናዎች ስለታደጉኝ ነው እንጂ አወዳደቁ የከፋ ነበር። ምክንያቱም እኛ ከኦራልም ከፓትሮልም እንደየተሰጠን ግዳጅ ዓላማውን ለማሳካት እንዘልላለን፤ መዝለል የዚያን ያህል ከባድ ሆኖ አይደለም፤ አጋጣሚው ግን ፓትሮሉ በኃይለኛ ፍጥነት ላይ እያለ ድንገት ፍሬን በፍጥነት በመያዙ መኪናው ወደ ላይ ተነሳ፤ እሱ የከፋ ስለነበር ነው። እኔም የወድቅኩት በአየር ላይ ከተንሳፈፍኩ በኋላ ነው። በወቅቱ እጄ የተጎዳ ቢሆንም፤ ሥልጠናው ባይኖር ኖሮ ምን ያህል እጎዳ እንደነበር መገንዘብ አይቸግርም» ትላለች።

ሻምበል የሩቅነሽን፣ ሀገርሽ የት ደርሳ ነው ማየት የምትፈልጊው? ብዬ ላነሳሁላት ጥያቄ "ሀገሬ ሰላም ነግሶባት ማየትን እሻለሁ።" ስትል መልሳልኛለች። "ዜጎቿ እርስ በእርስ ተዋድደው ማየትን እፈልጋለሁ። ወገኔ በልቶ ጠግቦ ለሌላውም ሲተርፍ ማየት ያስደስተኛል። ሰው በሰላም ወጥቶ ጉዳዩን ፈጽሞ በሰላም እንዲገባም ምኞቴ ነው። የእርስ በርስ መገፋፋት ቀርቶ አንዱ የሌላው ጠባቂና ወዳጅ ሆኖ ማየት እሻለሁ። የእርስ በእርስ መተሳሰብ እንዲኖርም ከመሻት በዘለለ ለዚህ መልካም እሴት ሁሉም የየበኩሉን እንዲያደርግ እፈልጋለሁ። በተለይ ሀገሬ ከችግር፣ ድህነትና ጸረ ሰላም ኃይሎች ተላቅቃ ማየት ያስደስተኛል» ብላኛለች ቦኔት አፍቃሪዋ ሰንደቅ አክባሪዋ ሻምበል የሩቅነሽ ጌታነህ ።

# የአንድ ወገን ሕመም

መስከረም ሰይፉ

የወር አበባ ሕመምና የሚያስከትለው የስሜት መዛባት ብዙዎች ቀላል አድርገው ይመለከቱታል። በመሆኑም አንድ ሴት በወር አበባ ሕመም ምክንያት ታምሜያለሁ ብትል ‹‹አታካብጂ›› የሚለው መልስ በብዙዎች ዘንድ የተለመደ መልስ ነው። ይህም ጉዳዩን በልኩ ካለመረዳት የመጣ ነው።

በኢንግሊዝ ሀገር የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው 80 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች የወር አበባ ሕመም ያጋጥማቸዋል። ጥናቱ ከነዚህ ሴቶች ውስጥ አንዳንዶቹ ከሳምንት በፊት ጀምሮ እንደ ማቅለሽለሽ፣ የሆድ መነፋት፣ የስሜት መለዋወጥ፣ ድብርት፣ ድካም የመሰሉ ስሜቶች እንደሚያዩ የሚያትት ሲሆን የወር አበባ በመጣበት የመጀመሪያው ቀን ግን ብዙ ሴቶች ከፍ ያለ ሕመም ይሰማቸዋል ይላል።

የወር አበባ ሕመም መኖር በጥናት የተደገፈ ቢሆንም ሴቶች በወር አበባ ምክንያት የሚሰማቸው ሕመምና የስሜት መዛባት መረዳት ላይ ችግር እንዳለ አምናለሁ። እንደኔ አመለካከት ከትምህርት ቤት ጀምሮ ቤት ውስጥ የሚሰጡ ምክሮች የወር አበባ ማየት የሴት ልጅ ተፈጥሯዊ ሂደት ከመሆኑ በተጨማሪ በዛ ጊዜ ስለሚሰማት ሕመምና ሊደረግ ስለሚገባው እንክብካቤ አለማስተማር እንዲሁም በመጠኑም ቢሆን ስለ የወር አበባ የሚሰጠው ግንዛቤ ወንዶችን ያገለለ መሆኑ ለዚሁ ምክንያት እንደሆነ አስባለሁ።

በዚህ ዙሪያ በቅርቡ የገጠመኝን አንድ ገጠመኝ በማሳያነት ላንሳ፤ በእንግድነት በሄድኩበት ቤት ውስጥ የ11 ዓመት ሴት ልጅ እና የ13 ዓመት ወንድ ልጅ አላቸው እነዚህ ቤተሰቦች በጾታ እኩልነት የሚያምኑ ለወንድና ሴት ልጆቻቸው እኩል እድል የሚሰጡ ይህንንም አመለካከት በልጆቻቸው ማስረጽ የሚፈልጉ መሆናቸውን አውቃለሁ። እንግድነት በሄድኩበት ቀን የተመለከትኩት ጉዳይ ግን ለምን የሚል ጥያቄ እንዳነሳ አድርጎኛል።

የ11 ዓመቷ ሴት ልጅ ሆዷን ታማ ተኝታለች። ወቅቱ የበዓል ማግስት እንደሆኑ የበዓል ምግብ አለመስማማት ነው የሚል እሳቤ ተይዟል። ያም ቢሆን ታዲያ እኔና እናቷ ያሽላታል ብለን ያሰብነውን ስናደር ቆየን። መፍትሔው ያላሻላት ልጅ ሕመሙ ከብዷት ከተኛችበት ሶፋ ስትነሳ ታዲያ ሶፋውም ልብሷም ደም ነክቶ ነበር።

ልጅቷ የወር አበባ ስታይ የመጀመሪያዋ በመሆኑ ተደናግጣለች። ይሁን እንጂ ስለጉዳዩ በቂ ዕውቀት እንዳላት ከወላጅ እናቷ ጋር በነበራት መግባባት መረዳት ችያለሁ።

እኔን ያስገረመኝና ጥያቄ የጫረብኝ የታላቅ ወንድሟ ሁኔታ ነበር በእድሜ ሁለት ዓመት ቢበልጣትም ስለ ወር አበባ ምንም ዓይነት ግንዛቤ አልነበረውም። የሆነውን ሁሉ አብሮን እያየ ስለ ነበር እኛ ሁኔታውን እረስተን ቁጭ ብለን እንኳን እሱ በምግብ አለመስማማት ምክንያት መድማቷ አስጨንቆት እህቱ ምን እንደሆነች ሲጠይቅ ነበር። ልጁ እድሜው ከትምህርት ቤት ስለ ወር አበባ በጥቂቱም ቢሆን ግንዛቤ የሚይዝበት እድሜ ላይ ቢሆንም ጉዳዩን በቅጡ አልተረዳውም።

ወላጅ እናት ይህንን ጉዳይ ለታናሽ እህቱ በዝርዝር ስታስተምር ለወንድ ልጇ እህቱ የወር አበባ እንደሚያጋጥማትና በምን መልክ ሊረዳት እንደሚችል አላስረዳቸውም። እናት አሁንም የገጠማት ሕመም ቀላል መሆኑንና እንደማይመለከተው አስረድታ መጠየቁ እንዳስገረማት ለእኔ በጥቅሻ ነግራኝ ጉዳዩን አለፈችው። ይህ ነገር እየቆየም ቢሆን እንዳሳሰበው ተረድቻለሁ። እኔም ጋር ጥያቄ እንዲፈጠር አድርጓል።

የወር አበባ ሕመምን ወንዶች ለምን አይረዱትም ብዬ ከሚጠይቁ ሴቶች መካከል አንዷ ነኝና ምን አልባት አድገው ባል፣ የሥራ ባልደረባ፣ ጓደኛ ሆነው የምናገኛቸው ወንዶች ይህን ሕመም እንደቀላል የሚያዩት በዚህ መልኩ ስላደጉ ይሆን ብዬ እንዳስብ አድርጎኛል። የወር አበባ የሴቶች የግል ጉዳይ ተደርጎ መነገሩ ወንዶች የሴቶችን ሕመም እንዳይረዱ ከማድረጉ በተጨማሪ ብዙ ሴቶች ስለ ወር አበባ ሕመም ለመናገር እንዳይችሉና ቢናገሩ እንኳን ሀፍረት እየተሰማቸው እንዲሆን አድርጓል ባይ ነኝ።

ስለ ወር አበባና ሕመሙ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚነግሩበትን አነሳሁ እንጂ ችግሩን አዋቂና ተማሩ የሚባሉ ሰዎች ጋርም አስተውዬው አውቃለሁ። እዚህ ጋ የ10ኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ አብራኝ ትማር የነበረች ጓደኛዬን አስታውሳለሁ። ጓደኛዬ የወር አበባዋ ከመምጣቱ ከቀናት በፊት ጀምሮ ሆዴን ስትል የምሰማት ቢሆንም ከመጣበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ቀናት ት/ቤት ድርሽ አትልም። የዚህች ጓደኛዬ የወር አበባ ሕመም መጸዳጃ ቤት እንኳን እንደልብ መሄድ የማያስችላት ዓይነት ነበር። ጓደኛዬ የወር አበባዋ መጥቶ ከሁለት የትምህርት ቀናት ቆይታ በኋላ የደከመ ሰውነቷን ይዛ ነው ወደ ትምህርት ቤት የምትመለሰው።

የእኔ የጓደኝነት ድርሻም የሚቀጥለው ወር ላይ የወር አበባዋ መቼ እንደሚመጣ ቀን መቁጠርና ቅዳሜ ከሆነ ‹‹ደስ ሲል›› በማለት ሥራ ማቃለል ነበር።



ኢትዮጵያ ውስጥ ሴት ልጅ በወር አበባ ወቅት በሚያጋጥም ሕመም ምክንያት የትምህርትና የሥራ ፍቃድ መጠየቅ ቀርቶ የወር አበባን ሕመም ተረዱን ብሎ መናገር የሚያሳፍር የሆነበት ምክንያትም ይኸው ነው

ጓደኛዬ፤ በአንዱ ወር ላይ የወር አበባዋ በመምጣቱ እንደተለመደው ሁለት ቀናት ከትምህርት ቀርታ ወደ ትምህርት ቤት ስትመለስ የክፍል ኃላፊ መምህራችን ከክፍል የመቅረቷን ምክንያት ሲጠይቃት የወር አበባ ሕመም መሆኑን አስረዳችው። ነገር ግን ‹‹ይሄ ሰበብ ነው›› በማለት ወላጅ እንድታመጣ አድርጓታል። ከዛን ጊዜ ጀምሮ ታዲያ ጓደኛዬ፤ የየወሩ ጭንቀቷ ሕመሟ ሳይሆን ለቀረችበት አሳማኝ የሆነ የውሸት ምክንያት መፍጥር እንደነበር አስታውሳለሁ።

ጓደኛዬ ትምህርቷን ጨርሳ ወደ ሥራው ዓለም ስትቀላቀል ሕመሟን መረዳት የማይችሉ ሰዎች በሌላ ተተክተው አግኝታለቸዋለች። ተቀጥራ ሥራ በጀመረችበት የግል ድርጅት በዚህ ሕመሟ ሳቢያ በተደጋጋሚ ደመወዝ ተቆርጦባታል። ያለ በቂ ምክንያት በመቅረት በሚል የጽሑፍ ማስጠንቀቂያም ደርሷታል። ስለሆነም አማራጯ በየወሩ የሕመም ማስታገሻ መድኃኒቶችን በእጥፍ እየወሰደች በሥራ ገበታዋ ላይ መገኘት እንደሆነ አጫውታኛለች።

በግሌ ይህ ታሪክ የአንድ ጓደኛዬ ታሪክ ብቻ አይመስለኝም። ብዙ እንስቶች ‹‹እኔም እኔም›› እያሉ እንደሚጋሩት አምናለሁ። የወር አበባ ሕመምና ስሜት አለመረዳት ወንዶች ላይ የጎላ ቢሆንም የወር አበባ ሕመም ሁሉም ሴት የሚያጋጥማት ባለመሆኑ የማያቁትና የተካበደ የሚመስላቸው እንዳሉም አውቃለሁ። በቅርቡ እንኳን ስለሴቶች ያገባኛል ስትል የማውቃት አንዷት ሴት ጉዳዩ ይሰማታል ብዬ ስለ ጓደኛዬ ስለሁኔታው ባጫውታት ‹‹አንቺ ደግሞ ምን ይሁን ነው የምትይው ስንት ችግር ባለበት ሀገር ስለ ሴት ልጅ የወር አበባ እናውራ›› በማለት ነገሩን አጣጥላዋለች።

እንግዲህ እንደ እኔ እምነት እንዲህ ዓይነቱ ማሸማቀቅ ጉዳዩ ትኩረት እንዳያገኝ አድርጓል። ባይ ነኝ። ኢትዮጵያ ውስጥ ሴት ልጅ በወር አበባ ወቅት በሚያጋጥም ሕመም ምክንያት የትምህርትና የሥራ ፍቃድ መጠየቅ ቀርቶ የወር አበባን ሕመም ተረዱን ብሎ መናገር የሚያሳፍር የሆነበት ምክንያትም ይኸው ነው።

ለወር አበባ የሥራና የትምህርት ፍቃድ መጠየቅ በእኛ ሀገር ገና ያልታሰበበት ጉዳይ ቢሆንም በዓለማችን ጃፓን፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ታይዋንና አፍሪካዊቷ ታንዛንያ የሴት ልጅ እኩልነትና መብትን ሲያስቡ ተያያዥ የሆነውን የወር አበባ ፍቃድን አስበው በሕግ ደረጃ ካስተዋወቁ ሀገራት መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

የወር አበባን በተመለከተ ሕመሙን አለመረዳትና ፍቃድ አለማግኘትን በሀገራችን ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ መሆኑን አነሳሁ እንጂ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ሌሎች ብዙ ችግሮች አሉ። ለሴት ልጅ ንጽህና መጠበቂያ የሚያገለግለው ሞዴስ እንኳ ሁሉም ሴት እንደልቡ የሚያገኘውና በቀላሉ ዋጋ ሊሸምተው የሚችል አይደለም። በሞዴስ መወደድ ሳቢያ የንጽሕና መጠበቂያ ሞዴሷን በሰዓት መቀየር ያልቻለች ሴት ልጅ ተቀምጣ በተነሳች ቁጥር ወንበሯን ዞራ ማየቷና ልብሴ ነካ አልነካ በሚል መሳቀቋ የተለመደ ነው። አለፍ ሲልም ከትምህርት ገበታዋ መቅረቷ ግዴታዋ ነው።

ባደጉት ሀገራት ሞዴስ የሚያስፈልጋቸው ሴቶች እንዲጠቀሙ መንገድ ላይ የሚቀመጥ ነገር እንደሆነ እንሰማለን እኛም ሀገር ሞዴስ ለመግዛት አቅም የሌላቸው ሴቶች ይህን እድል ያግኙና ዋጋው ተመጣጣኝ ይሁን የሚል ጩኸት ሰሚ የሌለው ጉዳያችን ነው።

እንደኔ እንደኔ ሀገራችን የቱንም ያህል ድሃ ብትሆን እንኳን ሞዴስ ማግኘትና የወር አበባ ሕመም ፍቃድ መጠየቅ ቅንጦት ሳይሆን፤ የሴትን ልጅ ተፈጥሮ ማክበርና መብቷን መጠበቅ ነው ባይ ነኝ።

ልዩ ዕትም

# ‹‹ብቁዋ ሴት ማጀት እንዳትቀር በሴት አክባሪ ሴቶች ትደገፍ››

ወይዘሮ ሲና ጌታቸው የሚዲያ ማናጀር



**አስመረት ብስራት**

በትምህርት እውቀት ያካበቱ፣ በተሰማሩበት የሙያ ዘርፍም ችሎታ ያዳበሩ ሰዎች የሀገር ባለውለታና የሕዝብ አለኝታ እንዲሆኑ ይታሰባል። ሀገርም በእውቀት ከመጠቁት በትምህርት ካደጉት ዜጎቿ ብዙ ትጠብቃለች። ይሁን እንጂ የመማር እድሉን አግኝተው በትምህርት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ አንዳንድ ሴቶች ሀገርና ሕዝብ የሚጠብቅባቸውን ሲወጡ አይስተዋሉም።

ምክንያቱ ደግሞ እናት ከመሆን ጋር የተያያዘ ነው። እናት በመሆናቸው ብቻ በተማሩት ትምህርት ሀገራቸውን ሳያገለግሉ። ራሳቸውንም በኢኮኖሚ ሳያሳድጉ ልጅ በማሳደግ በቤት ውስጥ ተወስነው ይቀራሉ። ምን ያህሉ ሴቶች በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙ ጥናት የሚያስፈልግ ቢሆንም ጥቂት እንዳልሆኑ ግን አሁን እየታየ ካለው ነባራዊ ሁኔታ መገንዘብ ይቻላል።

ልጅን በማሳደግ ቤተሰብን መንከባከብ ሴቶች ከፍተኛው ድርሻ እንዳላቸው ይታወቃል። ግን ደግሞ በጤናው ዘርፍ ተምራ ብዙዎችን ትታደጋለች ተብላ የምትጠበቅ ሐኪም ልጅ በመውለድ ምክንያት በቤት ውስጥ መወሰኗ ምን ያህል አግባብነት አለው? ጥያቄ ይፈጥራል። እንደ ሀገር ሲታሰብም ጉዳቱ ከፍተኛ ነው። የሕክምና ትምህርት ለመማር የተማረችው ሴት ድካም ብቻ ሳይሆን፤ ለትምህርት የወጣው ወጪ ጥቅም ላይ ሳይውል ባክኖ መቅረቱ ከኢኮኖሚያዊ ጥቅም አንፃር ጉዳት አለው።

የተነሳው ርዕሰ ጉዳይ በቀላሉ የሚታለፍ ጉዳይ እንዳልሆነም በችግሩ ውስጥ ያሉት ሴቶች ሲያነሱት አሳሳቢነቱን መገንዘብ ይቻላል። ተምረው ግን ልጅ በመውለዳቸው ምክንያት በተማሩት ትምህርት ሥራ መሥራት ካልቻሉትና ልጅ በማሳደግ በቤት ውስጥ ከተወሰኑት መካከል አንዷ ከሆነችው ወይዘሮ መክሊት አየነው ጋር ተጨዋውተናል።

ወይዘሮ መክሊት በመካከለኛ ዕድሜ ውስጥ የምትገኝ ሴት ናት። እናቷ የቤት እመቤት ናቸው። አባቷ ደግሞ የሕክምና ባለሙያ ናቸው። ከአምስት ልጆች መካከል ሶስተኛ ልጅ ናት። ትልቅ ደረጃ ላይ መድረስ የሚቻለው በትምህርት ብቻ እንደሆነ ከቤተሰቦችዋ እየሰማች ነው ያደገችው። እርስዋም በትምህርቷ ጠንክራ ውጤታማ ለመሆን ለትምህርቷ ትኩረት ሰጥታ ቀን ተሌት ነበር በጥናትና በንባብ የምታሳልፈው።

ወይዘሮ መክሊት ለትምህርቷ ጊዜ ብትሰጥም፤ በቤት ውስጥ የሚያስጨንቃት ነገር ደግሞ የመማር ጉጉቷን መጨመሩንም ታስታውሳለች። እናቷ ልጆች ለማሳደግ፣ በተለይም በወር መጨረሻ ላይ ጓዳቸው ጎሎ ለማሟላት ሲጨነቁ ታይ ስለነበር እናቷን ከጭንቀታቸው ለማውጣት ነበር ህልሟ። እድል ቀንቷትም በትምህርቷ ገፍታ በመጀመሪያ ዲግሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመረቀች።

ከፍ ማለት፤ የተሻለች ሆና ለመገኘት የነበራት ህልሟንም ለማሳካት ትምህርት ተቀዳሚ ምርጫዬ ነው ያለችው ወጣት ወዲያው ነበር ሁለተኛ ዲግሪዋን ለማግኘት የተመዘገበችው። የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቷን በመከታተል ላይ እያለች ነበር ከልጅነት ጓደኛዋ ጋር ወደ ትዳር የገባችው። ትዳር መያዝዋ ግን የጀመረችውን ትምህርት ከማጠናቀቅ አላገዳትም። ይሁን እንጂ በተማረችው ትምህርት ሥራ ለመሥራት አልወሰነችም። በወቅቱ “አንደኛሽን ወልደሽ ሥራ ትፈለጊያለሽ” የሚል አስተያየት የበዛ ስለነበር እርሷም ተቀበለችው። በተከታታይ ሶስት ልጆች ወለደች።

እርስዋ እንዳለችው፤ የትዳር መጀመሪያ አካባቢ ሁሉ የሞላላት የቤት እመቤት እንደሆነች ዓይነት ስሜት ነው የነበራት። ውሎ ሲያድር ግን የእሷ መማርና የሁለት ዲግሪ ባለቤት መሆን ካልተማረቸው እናቷ የተለየ ሕይወት ሊሰጣት ያለመቻሉ ነገር ውስጧን ይከነከናት ገባ።

ልጅ በልጅ ላይ ሲደራረብ በአንድ ሰው አቅም ቤተሰብን እንደ ልብ መምራት ሲያቅት ቤት ያለው ጭቅጭቅ እየጨመረ ቤተሰቡ ደስተኝነቱ እየጠፋ እሷም ያላሰበችው ዓይነት የእእምሮ ውጥረት ውስጥ ልተገባ ቻለች። በራሷ ሰርታ ማግኘት ባለመቻሏና የሌላ ሰው እጅ ጠባቂ መሆኗ ከእለት ወደ እለት እያስከፋት መጣ።

ያንን ታግላ ለማሸነፍ ብታስብም እችላለሁ የሚል አስተሳሰብ ከውስጧ ቀስ በቀስ ወጥቶ በራስ መተማመኗ መጥፋቱን ታስተውላለች። ወይዘሮ መክሊት ደጋግሞ መውለድ ያመጣባት ድባቴ፤ የኢኮኖሚ ጥገኝነቱ፤ የማኅበረሰብ ጫናን መቋቋም አቅቷት እጅግ ከባድ የሚባሉ ቀናትን አሳልፋ እንደነበረ ታስታውሳለች።

በትምህርትም፤ በደረጃም ከእሷ ጋር ከማይስተካከሉ ሰዎች ጋር መዋሏ ለዓመታት የለፋችበት የትምህርቷ ነገር በዜሮ መባዛቱን ስታስብ ነበር ከባድ ሀዘን ውስጥ የገባችው። ያኔ ነው አብረዋት የተማሩት ከሷ ቀድመው ሥራ የያዙ ጓደኞቿ በሰጧት ልባዊ ድጋፍ ተገፋፍታ ከጓዳ የወጣችው። ሰፊ ቀሚሷን አውልቃ በሥራ ልብስ አደባባይ መውጣቷን ማመን እስኪያቅታት ድረስ እጅግ ብዙ ከባድ የሕይወት ትግልን አሳልፋ ኃላፊነት ቦታ የደረሰችው።

ሴቶች ለልጅ ብለው ከከፍተኛ ኃላፊነታቸው የወረዱ፤ ተምረው ጓዳ የዋሉ እናቶችን ዳግም በልበ ሙሉነት ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ሊያደርግ የሚችል ተቋም ቢኖር ስትል ምኞቷን ተናገራለች።

በርካታ የመክሊት ዓይነት እናቶች ከሁለት ዲግሪ በላይ ይዘው ልጅ በማሳደግ ሰበብ ቤት ከዋሉ በኋላ በተለያዩ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ ስር በመውደቃቸው በራስ መተማመናቸው ሲጠፋ መታየቱንም፤ በተለያዩ እናቶች ሃሳባቸውን በሚያካፍሉበት ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ለመመልከት ይቻላል። እናት እናትን ብትደግፍ፤ ሴት አክባሪ ሴት ብትፈጠር፤ ሀገር ካላት ላይ በርካታ ገንዘብ ያፈሰሰችባቸው የተማሩ ሴቶች ቤት ከመቀረት አደባባይ ወጥተው ማገልግለ ይጀምራሉ።

ሌላዋ ባለታሪካችን ይህ ጉዳዩ ነው ያለች ተምሮ ቤት መቅረት በእኔ ይብቃ ያለች፤ ቤት የቀሩ የተማሩ ሴቶችን አነቃቅቶ አደባባይ ማውጣትን ዓላማው አድርጎ የሚንቀሳቀስ “ሴት አክባሪ ሴት” የሚል መሪ ሃሳብ ያለው ፕሮጀክት ቀርፃ መንቀሳቀስ ጀመረች። በፕሮጀክቱ የተማሩ አቅም ያላቸው እናቶች ጓዳ አይቅሩ የምትለን የአንድ ሰው ፕሮሞሽንና ኢቨንት ሚዲያ ማናጀር የሆነችው ወይዘሮ ሲና ጌታቸው ናት። ይህች ሴት “የሴት አክባሪ ሴት” የተባለው ፕሮጀክት ኃላፊ ናት።

ይህን ፕሮጀክት እንድታስብ ያደረጋት በሙሉ ጊዜ የእናትነት ወቅት ልጆቿ ሲተኙ የተለያዩ ፊልሞችና ድራማዎች ስትፅፍ የቆየች ሲሆን፤ ሥራዎቿ እጇ ላይ ሲጠራቀሙ ልጆቿ እያደጉ ቢሄዱም ወደ ሥራ ለመመለስ ማሰብ ብትጀመርም ወደ ሥራዋ እንድትመለስ የሚያበረታት ሁኔታም ሆነ ሰው ከጎኗ ታጣለች።

እናቷ እህቶቿ በአጠቃላይ ዙሪያዋ ያሉ ሰዎች በሙሉ ሴት ካገባችና ከወለደች በኋላ ባለቤቷንና ልጆቿን መንከባከብ ብቻ ይበቃታል የሚል አስተሳሰብ ይዘው የመውጣት ፍላጎቷን እንድታቆም ይጎተጉቷት ጀመር። ያኔ ነው እንግዲህ ለአርት የተፈጠረችው ይች ሴት ቢያንስ የፃፈቻቸው ጽሑፎች ለመድረክ መብቃት ይኖርባቸዋል የሚል ሃሳብ ይዛ ተነሳች።

እናትነት፤ ለቤተሰብ ኃላፊ፤ ለባልም ጥሩ ሚስት መሆን ጥሩ ቢሆንም እየሠሩ ያንን ማድረግ መቻል የሚቻል መሆንን ለማየት በማህበራዊ ሚዲያ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ማውራት ጀመረች። ያኔ ብዙ ሰዎች ልጆቼ ሲያድጉ ወደ ሥራ እመለሳለሁ ብለው ቤታቸው ቢቀሩም መልሶ መውጣት ግን እጅግ አስቸጋሪ የሚሆንባቸው ብዙ ሴቶች በየቤታቸው እንዳሉ ታውቃለች።

**ሴቶች ለልጅ ብለው ከከፍተኛ ኃላፊነታቸው የወረዱ፤ ተምረው ጓዳ የዋሉ እናቶችን ዳግም በልበ ሙሉነት ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ሊያደርግ የሚችል ተቋም ቢኖር ብዬ እመኛለሁ**

አብዛኛዎቹ ሴቶች ገንዘብ አግኝተው በራሳቸው ገንዘብ በርካታ ነገሮችን ሲደርጉ ቆይተው አሁን ግን ተቀባይ መሆን ሲጀመሩ በራስ መተማመናቸው መጥፋትና ደስ የማይል ስሜት ውስጥ መግባት ይጀምራሉ። ሴት ልጅ ውጭ ውላ ስትገባ ራሷን እንደምትጠብቀው ቤት ስትውል ግን የቤት ውስጥ ሥራ ጫና ጋር ራሷን መጣል በዛው ለራሷ ያላት ግምት የመውረድ ዓይነት ባህሪ ታሳያለች።

የተማረች ሴት ልጆቿ ካደጉ በኋላ እንኳን ወጥታ ለመሥራት ያላት ፍላጎት እየጠፋ ትናንት የነበረችበት አቋም እየወረደ ሲሄድ በትዳር አጋሮች በኩልም የሚመጡ ጫናዎች ይበዛሉ። የተቀባይነት መንፈሱና አልችልም የሚለው ስሜት እያደገ መምጣቱ በራሱ ከባድ መሆን ይጀምራል ትለናለች። ያኔ ልጆቿ አድገው ትምህርት ቤት ሲገቡ ነበር ከወሊድ በኋላ ካለው ድባቴ ውስጥ ለመውጣት መታገል የጀመረችው።

ይህን ሥራ ስታስብ የአስራ ሶስት ዓመት ሴት ልጇ ሴት ልጅ መውለዷ ካሰበችው ሕልም ሊያስቀራት የማይችል መሆኑን ለማሳየት ብሎም እሷን መሰሎችን አቅም ሆና ካሉበት ማህበራዊና ሥነ ልቦናዊ ተፅእኖ ገፍታ መውጣት ጀመረች። ለራስ ችግር እራስ ካልበረቱ ማንም ሰው እጅን ይዞ ሊያስወጣ የማይችል መሆኑን በማወቅ ሴት አክባሪ ሴት በሚል ቀድመው የወጡቱ ቤት የቀሩትን ሴቶች አቅም በማጎልበት አደባባይ እንዲወጡ የማገዝ ሥራ ላይ ተሰማራች።

እናትነት በራሱ የሚያመጣቸው ተፅእኖ በላይ ያለው ሥነ ልቦናዊ ጫና ከባድ መሆኑን ለማሸነፍ ስትሞክር እራሳቸው ሴቶቹ ጉዳዩን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸው ሥራው እንዳይሳካ አድርጎት እንደነበረ ሲና ትናገራለች።

ዳግም የመወለድ ያህል ሕይወትን እንደገና ለመጀመር የምትተጋውን ሴት በቅድሚያ የማነቃቂያ ሥልጠናዎችን መስጠት ማኅበረሰቡም ግንዛቤው ከፍ እንዲል የተለያዩ ዓይነት ሥልጠናዎች በሴት አክባሪ ሴት ፕሮጀክት ስር እንዲሰጥ መሥራት ጀመረች።

**ሴት አክባሪ ሴት የሚለው ሃሳብ የተነሳው ሴቶች ራሳቸው ሌሎች ሴቶች አይችሉም የሚል አመለካከት ከውስጣቸው አውጥተው በመደጋገፍ ችግሮቻቸውን በመጋፈጥ ፊት መቆም እንደሚገባቸው ለማሳየት ነው**

ሴት አክባሪ ሴት የሚለው ሃሳብ የተነሳው ሴቶች ራሳቸው ሌሎች ሴቶች አይችሉም የሚል አመለካከት ከውስጣቸው አውጥተው በመደጋገፍ ችግሮቻቸውን በመጋፈጥ ፊት መቆም እንደሚገባቸው ለማሳየት ነው የምትለው ወይዘሮ ሲና ይህንን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ የተለያዩ ኪነጥበባዊ መድረኮች፤ ድራማዎችና ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በሰፊው እየሠራች ትገኛለች።

ከክፍለ ከተሞች ከሴቶች ጉዳይ ጋር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥራውን ያስጀመረችው ወይዘሮ ሲና አንዲት ሴት ልጆቼ አድገዋል ይበቃል መውጣትና መሥራት አለብኝ ብላ ለመነሳት የሌላዋ ጠንካራ ሴት ድጋፍ እንድትሰጥ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ይሰራል።

ይህ ሃሳብ የተነሳው እህቷ ላይ በር የምትዘጋ ሳይሆን፤ እህቷን የምትደገፍ ትውልድን ያፈራች ለሀገር ተረካቢ አበራካች የሆነች እናትን ሴቶች በራሳቸው ተደጋግፈው መቆም የሚችሉበት ምቹ ሁኔታን መፈጠር ነው። ሴቶች እናትነት የተሰጣቸው ትልቅ ፀጋ ሲሆን፤ እናት በመሆናቸው የተነሳ የተለያዩ ጫናዎች እንዳይፈጠርባቸው መደጋገፍ ላይ መሥራት ይገባል።

መንግሥት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለሚወለዱ እናቶች የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ መሆኑ ያስመሰግንዋል የምትለው ሲና የወሊድ ፍቃድ ወደ አራት ወር ማደጉ፤ የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የሕፃናት ማቆያ መቋቋሙ ይበል የሚያሰኝ ነው። ሴቶች እናት በመሆናቸው ብቻ ያለችው አቅም ይወርዳል ብለው የሚያስቡ ሰዎችም ይበልጥ ኃላፊነት የሚሰማት መሆኑን ተርደተው ለተሻለ ኃላፊነት የማጨት ልምድ እንዲኖር መደረግ አለበት። አሁን የበቃች ሴት ወለድኩ በሚል ምክንያት ጓዳዋ እንዳትቀር በርካታ ሴት አክባሪ ሴቶች መፈጠር ይገባቸዋል ብላለች።

እኛም ትልቅ ፀጋ የሆነው እናትነት የሴትን ስኬት ወደኋላ እንዳይጎተት የበቃች ልጆቿን እያሳደገችም ሀገር የምትመራ ሴት ትኖር ዘንድ ሴቶች ራሳቸው ለሴቶች ይቁም እላለሁ።

# ‹‹ሴትነት የፆታ መገለጫ እንጂ የአቅምና የብቃት ማሳያ አይደለም››

## ዮሐና ረታ
## የጎልደን ስታርስ ኮሌጅ ባለቤት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የብዙ ውጤታማ ሰዎች የስኬት መነሻ ከወደቁበት ለመነሳት በሚታገሉበት በዚያ ስፍራ እንደሆነ ታምናለች። ገና በለጋ እድሜዋ ያጋጠማትን ወድቆ የመነሳት አጋጣሚ እዚህ ለመድረሷ መሠረት እንደሆናት ትገልፃለች። ከገባችበት የተስፋ መቁረጥ ጎዳና ለመውጣትና ሌላ የሕይወት መስመር በመፈለግ ሙከራ ስታደርግ ነበር ከአዲሱ ሕልሟ ጋር የተገናኘችው። እንግዳችን ዮሐና ረታ ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ከምትገኘው ለምለሚና ውቢቷ ቢሾፍቱ ተወልዳ ማደጓንና ከሃገር ወዳድ ወታደር ቤተሰብ መምጣቷን በኩራት ትናገራለች። አሁን ላላት ስብዕናና ማንነት፣ ከሀገር ወዳዱ አባቷ የወረሰችው እንደሆነም ታስረዳለች። ለሌሎች ራስን መስዋዕት ማድረግን፣ የዓላማ ፅናትና፣ ላመነችበት ነገር እስከ መጨረሻ መታገልንና ድል ላይ መድረስንም ጭምር እንዲሁ።

የማንኛውም ሰው የመጀመሪያ ትምህርት ቤቱ ቤተሰብ፤ የሕይወት ተምሳሌቱ ደግሞ እናትና አባት እንደመሆናቸው መጠን የዚህች ጠንካራ ሴት ስብዕና የተገነባው በወላጆቿ መልካም አስተዳደግ መሆኑን አበክራ ትናገራለች። ‹‹አዎ ትውልድ መቀረፅ የሚጀምረው በቤተሰብ ውስጥ ነው”። ቤተሰብ ልጆቹን በፆታ ሳይለይ ማሳደግ አለበት። በተለይ እናት ደግሞ ለሴት ልጇ የመጀመሪያ የሕይወት ተምሳሌት ነችና በቤት ውስጥም ሆነ በውጪ ያላትን ተግባርን እያዩ ሲያድጉ ለልጆቿ ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖራታል።›› የምትለው እንግዳችን ዮሀና፤ ሴት መሆኔን ሳይሆን ዓላማ ያላት ሰው መሆኔን እየነገሩኝ ያሳደጉኝ ወላጆቼ ትልቅ አቅም ሆነውኛል ትላለች።

በተለይ የአባቷ መልሶች የእርሷ ጥንካሬና ስኬት እንደሆነም ታስረዳለች። ‹‹እኔ የበኩር ልጅ በመሆኔ ሰዎች ‹ቶሎ ወንድ ልጅ ውለድ ስምህን የሚያስጠራ› ሲሉት መልሱ ግን ሁሌ አንድ ነበር። ይህም ‹ስሜን የምታስጠራ ልጅ ወልጃለሁ ያውም የኔን ሥራ የምታስቀጥል ታላቅ ሴት › የሚል ነበር። እናም ይህ ነገሩ በሴትነቴ እንድኮራ፣ ካሰብኩት እንድደርስ፤ ሴት ሆኜ መሰናክልና ተግዳሮቶቼን እንዳልፋቸው አድርጎኛል›› ትላለች።

እንደዮሐና ገለፃ፤ ሕይወትን በተግባር እንድታይ፤ እንድትማር የሕይወት አሰልጣኝዋ ሆነው ያሳደጓት እናቷ ናቸው። በተለይም ከአባቷ ሞት በኋላ ብቻቸውን ያሳደጓት እናቷ በመሆናቸው ‹‹የሴት ልጅ›› እየተባለች ማደጓ እንድትኮራ እንጂ እንድታፍር አላደረጋትም። ይልቁንም ሁልጊዜ ‹‹ሴት ያሳደገኝ ያውም የጀግና ሴት ልጅ ነኝ” እንድትል አስችሏታል። የአባቷ መሞት እሷን ጨምሮ ሦስት ልጆችን የማሳደግ ኃላፊነት እናቷ ጫንቃ ላይ ወደቀ። እርትዋ እናት ያለማንም ድጋፍ ልጆቻቸው ምንም ሳይጎልባቸው፤ በሥነ-ምግባር ታንፀው እንዲያድጉ በማድረግ ሚናቸውን በሚገባ ተወጡ። የእናቷን ጥንካሬና ታታሪነት እያየች ማደጓ በራስ የመተማመን ችሎታ እንድታዳብር አድርጓታል። ኃላፊነትን መወጣትን፣ በሕይወትን በስኬት ለመምራት ተግዳሮቶችን እንዴት ማሸነፍ እንደሚቻል ተምራለች።

### ጊዜንና አጋጣሚዎችን መጠቀም

ዮሀና ጊዜንና መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ የመጠቀም ችሎታዋ ወደ ስኬት መድረሻ አንዱ መንገድ እንደሆነ ታምናለች። በተለያዩ ቦታዎች የሚገጥሙንን መልካምም ሆነ መጥፎ አጋጣሚዎችን ለሕይወታችን የስኬት ጉዞ እንድንጠቀመው ትመክራለች። ይህች ጠንካራ ሴት ጊዜን በአግባቡ መጠቀምን ማሳያም ነች። ምክንያቱም በአስራዎቹ መጨረሻዎች ያጋጠማትን ችግር ወደ መልካም ዕድል ቀይራ ለብዙዎች ተርፋለች።

ዮሐና በሃያዎቹ ግማሽ ደግሞ ትዳር በመመስረት የሁለት ሴት ልጆች እናትም ሆናለች። ሴቶች ሁሉን በወቅቱ በማድረግ ብልሆች መሆን አለብን የሚል አቋምም አላት። ሴቶች ስኬትና ቤተሰብን አብሮ ማስኬድ ተግዳሮት ይሆንባቸዋል። ይሁንና ቤተሰብ አንዱ የሕይወት ስኬት መገለጫም እንደመሆኑ ትኩረት ማድረግ ብልህነት በመሆኑ ችግሩን ወደ ድል ቀይረው እናያቸዋለን ትላለች።

ሴት ልጅ በቤት ውስጥ ካላት ከፍተኛ የትዳርና የልጆች እንዲሁም ቤት የመምራት ኃላፊነት ባሻገር በውጪ ወጥታ ሕልሟን ለመኖር የምታደርገው ትግል በአብዛኛው እኩል ማካሄድ ፈታኝ ይሆንባታል። እናም አንዱን በአንዱ ውስጥ ትሰዋለች፤ ሆኖም ጥቂቶች በርትተው ሁለቱንም በእኩል ለማስኬድ ችለዋልና ያን የመሆንን አጋጣሚ መጠቀም እንደሚገባም ታስረዳለች። ለዚህ ደግሞ ከትዳር አጋሯ ጀምሮ የቤተሰብ የማኅበረሰብ እንዲሁም መንግሥት ከፍተኛ ድጋፍ ያስፈልጋታል ባይም ነች።



‹‹ሴት ሆኜ ለመፈጠሬ አስተዋፅዖ ባይኖረኝም የማኅበረሰቡን ኋላቀር አስተሳሰብ ተጋፍጦ ማሸነፍ ግን እችላለሁ። በሴቶች ላይ ያስቀመጠውን ገደብ ማለፍ እንደሚቻልም በኔ ፅናትና ትጋት ማሳየት እችላለሁ››

‹‹በየዓመቱ አንድ ቀን ብቻ የሴቶች ቀንን በጋራ ከማክበር ባለፈ የሴቶችን አቅም ለማዳበር በሞራል፣ በኢኮኖሚ፣ የተለያዩ ግብዓቶች መደገፍ የዕለት ተዕለት ተግባር መሆን ይኖርበታል። ያኔ ነው ሀገራችን በተገቢው የሴቶችን አቅም በአግባቡ መጠቀም የምትችለው›› የምትለው ዮሐና፤ ሴትም የራሷ ድርሻ እንዳላት ታነሳለች። ሕይወት በብዙ አማራጭ ጎዳናዎች የተሞላች ነች። እኛም የምርጫችን ውጤት ነን፤ ይህ ከሆነ ደግሞ ምርጫችንና ውሳኔያችንን ራሳችን እንጂ ሌላ ሰው እንዲመርጥልን አሳልፈን መስጠት የለብንም የሚል እምነት አላት። መኖራችን ዓላማና ግብ ያለው መሆን ይገባዋል ብላ ታስባለችም። የምንወደውን በመሥራት የምንኖርንበትን ዓላማ ልናሳካ እንደሚገባ ትመክራለች።

### የሕይወት ፍልስፍና

‹‹ተመሳስሎ ሁሉም የሚኖረውን መኖር አልወድም፤ አዲስ ነገርን መሞከር ያስደስተኛል፣ ታግዬ ማሸነፍ ለሕይወቴ ትርጉም ይሰጠኛል፣ ሌሎች የፈጠሩልኝ ዓለም ተቀብሎ መኖር ሳይሆን ለሌሎች መትረፍ እርካታ ይሰጠኛል›› የምትለው እንግዳችን፤ ይህንን በተግባር የተረጎመች ትገኛለች። ገና በለጋ እድሜዋ የትላላቅ ዕራዮች ባለቤት፣ ከራስና ከቤተሰብ ያለፈ ኃላፊነት ያለባትና በዚህች የምድር ቆይታዋ በዓላማ ተፈጥራ፣ ለዓላማዋ ኖራ፣ ዓላማዋን ፈፅማ ለማለፍ እየታተረች ትገኛለች። በዚህ አቋሟም ብዙዎችን ከችግራቸው ታድጋለች። ለአብነት ሕጻናትና ሴቶችን የሚረዳ ሀገር በቀል በኋላም ዓለምአቀፍ የሆነውን ‹‹ሴቭ ሄቨን አሶሴሽን የእርዳታ ድርጅት›› በማቋቋምና በሥራ አስኪያጅነት በመምራት አጋርነቷን ማሳየት ችላለች። የብዙ ሺዎችን ሴትና ሕጻናት እንባ አብሳለች። የተጎዱና በኤች.አይ. ቪ በደማቸው ውስጥ ያሉ ሴቶችን አቅም አጎልብታ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች መኖርን እንዲጀምሩ አድርጋለች። በዚህም ሥራዋ ደግሞ በሀገራችንና በተለያዩ አሕጉረ አፍሪካ፣ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ በመዘዋወር ሽልማቶችን አግኝታለች። የሀገር ውስጥና የውጪም መጽሔቶችና ጋዜጦች ‹‹ወጣቷ በጎ አድራጊ›› በሚል ርዕስ ስለእሷ ከትበውላታል።

ዮሐና በመውደቅ መነሳት ውስጥ አቅሜን እፈትናለሁ የሚል አቋምም ያላት ወጣት ነች። ከዚህ አንጻርም በሰው አዕምሮ፣ ሕይወትና ስብዕና ላይ መሥራት ያስደስታታል። ብዙው ጊዜዋንም የምትፈጀው በዚሁ ተግባር ላይ ነው። በእሷ እድሜና በሴቶች የማይደፈሩ ሥራዎችን መሞከር ልምዷም ፍላጎቷም ነው። ምክንያቷ ደግሞ ለሌሎች ተምሳሌት መሆንን ትፈልጋለችና ነው። በተለይ የሁለት ሴት ልጆች እናት መሆኗ ይህንን ሥራ ይበልጥ እንድትገፋበት አድርጓታል። ሴት ልጆቿም ሆኑ ሌሎች ሴቶች ሴትነት ውበት፣ ጥንካሬ፣ ስኬታማነት መሆኑን እንዲያምኑና በዚያ መሠረት ላይ እንዲቆሙም ትፈልጋለች። ‹‹ሴትነት የፆታ መገለጫ እንጂ የአቅምና የብቃት ማሳያ አይደለም›› የሚለውን አቋሟን አበክራ ለሁሉም ማስረዳት ትሻለች።

### የሥራ ሕይወት

ዛሬ በሦስት ከተሞች ላይ ካምፓሶችን ከፍታ በማንኛውም ቦታ ላይ ብትሆን እንደምታሸንፍ አሳይታለች። አምስት ዓመታትን ያሳለፈው ‹‹ጎልደን ስታርስ ኮሌጅ›› በቲቪቲ፣ ዲግሪ ተማሪዎችን ያሠለጥናል። በቅርቡ ደግሞ በማስተርስ ለማስተማር በዝግጅት ላይ ይገኛል። ለበርካታ ምሑራን መምሕራንና ሠራተኞች የሥራ እድል ፈጥሯል። ማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎትም እየሰጠ ነው። የተለያዩ የምርምር ሥራዎችን በመሥራትም ሀገራዊ ኃላፊነቱን ይወጣል። ለበርካታ አቅመ ደካማ ተማሪዎች ነፃ ትምህርት ዕድልን፣ ለተማሪዎች፣ ሴቶችና ወጣቶች ሥልጠናዎችና ይሰጣል።

ዮሐና የወጣቶችና የሴቶችን አቅም ለማጎልበት ‹‹በጎልደን ብሪጅ ሥልጠናና ማማከር ድርጅትም›› የተለያዩ አመራርነት፣ የአቅም ግንባታ፣ የሥራ ፈጠራ ክህሎት እንዲሁም አጫጭር ሥልጠናዎችን ትሰጣለች። በማማከርና በአጠቃላይ በተለያዩ ከተሞች የሴቶችን የሚያበረታታ አቅም ግምባታና የማነቃቂያ ዎርክሾፕ በማድረግ የተለያዩ ወጣቶችንና ሴቶችን የሚያበረታቱ ተግባራትን ታከናውናለች። በውሳኔዋ መፅናቷና ተግዳሮቶቿን በድል በመወጣቷ በምታገኘው እርካታ የገጠሟትን መሰናክሎች ሁሉ እንደ መስፈንጠሪያ ድንጋይ መጠቀምን ትወዳለች። ዛሬ ለብዙዎች የምታካፍለውና በርካቶችን የምታበረታታውም ለዚህ ነው።

ሰው ሥራ ሲሠራ ደልዳላ የሕይወት ጎዳና መጠበቅ የለበትም። አባጣ ጎርባጣው ከስኬት ላይ እንደሚያደርስም መረዳት ያስፈልጋል። ድሉ ደግሞ ጣፋጭ እንደሚሆንም መመልከት ይገባል። ስለዚህም ስኬትን በቁስ፣ ዝናና፣ ክብር ብቻ መመልከት አይኖርብንም። ስኬት ከዚያም በላይ ነው፡ ሕልምን የመኖር፣ የሌሎች መትረፍም መሆኑን መገንዘብ አለብን›› የምትለው ዮሐና፤ በሀገሪቱ የሴቶች ቁጥር ከፍተኛ ቢሆንም በተለያዩ አስተሳሰብ፣ ችግሮችና ተግዳሮቶች ምክንያት አቅማቸውን ማውጣት ባለመቻላቸው ሀገር በሚፈለገው መጠን አልተጠቀመባቸውም። በኅብረተሰቡና በሌሎች ላይ በማሳበብ ያላቸውን እድል ሳይጠቀሙ አቅማቸውን በተገቢው ሳያወጡ፣ ሕልማቸውን ሳይኖሩ በሌላ ሰው ሕልም ተሸፍነው በቁጭት የሚኖሩ በርካቶች ናቸው። ስለሆነም ሴቶች ሕልምን ለመኖር ቆራጥነትን፣ የውሳኔ ሰው መሆንንና ውጣውረዶችን ለመጋፈጥ መወሰን ይኖርባቸዋል ትላለች።

### የሥራ ላይ ፈተና

‹‹ሴት ሆኜ ለመፈጠሬ አስተዋፅዖ ባይኖረኝም የማኅበረሰቡን ኋላቀር አስተሳሰብ ተጋፍጦ ማሸነፍ ግን እችላለሁ። በሴቶች ላይ ያስቀመጠውን ገደብ ማለፍ እንደሚቻልም በኔ ፅናትና ትጋት ማሳየት እችላለሁ›› የምትለው ዮሐና ለብዙዎች እንደ ችግር የሚመለከቱት ነገር ለጥቂቶች መልካም አጋጣሚ የሥራ እድልም ይፈጥራል ብላ ታስባለች። ለዚህም እንደማሳያነት የምትጠቅሰው በ2011 ዓ.ም በደቡብ ክልል የሆነውን ጉዳይ ነው። በወቅቱ የነበረውን የክልል መሆን ጥያቄና አለመረጋጋት ምክንያት ብዙዎች ሀዋሳ ከተማን ጥለው ቢወጡም እርሷ ግን ወደዚያ በማምራት ችግሩን ወደ ጎን ትታ የወቅቱ ሁኔታ ሳይበግራት ኮሌጅ መክፈት ለስኬት በቅታለች።

በእርግጥ በጊዜው በበርካታ ፈተና ተፈትናለች። በተለይም ወደማታውቀው ቦታ በድፍረት መሄዷና የአካባቢው ባሕልና ወግ ያለማወቋ እንዲሁም የተመቻቸ ኑሮዋን ቤተሰቧን ትታ መሄዷ ነው። ሌላኛው ደግሞ ለቅርብ ቤተሰቧና ጓደኞቿ በአካባቢው የነበረው የፀጥታ ችግር ስጋትና ጭንቀት ከፍተኛ እንደነበር ታስታውሳለች። በአብዛኛው በወንዶች የሚሠራ የከፍተኛ ትምህርት ሴክተር በመምረጧ ብዙዎችን ሴት ተቋም መርታ ለምርቃት ታበቃለች ብሎ ማመንና መቀበል አቅቷቸው ነበር። ሆኖም ከጎኗ በነበሩት ከቤተሰብ እስከ አንዳንድ በሀዋሳ ከተማ በነበሩ ጥቂት የኮሌጅ ባለቤቶችና አመራሮች እንዲሁም በማኅበረሰቡ ድጋፍ ነገሩን እንድታልፈው ሆናለች፤ በተለይ የልጆቿን ድጋፍ ሳታስታውስ ማለፍ አትችልም።

### ቀጣይ እቅድ

ዮሐና በቀጣይ ኮሌጁን ከዓለም አቀፋዊ የትምህርት ተቋማት ጋር በጋራ በመሥራት ጥራት ያለው የትምህርትና የምርምር ማዕከል ማድረግ ትፈልጋለች። በተመሳሳይ በሥልጠናውና ማማከሩ ዘርፍ እንደምትገፋበትም ትናገራለች። በቅርቡ ደግሞ በአዲስ አበባ እየከፈተች ባለችው ሴቶችና ወጣቶች ሥልጠናና ማማከር ማዕከል ጠንክራ መሥራት እንደምትሻ ትገልጻለች። ከዲግሪ እስከ ዶክትሬት በውጪ ሀገር ለመማር የሚፈልጉ ሰዎች በማማከር፣ ማገናኘትና ጉዞን ጭምር ማመቻቸት ሥራ በትኩረት እንደምትገፋበት ታስረዳለች። እንዲሁም ከኬጂ እስከ ዩኒቨርስቲ የሚያስተምር የትምህርት ማዕከል የመሥራትም ሕልም አላት። በመጨረሻም ሀገር የተወሰኑ ግለሰቦች ኃላፊነት ብቻ ሳትሆን የሁሉም ዜጋ ድርሻ ናትና አባቶቻችን በደም መስዋዕትነት ያቆሟትን ሀገር እያንዳንዱ ግለሰብ ማስቀጠል አለበት። እኔም በገንዘቤ፣ በእውቀቴ፣ በጉልበቴ ትውልድ ላይ በመሥራት ለልጆቼ የተሻለች ሀገር ለመገንባት የበኩሌን አደርጋለሁ በማለት ቃል ገብታ ሀሳቧን ትቋጫለች።

ልዩ ዕትም

# የትናየት- ተስፋን የሙጥኝ የማለት ምልክት

ዳግማዊት ግርማ

የትናየት ሰለሞን ትባላለች። በመዲናዋ አዲስ አበባ ተወልዳ በጎዳናዎቿ ተመላልሳለች። ባለ ትዳርና የአንድ ልጅ እናት ናት። ታታሪና ፈጣን ከመሆኗም በላይ ጭንቅላቷ አዲስ ነገርን ለመማር አይቦዝንም። ተስፋ መቁረጥ ከእርሷ ጋር ትውውቅ የለውም። በቃ የሚል ነገር በመዝገበ ቃላቷ ውስጥ የሉም። ሁሌም ከዜሮ ለመጀመር ትችላለች። ሌሎችን የማይጎዳ ከሆነ ምንም አይነት ሥራ ከመስራት ወደ ኋላ አትልም። የማታውቀውን ለመጠየቅ አታፍርም። ለተደረገላት ነገር ደግሞ አመስጋኝ ናት።

በልጅነቷ ወላጆቿን አጥታለች። የእናትና አባት ፍቅር የተጠማ ልጅነት አላት። በዚህ ክቡድ የህይወት ጊዜ አንድ ሰው ነበራት። እርሳቸውም አሳዳጊ አያቷ ናቸው። ለቤቷ ብቸኛ ልጅ ናት። ወንድም ወይ እህት የላትም። አያቷ ሁሉንም ሆነው አሳደጓት።

## የልጅነት ህይወት

በልጅነቷ ነገሮች እየተሟሉላት አላደገችም። በርካታ ነገር እየጎደላት አደገች። እሷና ቤተሰቦቿ በዝቅተኛ ገቢ ይተዳደሩ ነበር። በከባድ ሁኔታ ውስጥ ግን የአያቷ ፍቅር ያሻግራት ነበር። በአያቷ ተወዳጅ ናት ። ያልተማሩ አያቷ ከመጽሐፍ ጋር ፍቅር ለመውደቅ አልሰነፉም ነበር። የትናየትም ገና በልጅነት ፊደል እየገጣጠመች ፍቅር እስከ መቃብርን እንድታነብላቸው አድርገዋል። በልጅነት የንባብ ፍቅር እንዲያድርባት ሆናለች።

"ያኔ በጣም ቀዝቃዛና አስቸጋሪ ልጅ ነበርኩ" ትላለች። ጨዋታ አትጠግብም ነበር። በዚህም ያልተቀጣችው የቅጣት አይነት አልነበረም። በትምህርቷ ግን ጎበዝ ነበረች። በልጅነቷ ጋዜጠኛ የመሆን ትልቅ ፍላጎት ነበራት። ከልጅነት ወደ እናትነት ዓለም ተሸጋገረች። መውለድ የህይወቷን አቅጣጫ ቀየረው። ኃላፊነቶች መጡ። ህይወትን ከጥሩ ጎዶቿ ጋር ያስተዋወቋት አያቷ፤ ልጇን በወለደች በአንድ ዓመት በካንሰር ምክንያት አጣቻቸው። ከዛ በኋላ ህይወት አስቸጋሪ ነበር። የተሻለ ገንዘብ ለማግኘት በሚል ወደ አረብ ሀገር ተሰደደች።

እንደ እድል ሆኖ ብዙ ሰቆቃ አልደረሰባትም። መጀመሪያ አካባቢ የስራው ጫናና የልጅ ናፍቆት ተደራርበው ትንሽ ከብደዋት ነበር። ለእርሷ ህይወት ስደት ሌላ መልክ ነበረው። የአረብ ሀገር ኑሮዋ ጥንካሬና ትዕግስትን አደላት። የተለያየ ባህልና እምነት ካላቸው ሰዎች ጋር መኖር ብዙ አስተማራት። ህይወትን ከዜሮ የመጀመርን ጥበብ ታደለች። ብቻ "ብዙ ነገሮችን የተማርኩት በአርብ አገር ቆይታዬ ነው" ትላለች።

አሁን ከልጅነቷ ተቃራኒ ናት፤ ችኩል አይደለችም። ያንን እርጋታ ያመጣችው አረብ ሀገር ነው። ለዓመታት ከቤት ሳትወጣ ትቆያለች። ያም ፈርሶ የመስራት ያህል ፀባይዋ ላይ ለውጥ አመጣ። ወደ ሀገሯ ስትመለስ ለመስራት ትልቅ ጉጉት ነበራት። ያሰበችውን ያክል ግን መጓዝ አልቻለችም። የኑሮ ውድነት ጥረቷን ወደ ኋላ ጎተተባት። የመስሪያ ቦታ ማጣት የእቃ ዋጋ መናር የልቧን እንዳትከውን አገዳት።

የተለያዩ ስራዎችን ሞክራለች። የልብስ መሸጫ ሱቅም ከፍታ ነበር። የሱቅ ኪራይ ዋጋ መወደድ ስራዋን ለመቀጠል አዳገታት። በዚህም ምክንያት ስራዋን አቆመች። ስህተቶቿን መገምገም ጀመረች። ንግድ ስትጀምር ስለ ቦታና ስራው በቂ ጥናት አላደረገችም ነበር። የጀመረችው ስራም የተፈለገውን ያህል ሊዘልቅ አልቻለም። በብር ሲሰላ ኪሳራ በህይወት ልምድ ግን ትልቅ ትምህርት አገኘች።

ንግዷ እንደፈለገችው ባይሄድም ተስፋ መቁረጥ አልጎበኛትም። ከኪሳራው አገገምኩ ስትል ቤታቸው ተዘረፈ። ብዙ የለፋችበትን ነገር አጣች። ዛሬም በልበ ሙሉነት አዲስ ሥራ ለመጀመር በዝግጅት ላይ ናት። በጣም የምትወደውን የጽሑፍ ስራም ላንድ ትልቅ ድርጅት እየሰራች ነው። የሶሻል ሚዲያ ኮንቴንት ክሬተር በመሆን በማገልገል ላይ ናት።

## ማህበራዊ ሚዲያና የትናየት

ማህበራዊ ሚዲያ ለየትናየት በጣም ጠቃሚ መድረክ ነው። ቋሚ ወዳጆችን ያገኘችበት፣ ሥራ ለመሥራት ደንበኛ የምታፈራበትና አሁን ደግሞ ለሥራ መነሻ የሚሆናትን ብር ያገኘችበት ጭምር ነው። በእርሷ እምነት ማህበራዊ ሚዲያ እራስንም ሥራንም ለማስተዋወቅ እጅግ ጠቃሚ ነው። የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀሟ ጤነኛ ነው። በተቻላት መጠን ስለእራሷና ስራዎቿ ለሰዎች ታስተዋውቃለች። ጥሩ አመኔታንም ገንብታለች። ብዙ ሰው አምኖባትም የቢዝነስ ሃሳብ ውድድር ተወዳድራ ገንዘብ አገኘች።

ሰዎች ጋር የሚደርስ ሥራ ላለው ሚዲያው ወሳኝ መሆኑን መስክራለች። በተለያየ መንገድ ስለ ማንነትና ራስ ማስተዋወቅ ግድ ነው ትላለች። ለዚህ ደግሞ ቀላሉ መንገድ ማህበራዊ ሚዲያው መሆኑን ትጠቅሳለች። የትናየት ምንም ጠቃሚ እድል ከመሞከር ወደ ኋላ አትልም። ቢጃይ ናይከር በተባለ መልካም ሰው አማካኝነት ሥራ መጀመሪያ ገንዘብ ማግኘት ችላለች። ከውድድሩ በፊት ጀምሮ ጠቃሚ የሥራ ሃሳቦች የጋራ ስለነበር ትከተለዋለች። ውድድሩን እንዳየች ሳታመነታ ተወዳደረች። በጣም ብዙ ጊዜ በተለያዩ የሥራ ሃሳቦች ተወዳድራ ነበር። በመጨረሻ ግን ተሳካላት። የስራዋን ፍሬ መብላት ቻለች። በእዚህኛው ባይሳካላትም በእርግጥ ከመሞከር አላቆምም ነበር ትላለች።

ውድድሩ ብዙ የሥራ ሃሳቦችን እንድታይ ረድቷታል። ከዚህም ባሻገር ሰዎች እሷን እንዴት ያዩዋታል የሚለውንም አሳይቷታል። በማህበራዊ ሚዲያ ቆይታዋ ጥሩ ስምን እንደገነባችም ተገንዝባበታለች። በጣም ብዙ ሰዎች ጠንካራ ጎበዝ ሠራተኛ ናት ሲሉ መስክረውላታል። ሽልማቱን ብታገኝም ጥሩ ቦታ ታውለዋለች በሚል አምነዋል። ይህን ምስክርነት ማየት በራሱ ከሽልማቱ ያልተናነሰ ደስታ ይሰጣል ትላለች።



የትናየት ሰለሞን

**‹‹እንባ ብቻ ሳይሆን ሳቅም ሁሉም ቋሚ አለመሆናቸውን አውቀን ሁሌም ምንም ቢመጣ የምንቋቋምበት ሰፊ ትከሻ ማዘጋጀትን ህይወት አስተምራኛለች››**

## የቢዝነስ ሃሳቧ

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ 22 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሴቶች የወር አበባ መቀበያ ማግኘት አይችሉም። በሀገሪቷ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ ችግሩን ያከፋዋል። የሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ችግሮችን ተከትሎ የሚከሰተው መፈናቀል የኢኮኖሚ መንገጫገጭ ይህን ችግር እንዲባባስ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

የትናየት ያሸነፈችበት ሃሳብ የሚታጠብ የወር አበባ መቀበያ ማምረት ነው። ይህ ሃሳብ ከአረብ ሀገር እንደመጣች ከዓመት በፊት ልትሰራበት ወስና ነበር። ብዙ መንገድ ከተጓዘች በኋላ በአንዳንድ ነገሮች አለመስተካከል ትታው ነው። ለመነሻ ደህና ካፒታል ስለሚፈልግ ሌሎች ውድድሮች ላይም አላነሳችውም። አሁን ግን የውድድሩ ሽልማት እንዳደገ ስታውቅ ተወዳደረች። በአጋጣሚ የፋሽን ዲዛይና የልብስ ስፌት ስልጠና እየወሰደች መሆኑ ጠቅሟታል። በመሆኑም ያለምንም ማቅማማት ተወዳደረች። በመጨረሻም ማሸነፍ ቻለች።

"በርካታ ታዳጊና ሴት ሕፃናት በንፅህን መጠበቂያ እጥረት ከትምህርት ገበታቸው ይቀራሉ። በቅርቡ እንኳን አንዲት ህሊና የተባለች ልጅ በምትማርበት ዩኒቨርሲቲ ያሉ ሴቶች የወር አበባቸው ሲመጣ የሚተኙበትን ፍራሽ ስፖንጅ እንደሞዴስ እንደሚጠቀሙ አንስታለች። ሴቶቹ ችግር ላይ እንዳሉ በማህበራዊ ሚዲያ ገጿ አጋርታ ከተለያዩ ሰዎች ገንዘብ ተሰባስቦ ለተወሰነ ወራት የሚሆን ገዝተን ልከናል። ይህ ከብዙዎቹ አሳዛኝ ታሪኮች አንዱ ብቻ ነው። ይህም የችግሩን ጥልቀት ያሳያል።" ትላለች። የእርሷ ምርት ሥራ ላይ ሲውል ለብዙ ሴቶች መፍትሔ መሆን የሚችል ስለመሆኑ አንስታለች።

## የትዳርና የፍቅር ህይወት

ጥሩ ትዳር አላትና ደስተኛ ናት። ያ ደሞ ብዙ ነገርን ለማሰብ ጠቅሞኛል ትላለች። ባለቤቷ ለምትሰራቸው ስራዎች ሁሉ ቀደምት አድናቂዋ ነው። ደጋፊና የሚወዳት ባል እንዲሁም ጎበዝ ልጅ አላት። ባለቤቷ ከመሆኑ አስቀድሞ ጓደኛዋ ነበር። በጓደኝነትም በፍቅርም ደጋፊዋ ነው። እንደ ልጅነቷ የብቸኝነት ስሜት የላትም። ቤተሰብ የሚባለውን ህይወት እያየችው ነው።

‹‹ባላገባ እዚህ እደርስ ይሄን አደርግ ነበር ለማለት እቸገራለሁ›› ትላለች። በተቃራኒው ባላገባ በህይወቴ እየገጠመኝ ያለውን ውጣ ውረድ እንዴት አወጣው ነበር? ብላ ታስባለች። ከብዙ ስኬታማ ወንዶች ጀርባ ጠንካራ ሴቶች አሉ። እርሷም ከብዙ ጎበዝ ሴቶች ጀርባ ደግሞ ደጋፊ ባሎች አሉ ባይ ናት። ባለቤቴ እንዲሳካልኝ ብቻ ሳይሆን እንድሳሳትም ይፈቅድልኛል። ብዙ ሙከራዎቼ ሲከሽፉ አብሮኝ ነበር። አትችይውም ይቅርብሽ ሳይሆን ሞክሪና ካልተሳካ ግን እንዳትበሳጪ እንደሚላት ትናገራለች። እድለኛ ሴት ነኝ ስትልም ታክላለች።

## ከህይወት ምን ተማረች

አረብ ሀገር በነበረችበት ጊዜ በጥሩ ሁኔታ የተገነባ በጣም ውድ እቃ የተሟላ ቤት በእሳት አመድ ሲሆን ቆሟ ባይና አይታለች። በህይወት ምንም ነገር ቋሚ አለመሆኑን ተምራለች። ሀብት ውበት ሌላም ነገር አመድ ለመሆን ሰአታት እንኳን አልፈጀበትምና ሁሉም ማለፉን ተገንዝባለች። ብዙ ጊዜ ያልፋል ብለን የምናስበው መጥፎ ጊዜን ብቻ ነው። ነገር ግን ሀዘን ብቻ ሳይሆን ደስታም ያልፋል ትላለች።

‹‹እንባ ብቻ ሳይሆን ሳቅም ሁሉም ቋሚ አለመሆናቸውን አውቀን ሁሌም ምንም ቢመጣ የምንቋቋምበት ሰፊ ትከሻ ማዘጋጀትን ህይወት አስተምራኛለች።›› የምትለዋ የትናየት እማዬ ከምትላቸው አያቷ ሰው የተረፈውን ሳይሆን ያለውን ማካፈል እንዳለበት ተምራለች። የወደፊት እቅዷ የቲ ገበያ የሚባል ትልቅ ብራንድ መፍጠር ነው። አሁን የምትሰራቸውን ትንንሽ ስራዎች አሳድጋ የቲ ገበያ ከሶሻል ሚዲያ መጠሪያነት ወደ አንድ ትልቅ የንግድ ስያሜ እቀይረዋለሁ የሚል ህልም አላት። በንፅህና መጠበቂያው ስራም አሁን ገበያ ላይ ካሉት አምራቾች ተፎካካሪ እሆናለሁ ብዬ አስባለሁ ትላለች። በርግጥ ሽልማቱ ያሰበችውን ሥራ ለመጀመር በቂ አይደለም። ግን ደሞ ህልሟ ግብ እንዲመታ አሁንም ጥረቷን እንደማታቋርጥም ገልፃለች። እርግጠኛ ነኝ ይሳካልኛልም ባይ ናት።

ልዩ ዕትም

# በሀረሪ
## የሴቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ

**ስምስም መንግሥቱ**

ወይዘሮ እመቤት መንግሥቱ ትባላለች። የአራት ልጆች እናት ናት። የልጆችዋ አባት ከጎኗ ባለመኖሩ ያለ ረዳት ነው ብቻዋን የምታሳድገው። ሻይ ቡና፣ ፈጣን ምግብ አዘጋጅታ በማቅረብ በተሰማርችበት አነስተኛ የንግድ ሥራ በምታገኘው ገቢ ነው ራስዋን ጨምሮ አምስት ቤተሰቧን የምታስተዳድረው።

የምትኖረውና የምትሰራበት ቦታ የግለሰብ ቤት ኪራይ በመሆኑ ጫና ፈጥሮባታል። ግን ደግሞ ሌላ አማራጭ የላትም። ሁሉንም ተቋቁማ ልጆችዋን ማሳደግ አለባት። ወደ አነስተኛ ንግድ ሥራ ውስጥ የገባችው ከቤተሰብ በብድር ባገኘችው 10ሺ ብር መነሻ ሲሆን በሥራው ላይ ከአንድ ዓመት በላይ እንደሆናት ትናገራለች።

ወይዘሮ እመቤት እንደምትለው፤ በሥራዋ ትርፍ ከማግኘት ይልቅ ኪሰራው ስለበዛባት ብድሯንም መመለስ አልቻለችም። ንግዷን የማሳደግ ፍላጎት ቢኖራትም በገንዘብ አቅም ማነስ ምክንያት አልተሳካላትም። ይህ ደግሞ ኑሮዋ ከእጅ ወደአፍ እንዲሆን አድርጎታል።

ወይዘሮ እመቤት፤ ያጋጠማትን የገንዘብ አቅም የመፍጠር ችግር ለመፍታት ከመንግሥት ብድር የምታገኝበትን መንገድ ለማመቻቸት፣ እንዲሁም ከሌሎች ጋር በመሆን በማህበር ተደራጅታ ለመሥራት አማራጮችን ለማየት ጥረት አድርጋ እንደሆን ጠይቄያት አንዱንም እንዳልሞከረች ነው የገለጸችው። ምክንያቷ ደግሞ፤ በማህበር ተደራጅተው ብድር ወስደው ወደ ሥራ እንደገቡ የተበደሩትን ለመመለስ ሲጨናነቁ፣ አንዳንዶችም ገንዘቡ ሥራ ላይ ሳይውል ሲባክንባቸው፣ ከመካከላቸውም ገንዘቡን ይዞ የሚጠፋባቸው መኖሩን በወሬ ደረጃ በመስማቷ እርስዋም ይሄ እጣፈንታ ይገጥመኛል በሚል ቀድማ ስጋት ስላደረባት ነው። ሁሉም የማህበሩ አባላት በሥራ ላይ ያላቸው እንቅስቃሴ እኩል አለመሆንም ሌላው ምክንያቷ ነው። በዚህ ስጋት ነው ከዘመድ ገንዘብ ተበድራ ሥራ የጀመረችው።

አንዳንድ ደንበኞችዋ ብድር ብትጠይቅና በማህበርም ተደራጅታ ብትሰራ ተጠቃሚ ልትሆን እንደምትችል ምክር እንደሰጧትም ነግራኛለች። ይሁን እንጂ ገና አልወሰነችም። ገቢዋን ማሳደግ እንዳለባት ግን የኑሮው ሁኔታ እያስገደዳት እንደሆነ ነው የገለጸችው።

እንደ ወይዘሮ እመቤት ትኩስ ነገር ሻይ ቡና፣ የታሸገ ውሃ፣ ብስኩት(ፓስቴ)፣ ፉል፣ የመሳሰሉ ፈጣን ምግቦችን በጎዳና ላይ በማቅረብ አነስተኛ የሥራ መስክ ላይ የተሰማሩ ሴት እህቶች ናቸው በስፋት የተሰማሩት። የተሰማሩበት ሥራ የእለት ጉርስ ለመሸፈን እንደሚያስችላቸው ግልጽ ነው።

ነገር ግን እነዚህ ሴቶች የእለት ኑሮን ከመደገፍ ባለፈ ውጤታማ እንዲሆኑ ምን ድጋፍ እየተደረገላቸው ነው? በገንዘብ አያያዝና ቁጠባ ላይም ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ የሴቶችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመፍታት፣ ብሎም የፖለቲካ ተሳትፎአቸውን ለማጎልበት የተቋቋመው የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ምን እየሰራ ነው? ስንል ለሀረሪ ክልል ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ምክትል ኃላፊ፤ ለሆኑት ወይዘሮ መፍቱህ አሊዩ ጥያቄን አቅርበናል ፤ ቢሮው ትልቅ ተልዕኮ ይዞ እየሰራ ያለው ግንዛቤ መፍጠር ላይ ነው። እየተከናወነ ባለው የግንዛቤ ፈጠራ ሥራም ሴቶች በማህበር ተደራጅተው ቢንቀሳቀሱ ያሉባቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በጋራ፤ መፍታት እንደሚያስችሏቸው ነው በማለት ይመልሳሉ።

በማህበር እንዲደራጁ ማበረታታት ብቻ ሳይሆን፣ ለንግድ ሥራ የሚያስፈልጋቸውን ክህሎትም እንዲያገኙ ነው የሚሰራው የሚሉት ኃላፊዋ ለአብነትም በንግድ አሠራር ውስጥ የገንዘብ አጠቃቀምና አያያዝ፣ በተለይም የቁጠባ ባህልን ማዳበር፣ አዋጭ በሆነ ንግድ ላይ ለመሰማራት ቀድሞ ማቀድ፣ በዚህ ረገድ በማህበራዊ አገልግሎቶች በተከናወኑት ሥራዎች እስካሁን ባለው ተሞክሮም ተጠቃሚ እየሆኑ ያሉት በማህበር ተደራጅተው ክህሎት አግኝተው በተለያየ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ናቸው።

ሌላው የግንዛቤ ማስጨበጫ የትኩረት አቅጣጫ ሴቶች በራስ መተማመንን እንዲያዳብሩ ነው። ሴቷ በምትሰራው ሥራም ሆነ፣ በተለያየ ተሳትፎ ላይ በምታደርገው እንቅስቃሴ በራስ መተማመን እንድትፈጽም ማስቻል ነው።

> “ግንዛቤ የመፍጠሩ ሥራ በማኅበረሰብ ውስጥ ሰርጾ ሁሉም በያገባኛል ስሜት እንዲንቀሳቀስ፤ በቢሮው በኩል እየተከናወነ ያለው ሥራ ጥሩ ጅምር ሲሆን በተያዘው 2016 በጀት ዓመት ሰፊ የንቅናቄ ሥራ ነው የተሠራው::”

ሴቶች ለአካላዊ፣ ለሥነልቦና እና ለጾታዊ ጥቃት ተጋላጭ እንዳይሆኑም ቢሮው ሰፊ የግንዛቤ ሥራ እየሠራ ይገኛል። በዚህ በኩል ግንዛቤ ከሚፈጠርባቸውና ተደራሽ ከሆኑት ትምህርት ቤቶች ይገኙባቸዋል። ሴት ተማሪዎች በሚደርስባቸው የተለያየ ጥቃት ከትምህርት ገበታቸው እንዳይስተጓጎሉ አስቀድሞ ለመከላከል ያስችላል። በተጨማሪም በክልሉ በሚገኙ ዘጠኝ ወረዳዎችም በተመሳሳይ እየተሠራ ይገኛል። በወረዳዎች ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ አባላት የተካተቱበት የጥቃት ተከላካይ ኮሚቴ ተዋቅሮ ነው የግንዛቤ መፍጠሩ ሥራ ተጠናክሮ እየተሰራ ያለው። የኤፍኤም ጣቢያዎችን በመጠቀምም ግንዘቤን የማዳበሩ ሥራ በተጨማሪ እየተሰራ ነው። በተለያዩ አመራጮች ግንዛቤ የመፍጠሩ ሥራ መከናወኑ በከተማና በገጠር የሚኖረውም እኩል የሆነ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ ያስችላል።

እንደ ወይዘሮ መፍቱህ ማብራሪያ ግንዛቤ መፍጠሩ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈለገው፤ ሴቶች በተለያየ መንገድ የሚያጋጥሟቸውን ማህበራዊ ችግሮች መፍታት የሚቻለው ሁሉም የኅብረሰተብ ክፍል ተሳትፎ ሲያደርግ ነው። ስለሴቶችም ሆነ የሕፃናትን ጉዳይ ሁሉም ኃላፊነት ወስዶ ሲንቀሳቀስ ነው። አንድ ቢሮ ብቻውን እንዲሰራ ማድረግ የትም አያደርስም።

ግንዛቤ የመፍጠሩ ሥራ በማኅበረሰብ ውስጥ ሰርጾ ሁሉም በያገባኛል ስሜት እንዲንቀሳቀስ፤ በቢሮው በኩል እየተከናወነ ያለው ሥራ ጥሩ ጅምር ሲሆን በተያዘው 2016 በጀት ዓመት ሰፊ የንቅናቄ ሥራ ነው የተሠራው። ለአብነትም የ16ቱ የፀረ ጾታ የጥቃት ቀንን በመጠቀም ተጽእኖ ፈጣሪ የሆኑ ሴቶችን በማሳተፍ በስፋት ተንቀሳቅሰናል።

ሴቶች በኢኮኖሚ ተሸለው አለመገኘታቸውም ለተለያየ ችግር እንዲዳረጉ እንደሚያደርጋቸው የጠቀሱት ወይዘሮ መፍቱህ፤ የኢኮኖሚ አቅም ፈጥረው በራስ ለመቆም እንዲችሉም በቢሮው በኩል ጥረት እየተደረገ መሆኑን ነው የገለጹት። ‹‹በኢኮኖሚ ያደገች ሴት ለቤተሰቧም ትተርፋለች። አንዲት በኢኮኖሚ አቅም የፈጠረች ሴት ደግሞ ለአካባቢዋም ምሳሌ ሆና ታገለግላለች። እርሷን እያዩ ለማደግ የሚጥሩ ሴቶች ይፈጠራሉ። በዚህ መልኩ ነው ሥራ መሠራት ያለበት›› ብለዋል።

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በአካባቢያቸው ቀለብ(መሸሩፍ) አጥተው ለችግር የሚዳረጉ ሴቶች መኖራቸውንና አንዳንዶችም ለልጆቻቸው ምግብ ለማቅረብ፣ የትምህርት ቤት ቁሳቁስ ለማሟላት ሲቸገሩ ለቢሮአቸው ጥያቄ እንደሚያቀርቡ ወይዘሮ መፍቱህ ይናገራሉ።

እንዲህ ያሉ ችግሮችን ለመፍታትና በአጠቃላይ



ፎቶ - ዳኜ አበራ

**ወይዘሮ መፍቱህ አሲዩ**

ሴቶች የኢኮኖሚ አቅም ፈጥረው እራሳቸውን መርዳት እንዲችሉ፤ የሥራ እድል እና ብድር የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻችላቸው፣ ስለሚሰሩት ሥራ፣ ወጪ ገቢያቸውን እንዲያውቁ፣ እየሠሩ የተበደሩትን ገንዘብ እንዴት መመለስ እንደሚችሉ፣ አጭር ሥልጠና በመስጠት ሥራ እንዲፈጥሩ እንደሚደረግ ወይዘሮ መፍቱህ አስረድተዋል።

እንደ ወይዘሮ መፍቱህ ገለጻ፤ የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ቢሮው የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ብድር ማግኘት እንዲችሉ፣ ድጋፍም እንዲያገኙ ቢያደርግም ከዚህም በኋላ ብዙ መሥራት የሚጠበቅበት ነው ፤ ነገር ግን ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎችም ብዙዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል።

በአጠቃላይ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ የሴቶችን ሁለተናዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ሰላምና መረጋጋት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ የሚናገሩት ወይዘሮ መፍቱህ፤ ሴቶችም ሰላምን ለማስፈን ድርሻቸውን እንዲወጡ በቢሮው በኩል እየተሰራ ነው።

‹‹አሁን ላይ አንጻራዊ ሰላም በሀገራችን እየተፈጠረ ቢሆንም ከጥቂት ዓመታት በፊት ግን የነበሩት አለመረጋጋቶች፣ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የተካሄደው ጦርነት ከፍተኛ ቀውስን አስከትሏል። በዚህም በከፍተኛ ሁኔታ የተጎዱት ሴቶችና ሕፃናት ናቸው። በመሆኑም ሰላም ለነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ወሳኝ ነው። ሴቶች ከአካባቢያቸው ጀምሮ በሀገር ላይ ሰላም እንዲስፍን በማድረግ ሚናቸው ከፍ ያለ በመሆኑ በዚህ ላይ ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የማድረግ ሥራ ተሰርቷል›› ሲሉም አስረድተዋል።

ወይዘሮ መፍቱህ እንዳሉት፤ ሰላም የማስፈኑ ሥራ የክልሉ ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ከክልሉ ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ጋር በጋራ በመሆን ነው የሚሰራው በዚህ የሰላም ማስፍን ላይ ሚና እንዲኖራቸው የተደረገው የሰላም አምባሳደሮች ምርጫ ተካሂዷል። ተሳትፎአቸውም አካባቢያቸውን ከመጠበቅ ይጀምራል። የአካባቢያቸው ሰው ያለስጋት በሰላም ወጥቶ እንዲገባ ፀረ ሰላም የሆኑ ኃይሎች በአካባቢው ላይ እንዳይኖር የጥበቃ ሥራ ይሰራሉ። በተጨማሪም በአካባቢያቸው ላይ ፀበኞች ካሉና በተለያየ ምክንያት ችግር ተፈጥሮም ከሆነ የተመረጡት የሰላም አምባሳደሮች በሽምግልና በማስታረቅ ሰላም እንዲፈጠር ያደርጋሉ።

በተለያየ ጉዳይ የሕግ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሴቶችንም የክልሉ ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ በማገዝ ከጎናቸው ይቆማል ያሉት ወይዘሮ መፍቱህ፤ ችግራቸው በውል ተለይቶ አቅጣጫ በመጠቆም መፍትሔ እንደሚሰጥ ነው የገለጹት። እርሳቸው እንዳሉት የፍትህ ጥያቄ ብዙ ሂደቶችን የሚጠይቅ በመሆኑ፤ በአጭር ጊዜ መልስ ለመስጠት ያስቸግራል። በዚህ በኩል ለጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት በሚፈጠር መዘግየት ቅሬታ ሊፈጠር ይችላል።

እንዲህ ያለውን ችግር ወይንም ክፍተት ለማስቀረት የተሻለ የሚሆነው ችግሮች ከምንጩ የሚቀሩበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሆነና ቢሮውም ይህን እንደ አማራጭ እየሰራበት እንደሚገኝ ወይዘሮ መፍቱህ ይናገራሉ። ቢሮው ከፍትህ ጋር ለተያያዙት ጉዳዮች የሕግ ክፍል እንዳለውና በክፍሉ እየሠሩ ያሉ ባለሙያዎችም ተገቢውን እገዛ እያደረጉ እንደሆነ ነው ያስረዱት።

እንደ ወይዘሮ መፍቱህ ገለጻ፤ ከፍትህ ጋር በተያያዘ ከሚነሱት መካከል የቀለብ መቁረጥ ጉዳይ አንዱ ነው። ችግሩ ከፍች ጋር የሚያያዝ በመሆኑ፣ ቤተሰብ እንዳይበተን፣ ልጆችም በሁለቱም ወላጆቻቸው እንዲያድጉ፣ በሚፈጠረው ፍችም አንዱ ወገን ተጎጂ መሆኑ ስለማይቀር በተቻለ መጠንም በስምምነት እንዲያልቅ በሕግ ክፍሉ በኩል ተገቢው ምክር ይሰጣል።

ከቢሮው አቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ ግን እንደ አስፈላጊነቱ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይላካል። ጉዳያቸው ወደነዚህ ተቋማት ሲላክም የቢሮው እገዛ አይለያቸውም። የገንዘብ እና የተለያየ አቅም ማነስ ሊኖራቸው ስለሚችል ጉዳያቸውን ለመከታተል እንዲችሉ የተለያየ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

የተለያየ ችግር ሲያጋጥማቸው የት መሄድ እንዳለባቸው እንኳን የማያውቁ ሴቶች መኖራቸውን የጠቀሱት ወይዘሮ መፍቱህ፤ በዚህ በኩል ቢሮው ብዙዎችን ማገዝ ችሏል ብለዋል። የቢሮው መኖር አስፈላጊ እንደሆነ እየሰጠ ካለው አገልግሎት መገንዘብ መቻሉንም አመልክተዋል። ሴቶቹ አገልግሎት ማግኘታቸው ብቻ ሳይሆን፤ በእነርሱ ላይ ጥቃት ወይንም ጉዳት ለማድረስ የሚነሳሳ እንኳን ቢኖር ጉዳያቸውን የሚከታተልላቸው ተቋም መኖሩን በመገንዘብ ከድርጊቱ ሊቆጠብ እንደሚችል ነው ያስረዱት።

ቢሮው ሴቶች ከሚያጋጥሟቸው የተለያዩ ችግሮች፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክፍተቶች አንጻር ምን ያህሉን ማቅለል ችሏል? ወይንም ሥራውን በስኬት ያየዋል? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ወይዘሮ መፍቱህ በሰጡት ምላሽ፤ ብዙ ሥራዎች እንደሚቀሩና የተሻለ ሥራን ለመሥራት አቅም በፈቀደ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ነው የሚናገሩት።

በ2016 በጀት ዓመት በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በተከናወኑ ሥራዎች ለቢሮው ከሚበጀተው በጀት በተጨማሪ አጋሮችን በማፈላለግ በተሰራ ሥራ ለ1ሺ 5መቶ ሴቶች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል። 27 ሴቶች ደግሞ ለሥራ መነሻ የሚሆን ወደ 55ሺ ብር ብድር እንዲያገኙ ተደርጎ ወደ ሥራ ገብተዋል። በተጨማሪም ለሴቶችና ወጣቶች የሥራ እድል ለመፍጠር ከሚሰሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመሆንም ሴቶች ምን ያህል የሥራ እድል እየተፈጠረላቸው እንደሆነ እየሠራን እንገኛለን።

ግርዛት፣ ያለእድሜ ጋብቻ ወዘተ በሴቶች ላይ ከሚፈጸም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ጥቂቶቹ ናቸው። በዚህ ረገድ የተሠሩ ሥራዎችን በተመለከተም ወይዘሮ መፍቱህ እንደገለጹት፤ በአካባቢው ላይ ከሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አንዱ ያለእድሜ ጋብቻ ነው። በዚህ ምክንያት ሴት ልጆች ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ይገደዳሉ። በተጨማሪም ለኢኮኖሚያዊ ጫና ይዳረጋሉ ልጆች ወልደውም ይቸገራሉ።

ሌላው ጠለፋ ነው። አሁን ላይ እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም እንደ አንድ ተግዳሮት ይወሰዳል። ግርዛትም በገጠሩ ሙሉ ለሙሉ አልጠፋም። ሃይማኖትን መሠረት አድርጎ ተደራራቢ ጋብቻም ይፈጸማል። በአጠቃላይ ሴቶችን ተጎጂ የሚያደርጉትን ሁሉ ለመከላከል የሰዎችን ግንዛቤ በማሳደግ ነው። በዚህ ላይ እየሰራን ነው። ወይዘሮ መፍቱህ ቢሮው በሚችለው ሁሉ እየሠራ ያለውን በዚህ መልኩ የገለጹ ቢሆንም ሴቶችን ተጠቃሚ የማድረጉ ሥራ ከዚህም በላይ ተጠናክሮ መከናወን ይኖርበታል።

# ‹‹ልምድና ትምህርት ለመቅሰም ቅድሚያ መስጠት አለብን››

- ወጣት ዲቦራ ኤርሚያስ

**ሰላማዊት ውቤ**

ዲቦራ ኤርሚያስ የ21 ዓመት ወጣት ስትሆን፤ እርሷን ጨምሮ ሁለት ሴት ልጆች ላላቸው ወላጆቿ የበኩር ልጅ ነች። ተወልዳ ያደገችው ብዙ ዕድል ይገኝባታል ብላ በምታምንባት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው። አዲስ አበባ ውስጥ የትምህርት፣ የሥራ፣ ራስን የማብቃት እና የማሳደግ፣ ከጥቃት የመጠበቅ፣ በተሻለ ሁኔታ የመኖር እና ሌሎች ብዙ ዕድሎች አሉ ብላ እንደምታምን ትናገራለች። እነዚህ ዕድሎች መኖራቸው ትንንሽ ከተሞችና በገጠራቱ የኢትዮጵያ አካባቢ ላሉ ሴቶች ተስፋ መሆናቸውን ትገልፃለች።

ዲቦራ በዕድሉ በመጠቀሟ ገና በጠዋቱ ዕድሜዋ ብዙ ኃላፊነቶችን መውሰድ፤ በርካታ ተግባራትን በተመሳሳይ ጊዜ መፈፀም ችላለች። ዕድሎችን ፈጥና ትጠቀማለች። በቅርቡ አዲስ አበባ ከተማ ላይ የተዘጋጀውን ቀጣናዊ ትስስር ለዘላቂ ልማት መድረክ እንድትመራና እንድታስተባብር በስልክ ሲነገራት፤ መዘጋጃ ጊዜ የለኝም ብላ አልገፋችም። ፈጥና ፈቃዷን አሳየች። ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተለመደውን ባሕል በመስበር የተማሪ ተቀጣሪ ሆና የደሞዝ ተከፋይ መሆን የቻለች ጀግና ነች።

ነገር ግን ገንዘብ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ ብዙ ነገሮችን ገና ከማለዳው ሊያበላሽ ስለሚችል፤ ልምድና ትምህርት ለመቅሰም ቅድሚያ መስጠት አዋጭ ነው ባይ ናት። ከዚህ አኳያ አብዛኛውን ጊዜዋን የምታሳልፈው ይሄንኑ በምታገኝበት የበጎ ፈቃድ ሥራ ላይ ነው። ሥራውን የምታከናውነውም ትልልቅ የኃላፊነት ቦታዎችን ወስዳ ነው። ለአብነት በእንደራሴ ወጣቶች ማኅበር ውስጥ የፕላንና ፕሮጀክት ዳይሬክተር ሆና እያገለገለች የምትገኘው ዲቦራ፤ እርሷን ያገኘንበትን ቀጣናዊ ትስስር ለዘላቂ ልማት የተሰኘውን ጨምሮ ትልልቅ ዓለም አቀፍ መድረኮችን በማስተባበርና በማስተዋወቅ ልምድ አካብታለች።

ለብዙ ወጣት ሴቶች አርዓያና ተስፋም ሆናለች። ዲቦራ በማናቸውም በአዲስ አበባ ከተማ በሚካሄዱ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች መድረክ አትታጣም። ቢበዛ መድረኮቹን ስታስተባብርና ስትመራ ቢያንስ በመጋበዝ ስትሳተፍ ትታያለች። በእነዚህ መድረኮች የሚያስፈልገው የቋንቋ ተግባቦት ክህሎትም እሷ ጋር አለ። እታች ከአፀደ ሕፃናት ጀምሮ ኤቢሲዲ እያልን የመጣንበት ነው በምትለው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከዓለም ሀገራት ከተውጣጡት የመድረኩ ታዳሚዎች ሁሉ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ያህል ስታወጋ ታፈዛለች። እየተማርኩት ነው በምትለው ፈረንሳይኛ ቋንቋም ጥሩ ተግባቦት አላት። ኢትዮጵያ ውስጥ ተግባቦቷን ለማስፋትም የሀገር ውስጥ ቋንቋዎችን እየተማረች ትገኛለች።

ዲቦራ አሁን ላይ በኒው ጀነሬሽን ዩኒቨርሲቲ የሦስተኛ ዓመት የዓለም አቀፍ ግንኙነት ተማሪ ነች። ጎን ለጎንም በገሊላ ኢንተርናሽናል ሴሚናሪ ክርስቲያን የራስን ሀሳብና ዓላማ በመለየት ትኩረት በማድረግ የሚያጠነጥን ሶሻል ወርክ የሁለተኛ ዓመት ትምህርቷን እየተከታተለች ትገኛለች። በኢትዮጵያ አንድ ወጣት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሆኖ ተቀጥሮ የሚሠራበት ባሕል ባይጎለብትም እርሷ ከትምህርቷ በሚተርፋት ጊዜም ተቀጥራ ትሠራለች። ይሄ ተቀጥራ የምትሠራበት ቦታ ኤዲት ኤዱኬሽን ሰርቪስ ሲሰኝ ከስድስት እስከ 12 ዓመት ላሉ ታዳጊዎች ክህሎታቸውን የሚያሳድጉበት ሥልጠናዎችን በጨዋታ መልክ ትሰጣለች። በዚህ ቦታ ላይም ዲቦራ እንደተለመደው ትልቅ ኃላፊነትን በመውሰድ ረዳት አስተዳዳሪ ሆና እየሠራች ነው።

ገና በ21 ዓመት ለጋ ዕድሜዋ እነዚህን ሁሉ ትልልቅ ኃላፊነቶችን የሰነቁ ተግባራትን ማከናወን የቻለችው ለራሷ ወሰን የምትለውን ገደብ ባለማስቀመጧ እንደሆነ ትናገራለች። አቋም ያላት በመሆኑ በተቃራኒ ጾታ ግፊትም ሆነ በአቻ ተፅዕኖ ጉዞዋ ተሰናክሎ አልቆመም። በዚህ በኩል በወላጅና በትምህርት ቤት የተቃኘው አስተዳደጓ አስተዋፅዖ እንዳደረገላትም አጫውታናለች።

‹‹አስተዳደጋችን አቋም ለመያዝ እና ውጤታማ ለመሆን አስፈላጊና ወሳኝ ነው›› ብላናለች። ዲቦራን ያናገርናት በዓለም የሴቶች ቀን መባቻ እንደመሆኑ በዓሉ አዲስ አበባ ከሚገኙ ትላልቅ ሆቴሎች ወጥቶ በገጠራቱ ኢትዮጵያ ቢያንስ በአዲስ አበባ ዙሪያ ባሉ ከተሞች የሚከበርበት ሁኔታ ቢለመድ ለእንስቶች ሕይወት የተሻለ ለውጥ እንደሚያመጣም ትናገራለች።

‹‹እኔ ሁለቱንም ቋንቋ አውቅ ነበር። በተለይ እንግሊዝኛ ኤ፤ቢ፤ሲ፤ዲ እያልን ቆጥረን ለረጅም ጊዜ እየተማርን ያደግንበት፤ ረጅም ጊዜ የተማርነውና በሥራችንና በትምህርታችን ላይ የምንጠቀመው በመሆኑ መናገሩ የአፍ መፍቻዬ ያህል አልከበደኝም። ፈረንሳይኛም እየተማርኩት ያለ ቢሆንም አልታማበትም››



ፎቶ - ዳኜ አበራ

ይሄን ያህል ስለ ወጣቷ ካስተዋወቅናችሁ ሰፋ ለማድረግ ስናነጋግራት ወደ አጫወተችን ወግ እንውሰዳችሁና አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተወለደችው ዲቦራ የተወለደችበት አካባቢ ሳሪስ ነው። አራት ዓመት ሲሆናት ወላጆቿ መኖሪያቸውን ወደ ጎሮ በማዛወራቸው እስከ አስራ አራት ዓመቷ ለተማረችበት አቤኔዘር የአፀደ ሕፃናት ትምህርት ቤት በአዕምሮዋ ያስቀረችው ትዝታ የላትም። የታዳጊነትና የወጣትነት ሕይወቷ ከአሁኑ መኖሪያዋ ጎሮ አካባቢ ጋር ይሰናሰላል። ጎሮ ፒስ ስኩል ቅድመ መደበኛ ትምህርቷን ተምራ ከአንደኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያለውን ትምህርቷን ያጠናቀቀችው በአካባቢው በሚገኝ በቪዥን አካዳሚ ነው።

እዚህ ለሴቱም ለወንዱም ተማሪ መርዳትና ማገዝ የሚፈልጉ መምህራኖች አግኝታለች። ትምህርት ቤቱ ትምህርት በትክክል የሚሰጥበትና በሥነ ሥርዓት የሚታወቅ መሆኑም ረድቷታል። የሚናገሩበትን፤ ራሳቸውን የሚገልፁበትን ዕድሎች የሚሰጧቸው መሆኑም ለኋላ ሕይወቷ ጠቅሟታል። በትምህርት ቤቱ ሚኒ ሚዲያ ስታዘጋጅ ያደገች በመሆኗ ጋዜጠኛ ትሆናለችም እየተባለች ቆይታለች። እነዚህ ዕድሎች በተገቢው መንገድ ማውራትና ራሷን መግለጽ እንድትችል አግዟታል። ቤተሰቦቿ ከጣሉላት መሠረት ጋር ተዳምሮም የራሴ የምትለው አቋም እንድትገነባ በማድረጉ ረገድ አበርክቶው የጎላ ነበር።

ይሄ ለራስ ወሰን ማበጀት የምትለው አቋሟ ወደ ዩኒቨርስቲ ከገባች በኋላም ቢሆን በይሉኝታና ችግር ላይ እንዳትወድቅ አግዟታል። በተለይ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ሆና ጊቢ ውስጥ የምትቆየው ለትምህርት ብቻ ነበር። ከትምህርት በኋላ መድረኮችን ወደምትመራባቸው፤ ስዕል ወደምትስልባቸውና ሙዚቃ ወደ ምትጫወትባቸው ቦታዎች ትሄዳለች፤ አብዛኛውን ጊዜዋንም ከቤተሰቦቿ ጋር ታሳልፍ ስለነበር የደረሰባት ችግር አልነበረም። ግንኙነቷ ውሱን መሆኑና ለግንኙነቷ ገደብ ማስቀመጧ በዩኒቨርስቲ ቆይታዋ በተለይም በአዲስ ተማሪነት ወቅቷ ሊደርሱባት ከሚችሉ አላስፈላጊ ተግባራት የጠበቃት እንደሆነ በማስታወስ ሌሎች ታዳጊዎች በተለይም ለእያንዳንዱ ጉዳይ ይሄንኑ የእርሷ ዓይነት የግንኙነት ገደብ በማስቀመጥ ወይም አቋም በመያዝ ራሳቸውን እንዲጠብቁም ትመክራለች። በተለይ ችግር የለም ተብለው በይሉኝታም ሆነ በሌላ የሚገባባቸው ነገሮች ብዙ ጥፋቶች ይዘው እንደሚመጡና ሴቶች በተፈጥሮ ሊጎዱ ለሚችሉ ነገሮች ተጋላጭ በመሆናቸው እራሳችንን የምንሆንበትን ልክ ለራሳችን ማስቀመጥ ይገባል ትላለች።

ወደ መጀመሪያ ትምህርት ተማሪነቷ ወቅት እንመለስና ዲቦራ ስለ ወር አበባ ጉዳይ ያወቀችበትን ጊዜ ታስታውሳለች። ይሄንንም ስታብራራ ትምህርት ቤታቸው ለብቻ ሴቶችን ሰብስቦ ስለ ወር አበባና በእድገት ሂደት ውስጥ ስለሚታዩ የባሕሪ ለውጦች ያስተማረበት ሁኔታ ነበር ትላለች። በትምህርት ቤታቸው ይሄ ግንዛቤ እንዲኖር መደረጉ በጣም ትልቅ ነገር ነው የምትለው ዲቦራ፤ ያኔ የ11 ዓመት ታዳጊና የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ነበረች። ተማሪዋ ስለ ወር አበባና ከተቃራኒ ጾታ ጋር የሚኖር ግንኙነት ቤተሰብ ካልነገራት ወይም በምንም ሁኔታ የማታውቅ ሴት ከሆነች ልትደነግጥ ታምሜ ነው ብላ ልትጨነቅ ስለምትችል በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትምህርት ቤቶች ትልቅ ሚና መጫወት እንዳለባቸው ትናገራለች።

በዚህ ላይ ትምህርት ቤት ከማስተማር ባለፈ አንዳንዴ በቤተሰብና በልጆች መካከል የሚኖር ክፍተት እንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ ለልጆች ላይነገር ስለሚችል ክፍተቱን ይሸፍናል ትላለች። ዲቦራ ታዳጊ ሴቶች አብዛኛውን ጊዜያቸውን በቀን ውስጥ ስምንት ሰዓት ያህሉን ትምህርት ቤት ውስጥ በሚያሳልፉበት ሁኔታ፤ አሁን ላይ ምን ያህል ትምህርት ቤቶች ለሴት ታዳጊ ተማሪዎቻቸው ይሄንን እያደረጉ እንዳሉም ትጠይቃለች። ትምህርት ቤቶች ላይ ታዳጊ ሴቶችን ለብቻ ሰብስቦ በጉዳዩ ላይ ማስተማርና ማሠልጠን ቢኖር ብዙ ክፍተቶችን ሊሞላ እንደሚችልም ትመክራለች። እርሷ በዚህ በኩል ትምህርት ቤቷ ላደረገላትም ታመሰግናለች።

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለች ትምህርት በክብደቱ በብርቱ ፈትኗት እንደነበር ትናገራለች። ይሄኔ የደረጃ ተማሪ አልነበረችም። በውጤቷ የምታዘቀዝቅባቸውም የምትነሳባቸውም ጊዜያት ነበሩ። እነዚህ ጊዜያት ብዙ ትምህርት አስተምረዋት አልፈዋል። ከዚህ ተነስታም የደረጃ ተማሪ አይደለሁም ማለት ሕይወት ላይ ውጤታማ አልሆንም ማለት አይደለም ትላለች። ሕይወት ትምህርት የሚያስፈልገው ለብቻው የሚሠራበት ጉዳይ እንደሆነም ትናገራለች። በቆይታዬ የምጠላው ትምህርት አልነበረም። በጣም የሚከብደኝ ትምህርት ሂሳብ ቢሆንም እጠላዋለሁ አልልም። እጠላለሁ ካልኩ ራሴን አሳምኜ ልወድቅ ነውና፤

ወደ ገጽ 19 ዞሯል

# ‹‹ልምድና ትምህርት ለመቅሰም ...

ከገጽ 18 የዞረ

ሂሳብን እወደው ነበር ማለት አልችልም ትላለች። ያደኩት ግን ሁሉንም እወዳቸዋለሁ፤ አጠናቸዋለሁና ጥሩ ውጤት አመጣባቸዋለሁ እያልኩ ነው ትላለች።

ዲቦራ ባዮሎጂና ኬሚስትሪ ትምህርቶችን ብትወድም፤ 11ኛ ክፍል ላይ ምረጡ ሲባል የተፈጥሮ ሳይንስ ብትመርጥም ወደ ዩኒቨርሲቲ ስትገባ መጨረሻዋ የሶሻል ተማሪ ሆኗል። ምንም እንኳን የሚታወቀው ስትመረቅ ቢሆንም ለሦስት ተከታታይ ዓመታት እያስመዘገበች ባለችው የላቀ አፈፃፀም ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገቧ ተመራቂነቷ ለመረጋገጡ ጫፍ ላይ ደርሳለች።

ያኔ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆና የደረጃ ተማሪ ሆና ሳይሆን ስዕልና ሙዚቃ ውድድሮችን በማሸነፍ፤ የሚኒ ሚዲያና የተለያዩ ሌሎች መርሐ ግብሮችን በማዘጋጀትና በማቅረብ በተደጋጋሚ ትሸለም ነበር። ያ በልጅነቷ ታከናውን በነበረው ተግባር ዛሬ ዓለም አቀፍ መድረኮችን መምራትና ማስተባበር ላይ ደርሳለች። ከ200 በላይ የምስክር ወረቀቶችም ያሏት ሲሆን፤ ከትምህርቱ ጎን ለጎን ስዕል የመሳል፤ በተለያዩ የስዕል ውድድሮች ከመሳተፍ በተጨማሪ ሙዚቃ መጫወት ጀምራለች። በሚኒ ሚዲያም የተለያዩ መርሐ ግብሮችን ታዘጋጅ ነበር። ከጠዋት እስከ ማታ ከሚሰጠውና ፋታ ከሌለው አጨናናቂ ትምህርት ይልቅ፤ ስዕል መሳልና ሙዚቃ መጫወት ይስባት እንደነበረም ታስታውሳለች።

ዲቦራ ልክ ዩኒቨርስቲ ስትገባ ትምህርት አሰጣጡ ላይ የነበረው ጫና ቀለል ስላለላት ወደ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ችላለች። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ባላት ልምድ ታግዛ የበለጠ ራሷን መግለጽ፤ በራስ መተማመኗን አጠናከረች። እንደውም ጎን ለጎን ሌሎች ትምህርቶችን መማር፤ ተቀጥራ የምትሠራበትን ጨምሮ በርካታ ሥራዎችን ለማከናወንም በቅታለች። የተዋጣላት ዓለም ዓቀፍ መድረክ አስተዋዋቂና አስተባባሪም ለመሆን የቻለችው ዲቦራ፤ በዚህ በኩል ከተማረችባቸው ትምህርት ቤቶች ባሻገር የአሁኑ ዘመን ቤተሰብ አይመስሉም የምትላቸው ወላጆቿ ትልቅ ሚና መጫወታቸውን ትገልፃለች።

‹‹የአሁን ዘመን ወላጅ በአብዛኛው ልጆቹ የቀለም ትምህርት ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ እንጂ ሌላ ነገር እንዲሠሩ አይፈልግም፤ የውስጥ ስሜታቸውን አያዳምጥም። የእኔ ወላጆች ግን ስዕል ልሳል ስላቸው ብዙ ነገር ተመቻችቶላቸው ባይሆንም የስዕል ደብተር፤ እርሳስ ከለር ያቀርቡልኛል። ሙዚቃ ልጫወት ስላቸውም እንዲሁ ጊታር፤ በገና፤ መሰንቆና ሌሎች መሣሪያዎችን ሳይቀር ይገዙልኛል። እንደ አባትና እናት በመካከላችን ክፍተት ሳይኖር ጉዳዮችን እያነሳሁ ከእነርሱ ጋር እንድወያይም ሰፊ ዕድል ሰጥተውኛል። እኔና ታናሽ እህቴ ከወላጆቻችን ጋር የምናደርገው ውይይት ውጭ ስንወጣ እንዳንሸማቀቅና በራስ መተማመን እንዲኖረን አድርጎናል። ከቤተሰብ ጋር ያሳለፍነው ጊዜ ብቻ ለዛሬ ማንነታችን ትልቅ አበርክቶ አለው›› ትላለች።

በኢትዮጵያ አንድ ወጣት የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሆኖ ተቀጥሮ የሚሠራበት ልምድ ባይጎለብትም እርሷ ከትምህርት ጎን ተከፋይ ሆና ትሠራለች። ይሄ ተቀጥራ የምትሠራበት ቦታ ኤዲት ኤዱኬሽን ሰርቪስ ሲሰኝ ከስድስት እስከ 12 ዓመት ላሉ ታዳጊዎች ክህሎታቸውን የሚያሳድጉበት ሥልጠናዎችን በጨዋታ መልክ ትሰጣለች። ወጣቷ በዚህ ቦታ ላይ ረዳት አስተዳዳሪም ሆና እየሠራች ትገኛለች።

ዲቦራ ከ1 ሺ በላይ አባላትና 13 የአስተዳደር ኮሚቴ ባለው በእንደራሴ ወጣቶች ማኅበርም አባል ነች። ማኅበሩ ከተመሠረተ ሁለተኛ ዓመቱ ቢሆንም እርሷ የተቀላቀለችው በተያዘው ዓመት መስከረም ወር ውስጥ ነው። እንድትቀላቀል ያደረጋት አብሯት የሚማረውና በተደጋጋሚ እርሷ በምትሳተፍባቸውና በምታስተባብራቸው ዓለም አቀፍ መድረኮች ታገኘው የነበረው የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ብሩክ አስቻለው ነው። ዲቦራ ከብሩክ ጋር አብራ መማሯንም ታስታውሳለች። በመድረኮቹ መገናኘታቸው ሲጨመር አብረው ቢሠሩ ብዙ ወጣቶችን ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚችሉ ተወያዩና ወደ ማኅበሩ ተቀላቀለች። እዚህም ወጣቱን ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ከማዘጋጀት ጀምሮ በጋራ እንዲገመገም፤ ውይይት እንዲደረግበት፤ በውይይት እንዲዳብር ከማድረግ ጀምሮ በርካታ ተግባራትን ታከናውናለች።

ዲቦራ አሁን እዛም እዚህም በዝታለች። በማኅበሩ ውስጥ እንደተለመደው ትልቁንና ለእርሷ ብቃት



**ዓለም የሴቶች ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበር ሲሆን የተነሳበት ዓላማም አለው። ከዓላማው ሴቶችን ከጥቃት መጠበቅና ለሴቶች ዕድል መስጠት በዋንኛነት ይጠቀሳሉ። በዓለማችን እኛ እንድንማር፤ ከወንድ እኩል የተሻለ ደሞዝ ተከፋይ እንድንሆንና በተሻለ ሁኔታ እንድንኖር፤ ዕድሎች እንድናገኝ ብዙ ሴቶች ዋጋ ከፍለዋል።**

የሚመጥነውን ኃላፊነት በመውሰድ የፕላንና ፕሮጀክት ዳይሬክተር ሆና እየሠራች ትገኛለች። የሚሠሩት እንደ ሀገር አቀፍ ባሉ ወጣቶች ላይ ሲሆን ወጣቶች የተለያዩ የሥልጠና፤ የሥራና ሌሎች ዕድሎችን እንዲያገኙና በማኅበሩ በኩል ድምፃቸውን እንዲያሰሙ ማድረግን ያማከለ ስለመሆኑ አጫውታናለች። በተለይ ወጣቶቹ በበጎ ፈቃደኝነት ነፃ አገልግሎት ማድረግ ሲፈልጉ የት እንደሚያደርጉ ስለማያውቁ ነፃ የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉበትን ቦታ ያመላክቷቸዋል።

ዲቦራ እንደምትለው በአሁኑ ሰዓት ሥራ ለመቀጠርም ሆነ ከተቀጠሩ በኋላ በውጤታማነት ለማገልገል ያለው የትምህርት ሥርዓት ብቻ በቂ ባለመሆኑ፤ ብዙ ልምድ፤ ተጨማሪ ዕውቀት፤ በማስፈለጉ ነፃ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጥተው የምስክር ወረቀት የሚያገኙበትን ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ተስማምተውም ያመቻቻሉ። በተለይ በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ ወጣቶችን ወደ አዲስ አበባ በማምጣት ለሦስት ቀን ሥልጠና በመስጠት ከዩኒሴፍ፤ ከዩኒስኮ ጋር በመነጋገርና ወደ እዛው መልሶ በመላክ የሚበቁበትና ወደ ሥራ የሚሠማሩበትን ሥልጠና እንዲያገኙና ኅብረተሰቡን እንዲያገለግሉ ያደርጋሉ። አሁን ላይም የማኅበሩን አባላት ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ያሉትን ወጣቶችም ለማድረስ ከሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር እየተነጋገሩ ይገኛሉ።

እርሷን ጨምሮ ሁሉም ወጣቶች በተለይም አብዛኞቹ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ተቀጣሪ እንዳልሆኑና በበጎ ፈቃደኝነት በማኅበሩ ውስጥ እንደሚያገለግሉም ነግራናለች። ማኅበሩ ከሜሪ ጆይ ጋር ቅርብ ጊዜ በነበረው ሩጫ ላይ አብረው ሠርተዋል። እርሷ ዓለም አቀፍ መድረክ የምትመራበትን ጨምሮ እንዲህ ዓይነቶቹን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራዎች ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ወጣቶች ካወንስል ጋር በመቀናጀት መሥራታቸውን አሁንም ከእነዚሁ አካላትና ከሌሎች ዓለም አቀፍ አካላት ጋር እየሠሩ መገኘታቸውን አንስታለች። እርሷን ጨምሮ ብዙዎቹ ወጣቶች ግን በጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ አገልግሎት የሚሰጡ እንጂ ገንዘብ ተከፋይ አይደሉም። ነገር ግን ለአገልግሎታችን ለምን አልተከፈለንም አይሉም። አንድ ሰው ሁል ጊዜ ግቡ ገንዘብ ማግኘት ከሆነ አደጋ አለው። ስለመሆኑም በተለይ ወላጆች እንደ ወላጅ ኅብረተሰቡም እንደ ኅብረተሰብ ከገንዘቡ ጋር ተያይዞ ለወጣቶች ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባውም ትመክራለች።

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆና ብር ዝም ብለው ወላጆቿ እንደማይሰጧትና ብሩን የፈለገችበት ምክንያት ትጠየቅ የነበረበትን ሁኔታ ተገቢነቱን ታስታውሳለች። በሌላ በኩል በፊልምም ሆነ በሌላ አጋጣሚ በእርሷ ዕድሜ የሚገኙ የውጭ ተማሪዎችን የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ባገኙት ገንዘብ የትራንስፖርት ወጪያቸውን ሲሸፍኑ በማየቷ፤ ወላጆቿን ‹‹ለምን እኔና እህቴም እንዲህ እንድናደርግ ገቢ የሚያስገኝ ትንንሽ ሥራ እንድንሠራ አትፈቅዱልንም? ስትላቸው ወላጆቿን ትጠይቃለች።›› ገና የ16 ዓመት ልጅ እኮ ነሽ ትባል እንደነበር ትናገራለች። ሥራ የምትይዙት ዩኒቨርስቲ ገብታችሁ ተምራችሁ ዲግሪያችሁን ከያዛችሁ በኋላ ነው ይባሉ ነበር። ይህም አዕምሯዋ ውስጥ ተቀምጦ እንደነበር ትናገራለች። ይሄ ምን ያህል ኢትዮጵያዊ ወጣት ያለ ሥራ እንዲቀመጥ ተፅዕኖ እንዳደረገ ስለማሳየቱም ትጠቁማለች። ‹‹ሁልጊዜ ትንሽም ብትሆን በዕውቀትም በገንዘብም ራሳችንን የምናሳድግበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልገናል።›› ስትልም ሠርቶ ማግኘትን በበጎ ጎኑ ትጠቅሰዋለች።

ዲቦራ ተቀጣሪ ሆና ገንዘብ ከማግኘቷ በፊት ፎቶግራፍ፤ መሥራቷ፤ ቪዲዮግራፊ መሥራቷ፤ በተለይ በኮቪድ ጊዜ ብዙ ነገሮች መማሯ ትንሽ፤ ትንሽ ገንዘብ ያስገኙላት እንደነበር ነግራናለች። በእዚህም ለቤት የሆነ ነገር ትገዛና የትራንስፖርት ወጪዋን ራሷ ትሸፍን እንደነበረም አስታውሳለች። የተቀጣሪነት ዕድል የሚኖረው እንዲህ ዓይነቱ ትንሽ፤ ትንሽ ልምድ ሲኖር ነውም ትላለች። ይሄን እሴት በመጨመር ግራፊክ ዲዛይን የሚፈልጉ ሰዎች ጋር ሄጄ ግራፊክ ዲዛይን ተምሬያለሁ ማለት መቻሌ ተፈላጊነቴን ይጨምረዋል የሚልም ዕምነት አላት።

እሴት መጨመር ገንዘብ ላያስገኝ ቢችልም፤ እኔ አሁንም የያዝኩት እሴት መጨመርን ነው ብላናለች። ዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ሠርታ ምንም ገንዘብ ሊሰጣት ያልቻለበት ሁኔታ ገጥሟትም ያውቃል። ሆኖም ለምን አልተሰጠኝም ብላ ከዛ መድረክ አልቀረችም። በማግስቱም ከዚያም በኋላ በመሄድ ልምድ ያካበተችበት ተሞክሮ አላት። ከገንዘብ ይልቅ ልምድ ይበልጥብኛል፤ ሰዎችም እተዋወቅበታለሁ የምትላቸው ሁኔታዎችም አሏት። ዋናው መማራችን ማደጋችን ራሳችን ላይ እሴት መጨመራችን ነው። ገንዘብ የሚመጣው፤ ከዚህ በኋላ ነው። ገንዘብ የሚገኝበትን ሂደትም ማመን አለብን። በአንዴ ለምን እንደዚህ አልተደረገልንም ካልን ብዙ ነገሮች እናበላሻለን። ገንዘብ በሂደት ቀስ እያልን የምናገኘው ስለሆነ አሁን ራሳችን ላይ መጨመር ያለብንን እሴት እንጨምር፤ እኔም አሁን ላይ እያደረኩ ያለሁት ይሄንኑ ነው ትላለች። በርካታ ዓለም አቀፍ መድረኮችን መምራት የቻለችውም በዚህ ይዞታዋ ነው።

## ዓለም አቀፍ መድረክ የማስተባበር ልምድ

ዲቦራ እኛ ስታስተባብርና ስትመራ ያገኘናትን ቀጣናዊ ትስስር ለዘላቂ ልማት መድረክ ጨምሮ ብዙ ዓለም አቀፍ መድረኮችን አስተባብራለች። ወደ ሌሎቹ ሳንገባ ይሄን መድረክ ልትመራ ስለቻለችበት ሁኔታ ጠይቀናት እንደነገረችን፤ የእንደራሴ ወጣቶች ፕሬዚዳንት ብሩክ አስቻለው መድረኩን እንድትመራ የነገራት በዋዜማው ነበር። ፈጥና ፈቃደኝነቷን የሰጠች ሲሆን፤ ፈቃደኛ የሆነችው በዕድሉ ልጠቀም በሚል ብቻ አይደለም። ከዚህ በፊት በርካታ ተመሳሳይ መድረኮች አስተባብራለችና ነው። በተጨማሪ ሀገር ውስጥ ይሁኑ እንጂ በዓለም አቀፍ መድረኮች፤ ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብም አያሌ ሥልጠናዎችንም ሰጥታለች። ፈጣን ምላሽ የሰጠችው ልምድ በተለይም በራስ መተማመን በሌለበት እንዲህ ዓይነቱን ዓለም አቀፍ መድረክ መምራት የሀገር ገጽታ ጥሩ አንድምታ ላይኖረው ስለሚችል መጠንቀቁ ባይከፋም የትኛዋም ዓይነት ሴት ያገኘችውን ዕድል ማሳለፍ የለባትም ትላለች። ደረጃ በደረጃ ራስን እያበቁ መምጣት ዕድሎችን ላለማሳለፍ አንዱ ዘዴ እንደሆነም ትመክራለች።

መርሐ ግብሩ የተለያዩ የምሥራቅ አፍሪካ አመራሮች፤ ከቀጣናውና ከቀንዱም የተውጣጡ በርካታ ወጣቶች የተጋበዙበት ነበር። አብዛኞቹ እንግሊዘኛ አንዳንዶቹም ፈረንሳይኛ የሚናገሩ በመሆኑ፤ ብዙዎቹ ከውጭ ጉዳይ የመጣሁ ስለመሰላቸው እየጠሩ ስለሚፈልጉት ሁሉ መልስ እንድሰጣቸው ይጠይቁኝ ነበር ትላለች። በየደቂቃው እየጠሩ ብዙ ነገሮችን እንድታብራራላቸው የሚፈልጉም ነበሩ። ቋንቋ ሰውን ከሰው የሚያገናኝ እንደመሆኑ ሰውን በቋንቋው መልስ መስጠት የተሻለ ግንኙነት ይፈጥራል። ባሕልን እና ታሪክን ይዞ ይመጣል ትላለች።

‹‹እኔ ሁለቱንም ቋንቋ አውቅ ነበር። በተለይ እንግሊዝኛ ኤ፤ቢ፤ሲ፤ዲ እያልን ቆጥረን ለረጅም ጊዜ እየተማርን ያደግንበት፤ ረጅም ጊዜ የተማርነውና በሥራችንና በትምህርታችን ላይ የምንጠቀመው በመሆኑ መናገሩ የአፍ መፍቻዬ ያህል አልከበደኝም። ፈረንሳይኛም እየተማርኩት ያለ ቢሆንም አልታማበትም። በመሆኑም ከሁሉም ከቀጣናው ተውጣጥተው በመድረኩ ከተገኙ አመራሮች ጋር በጥሩ ሁኔታ መግባባት ችያለሁ።›› ትላለች።

እርሷ ማኅበሯን ወክላ ከኢትዮጵያ ወጣቶች ካውንስልና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር አብረው ሲሠሩ መቆየታቸውን ትናገራለች። ወጣቷ ‹‹አሁን ገና ትንሽ ነኝ፤ በዚህ ትንሽነቴ እነዚህን ትልልቅ ቦታዎችን ማየት ቀድሜ ብዙ ነገሮችን እንድዘጋጅ ቀድሜ ራሴን ብዙ እንዳሳድግ፤ ራሴ ላይ እንድሠራ ጥሩ ዕድል ሰጥቶኛልም።›› ብላናለች። የምናገለግልበት ይለያይ እንጂ ሁላችንም አገልጋዮች ነን የምትለው ዲቦራ ወደፊት የሕዝብ አገልጋይ እንድትሆን መሠረት የጣለላት ስለመሆኑም ታነሳለች። ቦታው ወደ ፊት የሕዝብ አገልጋይ መሆን ነው የምፈልገው ትላለች። ያኔ ቦታው ላይ መገልገል ያለበት ሰው እንዲገለገል የማድረግ ፍላጎቷ የሚሳካ ስለመሆኑም ትናገራለች።

## ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በዲቦራ ዕይታ

ዓለም የሴቶች ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበር ሲሆን የተነሳበት ዓላማም አለው። ከዓላማው ሴቶችን ከጥቃት መጠበቅና ለሴቶች ዕድል መስጠት በዋንኛነት ይጠቀሳሉ። በዓለማችን እኛ እንድንማር፤ ከወንድ እኩል የተሻለ ደሞዝ ተከፋይ እንድንሆንና በተሻለ ሁኔታ እንድንኖር፤ ዕድሎች እንድናገኝ ብዙ ሴቶች ዋጋ ከፍለዋል። ሆኖም በሴቶች ላይ የሚደርሰው ጥቃት እስካሁን አልቆመም። አሁን ወደ እዚህ ስመጣ ሴቶች እንደተደፈሩ የሚገልጽ ዜና እያነበብኩ ነበር። ይሄ በተለይ በገጠሩ አሁንም ፆታዊ ጥቃት እየደረሰባቸው ያሉ ሴቶች መኖራቸውን ያመለክታል። የሴቶች ቀን ማርች 8 ብቻ ሳይሆን ሁሌም እንደመሆኑ ሁልጊዜም በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለመከላከል መጮህ አለብን። አዲስ አበባ ላይ ሕግም አለ፤ ከሌሎች አካባቢዎች በተሻለ ሴቶች ከጥቃት ይጠበቁበታል። ገጠር ላይ ግን ይሄ ሊኖርም ላይኖርም፤ ቢኖርም ላይከበር የሚችልበት ሁኔታ አለ። በመሆኑም የዓለም የሴቶች ቀንን ስናከብር ከተማ ላይ ባሉ ሆቴሎች ባንገደብ መልካም ነው። አንድ ቀን ብቻ ሳይሆን ሁሌም ዕለቱን እያሰብን፤እያስተማርን፤ ለኅብረተሰቡ ሥልጠና እየሰጠን ወጣ ብለን ብናከብረው ጥቃታቸውን መከላከል እንችላለን። በሕይወታቸውም ላይ ለውጥ እናመጣለን ብዬ አምናለሁ ብላለች። መልካም በዓል!

# ልጅ ለማሳደግ የሚከፈል ዋጋ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

እናትነት ስስት ነው፤ እናት ለልጆቿ ያላት ስስት ጥግ የለውም። ይህም ለሴት ልጅ ብቻ የተሰጠ ፀጋ ነው። ሴት ልጅ በተፈጥሮ ከታደለቻቸው እልፍ በረከቶች መካከል ልጇን ዘጠኝ ወር በሆዷ መሸከሟ፣ አምጣ መውለዷና ጡቶቿን አጥብታ ማሳደጓ ሲሆን፤ ለልጆቿ ካላት ስስትና ጥልቅ ፍቅር የተነሳ በልተው የሚጠግቡ፣ ጠጥተው የሚረኩ፣ ለብሰው የሚሞቃቸው አይመስላትም። ‹‹ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች›› እንዲሉ ሴት ልጅ እናት ስትሆን ልጆቿ የመኖሯ ትርጉም ይሆኑና እሷ አዳፋ ለብሳ ልጆቿን ፀአዳ ታለብሳለች፤ የእኔ የምትለው ሁሉ ቢጎድልም የልጆቿን ጎደሎ ግን ከአፍ እስከ ገደፉ ትሞላለች፤

እናትነት እንግዲህ ይህ ነው፤ በአባጣ ጎርባጣው በጠመዝማዛው መንገድ ሁሉ አልፋ የራቀውን አቅርባ በደበዘዘ ማንነቷ ውስጥ ልጆቿ ፈክተው፣ ደምቀውና ቀድመው እንዲታዩ ታደርጋለች። ይህ የእናትነት መገለጫ ነው። እርግጥ ነው በልጆች አስተዳደግ ላይ ወላጅ አባትም ጉልህ ሚና አለው። ወላጅ አባቶች በልጆች አስተዳደግ የድርሻቸውን መወጣት ከቻሉ የእናቶችን ድካም በብዙ እጥፍ ማቃለል እንደሚችሉ ይታመናል። ይሁንና ሴቶች ብዙ ጊዜ የማኅበረሰቡ ግፍ ሰለባዎችና የማኅበራዊ ፍትሕ ጉድለት ሰለባዎች ሲሆኑ ይስተዋላል። ያም ቢሆን ታዲያ ሴት ልጅ ጀግና እና ብልህ ናት። በተለይም እናት ስትሆን የቤተሰብ መሠረት የደስታ ምንጭ ናት።

የቤተሰብ መሠረት የደስታ ምንጭ የሆነችው እናት በቤት ውስጥ የሚኖሯት ኃላፊነቶች እጅግ ሰፊ፣ ጥልቅና ውስብስብ በመሆናቸው አባት በጎደለ ጊዜ ደግሞ ኃላፊነቶቹ ድርብ ድርብርብ መሆናቸው አይቀሬ ነው። እናቶች በተፈጥሮ ከታደሉትና ማኅበረሰቡ ከጣለባቸው ኃላፊነቶች በተጨማሪ በልጆች አስተዳደግ ላይ ትልቅ ድርሻ ያላቸው ቢሆንም የወላጅ አባቶች ሚናም እንዲሁ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። በመሆኑም መልካም አባቶች በብዙ መልኩ የእናቶችን ጫና ማቃለል እንደሚችሉ ሁሉ ልጆቻቸውን ያለ አባት የሚያሳድጉ እናቶች ደግሞ የሚወጡት ኃላፊነት እንደ ሰማዕታት ገድል እጥፍ ድርብ እንደሆነ ይታመናል።

እነዚህ እናቶች ታዲያ እጥፍ ድርብ ኃላፊነቶችን ለመወጣት ወደኋላ የሚሉ አይደሉም። በብርቱ ጥረታቸው ልጆቻቸውን ያለአባት ያሳድጋሉ፣ ያስተምራሉ፣ ለወግ ለማዕረግ ያበቃሉ። ይህም በየአካባቢያችንና በየጓዳችን የምናስተውለው ሐቅ ነው። በዛሬው ዕለት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ113 በኢትዮጵያ ደግሞ ለ48 ጊዜ እየተከበረ ያለውን ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን (March 8) ምክንያት በማድረግ ልጆቻቸውን ያለአባት የሚያሳድጉ ጠንካራ እናቶችን ልናነሳ ወደናል።

በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ሴቶች ዘርፈ ብዙ የሆኑ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች ያሉባቸው ቢሆንም ጫናዎቹን ሁሉ ተቋቁመው ልጆች በማሳደግ ትልቁን ኃላፊነት ይወጣሉ። በተለይም የኢኮኖሚ ጥገኛ ሆነው ለልጆቻቸው ብዙ ዋጋ የሚከፍሉ እናቶችን ቤት ይቁጠራቸው።

እናቶች ልጆቻቸውን ከአባት ውጭ ለማሳደግ ከሚገደዱባቸው የተለያዩ ምክንያቶች መካከል መደፈር አንዱ ምክንያት ሲሆን፤ በሞት መለየትና ባለመግባባት መለያየትም ሌላው ምክንያት ነው። ይሁንና ከእነዚህ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ከሆኑ ምክንያቶች ባለፈ አሁን አሁን ደግሞ ልጅ ለመውለድ ብቻ ባል የሚያገቡና ልጅ ከወለዱ በኋላ ተለያይተው ልጆቻቸውን የሚያሳድጉ እናቶች እየመጡ ነው። ነገር ግን እንደዚህ አይነት እናቶች ለጊዜው ጉዳያችን አይደሉም። ለጊዜው ጉዳያችን ይሁኑ ያልናቸው እናቶች ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ልጆቻቸውን ያለ አባት እያሳደጉ ያሉትን ነው። እነዚህ እናቶች ልጆቻቸውን ያለ አባት ሲያሳድጉ የሚገጥማቸው ችግር ምንድን ነው፤ እንዴትስ እየተወጡት ነው፤ ምን መልዕክትስ አላቸው የሚለው ዋናው ትኩረታችን ነው።

አርቲስት የትናየት ታምራት ወይም በቤት ስሟ ሚሚ ታምራት በመባል ትታወቃለች። በኪነጥበብ ውስጥ በነበራት የትወና ሥራ በበርካታ ፊልሞች መሪ ተዋናይት በመሆን ተውናለች። ከትወና ሥራዋ በተጨማሪም በጤናው ዘርፍ ተሠማርታ በአይነቱ ልዩ የሆነ የስዊዝ ዲያግኖስቲክስ የሕክምና ማዕከልን ያቋቋመች ብርቱ ሴት እንዲሁም እናት ናት። የትዳር ሕይወት ባይኖራትም ትዳር አክባሪና ትዳር ለሰው ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጠ ክቡር ስጦታ መሆኑን ታምናለች። ያም ቢሆን ታዲያ ሴት ልጅ ትዳር ካልተመቻት ልጆቿን ያለ አባት ማሳደግ ትችላለች የሚል ጽኑ አቋም አላት።

እግዚአብሔር በአራት ሴት ልጆች ባርኮኛል የምትለው አርቲስት የትናየት፤ ልጆችን ከአባት ጋር ሆኖ ማሳደግም ከችግር ነፃ የሚያደርግ እንዳልሆነ ጠቅሳ፤ በተለይም በአሁን ወቅት ልጆች ከወላጆች ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ በራሱ እጅግ ጥቂት እንደሆነ ነው የገለጸችው። እሷ እንዳለችው ልጆቿ አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በትምህርት ነው ከትምህርት መልስም ከአስጠኚ ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ በመኖሩ ከወላጆቻቸው ጋር የሚሳልፉት ጊዜ እጅግ የተወሰነና የተቆጠበ ነው ትላለች።

‹‹ወላጆችም በተመሳሳይ በሥራ የሚጠመዱ በመሆናቸው በተወሰነ ጊዜ ፕሮግራም አድርገው ካላገኟቸው በስተቀር አሁን ያለው ሁኔታ እንደቀደመው ጊዜ አይደለም። በተለይም ትምህርት ቤት ከገቡ ልጆቹም ጊዜ አይኖራቸውም። ይሁን እንጂ ወላጆች በተቻለ አቅም በየዕለቱ ለልጆቻቸው የሚተርፍ ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል›› በማለት እሷ በቀን ውስጥ ካላት ጊዜ አብቃቅታ ለልጆቿ የምትሰጥ መሆኗን ነው የገለጸችው።

ጊዜ ከመስጠት ባለፈም ልጆች የሚስፈልጋቸው ብዙ ጉዳዮች ስለመኖሩ ያነሳችው አርቲስት የትናየት፤ ያለአባት በማሳደጓ ግን ይህ ነገር ቀረባቸው ብላ የምትቆጭበት አንድም ነገር እንደሌለ ነው የገለጸችው። እሷ እንደምትለው፤ ለልጆች አስፈላጊ የተባሉ ማናቸውንም ሁኔታዎች በማሟላት እናትም አባትም በአንድ ላይ ሆነው ከሚያሳድጓቸው ልጆች ባልተናነሰና እንዲያውም በተሻለ ሁኔታ ልጆቿን እያሳደገች ነው። ‹‹ልጆቼን ያለ አባት በማሳደጌ ቀረባቸው ብዬ የምለው ነገር ቢኖር ‹‹አባባ›› ብሎ መጣራት ብቻ ነው›› ትላለች።

ጥሩ አባቶች እንዳሉ ሁሉ ጥሩ እናቶች አሉ የምትለው አርቲስት የትናየት፤ ለሰው ልጅ አባት መሆን የሚችለው እግዚአብሔር ነው የሚል ዕምነትም አላት። ‹‹እግዚአብሔርን አባት በማድረግ ልጆቼን ሳላጎድላቸው፣ እግዚአብሔርን አውቀው፣ የሥራን ክቡርነት ተረድተው፣ ጥገኝነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተገንዝበው እንዲያድጉ ትልቁን ድርሻ ወስጄ ማሳደግ ችያለሁ›› በማለት አንዳንድ ጊዜ በትዳር ውስጥም ሆነው ልጆችን ማሳደግ እጅግ ፈታኝና አስቸጋሪ የሚሆንበት አጋጣሚ ስለመኖሩ ታነሳለች።

ትዳር ባይኖራትም አራት ሴት ልጆቿን እናትም አባትም ሆና ማሳደግ መቻሏ ብዙም ፈተና እንዳልሆነባት ስትገልጽ፤ ለራሷ በቂ ጊዜ ባይኖራትም ለልጆቿ ግን ካላት ሁሉ ቀንሳ ጊዜ በመስጠት መልካም፣ ጥሩና ሀገራቸውን የሚወዱ ልጆች ሆነው እንዲያድጉ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ የምታሳድግ መሆኗን ነው ያስረዳችው።

ልጆችን በማሳደግ ሂደት ውስጥ አባት ትልቅ ድርሻ እንዳለው የገለጸችው አርቲስት የትናየት፤ በዙሪያዋ የምታስተውለውም ይህንኑ እንደሆነና አብዛኞቹ አባቶች በልጆች አስተዳደግ ላይ ትልቁን ሚና ሲወጡና እናቶችን ነፃ ሲያደርጉ መታዘቧን ገልጻ፤ ሁሉም ሰው ግን አንድ አይደለምና ሁኔታዎች ካልፈቀዱ ሴቶች ልጆቻቸውን በብቸኝነት ማሳደግ ይችላሉ። አባቶችም እንዲሁ እናት ሳትኖር ልጆቻቸውን ማሳደግ እንደሚችሉ ትገልጻለች። በልጆች አስተዳደግ እናትም ሆነች አባት ትልቅ ድርሻ አላቸው። የምትለው አርቲስት የትናየት፤ ነገር ግን የአባት አለመኖር ልጆች ተጎድተው እንዲያድጉ ምክንያት መሆን የለበትም ባይ ናት።

ሴት ብቻዋን ሆና መሥራት፣ ልጆች ማሳደግ፣ አገር መምራት፣ ተፅዕኖ መፍጠርና ሌላም ሌላም ማድረግ እንደምትችል ለልጆቼ ማሳየት እፈልጋለሁ›› የምትለው አርቲስት የትናየት፤ ይህን ለማስተማር ጥሩ እናት መሆን ቀዳሚ ጉዳይ እንደሆነ ነው የገለጸችው። አለፍ ሲልም ሴቶች የአባትን ድርሻ ጭምር ደርበው መወጣት ሲችሉ ይህን እየተመለከቱ የሚያድጉ ልጆች በራሳቸው መቆም የሚችሉ ጎበዝና ጠንካራ ሆነው የሚያድጉበትን ዕድል ይፈጥራልም ብላለች።

በመጨረሻም በብዙ ችግር ውስጥ ሆነው ልጆቻቸውን ያለአባት የሚያሳድጉ እናቶች የችግሮቻቸው መነሻ ባል መፍታታቸው አልያም ከትዳር ውጭ ልጅ መውለዳቸው አይደለም። በማለት በተለያየ አጋጣሚ ልጆቻቸውን ያለአባት የሚሳድጉ እናቶች አዕምሯቸውን ለሥራና ሥራ ብቻ ዝግጁ ማድረግ እንዳለባቸውና ከአባት ውጭ ልጆችን ማሳደግ እንደሚችሉ ትገልጻለች። ለዚህም ትላለች ለዚህም በየአካባቢው በርካታ ሴቶች ልጆቻቸውን እናትም አባትም ሆነው እንደሚያሳድጉና ስኬታማ እንደሆኑም ጭምር ማየት ይቻላል በማለት አንድ ምሳሌ እንደሆነች ገልጻ በልጆች አስተዳደግ ላይ የአባት ድርሻ የጎላ ቢሆንም እናት ደግሞ የበለጠውን በማድረግ ሁሉን ትችላላች በማለት ሃሳቧን አጠቃላለች።

ሌላኛዋ ባለታሪካችን ደግሞ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጫናዎችን ተቋቁመው ልጇን በብዙ ውጣውረድ እያሳደገች እንደሆነ የገለጸችው ወይዘሮ ፀሐይ ሞላ ስሟ የተቀየረ ባለታሪካችን ናት። ባለታሪካችን የ14 ዓመት ሴት ልጅ ያላት ሲሆን፤ ልጇን የምታሳድገው በብቸኝነት ነው። ‹‹ትዳር ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ትልቅ ፀጋ ነው። ልጆች ደግሞ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው›› የምትለው ወይዘሮ ፀሐይ፤ እናት ለልጆች እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ብትሆንም ልጆች በእናትና በአባት እቅፍ ውስጥ ሆነው ቢያድጉ መልካም ነው። ካልሆነ ግን ከባድ ነው ትላለች።

ከልጇ አባት ጋር በተፈጠረ አለመግባባት ተለያይታ በቤተሰብ እገዛ ልጇን እያሳደገች መሆኑን ስትገልጽ፤ ‹‹የቱንም ያህል ቢሞላላት አባት ከሌለ ጎዶሎ አለው›› በማለት ነው። የምታስረዳው። እሷ እንዳለችው ልጆች የእናት ፍቅርና እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ የአባት ፍቅርና እንክብካቤም የግድ ያስፈልጋቸዋል። ያ ካልሆነ ግን እናት አባትም እናትም ሆና የማሳደግ ኃላፊነት አለባት። በዚህ ሂደት ውስጥ ታዲያ ብዙ ፈተናዎች አሉ። እርግጥ ነው የሚያጋጥሙ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፈተናዎች ሁሉ እናቶችን ያንገዳግዱን ይሆናል እንጂ ፈጽሞ አይጥሉም። ምክንያቱም እናትነት ሁሉን መቻልና ሁሉን መሆን ነውና በማለት ገልጻለች።

ልጇን ከአባት ውጭ የምታሳድግ እናት ከማኅበረሰቡ አመለካከት ጀምሮ ፈታኝ የሆኑ ብዙ ችግሮች እንዳሉ በመጥቀስ፤ ማኅበረሰቡ ትዳር ውስጥ ለሚፈጠር ልጅ እና ከትዳር ውጭ ለሚመጣ ልጅ እኩል ዋጋ የሚሰጥ አለመሆኑንና ይህም የሥነልቦና ጫና ያለው መሆኑን የገለጹት ወይዘሮ ፀሐይ፤ በዚህ ምክንያት ብዙ ዋጋ ተከፍሎላቸው የሚያድጉት ልጆች አሉ። ያለአባት እናት ብቻዋን የምታሳድገው ልጅ ኢኮኖሚያዊ ጥያቄው ቢመለስለት የማኅበረሰቡ ጫና በራሱ ሌላ ፈተና ነው ይላሉ። እሳቸው እንደሚሉት፤ በተለይም እናት የገቢ ምንጭ ከሌላት ፈተናው ከባድ ነው። እርግጥ ነው የራሷን ፍላጎቶች ሁሉ ገድባ ለልጆቿ ቅድሚያ በመስጠት ጎዶሎውን ትሞላ ይሆናል። ነገር ግን ተፈጥሯዊ የሆኑና መመለስ የማትችላቸው ጥያቄዎች ግን ሁሌም በውስጣቸው ይኖራል ነው ያሉት።

እናትነት መልካም ገጽታዎችን አምቆ የያዘ የሴት ልጅ ትልቅ መገለጫ ነው የሚሉት ወይዘሮ ፀሐይ፤ ለልጆች የማይከፈል መስዋዕትነት ባለመኖሩ ብዙ እናቶች ልጆች የሚያሳድጉት ብዙ ዋጋ ከፍለው እንደሆነ ገልጸዋል። በተለይም ልጆቻቸውን ያለአባት የሚያሳድጉ እናቶች ብርቱ፣ ጎበዝና ጠንካራ መሆናቸውን ነው የገለጹት።

# በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸም የወሲብ ጥቃት በሕግ እይታ

**አመስወርቅ ከበደ**

ጋብቻ ከሥነ ፍጥረት አንስቶ የተጀመረ አንዱ የቤተሰብ፤ የሀገር እና አሁን የዓለም ሕዝብ ተብሎ ለሚጠራው መሠረት የሆነ የወንድና የሴት ጥምረት ነው::ማኅበረሰቡና ሕገ መንግሥቱ እውቅና የሰጠው፤ ለጤናማ ቤተሰብ እና ሀገር ምሰሶም ነው::ጤናማ ያልሆነ ጋብቻ ደግሞ ለፆታዊ ጥቃት ዋነኛ መንስኤ ነው::ከዚህ አኳያም ጥናቶች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ 35 በመቶ የሚሆኑ እድሜያቸው ከ15 እስከ 49 ያሉ ሴቶች ከባላቸው ወይም ከፍቅር አጋራቸው አካላዊ፣ ስሜታዊ እና ፆታዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል::ለመሆኑ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸም ጥቃትን ሕግ እንዴት ይመለከተዋል?

ጠበቃና የሕግ አማካሪ እንዲሁም በፐራይም ቴሌቪዥን የሕግ ጉዳይ አቅራቢና አዘጋጅ ወይዘሮ ትሩፋት በላይነህ እንደሚሉት፤ ጋብቻ በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ ውሕደት እንደሆነ የፌደራል የቤተሰብ ሕግ ይገልጻል::

ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ጋር ተያይዞ በቤተሰብ ሕጉ ባልና ሚስት ለጤናቸው አስጊ ካልሆነ በስተቀር ግዴታ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ አለባቸው ይላል::በመመሪያው ውስጥ የተመለከተው ስለ ጤና ብቻ ነው::ሌሎች ሊፈጠሩ የሚችሉ ጥቃቶችን ግን ታሳቢ ያላደረገ መመሪያ ነው::በዚህም በሕግ እንደ ግዴታ በመቀመጡ አንድ ሴት ፈቃደኛ ባትሆን እንኳን ተሰሚነት አታገኝም ይላሉ::

የግብረሥጋ ግንኙነት እንደ ግዴታ በመቀመጡ የተነሳ ችግር ገጥሟት የመጣች ደንበኛቸው እንደነበረች የሚጠቅሱት ወይዘሮ ትሩፋት፤ የደንበኛዋ ቤተሰብ በአንድ ክፍል ቤት የሚኖሩ በመሆኑ ባለቤታቸው በተደጋጋሚ በልጆቻቸው ፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንድታደርግ ያስገድዳታል::ሆኖም ይህ ሕግ ከሌሎች የዓለም ሀገራት አንጻር ሲታይ ተቃራኒ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ይህን ነገር እየተመለከቱ ያደጉ ሕጻናት ለአዕምሯቸው ጤንነት ጉዳት ከመሆኑም በተጨማሪ፤ ሕጉ ስለማይከለክል እነሱም ወደፊት እንደዚህ አይነት ነገር ማድረጋቸው አይቀርም የሚሉት የሕግ ባለሙያዋ፤ በሕጉ ላይ በተጨማሪም ባልና ሚስት በጋራ መኖር እንዳለባቸው ልጆቻቸውን በኃላፊነት ማሳደግ እንዳለባቸው ግዴታ ያስቀምጣልም ብለዋል::

ወሲባዊ ትንኮሳን በተመለከተ የወንጀል ሕጉ ምን እንደሚል ያነሱት ወይዘሮ ትሩፋት፤ ኃይልን በመጠቀም፣ በማስፈራራት ሴት ልጅ ላይ ወሲባዊ ጥቃት መፈጸም በወንጀል ያስቀጣል ይላል::ይህም የወንጀል ሕግ በትዳር ወስጥ የሚፈጸም ወሲባዊ ትንኮሳ አልተመለከተም ሲሉ ይጠቀሳሉ::በሌሎች በአውሮፓ፣ አሜሪካ እና አንዳንድ አፍሪካ ሀገራት ግን በግልጽ የተቀመጠበት ሁኔታ እንዳለ ያስረዳሉ::እንደውም ሕጉ ‹ወሲባዊ ትንኮሳን ‹‹ወሲባዊ ትንኮሳ ያለፈቃድ በባል፣ በሚስት ወይም በማንኛውም በሌላ አካል የሚፈጸም የወሲብ ጥቃት ነው፡፡›› በማለት ያስቀምጠዋል ይላሉ::

እንደ ሕግ አማካሪዋ ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያ ሕግ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸም የወሲብ ጥቃትን የሚከለክል እና የሚቀጣ አይደለም::በዚህም የሚያደርሰው አዕምሯዊ፤ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ቀላል አይደለም::

በጋብቻ ውስጥ በሚፈጸም የወሲብ ጥቃት ጉዳትን ያስተናገዱ በርካታ ሴቶች አሉ::ወደ ሕግ አካል ቢሄዱም ‹‹ባልሽ ነው›› ተብለው ሲመለሱ ይስተዋላል የሚሉት ወይዘሮ ትሩፋት፤ መፍትሔው ሴቶችንም በጉዳዩ በማካተት አዲስ ሕግ ማርቀቅ እንደሆነ ያስቀምጣሉ::በተጨማሪም ምናልባት ዛሬ መፍትሔ ባያገኙም ለነገ ግብዓት ይሆናልና እንደዚህ አይነት ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ወጥተው መናገር ይኖርባቸዋል ይላሉ::

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ የሥነ ልቦና መምህር ምሕረት አብርሃም በበኩላቸው እንደሚገልጹት፤ በጋብቻ ውሰጥ የሚፈጸም የወሲብ ጥቃት በቤት ውስጥ ከሚፈጸሙ ጥቃት ውስጥ አንዱ ነው::ጥቃት ሲኖር ምናልባትም ለረጅም ጊዜ ሊቆይ የሚችል ጠባሳ ይኖራል::በትዳር ውስጥ የሚፈጠር ጥቃት ሲሆን ደግሞ ውስብስብነቱ ከፍ ይላል::

‹‹ጥቃቱ የሚደርስበት አካል ጥቃቱን ከሚያደርሰው አካል ጋር ለረጅም ጊዜ የሚቆይ እንደመሆኑ መጠን ጠባሳው እያደገ የሚመጣ ነው፡፡›› የሚሉት የሥነልቦና ባለሙያዋ፤ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አካላዊ ብቻ ሳይሆን አዕምሯዊ ዝግጁነትን ይፈልጋል:: ይህንን ተከትሎ ሆርሞኖችም ዝግጁ ይሆናሉና::ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን የጤና ቀውስ ያስከትላል ሲሉ በጉዳዩ ዙሪያ የሚመጣውን ችግር ያብራራሉ፡፡

በትዳር ውስጥ ያለፈቃድ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት በባልና ሚስት መካከል መተማመን እንደሚያጠፋ፤ ንግግራቸው እንዲሻክር እንደሚያደርግና የትብብር መንፈስን እንደሚያዳክም የሚገልጹት መምህርት ምሕረት፤ ችግሩ ከሰፋ ደግሞ ለፍች ምክንያት እንደሚሆን ያነሳሉ::

መምህርቷ እንደሚሉት፤ መፍትሔው ወደ ትዳር የሚገቡ ሰዎች የሚያገቡት ሰው የሕይወት ግባቸውን እንደሚያሳካ፤ ልጆችም ሲወለዱ ለሚወለዱ ልጆች መልካም አባት ወይም እናት እንደሚሆን አምነው መግባት ነው::በተጨማሪም ተጋቢዎቹ ምን አይነት ቤተሰብ መመሥረት እንደሚፈልጉ ቀድሞ ማሰብ፤ ስለሚኖረው የወሲብ ግንኙነት መወያየት ነው::

ማኅበረሰቡም ምናልባት ወደ ሥነልቦና አማካሪዎች መጥቶ ምክር የማግኘት ባሕሉ ደካማ ቢሆንም፤ አንዱ ከአንዱ ጋር ሊወያይ ይገባል::የሃይማኖት አባቶችም ትዳር በፈጣሪ ዓላማ የተመሠረተ ተቋም እንደመሆኑ በደንብ ሊያስተምሩ እንደሚገባ ያክላሉ::

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተረጋጋ ቤተሰብን ከመፍጠር አንጻር ያሉትን ክፍተቶች በጥናት ተመልክቶ፤ አዲስ መመሪያ ለማዘጋጀት ኮሚቴ ተዋቅሮ እየሠራ እንደሆነ የሚናገሩት ደግሞ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአረጋውያን እና ቤተሰብ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ ሮበሌ ናቸው::እርሳቸው እንደሚሉት፤ የቤተሰብ ሕጉ ባልና ሚስት ሲለያዩ ሀብት መካፈል እንዳለባቸውና እንዴት መከፋፈል እንዳለባቸው ያስቀምጣል::ይህንን ደግሞ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የማስረዳት ሥራ ይሠራል::በተጨማሪም ባልና ሚስት በጋራ ሲኖሩ ጤናማ ቤተሰብ ለመፍጠር በሚያስችሉ መመሪያዎች ላይ ዝርዝር ጉዳዮችን ባካተተ መልኩ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናል::

ልዩ ዕትም

# ‹‹ ኢትዮጵያ በእኔ የኑሮ ደረጃ ልክ አትታይም ቢርበኝም ቢጠማኝም ሀገሬ ናት››

**የመቶ አለቃ አይዳ አላሮ**
**የአየር ወለድ ማሰልጠኛ የዲስፓቸር ባለሙያ**

መክሲት ወንድወሰን

ወኔ ፤ ድፍረትና ለሐገር መቆምን ከአባት ከአያቶቿ እንደወረሰችው ትናገራለች። በአየር ወለድ ውስጥ ለ 37 ጊዜያት ከአውሮፕላን ላይ ዘላለች። በልጅነቷ ከተቀላቀለችው የሀገር መከላከያ ሰራዊት ያገኘችው የሀገር ፍቅር ስሜትን የሚያላብስ ቁርጠኝነት በሙያው በጽናት ለ18 አመታት እንድትቆይበት አድርጓታል ። ጊዜዋን እና ህይወቷን የሰጠችለት ሙያዋ በአየር ወለድ ውስጥ በሁለቱም ጾታዎች ከአውሮፕላን ላይ ለ37 ጊዜያት የዘለለች ብቸኛዋ ሴት ሆና እንድትመዘገብ አድርጓታል ። የዛሬዋ የአዲስ ዘመን የሴቶች ቀን (ማርች 8 ) ልዩ እትም እንግዳችን የመቶ አለቃ አይዳ አላሮ ።

የመቶ አለቃ አይዳ ተወልዳ ያደገችው በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ አካባቢ ደንበል ህንጻ ጀርባ ልዩ ስሙ ‹‹ፍላሚንጎ›› በሚባለው ሰፈር ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷንም በነጻነት ብርሃን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተምራለች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ በቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቃለች። የዲፕሎማ ትምህርቷን ለመከታተል ደግሞ በቀድሞው ምስራቅ አጠቃላይ በአሁኑ ምስራቅ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ነበር ያቀናችው።

ወደ ውትድርናው ዓለም ስትገባ በእድሜ ልጅ እንደነበረች የምትናገረው መቶ አለቃ አይዳ በወቅቱ ስለ ውትድርና በቂ ግንዛቤ እንዳልነበራት ታስታውሳለች። ይሁን እንጂ ተወልዳ ባደገችበት “መሿለኪያ አካባቢ አራተኛ “ የሚባል የወታደሮች ካምፕ ነበርና በልጅነት እድሜዋ በወታደር ልብስ የሚንቀሳቀሱትን ስትመለከት ልዩ ስሜት ይፈጥርባት እንደነበር ትዝ ይላታል።

ደጋግማ እንደምትለው ወደ ሙያው ስትቀላቀል እምብዛም እውቀቱ አልነበራትም ።ይሁን እንጂ በርካቶች ወደ ውትድርና ከገቡ በኋላ የሀገር ፍቅሩ እና ቁርጠኝነቱ እንሚያይልባቸው ሁሉ እኔም “ሳልወጣ ቀርቻለሁ” ትላለች። ይህ እውነታም ለ18 አመታት በሙያው ውስጥ እንድትዘለቅ ማድረጉን ትናገራለች።

መቶ አለቃ አይዳ የውትድርና ስልጠናን እንደዚህ ትገልጸዋለች። “አንዲት እናት ልጅ እንደወለደች በመጀመሪያው ቀኗ ለልጇ ጥሩ ጥቅልል ጉርሻ አታጎርሰውም። ጡት ታጠባዋለች። ያንን ሂደት ሲያልፍ ደግሞ የላመ ነገር ይበላል ፤ ከዛም ልጁ አቅሙ ሲጠነክር እራሱ ወደ አጥንት መጋጡ ይሄዳል። ልክ እንደዚሁ እኛም በአንድ ጊዜ ወደ አጥንት መጋጡ ስራ ወይም ወደ ከባዱ ስልጠና አልሄድንም” ትላለች።

በመጀመሪያ መሰረታዊ የእግረኛ ስልጠና ለስድስት ወራት በብር ሸለቆ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት፣ ሁርሶ እና ጦላይ ማሰልጠኛ ወስደዋል። የውትድርና ሙያ ሰዎች የራሳቸውን ባህል ፤ ወግ እና ስርአትን ይዘው የሚገናኙበት ከመሆኑ አንጻር ‹‹ትንሿ ኢትዮጵያ››ያለችው እዛ ውስጥ ነው። ሁሉም የራሱን ይሰጣል የሰውንም ይቀበላል። ውትድርና ውስጥ ሰው ያለውን ሲሰጥ ‹‹ያንተ ያንሳል›› እያለ አይደለም ሲቀበልም ‹‹የኔ ስለሚያንስ ነው›› አይልም። ውትድርና ሰዎች በደንብ የሚዋሃዱበት እና ኢትዮጵያን የሚያውቁበት ቦታ ነው።

አዲስ ወደ ውትድርና ሙያ የሚቀላቀል ሰው ያለው የባህል እና የቋንቋ መለያየት በጥቂቱ ሊፈትነው ይችላል። አንዳንድ ቃላት በአንዳንዱ ማህበረሰብ መደበኛ ሲሆን ያው ተመሳሳይ ቃል በሌላው ማህበረሰብ ዘንድ አጸያፊ ሊሆን ይችላል። በዚህም ሳይታሰብ አብሮን ከሚሰለጥነው ባለሙያ ጋር ሊያጋጭን ይችላል።

መሰረታዊ የውትድርና ስልጠና ተጠናቆ ወደ ኮማንዶ ስልጠና ሲገባ ፈታኝ የሆኑ ነገሮች ይኖሩታል። የአካላዊ እና ስነልቦናዊ ብስለትንም የሚጠይቅ ነው። መሰረታዊ የውትድርና እውቀቱን በመጀመሪያ ያገኘ ሰው ወደ ኮማንዶ ሲመጣ ከአካላዊ ጥንካሬ ጎን ለጎን የሚሰጠውን እያንዳንዱን ነገር ለመቀበል እና ለማድረግ ዝግጁ መሆን ይጠበቅበታል።

ኢትዮጵያ ላይ እንደተወለደች ሴት ከአባቶቻችን የምንወርሰው ወኔ እና ድፍረት አለ ። ይህ ደግሞ ያጀግነናል። እኔም ያለኝ ድፍረት ከአባት ከአያቶቼ የወሰድኩት ነው ።

መቶ አለቃዋ እንደምትናገረው በአየር ወለድ ውስጥ ለ37 ጊዜያት ከጦር አውሮፕላን ላይ ዘላለች። እንዲህ በሆነ ግዜ በመጀመሪያው አምስት ዝላይ የ አንድ ክንፍ መለያ /ዊንግ / ይሰጣል። አንድ አየር ሀይል 30 ዝላይ ሲያስመዘግብ ደግሞ ዊንግ ላይ ኮከብ ይጨመርበታል። አየር ወለድ ላይ ሰዎች የዝላይ ቁጥር በጨመሩ ሰአት ፍርሃታቸውም ይጨምራል። ምክንያቱም ሰዎች ሲሰበሩ፤ ፓራሹት ሳይከፈት ሲቀር የማየት እድል ስለሚያጋጥም ፍርሃትን ያጭራልና።

ምንም የማያውቅ ሰው ‹‹ ወጥቼ ምን ይገጥመኝ ይሆን? ይላል እንጂ ወድቄ እሰበራለሁ ፓራሹቱም ላይከፈት ይችላል›› አይልም። ምክንያቱም አጋጣሚውን ስለማያውቀው። የአየር ወለድ ህግ ‹‹የዝላይ ቁጥር በጨመርክ ቁጥር ስጋቱ ይጨምራል ›› ይላል። አሁን ላይ “የአየር ወለድን የበፊት ክብር ለመመለስ ያማረ ትምህርት ቤት ተገንብቷል። እኔም ለሀገሬ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታክል አስተዋጾ ማድረግ ከቻልኩና ስሟን ማስጠራት ከቻልኩ አደርገዋለሁ።” ትላለች።

“በዝላይ ህይወቴ ያን ያህል የከፋ አደጋ ደርሶብኝ አያውቅም ፤ በ33ተኛ ዝላይ ላይ ብቻ ትንሽ ወለምታ ተከስቶብኝ ነበር ፤ ይሁን እንጂ ከዛ በኋላም ሌሎች ዝላዮችን አድርጊያለሁ”ትላለች። የመጀመሪያውን የዝላይ ታሪኳን ስታስታውስም “ለመጀመሪያ ጊዜ በ1998 ዓም በአንቶኖቭ አውሮፕላን በፓራሹት ዲ 6 ዝላይ ስናደርግ አንድ ሰልጣኝ ተሰውቶ ነበር። አውሮፕላን ላይ ከተወጣ በኋላ ‹‹ወራጅ›› አለ ማለት አይቻልም፤ ሆዴን ቆረጠኝ አይቻልም። ምንም አይነት ሰበብ አይፈቀድም። ምናልባት በወቅቱ የነበረው ኳድ ስጋት ይኖርበት ይሆን እርግጠኛ አይደለሁም። ሰልጣኙ መሰዋቱን ያዩት የዝላይ አሰልጣኞች ወዲያው ፊታቸው ሲቀያየር አየሁ። ያን ጊዜ በጣም አስታውሰዋለሁ።”

የአየር ወለድ ከጠላት መሃል፤ ፊት፣ ወይም ኋላ የሚዘል እና ለወገኑ የሚደርስ ጦር ነው። አንድ ጦርነት ላይ አየር ወለድ ሲመጣ ድል ይጨምራል፤ አየር ወለድ ሲመጣ ታሪክን የሚቀይር እና ሀገርን የሚያስቀጥል ነው። አየር ወለድ ዝም ብሎ ለታይታ የሚዘል ብቻ አይደለም። እንደነ ብርጋዴል ጀነራል ተስፋዬ ሀብተማርያም ያሉ ሰዎችን የሚያፈራ ታላቅ ተቋም ነው። አየር ወለድ ‹‹ማርሽ ቀያሪ›› የሚባለውም ለዚሁ ነው።

አንድ የአየር ወለድ ከአውሮፕላን ከዘለለ በኋላ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን ይጓዛል። ትከሻው እስኪያብጥ ድረስ የሚሸከመው ሸክም አለ። ወገቡ እስኪጎብጥም ድረስ የሚይዘው ትጥቅ አለ። መሬት ላይ ከወረደ በኋላም ያለበትን የግጭት ህመም ተቋቁሞ፤ ፓራሹቱን ደብቆም ይሁን አቃጥሎ መድረስ ያለበት ቦታ ላይ መድረስ አለበት።

አየር ወለድ ከአውሮፕላን ላይ ሲጣል የሚጣለው የጠላት ወረዳ ላይ ነው። በዛ ውስጥ አለመብላት፤ መጠማት እና ብዙ ችግሮችን ተጋፍጦ የተላከበትን ሀገርን ከጠላት የመጠበቅ ተልዕኮ ማሳካት አለበት ። ይህም ዛሬ የምናያትን አንድ የሆነችዋን ኢትዮጵያ ቀና ለማድረግ የሚተጋ ባለሙያ ነው››

መቶ አለቃ አይዳ ትዳር አልመሰረተችም። ስለ ትዳር ያላትንም ሃሳብ እንዲህ ትገልጻለች። “ማግባት እና መውለድ ጥሩ ነገር ቢሆንም ሴቶች ወደ ትዳር ሲገቡ ብዙ ጊዜ እጅ ይሰጣሉ። ሰው የሚኖርበት አላማ ካለው ያንን መኖሩ ጥሩ ነው። ይህን ስንል ግን አግብተው ወልደው ሀገራቸውን ማስጠራት የቻሉ እንስቶች የሉም ማለት ግን አይደለም። ምሳሌ ብናነሳ እንደ አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ እና ደራርቱ ቱሉ ያሉ ድንቅ የሆኑ አትሌቶቻችን ካገቡ እና ከወለዱ በኋላም ለሀገራቸው ወርቅ ማምጣት ችለዋል። ነገር ግን ወደ ህይወታችን የሚመጣው አካል ወደ አላማችን ከመግፋት ይልቅ የሚያስቀረን ሊሆን አይገባም። ሆኖም ማግባት እና መውለድ አያስፈልግም ግን አልልም ፈጣሪ ሲፈቅድ የሚሆን ነገር ነው።”

በኢትዮጵያ ውስጥ በቀድሞ ሰራዊት ለበርካታ ጊዜ ከአየር ላይ የዘለሉ ቢኖሩም አሁን ባለው እውነታ ግን አይዳ ለ37ተኛ ጊዜ በመዝለል በሁለቱም ጾታዎች በአንደኝነት ደረጃ ላይ ትገኛለች። የመቶ አለቃዋ ለሴቶች



ያላትን ምክርም እንደዚህ ትለግሳለች ። “ አንድ ሰው ምድር ላይ ሲፈጠር ያለ ምክንያት አልተፈጠረም፤ የሚችለውን ጠጠር ለሀገሩ እንዲወረውር ነው ፤ ብዙ ጊዜ ባለንበት ሁኔታ ነገሮችን መለካት የለብንም። እኛ ያለንበት ሁኔታ ሊሆን ይችላል እንዳንሄድ የሚያደርገን። ለምሳሌ አግብተን ሊሆን ይችላል፤ ወልደንም ሊሆን ያችላል፤ ኤኮኖሚያዊ የሆኑ ችግሮች ሊኖሩብን ይችላሉ ፤ የስራ ሁኔታ ላይመቸን ይችላል፤ የማይመች ሁኔታ ውስጥም ልንሆን እንችላለን ነገር ግን ሰው ከስኬት ላይ የሚደርሰው በሚመች ሁኔታ ውስጥ ብቻ አልፎ በመሄድ አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

ለምሳሌ ማዕበል ሲነሳ አንዳንድ ነገሮች መያዝ ያለባቸውን ስፍራ እንዲይዙ ያደርጋል። ምናልባትም በህይወታችን ውስጥ የሚፈጠሩ ከፍታና ዝቅታዎች የኛን ነገር የሚያስተካክሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ሰዎች ፊታቸውን ጸጉራቸውን ጠብቀው ቢሮ ውስጥ መስራትን ሊወዱ ይችላሉ። አንዳንድ ነገሮች ምናልባትም የተፈቀዱት ለ10ሺ ሴቶች ሊሆን ይችላል።

አንዳንዶች ደግሞ በጦርነት ሜዳ ላይ ጀብድ እንዲሰሩ ፤ሌሎች ደግሞ ሲሚንቶ አቡክተው ግንባታ እንዲያሳምሩ ሊሆን ይችላል የተፈጠሩት ። ሁሉም ሰው የየራሱ መዳረሻ አለው። በሀገራችን እና በቤታችን ያልተስተካለ ነገር ካለ ያንን ለማስተካከል መስራት አለብን። የትኞቹንም ችግሮቻችን በሶስተኛ ወገን ብቻ የሚስተካከሉ ናቸው ብሎ መጠበቅም አያስፈልግም ።

ሴቶች በአድዋ ላይ የነበራቸው ተሳትፎ የሚዘነጋ ካለመሆኑም በላይ ድሉ እንዲመጣም የእቴጌ ጣይቱ ሚና የላቀ ነበር። እኔ ራሴን ከወንድ ጋር አላወዳድርም። ሴት ለወንድ ጥሩ አጋዥ መሆን ትችላለች ወንድም እንዲሁ ለሴት ጥሩ አጋዥ መሆን ይችላል በሚለው አምናለሁ።

አይዳ ስለኢትዮጵያ ያላት ስሜት ለየት ይላል። ውድ ሀገሯን የምትገልጻትም እንዲህ በማለት ነው።

‹‹ኢትዮጵያ በኔ የኑሮ ደረጃ ልክ አትታይም። ቢርበኝም ሀገሬ ናት ቢጠማኝም በውጣ ውረዷ ውስጥም ሀገሬ ናት። ምክንያቱም መሄጃ የለኝም፤ እሷም ያለኔ ማንም የላትም ።እኔም ያለሷ ማንም የለኝም። ብዙ ሰው ሀገሩን እንደሚወድ ይናገራል። ነገር ግን ድርጊት ከቃል ይበልጣልና የንግግራችንን ያህል ተግባርም ሊታከልበት ይገባል ።ኢትዮጵያ የቃልኪዳን ሃገር ናት። ኢትዮጵያ አምላክ አላት። ነገር ግን ለእኛ ለህዝቦቿ ተሰጥታናለች። ህዝቦቿ ናቸው የሚሰሯት። አንዳንዴ ምንም ባለማለት ሃገርን ማገዝ ይቻላል ፤ የምንናገረው ነገር ጥፋት ከሆነ ሌላውን የሚሰብር ከሆነ ፤ መከባበርን የማያመጣ ካሆነ ዝም ማለት ያስፈልጋል።

በሀገር ላይ በፍቅር፣ በመተሳሳብ አንድ ሆኖ ስለመዝለቅና አሁን ያለውን ገጽታ አይዳ ከሌሎች አገራት ወቅታዊ እውነታ በማነጻጸር እንዲህ ትገልጸዋለች። ‹‹ሁላችንም ከሚያጣሉን ታሪኮቻችን ይልቅ የሚያስማሙን ይበልጣሉና በፊት እንደልጅነታችን ተጣልተናል ብለን ተመልሰን እንደምንገናኝ ሁሉ አሁንም እንደዛ ማድረግ ይገባናል። ሶርያ ምንም አትሆንም ሶርያ ፈጣሪ አላት ኢራቅ ምንም አትሆንም ኢራቅ ፈጣሪ አላት ይባል ነበር ። ነገር ግን በአውሮፓውያን ደባ ዛሬ ላይ ህጻናት የት እንደሚሄዱ ግራ ገብቷቸዋል። ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያ ላይ ለሚሆነው ነገር ሃላፊነት አለበት። ሁሉም ለሰላም መስፈን ቆም ብሎ ማሰብ አለበት ብዬ አስባለሁ። ሰላም ከውስጥ ነው የሚፈልቀው ይህ ሰላም ነው ወደሌላ ሰው እና ማህበረሰብ የሚጋባው ። ሁላችንም የምንኮራባትን ሀገር ለማግኘት ዛሬን በመተሳሰብና በፍቅር ልንኖር ይገባል›› ።

ልዩ ዕትም

# ባለማዕረጓ - ሻምበል ማዕረግነሽ

አስቴር ኤልያስ

ከቀናት መካከል በአንዱ የሌሊት ተረኛ ጥበቃ ላይ ተሰማርታለች። ጊዜው ውድቅት ነው፤ ከባድ የሚሉት ዓይነት ዶፍ ዝናብ ይጥላል። ልጇን በጀርባዋ አዝላለች፤ ከፊት ለፊቷ ደግሞ መሳሪያዋን አንግባለች። ከጀርባዋ ያለው የነገው ትውልድ ትኩረቷን ይፈልጋል፤ ወዲህ ደግሞ በአደራ የተሰጣት የሀገር ጥበቃ ተልዕኮ አስተውሎትዋን ይሻል። የነገውን ሀገር ተረካቢ በዝናብ ኮት ሸፍናዋለች፤ የሀገር ጥበቃ ሥራዋ ስኬታማ ይሆን ዘንድ መሳሪያዋን አነጣጥራ ተጋፍጣለች። በዚህ መልኩ ያሳለፈችው የዕለቱ የሥራ ኃላፊነት ከባድ እንደነበር ታስታውሳለች - የልዩ ኃይሎች ማሰልጠኛ ማዕከል በደረጃ ሁለት ሆስፒታል ሎጂስቲክ ኃላፊ የሆነችው ሻምበል ማዕረግነሽ መንግሥቱ።

ሻምበሏ፣ ያንን ኃላፊነትም ሳታጓድል ለመወጣት ችላለች። ውትድርና እንደዚህ ነው ትላለች። ሴት የትኛውንም ተልዕኮ መወጣት ትችላለች፤ መውለድም ሆነ ማግባት ከተሰጣት ተልዕኮ ያግዳትም ስትል ትገልጻለች። የነገው ትውልድን በጀርባዋ አገሯዋ ደግሞ ፊትለፊ አድርጋ ሌቱን በስኬት አልፋዋለች።

ሻምበል ማዕረግነሽ መንግሥቱ፣ ተወልዳ ያደገችው በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን ነው። ከአንደኛ እስከ ሰባተኛ ያለውን ክፍል እዛው ያደገችበት አካባቢ የተማረች ሲሆን፣ የቀረውን ደግሞ በሻሸመኔ መሰናዶ ትምህርት ቤት አጠናቃለች። ጊዜው ከዛሬ 18 ዓመት በፊት በ1997 ዓ.ም አካባቢ ነው። ሰዎች የውትድርናውን ዘርፍ እንዲቀላቀሉ ቅስቀሳ ይደረግ ነበር። እርሷም ውትድርናውን የተቀላቀለችው በወቅቱ ይደረግ በነበረው ትልቅ የሆነ ቅስቀሳ ተነቃቅታ ነው።

ውትድርናን ለመቀላቀሏ ዋናው ምክንያት ገጠር አካባቢ የምታያቸው ሴት ፖሊሶች ተጠቃሽ ናቸው። በተለይ እያንዳንዷ የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ ያኮሯት ነበር። ሻምበል ማዕረግነሽ፣ በእነርሱ ሁኔታ ከመደነቅና ከመኩራት ባለፈ ግን ውትድርናን ለመቀላቀል ውሳኔ ላይ መድረሷን ትናገራለች።

በአንድ ወቅት ገና ልጅ እያለች ያደረገችው አንድ ነገር ትዝ ይላታል። ጊዜው ከሁለት አስርት ዓመት በፊት ነው። የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ነበረች። ወደ ትምህርት ቤት እየሄደች ነው። ድንገት አንዲት ፖሊስ ከፊቷ እየሄደች ታያታለች። በአቋሟ ዘለግ ያለች ያች ሴት ፖሊስ፣ ቀልቧን ትገዛዋለች፤

> “ሴት መምራት፣ ሀገር መጠበቅ፣ ማከም፣ ማስተማርም ሆነ ሌላ ሌላውንም ተግባር ማከናወን ትችላለች። በየትኛውም የሥራ መስክ ብትሰማራ ማከናወን ትችላለች።"



ፎቶ - ዳኜ አበራ

በውስጧም “እንደ እርሷ ነው መሆን የምፈልገው” እያለች ታሰላስል ያዘች። ሳታስበውም ትምህርት ቤቷን አልፋ ፖሊሷን ተከትላት ዘለቀች። ስትከተላት ቆይታ ወደቀልቧ መለስ ስትል ትምህርት ቤት የምትገባበበት ሰዓት ይረፍድባታል። የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ከመቃጠሉም በተጨማሪ በትምህርት ቤቱ ዩኒት መሪም ቅጣት ደርሶባታል። በቃ ይኸው ነው፤ የፖሊስነት ፍቅር። በወቅቱ ታደንቅ የነበረው ውትድርናን ሳይሆን ፖሊስነትን ነው። ይሁንና አሁን ላይ ራሷን ወታደር ሆና አግኝታዋለች።

ባለትዳርና የሁለት ልጆች እናት የሆነችው ሻምበል ማዕረግነሽ፣ ልክ መከላከያ ተቋም እንደመሆኑ ትዳር የሚባለውም በራሱ ራሱ ተቋም ነው ትላለች። የሰው ልጅ በዚህች ዓለም ላይ ሲኖር ራሱን ተክቶ ያልፋል፤ ለዚህ ደግሞ አንዱ መስመር ትዳር ነው። ለሀገሬ ትልቅ ክብር እንዳለኝ ሁሉ ለትዳሬ ደግሞ እንዲሁ ትልቅ ፍቅርና ክብር አለኝ ትላለች። ስለዚህም እናትነትና ውትድርና ትኩረቴን ሰጥቼ የማስተናግዳቸው ተግባሮቼ ናቸው ስትልም ትገልጻለች።

ውትድርና አልጋ በአልጋ አይደለም። ብዙ የማይመቹ ሁኔታዎች አሉ። በአሁኑ ወቅት ወደቢሾፍቱ ለሥራ ተጠርቼ ስመጣ የተገኘሁት ልጄን ይዤ ነው። የሁለት ዓመት ልጅ ይዤ ብመጣም ያስቀመጥኩት ሰው ዘንድ ነው። ስለዚህ ውትድርናውን የምናስኬደው በዚህ መልኩ ነው ትላለች። ልጅ፣ ትዳርና ሥራ አለ። እነዚህ በሕይወቴ ውስጥ የሚያልፉ ሂደቶች ናቸው። ሂደቶቹ ጠንካራ የሚያደርጉ እንጂ የሚያኮስሱ አይደሉም። መልፈስፈስ ደግሞ ውጤት አይሆንም ስትል ትናገራለች።

እኛ ሴቶች ሥራችንን ስንሰራ በብርታት ነው። እንደዚያ የሚሆነው ችግሮች ሳይኖሩ ቀርተው ሳይሆን በዛ ችግር መካከል እንዴት ጠንክሮ መውጣት እንዳለብን ስለምናውቅ ነው ትላለች። ከዚህ አንጻር ሁሉንም የምታስኬደው እንደየአመጣጡ ነው። ቤተሰብን መምራትም ሆነ ሥራ መሥራትንም ጎን ለጎን አጣጥሜ የማስኬዳቸው ናቸው ትላለች።

እርሷ የመጀመሪያውን ደረጃ ለአየር ወለድነት የሚያበቃውን የፓራሹት ዝላይ ከዘለለች በኋላ በዝላዩ አልገፋችበትም። በርግጥ ስድስት ጊዜ በፓራሹት ዘላለች። ይህንንም ሴት ማድረግ እንደምትችል አሳይታለች። ሴት የትኛውንም ፈተና ተጋፍጣ የአሸናፊነትን ድል መቀዳጀት እንደምትችልም በልበ ሙሉነት ታስረዳለች። ወደ እኛ ወደ አየር ወለዱ ዘርፍ ስንመጣ ደግሞ ዝላዩን ሴት ከወንድ እኩል መዝለል እንደምትችል አስመስክራለች። በጥቅሉ ወንድ የሠራውን ነገር ሴት መሥራት ትችላለች። ዋናው የሥነ ልቦና ዝግጅት ነው። ከዚያ ውጭ ምንም ዓይነት መስፈርት አይጠይቅም ስትል የሴትን ብርታት ታስረዳለች።።

እንደ ሻምበል ማዕረግነሽ አባባል፤ ሴት መምራት፣ ሀገር መጠበቅ፣ ማከም፣ ማስተማርም ሆነ ሌላ ሌላውንም ተግባር ማከናወን ትችላለች።። በየትኛውም የሥራ መስክ ብትሰማራ ማከናወን ትችላለች። እንዲያውም ሴቶች በሚያልፉበት ፈተና ውስጥ ወንዶች ቢገቡ እንደሴት ይወጡታል የሚል እምነት የላትም። ተፈጥሮ ራሱ ሴትን የሚያግዝ ነው ባይ ናት። ሴት በባህሪዋ አዕምሮዋ የሚያስበው አንድ ነገር ብቻ አይደለም። በአንዴ በርከት ያለ ነገር ማሰብም መሥራት ትችላለች። ስለዚህ ሴትነትን የምትወስደው በጥንካሬ ነው።

በሌላ በኩል ሴቶች በሰላም መስፈን ሂደት ውስጥ ያላቸው ሚና ቀላል አይደለም ትላለች። ለየትኛውም ነገር ሴቶች መሠረት ናቸው። ሌላው ቀርቶ በዚህ ሳምንት የተከበረው የዓድዋ ድል ላይ ሴት ትልቁን ሚና ተጫውታለች። ስለዚህ ሴት ሀገር ናት። ሴት እናት፣ እህት፣ የትዳር አጋር ናት። ሴት የሌለችበት ነገር ስኬታማነቱ አያስተማምንም ማለት ያስደፍራል። ሴት በአግባቡ የተካፈለችበት የትኛው መልካም የሆነ ሥራ የተሻለ መሆን የሚችል ነው የሚል እምነት አላት።

ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ለዚህች ሀገር የሚከፍሉት መስዋዕትነት እኩል ነው። ሁሉም ደግሞ የሚጠበቅበትን ድርሻ ከተወጣ ነገ የተሻለችዋን ኢትዮጵያ ማየት እንችላለን። ነገ የተሻለችዋን ኢትዮጵያ ለማየት ደግሞ ዛሬ ላይ መካበበር፣ አንድነትና መተሳሰብ የግድ ይለናል። ሁሉም ለብሔሩ ሳይሆን ለሀገሩ የሚያደላ መሆን አለበት። ብሔርተኝነት የሌለበት፣ የወንድማማችነት ጥላቻ የጠፋበት ኢትዮጵያን ማየት እናፍቃለሁ ብላለች።

# ከፖለቲከኛነት ወደ በጎ ተቋም መስራችነት

ዳግማዊት ግርማ

ወቅቱ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ነበር። የጊዜው ጠቅላይ ሚንስትር የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ ባለቤት ናቸው። ወይዘሮ ሙሉ ግርማይ ይባላሉ። ይህችን ምድር የተዋወቁት በቀድሞው አጠራር በወሎ ክፍለ ሀገር በሰቆጣ ከተማ ነው። በዚያው ስፍራ ጭቃ አቡክተው አፈር ፈጭተው አድገዋል። እናታቸው ወይዘሮ ማማዬ አሸብር ይባላሉ። ከአባታቸው ግርማይ ወልደትንሳኤ አብራክ ተከፍለዋል። የምድርን በጎ ጎን ቢያውቁትም ዓለም የከፋ ጎኗንም አስጎብኝታቸዋለች። በሕይወታቸው እልፍ የመከራ ሰልፎችን አልፈዋል።

ያለፉበት የሕይወት ውጣውረድ ለብዙዎች መማሪያ ይሆናል። የመሠረቱት የበጎ አድራጎት ድርጅትም ሰዎችን ደግፎ ይዟል። ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ጋር የሕይወት ልምዶቻቸውን አውግተዋል። ወደ ፖለቲካ ሕይወት አገባባቸውን ሲያወሱ፤ በ1973 ዓመተ ምህረት የቀድሞው ኢህዴን/ብአዴን የአሁኑ አዴፓ ፖለቲካ ድርጅት ተመሠረተ። ዓላማውም ደርግን ለመጣል ነበር። የትጥቅ ትግሉን በዋግ አካባቢ ሲጀምር እርሳቸውም ዕድሉ ደረሳቸው። እንደ ዘመኑ ወጣቶች የደርግን መንግሥት አምርረው ይጠሉ ነበር። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አቋርጠው በ1975 ዓመተ ምህረት የትጥቅ ትግሉን ተቀላቀሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ከጊዜ ወደ ጊዜ ጠነከረ። በ1983 ዓመተ ምህረት የደርግ መንግሥት ከስልጣን ተባረረ። ቀደም ሲል በአራት ድርጅቶች ጥምረት በተመሠረተው ኢህአዴግ፤ የበላይነት የሽግግር መንግሥት ተቋቋመ። ባለቤታቸው አቶ ታምራት ላይኔ የሽግግር መንግሥቱ ጠቅላይ ሚንስትር ነበሩ። እርሳቸው ደግሞ የአዲስ አበባ ሪጅን ጽሕፈት ቤት የኢህአዴግ ድርጅት



ወይዘሮ ሙሉ ግርማይ

ጉዳይ ኃላፊ ሆነው እየሰሩ ቆዩ።

ከዚህ በኋላ ሕይወት አልጋ በአልጋነቷ ቀረ። በ1989 ዓመተ ምህረት ባለቤታቸው ለእስር ተዳረጉ። በወይዘሮ ሙሉ አጠራር የባለቤታቸው መታሰሪያ ምክንያት “በሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም” የሚል የፖለቲካ ሴራ ነው። ኢህአዴግ አቶ ታምራትን ለእስር ዳረገ። ከባለቤታቸው መታሰር በኋላ ሕይወት ጨለማ ጎኗን አስጎበኘቻቸው። ወይዘሮ ሙሉ ‹‹በሕይወቴ ይገጥመኛል›› ብለው ከማይገምቱት ፈተና ላይ ወደቁ። የአቶ ታምራት ሚስት በመሆናቸው ብቻ የመከራ ፅዋን ተጎነጩ። ከሥራ ቦታቸው እና ከኃላፊነታቸው ያለ አንዳች ርህራሄ ተባረሩ።

ወይዘሮ ሙሉ በወቅቱ ምንም ዓይነት ገቢ አልነበራቸውም። እንደ ቤተሰብ ከሚያዩት ድርጅት መባረር ልባቸውን አቆሰለው። ያኔ የመጀመሪያ ልጃቸው አራት ዓመቱ ነበር። ሁለተኛ ልጃቸው የአንድ ወር ጨቅላ ሕፃን ነበረች። የአራስነት ወጉ እንደናፈቃቸው ቀረ። ሲኖሩበት ከነበረው የመንግሥት ቤትም ሳይቀር እንዲወጡ ተደረገ።

ከእለት ወደ እለት ማወከቦች ፣ የማፈን ሙከራዎች፣ ማስፈራሪያዎችና ልዩ ልዩ ፈተናዎችን ያሳልፉ ነበር። ይህ ችግር ሲጨምር በ1992 ሁለት ልጆቻቸውንና ታናሽ እህታቸውን ይዘው ወደ ኬንያ በግፍ ተሰደዱ። በጊዜው የደረሰባቸው መከራና መገፋትን ሲጎነጩ ቆዩ። በልጆች ላይ ሲሆን ደግሞ ከባድ ነው። እንደ እናት ራሳቸውን በድለው ለልጆቻቸው ኖሩ። ጥርሳቸውን በመንከስ ለወለዷቸው ሲሉ በረቱ።

ወይዘሮ ሙሉ በኬንያ አስቸጋሪ ሦስት ዓመታትን አሳለፉ። ከዚህ የስደት ቆይታ በኋላ በ1995 ሌላኛዋ የስደት መዳረሻቸው አሜሪካ ሆነች። በስደት እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው በኮሎራዶ ግዛት ዴንቨር ከተማ መኖር ጀመሩ። በአሜሪካን ሀገር ልጆቻቸውን ብቻቸውን ማሳደግ ቀጠሉ። በሀገሪቷ ያልሰሩት ሥራ የለም ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ብዙ ሥራዎችን ሰርተዋል። በጊዜውም የጋዝ ማደያ፣ የልብስ መሸጫ መደብርና የመሳሰሉት በእርሳቸው ከተሰሩት መሀል ናቸው። ሥራቸውን እየሰሩ ልጆቻቸውን ማሳደግና ማስተማር ቀጠሉ።

ለአስራ ሁለት ዓመታት ልጆቻቸውን ያለ አባት አሳደጉ። ባለቤታቸው አቶ ታምራት ላይኔ በ2000 ዓመተ ምህረት ከእስር ተፈቱ። ወደ አሜሪካን ሀገር በመሄድም ቤተሰቦቻቸውን ተቀላቀሉ። ባለቤታቸው አሜሪካ በመጡበት ወቅት ወይዘሮ ሙሉ ጋዝ ማደያ ተቀጥረው ይሰሩ እንደነበር ያስታውሳሉ። እነዚያን ረጅም ዓመታት ልጆቻቸውን ያለ አባት ማሳደጋቸው ብዙ አስተምሯቸዋል።

ሕይወት በመከራ ሞረድ ሞረደቻቸው። እርሳቸው ባለፉበት የመከራ ሕይወት ውስጥ ሌሎች እንዲያልፉ አልፈቅድም አሉ። ልጆችና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው እናቶችን በተለየ መንገድ ማሰብን ቻሉበት። በሚወዷቸውና የእኔ በሚሏቸው ሰዎች መጠላትና መገለል አሳዛኝ የሕይወት ክስተት መሆኑን ተገነዘቡ። እናም የተቸገረን ሰው ቀርቦ ማፅናናትና መደገፍ ምን ያህል የተቀደሰ ተግባር መሆኑን ከሕይወታቸው ተማሩ።

ከዚያም የእርሳቸው እና የቤተሰባቸው የመከራ ውጤት ፍሬ አፈራ። በ2005 ዓመተ ምህረት ቤተሰብ ጥየቃ ሲመጡ፤ በየመንገዱ የሚለምኑ እናቶችን ጎዳና የወጡ ሕፃናትን ተመለከቱ። ለችግር የተጋለጡ፤ ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆችና መበለቶችን የሚያግዝ ድርጅት በእርሳቸው ተከፈተ። በዚሁ ላይፍ ሴንተር ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሊመሰረት ቻለ። ላይፍ ሴንተር ኢትዮጵያ ሴቶችን የሚያበረታ የሚያፅናና ድርጅት ነው። ከራሳቸው ሕይወት በመነሳት የከበዳቸው ቀን እንደሚያልፍ ያሳዩዋቸዋል። በአቅምም በሞራልም ይደግፏቸዋል።

ድርጅቱ መቀመጫውን በተለያዩ ሥፍራዎች አድርጓል። በአዲስ አበባ ፣ በአማራ ክልል ዋግህምራ ሰቆጣ ላይ ከትሟል። ከ400 በላይ መበለቶችንና ከ280 ወላጆቻቸውን ያጡ ለችግር የተጋለጡ ልጆችን በመርዳት ላይ ነው። ይሄኛው ሕይወት ለወይዘሮ ሙሉ ተስማምቷቸዋል። በሚረዷቸው ዜጎች ዓይን ላይ የተኳለ ፈገግታ ታድለዋል። ልባቸው አርፏል።

በመልዕክታቸውም ሰዎች ካገለገሉበት ድርጅት ሲገለሉ ቤተሰብ ባይጎዳ ብለዋል። ከዚህም በላይ ሰው ካለፈበት ችግር ሊማር ይገባዋል ይላሉ። ሰዎች በራሳቸው ልጅ ማድረግ የማይፈልጉትን በሌላው ልጅ ባያደርግ የሚል አደራቸውን ሰጥተዋል።

# የባቡር ዘዋሪዋ
# አንቀጸ ብርሃን ግርማ

**እፀገነት አክሊሉ**



ሴቶች ይችላሉ ብዬ መነሳት አልፈልግም ፤ ምክንያቱም ከትላንት እስከ ዛሬ በተለያዩ መስኮች ችለው፤ ችለው ብቻም አይደለም በልጠው አሳይተውናል። ሴቶች እድል ያላገኙባቸው የተለያዩ ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ቢኖሩም፤ ዛሬም ድረስ ግን በተለይም በጥረታቸው ታግለው የወጡ ሴቶች አለምን ጉድ የሚያሰኙ ተግባራትን እየፈጸሙ አይተናል ።

ለወንዶች ብቻ ተለይተው ሴቷ አትችልም ተብለው የኖሩ ስራዎችን በጥረታቸውና በብቃታቸው ተወጥተውት የሴት ተምሳሌት ጀግና የተባሉም ብዙ ናቸው። እኛ እንደ ባህልም ይሁን አመለካከት ሴቶችን በውስን ነገሮች ላይ ገድበን አየናቸው እንጂ፤ ከጥንት ጀምሮ በፖለቲካዊ አመራር ብቃታቸው በሃገር መሪነታቸው ከወንዶች የበለጠ ውሳኔ ሲያሳልፉ የነበሩ እንደ ጣይቱ ብጡል አይነት ጀግና ሴት ያለን ህዝቦች ነን።

ከዛም በኋላ ቢሆን በተለያዩ አጋጣሚዎች ብቅ ያሉ ሴቶች በፖለቲካው፣ በማህበራዊው፣ በኢኮኖሚውና በዲፕሎማሲያዊው ዘርፍ ግንባር ቀደም ሆነው በመውጣት ለሃገራቸው ቀላል የማይባል አበርክቶ በማትረፍ ታሪክ ሲዘክራቸው የሚኖሩ ሴቶቻችንም ቁጥር ብዙ ነው።

ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ግን የባሎቻቸው የልጆቻቸው ደጀን በመሆን የእነሱን ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ ስኬታማ እንዲሆኑ ሌት ተቀን የሚለፉ ግን ደግሞ ልፋታቸው ያልተነገረላቸው በየቤቱ ያሉ አያሌ ጀግና ሴቶች ያለን ነን።ባል በተሰማራበት መስክ ውጤታማ እንዲሆን ሰርቶ ቤተሰቡን አገሩን ይጠቅም ዘንድ የልጆቿን ሙሉ ሀላፊነት ወስደው ደፋ ቀና የሚሉ እናቶች በተቃራኒው ባላቸውን በተለያየ ምክንያት አጥተው፤ ልጆቻቸውን ዝቅ ብለው ወርደው ሰርተው የሰው ፊት ገርፏቸው ዶክተርና ኢንጂነር ያደረጉ ለሃገራቸው መልካም ዜጋን ያፈሩ ሴቶችም ቤት ይቁጠራቸው።

እንደ አለመታደል ሆኖ ጀግኖቻችንን በተለይም ሴቶችን የማክበርና የማወደስ አቅማችን ውስን ሆኖ ነው እንጂ፤ ሲነገርላቸው ውሎ ሲነገርላቸው ቢያድር ከስራቸው አንጻር የሚያንስባቸው ብዙ ሴቶች አሉ።ህብረተሰቡ ውስጥ ያለው ጎታች አስተሳሰብ ከህልማቸው ያላስቀራቸው በራሳቸው ጥረትና ስራ ዛሬ ላይ ከፍ ብለው ዓለም ወዶ ሳይሆን ተገዶ ሊመሰክርላቸው የቻለ ሴቶችንም ማውሳት ይቻላል ።

በየዓመቱ የሚከበረው ዓለም አቀፉ የሴቶች ቀንም (ማርች 8) ዋናው አላማው በተለይም ጓዳ ተደብቀው ያሉ ሴቶችን ማውጣት፤ አደባባይ የወጡትንም ለበለጠ ስኬት ማበረታታት እንዴት አድርጌ ይሆንልኛል ብለው ወደኋላ የሚሉትንም ተምሳሌት የሆኑትን እያሳዩ ማውጣት ነው። እኛም የዘንድሮውን ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በማስመልከት በተለይም ለሴቶች አይደፈሬ የሆነውን እስከ አሁንም በብቸኝነት በአንዲት ሴት ብቻ እየተሰራ ያለውን የባቡር አሽከርካሪነት ሙያ ልንቃኝ ወደናል ።

ወይዘሮ አንቀጸብርሃን ግርማ ትባላለች።አንቀጸ በኢትዮ ጅቡቲ የምድር ባቡር የባቡር አሽከርካሪ ናት። የትውልድ ቦታዋ አርሲ ኮፈሌ በሚባል ቦታ ሲሆን ያደገችው ደግሞ አሰላ ከተማ ነው።የአስተማሪ ልጅ የሆነችው አንቀጸ ለቤተሰቦቿ ሶስተኛ ልጅ ናት።የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም የመሰናዶ ትምህርቷን ባደገችበት አሰላ ከተማ ስለመማሯም ትናገራለች።

“........በትምህርቴ በጣም ጎበዝ የምባል ባልሆንም ለራሴ ግን የማንስ አልነበርኩም።ቤተሰቦቼ እናቴና አባቴ ሁለቱም መምህራን ስለነበሩ ለትምህርት ትኩረት ይሰጣሉ ፤ እኛም ትኩረት እንድንሰጥ ያበረታቱን ይደግፉን ነበር። በዚህም ደህና ተማሪ ነበርኩ” በማለት ሁኔታውን ታስታውሳለች።

ወይዘሮ አንቀጸ 12ተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከተፈተነች በኋላ በቀን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ገብቶ ለመማር የሚያስችላት ነጥብ ባለማምጣቷ በማታው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለመማር በቀጥታ ያመራችው ወደ አዳማ ዩኒቨርሲቲ ነበር ፤ በዛም የኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ትምህርቷን ለመማር ተመዘገበች ።

“.......በወቅቱ የ12ተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤት ላይመጣልኝ ይችላል የሚል ግምት አልነበረኝም ፤ የሚገርመው ነገር ከመግቢያ ነጥቡ ያነሰኩት በአንዲት ነጥብ ነበር፤ በወቅቱ በጣም ብናደድም በቀጣይ ምን ማድረግ አለብኝ የሚለውን ግን በደንብ አሰብኩበት። በዚህም ውጤት ስላልመጣልኝ ብዬ ከመናደድ በማለት አዳማ ዩኒቨርሲቲ በማታው ክፍለ ጊዜ ተመዝግቤ የኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ትምህርቴን ቀጠልኩ “ ትላለች።

አንቀጸ እንደዚህ ወስና ትምህርቷን በማታው ክፍለ ጊዜ ትቀጥል እንጂ ትምህርቱን በቀን ፕሮግራም እንደመማር አስደሳች አልሆነላትም።እንደውም የመጀመሪያ አመት ትምህርቷን ለጊዜ ማሳለፊያ ሁሉ የምትማር አድርጋ በመውሰድ ብዙም ትኩረት ሳትሰጠው ማለፏን ትናገራለች።ነገር ግን ዋል አደር እያለች ትምህርቱንም ስታየው እየወደደችው ከዛም የክፍለ ጊዜ ቀንና ማታ መሆን በትምህርቱ ላይ ለወጥ እንደማያመጣ ተግቶ መስራት ከተቻለ በሁሉም ወደስኬት እንደሚወስድ ስለገባት አንደኛ አመት ላይ ላላ አድርጋ የተማረችውን ትምህርት በሁለተኛው አመት አጥብቃ ያዘችው። በዚህም ውጤቷ ሲሻሻል በጣም አስደሳች ሲሆን መመልከቷ ሞራሏን ገነባላት።በጣም ደስም ስላላት እንደውም የቀኑን ክፍለ ጊዜዬን በመቀመጥ ማሳለፍ የለብኝም ሌላ ነገር ደግሞ ላስብ ልማር በማለት ተነሳሳች።

“........እንዳልኩሽ የማታ መማር ብዙም ምቾት አልሰጠኝም ነበር። የጊዜ ማሳለፊያ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር ፤ ነገር ግን በመካከል የሃሳብ ለውጥ አመጣሁ። ለትምህርቴም ከፍ ያለ ትኩረትን መስጠት ጀመርኩ፤ በዚህም ውጤቴ ሲሻሻል አየሁ ይህ ከሆነማ በማለት ያለትምህርት የማሳልፈውን የቀኑን ክፍለ ጊዜ ለምን አልጠቀምበትም ብዬ አዳማ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በመሄድ የኤሌክትሮኒክስ ትምህርት ለመማር ተመዘገብኩ” ትላለች ።

ከሁለተኛ አመት ትምህርቷ በኋላ ሙሉ ትኩረቷን በትምህርቷ ላይ ያደረገችው አንቀጸ፤ ሁለቱ ትምህርቶች ደግሞ እየተመጋገቡላት አንዱ አንዱን እየደገፈላት ውጤቷም ያማረ የሰመረ እየሆነ ሄደ።አንቀጸ በጣም በሞራል ስለምትማር እንዲሁም አንዱ ትምህርት ከአንዱ ተደጋጋፊ በመሆኑ ውጤቷ ላቅ ያለ ነበር።የዲግሪ ትምህረቷን ሳትጨርስ የቴክኒክና ሙያ ትምህትርቱ አለቀና ተመረቀች።ከአንድ አመት በኋላ ደግሞ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን አጠናቃ ተመረቀች።

“........የመረጥኳቸው ትምህርቶች ተመጋጋቢ መሆናቸው በጣም ጠቅሞኛል፤ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ደግሞ አብዛኛውን ጽንሰ ሃሳቡን መማር በመሆኑና በቴክኒክና ሙያው ደግሞ ከጽንሰ ሃሳብ ባሻገር ተግባራዊ ልምምድንም ማጠቃለሉ ለውጤታማነቴ በጣም አግዞኛል”ትላለች።

አንቀጸ ኢትዮ ጅቡቲ የምድር ባቡርን የተቀላቀለችው የማታውን የዲግሪ ትምህርቷን ሳታጠናቅቀ በቴክኒክና ሙያ የትምህርት ማስረጃዋ ነበር።” ......ዲግሪውን እየተማርኩ ቴክኒክና ሙያ ትምህርቴን አጠናቅቄ ባለሁበት ወቅት ኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር የስራ ማስታወቂያ አወጣ። እኔም ስራ ስለምፈልግና ረዳት የባቡር ሹፌር የሚለውን ማስታወቂያ አሟላ ስለነበር ስራውን ተመዘገብኩ” ትላለች።

ረዳት ባቡር ሹፌርነት ስራ ተመዘገብኩ እንጂ ከዛ በፊት ባቡር የሚባለውን ነገር እንኳን አላውቀውም ነበር፤ የምትለው አንቀጸ ነገር ግን ፈርቶ ወደኋላ ከማለት ይልቅ ልየውና ከሆነ ይሆናል ካልሆነ ይቀራል ብላ ስለመመዝገቧ ትናገራለች። እንዳሰበችውም አንቀጸ ድርጅቱ የትምህርት ዝግጅቷን በማየት ለፈተና ጠራት ፈተናውን አልፋም ድርጅቱን ተቀላቀለች።

“.......ፈተናውን እንዳለፍኩ ለስድስት ወር ስልጠና አለ ተብሎ፤ ቻይናዎቹ የሚያሽከረክሩት ባቡር ረዳት በመሆን ለመሰልጠን ስሄድ ምድር ባቡር ግቢን ለመጀመሪያ ጊዜም ዓየሁት ፤ በወቅቱም የተሰማኝ ስሜት ከባቡሩ ትልቅነት አንጻር ይከብድ ይሆን ብዬ ብፈራም እሞክረዋለሁ በማለት ራሴን አበረታትቼ ወደስልጠናው ገባሁ” ትላለች።

ስልጠናው ልክ እንደትምህርት ቤት ንድፈ ሃሳብን ከልምምድ ጋር ያጣመረ ነበር። አዳዲስ መጽሃፎች አጋዥ የሆኑ ሞጁሎች ተሰጥተውን ተማርን የምትለው አንቀጸ፤ ይህ መሆኑ ደግሞ ባቡሩን በአግባቡ እንድትረዳው ከማድረጉም በላይ የባቡሩ ኤሌክትሪካልነት ከትምህርቴም ጋር ስለሚሄድ ብዙም የከበደ ነገር አልሆነብኝም በማለት ሁኔታውን ታብራራለች።

ሶስቱን ወር የንድፈ ሃሳብ ትምህርት በክፍል ከሰለጠንን በኋላ በስራ ላይ ልምምድ ለማድረግ ወጣን፤ ጅቡቲም ሄድን ብቻ በጣም አሪፍ ጊዜን በማሳለፍ ስራውን እንደተቀላቀለችውም ታብራራለች። ማስታወቂያው ወጥቶ መጀመሪያ ቅጥር ሲፈጸም ከአንቀጸ ጋር ስድስት ያህል ሴቶች እንደነበሩ በማስታወስ፤ ተጠርተን ስራውን ስንጀምር ግን እኔ ብቻ ነበርኩ የቀረሁት ትላለች። ሌሎቹ ሴቶች በመፍራትም ይሁን ሌሎች ምክንያቶች ብቻ ስራውን እንዳልተቀላቀሉትም ትናገራለች።

አንቀጸና ሌሎች ወንድ ጓደኞቿ ለምድር ባቡር የመጀመሪያ ቅጥሮች ቢሆኑም በቀጣይ ግን ተቋሙ ተከታታይ ማስታወቂያዎች ያወጣ ቢሆንም ሴት አመልካቾችን ግን ማግኘት አለመቻሉን ትናገራለች። ይህ የሆነው ደግሞ ምንልባትም ስራው አገር አቋራጭ በመሆኑ ሴቶች መድፈር አቅቷቸው፤ አልያም የትዳር ጓደኛና የቤተሰብ ማበረታቻ አንሷቸው ሊሆን እንደሚችልም ትገምታለች። ይህም ቢሆን ግን አንቀጸ እዛው እንደራሷ የባቡር ሹፌር ከሆነው የትዳር አጋሯ ጋር በመሆን ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ብዙ ማይሎችን አቋርጦ የሚሄደውን ባቡር በብቃት እየዘወረችው ትገኛለች።

“.......ባቡሩ መጠኑ በጣም ትልቅ ነው። የሚጎትተው እቃም በተመሳሳይ ትልቅ ነው፤ በሃገራችን በማህበረሰባችን የተለመደው ደግሞ ትልልቅ ነገሮችን ማድረግ የሚችሉት ወንዶች ብቻ እንደሆኑ ነው፤ ይህ አስተሳሰብ ደግሞ ሴቶቹም ላይ ይንጸባረቃል። ከዚህ አንጻር ስራውን እስከ አሁን መድፈር አልቻሉም” ትላለች።

በመሰረቱ ትላለች አንቀጸ፤ ስራውን እንደጀመርኩ አካባቢ ምንም ዓይነት ሴት በዙሪያዬ ሳጣ የማይሆን ቦታ ላይ የተገኘሁ መስሎኝ ነበር። ነገር ግን ቤተሰቦቼ ችግር የለውም ሞክሪውና ካልቻልሽ ትወጪያለሽ በማለት ከፍተኛ ድጋፍን ያደርጉልኝ ነበር። በእነሱ ብርታት ጀመርኩት ሳየውም የሚያስፈራ አልነበረም እንደውም ደስ የሚል ሆኖ አገኘሁት” ትላለች።

ላለፉት አምስት ዓመታት ባቡርን በብቃት ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ከጅቡቲ ደግሞ አዲስ አበባ ስታመላልስ ብዙ አስፈሪ ገጠመኞች ገጥመዋት እንደሚያውቁ የምትናገረው አንቀጸ፤ በተለይም ባቡር ሲበላሽ የመብራት መቆራረጥ ሲያጋጥም አጉል ቦታ ምናልብትም በረሃ ላይ ሁሉ መዋል ማደር ስለሚያጋጥም እሱ ፈታኝ መሆኑን ታብራራለች። እንደጀመሩ አካባቢ መብራት ጠፍቶ እልም ያለ በረሃ ላይ ለአንድ ሳምንት ያህል መቆየቷን ታስታውሳለች። ከዛ ውጪ ግን ቀኑን ሙሉ ወይም ለአንድና ለሁለት ቀን ጫካ ውስጥ መቆየት የተለመደ ነው ትላለች።

ባቡር የሚሄደው ከከተማ ውጪ ነው። ድንበር ተሻግሮ ሰው አገር ስገባም ቋንቋው ምግቡ የተለየ ነው፤ በመንገዱ ላይም ብዙ የሚያጋጥሙ ነገሮች አሉ። አሁን ደግሞ ሰዎችና ከብት ወደባቡር መንገድ እየገቡ ስለሚያስቸግሩ ለአደጋ ላለመጋለጥ በትኩረት መስራትን ይፈልጋል፤ በጠቅላላው ግን ባቡር ለመንዳት መሪውን ስይዝ ጀምሮ ሃሳቤን ሰብስቤ ስራዬ ላይ ትኩረት አድርጌ ነው የምሄደው” ስትል ትናገራለች ። በዚህም እስከ አሁን ድረስ ምንም አይነት አደጋ አጋጥሟት እንደማያውቅም ታብራራለች።

“......ባቡር ከተማን ሳይሆን ገጠሩን ከፍሎ የሚያልፍ ከመሆኑ አንፃር በርካታ የማያቸው ነገሮች አሉ፤ በተለይም ሴት ህጻናት በእረኝነት ትልልቆቹ ደግሞ ከአንዱ ቦታ ወደሌላው ልጆቻቸው ተሸክመው የሚሸጡትን ወይም የሚገዙትን እቃ አዝለው ሲሄዱ አያለሁ፤ ይህ በጣም ልቤን ይነካኛል። ልቤን መንካት ብቻ ሳይሆን እነዚህ ሴቶች እንደ ከተማ ሴቶች እድል ቢያገኙ ቢማሩ ለአገር ምን ሊያበረክቱ ይችላሉ የሚለውንም አስባለሁ። በተጨማሪም ከተማ ውስጥ ያለን ሴቶች ከትዳር አጋሮቻችን ጋር ልጅ በማሳደግም ሆነ ሌሎች ሃላፊነቶቻችንን በመወጣቱ በኩል ምን ማድረግ እንዳለብን እናውቃለን እንረዳዳለን። እነዛም ሴቶች ይህንን እድል ቢያገኙ ብዬ እመኛለሁ።” በማለት በስራው ላይ ስትሆን ስለ ሴቶች የምታስበውንና የሚሰማትን ትናገራለች።

ሴቶች አትችሉም ስንባል ኖረናል ነገር ግን እንደምንችል ልናሳይ የሚገባን ራሳችን ነን፤ አሁን ላይ በመጠኑም ቢሆን የተሻሻለ ነገር ያለ ቢመስለም ግን ደግሞ ሴቶች መስራትም መዋልም ያለባቸው ቢሮ ነው የሚለው ነገር አልተቀረፈ ። ስለዚህ ይህንን ነገር ማሻሻል ወንዶች የሚሰሩትን መስራት እንደምንችል ማሳያት አለብን። ሴቶችም ሴት ወንድ የሚለው ነገር ጾታ መለያ እንጂ የአቅም መለኪያ አለመሆኑን በመረዳት በተለያዩ ዘርፎች መሰማራትና መሞከር ተገቢም አስፈላጊም ነው ትላለች።

በመጨረሻም በሌላ በኩልም ሴቶች ፍላጎቱም አቅሙም ቢኖራቸውም፤ ያንን የሚያወጡበት እድል ካላገኙ ውጤቱ ምንም ነውና ተቋማት በሚያወጧቸው የስራ መስኮች ላይ የሴቶችን ተሳትፎ የእውነት በሆነ መልኩ ማጉላት፣ ማሳየት፣ እድል መፍጠር አለባቸው ስትል ሃሳቧን አጠቃላለች።

ልዩ ዕትም

# ሻሎ - እጀ ብረቷ ገበሬ

መልካምሥራ አፈወርቅ



ሻሎ ጠንካራ እጆች በየጊዜው የእንጨት ቆጣቢ ምድጃዎችን እያመረቱ ያወጣሉ። በእጆቿ ጥበብ የምታዘጋጃቸው የቁም ምድጃዎች በበርካቶች ዘንድ የሚፈለጉ፣ የሚመረጡ ሆነው ዓመታትን ዘልቀዋል።

አርሲ ምድር ፤ ‹‹አድአ ሻቄ›› ቀበሌ። የለም መሬት፣ ማሳያ የአረንጓዴ ምርት መገለጫ ነው። አካባቢው ሁሌም የሰጡትን አይነሳም። ከዓመት ዓመት ምርት ያሳፍሳል። ኩንታል እህል ያስከምራል። በዚህ መንደር ሕይወታቸው ግብርና የሆነ ብርቱዎች ከእርሻ አርፍደው ይውላሉ።

የአድአ ሻቂ ሰዎች ሕይወታቸው በግብርና ተመስርቷል። ማልደው ሲወጡ መገኛቸው ከማሳው ፣ ከመስኩ ነው። እንዲያም ሆኖ ልጆቻቸው ቢማሩ፣ ቀለም ቢቆጥሩ ይወዳሉ። ልጆቹ መሬት አርሰው፣ ምርት አፍሰው ብቻ እንዲኖሩ አይሹም። እነሱም እንደሌሎች ዕውቀት ቀስመው ወግ ማዕረግ ቢያዩ፣ ካሰቡት ቢደርሱ ደስታቸው ነው።

**ሻሉ የሻቂ ፍሬ...**

ልጅቷ ገና ስትወለድ እንደብርሃን መድመቋን፣ እንደ ጸሀይ መፍካቷን ያዩ ወላጆቿ ‹‹ሻሎ›› ሊሏት አልዘገዩም። ሻሎ የፈካ፣ የደመቀ ብርሃን እንደ ማለት ነው። የሻቂዋ ፍሬ ሻሎ ዓለሙ በዚህ መንደር ልጅነቷ ሲያብብ ግብሯም እንደ መልኳ የፈካ፣ የደመቀ ሆነ። በምግባሯ የሚወዷት፣ የሚያደንቋት በረከቱ። ስለ ሻሎ ወላጆቿ ይሳሳሉ። በሩቅ የሚያውቋት ደግሞ ውበቷን አይተው ያደንቃሉ።

የገጠሯ ጉብል ሻሎ መልካም ቆንጆ ናት። ከግብርናው ስትውል ክንደ ብርቱ፣ ከቀለም ስትገኝ አዕምሮ ብሩህ ወጣት። ሻሎ ስንፍና ይሉት አያውቃትም። ድካም አይጎበኛትም። ከጠዋት እስከ ማታ በእርሻና ትምህርት ተጠምዳ ትውላለች። ቤት ስትደርስ ደግሞ ጉልበቷ አይደክምም። እንደሴትነቷ ከእናቷን ማጀት ገብታ ጎንበስ ቀና ትላለች።

ልጅ ብትሆንም ውጥኗ የበዛ ፣ ሃሳቧ የሰፋ ነው። ባላት ትርፍ ጊዜ ከውሃ ልማት ተቀጥራ የቦኖ ውሃ ታስቀዳለች። የዛኔ የሚከፈላት ደሞዝ አንድ መቶ አምስት ብር ነበር። ሻሎ ብሩ ‹‹አነሰኝ›› ሳትል በቆጠበችው ገንዘብ ሁለት ጥማድ መሬት ገዝታ ታሳርሳለች። የሚገኘው ምርት የገቢ ምንጯ፣ የቤቷ መደጎሚያ ነው።

ሻሎ ስምንተኛ ክፍል እንደገባች የአንድ ሰው ዓይን አረፈባት። ወዶ የቀረባትን፣ ቀርቦ ያዋያትን ሰው አልገፋችውም፣ አልጠላችውም። የእሷም ልብ እንደሱ፣ ቢወድ ቢፈቅደው በይሁንታ ቀረበችው። ውሎ አድሮ ስሜት ዓላማቸው አንድ ሆነ። ለቁም ነገር ያሰባት እጮኛዋ ሽማግሌ ልኮ ጋብቻ ጠየቀ። ቤቶቿ ለብርቱው ገበሬ ልጃቸውን ‹‹እምቢኝ ›› አላሉም። ወደውና ፈቅደው መርቀው ሰጡት።

**ሙሽሪት ልመዷ ...**

የሻሎ ባለቤት ከቀለም የተዋደደ፣ ከዕውቀት የቀረበ ነው። ቀድሞ ወታደር ነበርና በብዙ ፈተናዎች ተመላልሷል። ይህ እውነት ከማንነቱ ተዳምሮ ፣ መልካም አባወራ ሊሆን አስችሎታል። ለግማሽ አካሉ ደግ ባለቤት ነው። የሚያውቁትን ሁሉ ያከብራል። የቀረቡትን ይወዳል። ሚስቱ ሻሎ የዋህነቱን፣ አርቆ አሳቢነቱን ትወድለታለች። ለእሷ ሁሌም አክባሪ ባሏ ነው። በፍቅር በአክብሮት ማደርን አስተምሯታል።

በእነሱ ጎጆ ፍቅርና ሰላም ሰፍኗል። ባሏ እንደ ወንድም መካር፣ እንደ አባት ተቆጪ፣ እንደ ባል አባወራ ነው። ከእሱ ለምዳ ሕይወት ለመጋራት፣ ኑሮ ለመምራት አልከበዳትም። አስተዋዩ ባሏ ትዳሩን በክብር ፣ ቤቱን በፍቅር ይይዛል። በእነሱ ጎጆ የሴት፣ የወንድ ይሉት ሥራ የለም።

እሷ እንጀራ ብትጋግር ወጡ የእሱ ድርሻ ነው። ልብስ ብታጥብ ቡና ማፍላት ግዴታው ይሆናል። ጥንዶቹ ሁሌም በፍቅር ያድራሉ። በመስማማት ይኖራሉ። ሁለቱም ስለነገው የወጠኑት ህልም አንድ አይነት ነው። በላብ በወዛቸው ድካም ነገን ትጉህ ገበሬ መሆን ዓላማቸው ሆኗል።

**ትምህርት ፣ ልጆች፣ ሥራ**

ሻሌ ተማሪ ሳለች የያዘችው ጥማድ ከአባወራዋ መሬት ተዳምሮ ሥራ ከጀመረ ሰንብቷል። ብርቱዎቹ ባልና ሚስት ዛሬም ቋንቋቸው ፍቅር ነው። ‹‹አንተ ትብስ አንቺ›› መባባሉ ብርቃቸው አይደለም። በቤታቸው ሶስት ልጆች ከተወለዱ በኋላ አባወራው ሚስቱ ትምህርት እንድትቀጥል ፈልጓል። ይህ ደግነት ብርታት የሆናት ሻሌ ከዓመታት በኋላ ደብተር ይዛ ትምህርት ቤት መዋል ጀምራለች።

ሻሌ አሁንም የቦኖ ማስቀዳት ሥራዋን ላይ ነች። የምታገኘው ጥቂት ገቢ ለጎጆዋ ይደጉማል። መማሯን ያስተዋሉ አሰሪዎቿ ግን ዓላማዋን አልወደዱም። ትምህርቷን እንድታቆም ማስገደድ ይዘዋል። ጥሩ አሳቢው ባሏ ዛሬም ከጎኗ ነው። ጅምሯን እንድትለቅ፣ ሥራዋን እንድትተው አይሻም።

ይህ እውነት አማራጮች አሰፋ። በግል ተመዝግባ ለፈተናው እንድትዘጋጅ ሆነ። ሻሌ በወጉ አጥንታ ያሰበችውን ፈጸመች። ሚኒስትሪን በጥሩ ውጤት አልፋ ለዘጠነኛ ክፍል በቃች። ይህ ውጤት የእሷ ብቻ አይደለም። የበጎ አሳቢው ባለቤቷ ድርሻ ጭምር እንጂ።

ሻሎ ዘጠነኛን ክፍል ከመጀመሯ አራተኛውን ልጅ ነብሰጡር መሆኗን አወቀች። ትምህርቱ ሲገፋ ፈተናው ሲዳረስ ድካሙን አልቻለችም። የቤት ኃላፊነት ልጆች ከማሳደግ ጋር ይከብዳት ያዘ። ይህኔ ባልና ሚስት ተቀምጠው መከሩ። ሁሉን ትታ ወደፊት በሚያስቡት እቅዳቸው ላይ ብቻ እንድታተኩር ተስማሙ። የታሰበው ሁሉ በጊዜው ተከወነ። እጅን በአፍ የሚያስጭን፣ የላብ የድካም ፍሬ ዕውን መሆን ያዘ።

**ከዓመታት በኋላ...**

እነሆ ! ሂጦሳ ወረዳ ‹‹ሻቂ ሸረራ›› ቀበሌ ላይ ነኝ። ከወይዘሮ ሻሌ ወብ ጊቢ ተገኝቻለሁ። ሥፍራው ገጠር ነውና ነፋሻው አየር ይማርካል። ፊት ለፊት የቆመው ግዙፍ ቪላ ዘመናዊ የሚባል ነውና ለጊቢው ግርማ ሞገስ ሆኖታል። የማየው እውነት ለአፍታ በእንግድነት የሚያስቀምጠኝ አልሆነም። ሰፊውን አጸድ ተዘዋውሬ ከማየቴ በአድናቆት መደመም ፣ መገረም ጀምሪያለሁ።

ሻሌ ጠንካራዋ ወይዘሮ፣ ክንደ ብርቱዋ ገበሬ። ዛሬም በሥራ ላይ ነች። ለአፍታ እረፍት ይሉት የላትም። መባተል ከጀመረች ቀን ሌቱ አይበቃትም። ከጊቢው ተዘዋውሬ ሁሉን ባየሁ ጊዜ ድካም ልፋቷ ፍሬ መያዙ ገባኝ። ከሰፊው ቦታ ላይ አንዳች ቁራሽ መሬት አልባከነም። እያንዳንዱ ሥፍራ የተሰጠው የሥራ ድርሻ በግልጽ ይስተዋላል።

ማንም አጋጣሚ አግኝቶ ወደዚህ ሥፍራ ቢገባ ለአፍንጫው የሚደርሰውን መልካም መአዛ እንደዋዛ ችላ ማለት አይቻለውም። ውሰጡ ፍጹም በሆነ የአዕምሮ እርካታ ይሞላል። እግሮቹ ከአረንጓዴው የአትክልክት ቦታ ላይ ቆመዋል።

በአቦአካዶ ፣ ሙዝና ማንጎ፣ በቡና አፕልና የንብ ቀፎ የተሞላው ጊቢ ለዓይን ይማርካል። ዙሪያውን የታጀበው የጤናአዳም፣ የበሶብላ፣ አዝመሪኖና ቃሪያ ሽታ አሁንም እየተከተለኝ ነው። በቀላሉ የማይገለጽ እርካታ ተሰማኝ። በየአፍታው ደስታና አድናቆት ይፈራረቁብኝ ያዙ። የማየው በረከት ሁሉ አስደመመኝ። በውስጤ ይህን ላደረጉ ጠንካራ እጆች አድናቆትና ምስጋና አቀረብኩ። ‹‹ሻሎ አንቺ! ድንቅ ሴት ጉልበትሽ አይድከም፣ እጆችሽ አይዛሉ››።

**የሻሉ በረከቶች...**

ሻሎ ክንደ ብርቱዋ ገበሬ ከሌላት ጊዜ፣ ከምትሳሳለት ቀን ደቂቃዎችን ተበድራ የልፋት ድካሟን ፍሬ እያስጎበኘችኝ ነው። በእርግጥ ብቻዬን አይደለሁም። እንደኔው የእሷን በረከት የሚጎበኙና ስለማንነቷ ጠንቅቀው የሚያውቁ የግብርና ባለሙያዎች አብረውኝ አሉ። አሁን በኮባና ፍራፍሬ የተሞላውን ሰፊ ጊቢ እያለፍን ነው። ብዙ የተለፋበትን መሬት ለመርገጥ ጥንቃቄ ያሻል። እንዲያም ሆኖ እግራችን ከአንድ የባዮ ጋዝ ማብላያ አድርሶናል።

በሻሎ እጆች በጥልቀት የተዘጋጀው ጉድጓድ በከብቶች አዛባ ተሞልቶ መዋሀድ፣ መብላላት ጀምሯል። ሽታው ለአፍንጫ አይረብሽም። ሻሎ አዛባውን በረጅም እንጨት እየበጠበጠች በቀጭኑ በተዘረጋው የቧንቧ መስመር ትለቀዋለች። የተለቀቀው ፍሳሽ መድረሻውን አይስትም። በአፍታ ራሱን ቀይሮ ጋዝ በመሆን ለማጀቷ ይደርሳል።

ወደ ገጽ 25 ዞሯል

# ሻሎ - እጀ ...

ከገጽ 24 የዞረ



ማጀቷን ለማየት ተከትለናት ገባን። ጨለም ያለውን የማብሰያ ክፍል በትልቁ አምፖል ወገግ አድርጋ አበራችው። በዚህ ብቻ አልቆመችም። እንደ ከተሜው ኤሌክትሪክ ያለውን ምድጃ በአንዴ ለኩሳ ብረት ድስቷን ጣደች። እሳቱ እንዳሻው እየጨመረ ፣ እየቀነሰ ሃይሉን አሳየን። ምግብ ሲበስልበት፣ ሻይ ቡና ሲፈላበት ተመልክተን አደነቅን፣ ተደነቅን።

ከባዮ ጋዝ ማብለያው ጥግ በወጉ የተዘጋጀ የአፈር ማዳበሪያ ለዓይን ይስባል። አፈሩን የሚያዳብሩት ትሎች ሆን ተብለው የተፈጠሩ ናቸው። ሻሎ ትሎቹን ለአፈሩ ማዳበሪያነት ትጠቀማቸዋለች። እነሱ ለእሷ የገቢ ምንጭ ሆነዋል። ማዳበሪያውን በኩንታል መግዛት የሚሹ ደንበኞች በርካቶች መሆናቸውን ነግራናለች።

የሻሎ ጠንካራ እጆች በየጊዜው የእንጨት ቆጣቢ ምድጃዎችን እያመረቱ ያወጣሉ። በእጆቿ ጥበብ የምታዘጋጃቸው የቁም ምድጃዎች በበርካቶች ዘንድ የሚፈለጉ፣ የሚመረጡ ሆነው ዓመታትን ዘልቀዋል።

ሻሎ ለአካባቢው ዘመናዊነትን የተረዳች ይመስላል። ለከብቶች የሚያስፈልጋትን መኖ የምታዘጋጀው በጊቢዋ ባቆመችው የመፍጫ ማሽን ታግዛ ነው። ይህ ማሽን የእርሻ በሬዎቿን ጨምሮ ዛሬም በበረት ለሚገኙ ከብቶች መድህን ነው። በሆዱ ምግቡን አላምጦ፣ አድቅቆ ያጎርሳቸዋል። እንዲህ መሆኑ ለባተሌዋ ወይዘሮ እፎይታን ፈጥሯል። ከዚህ ቀደም በርከት ያሉ የፈረንጅ ላሞች ነበሯት። ወተታቸውን፣ እርጎና ዓይባቸውን እየሸጠች ተጠቅማለች።

ወይዘሮዋ መሬት ተከራይታ እያረሰች ሸንኩርት ተክላ ትሸጣለች። የጊቢዋ አቦካዶ በደረሰ ጊዜም በሳጥን እየሞላች ለገበያ ታቀርባለች። ከአካባቢዋ ወጣ ከሚል ገጠር ባላት የእርሻ መሬት ስንዴ እየዘራች ታበቅላለች። ምርቱ ለገበያ ውሎ ጎኗን፣ ቤቷን ይደጉማል።

ሻሎ በጤና አጠባበቅና ቤት አያያዝ ላይ ያላት ልምድ ለየት ይለያል። ጥንካሬዋም ለሌሎች ተምሳሌት እስከመሆን ደርሷል። በትልቁ ቤት ግርጌ ማለፍ እንደያዝን ገርበብ ያለውን ክፍል ዓይኖቼ ቃኙት። ከአፍ እስከ ገደፉ እህል በተሞሉ ማዳበሪያዎች ተጨናንቋል። አዕምሮዬ እርፍ ነቅንቆ ጠንክሮ ስላረሰው ገበሬ አስታወሰኝ። ሻሎ ማለት እንደእሱ ናት። ከዓመት ዓመት ጎተራዋ የሞላ ፣ ጓሮዋ የለመለመ ጠንካራ አራሽ።

የሻሎን አፀድ ዙሪያ ገባ እየቃኘን ነው። የእሷ ጠንካራ ክንዶች ያረፉባቸው በረከቶች ታይተው አይታለፉም። አካባቢው የገጠር ቀበሌ ቢሆንም በከተማ ካሉት እውነታዎች እምብዛም አይለይም። የቪላዋን በረንዳ አልፈን ወደሳሎን በገባን ጊዜ አረፍ ያልንበት መቀመጫ ምቾት ሰጠን። መልካም ይሉት ሶፋ ነው። ብፌዋን የሞሉት ዘመናዊ ዕቃዎች ድንቅ ናቸው።

የቤት አያያዟ ይማርካል። ከማጀቷ የሚጋገረው ትኩስ እንጀራ የኤሌክትሪክ ምጣድ መሆኑን አይቻለሁ። የቤተሰቡ ልብስ የሚታጠበው በዘመናዊ የልብስ ማጠቢያ ማሽን ነው። ምግብ በስሎ ከፍሪጅ ይቀመጣል። የእሷና የልጆቿ መኝታ ቤቶች በወጉ የተዘጋጁ፣ በንጽህና የተያዙ ናቸው።

በሻሎ ጊቢ ሌላው አቅጣጫ የተሠሩ ቤቶች መኖሪያዎች ብቻ አይደሉም። መዝናናትን ለሚሹ ሻይ ቡና የሚባልባቸው ማረፊያዎች ጭምር እንጂ። በዚህ ስፍራ ያለው የፑል ማጫወቻ ለአካባቢው ወጣቶች ጊዜ ማሳለፊያ ሆኗል። በርካቶች ሰብሰብ ብለው ይዝናኑበታል።

በሻሎ ሳሎን የጀመርነው ውይይት ቀጥሏል። በጨዋታ መሀል በየሰበቡ ስለምታነሳው ባለቤቷ እያወጋችኝ ነው። እሷ ስለእሱ ያላት አክብሮት በእጅጉ ይለያል። ዛሬ ለደረሰችበት ታላቅነት ሰፊውን ድርሻ የሚወስደው የትዳር አጋሯ መሆኑን አትሸሽግም።

### የስድስቶች እናት ሻሎ ...

አቶ በየነ የልጅነት ባሏ ነው። ትምህርቷን ትታ ከእሱ ወዳ፣ ፈቅዳ የተጣመረችው ግማሽ አካሏ። ስለ ባለቤቷ ስታወጋ ዓይኖቿ ውሃ ይሞላሉ። ደግነቱን፣ የዋህነቱን፣ ለትዳር ታማኝነቱን የተለየ ቦታ ትሰጣዋለች። ሻሌ 22 ዓመታትን በትዳር ስታሳልፍ ስድስት ልጆችን አፍርታለች።

እሷ ለልጆቿ ልዩ ክብርና ፍቅር አላት። ቤት ጎጆዋን ስታስብ ፣ ስኬቷን ስታይ ደግሞ ለአፍታ የግማሽ አካሏን ውለታ አትዘነጋም። ጥቂት ዓመታትን ወደ ኋላ መለስ ስትል በሕይወቷ የተፈተነችበት ፣አንገቷን ደፍታ ያዘነችበት ክፉ ጊዜ ትዝ ይላታል። ዛሬም ቢሆን ይህ ስሜት በአዕምሮዋ ውል እያለ ያስተክዛታል። ‹‹ልርሳው፣ ልተወው›› ብትል የማይቻላት ነውና።

### ስብራትን በትዝታ...

ሻሌ አራተኛ ልጇን ነፍሰጡር ሳለች ባለቤቷ በየነ በድንገት ታመመ። ሌቱን ሲያስጨንቀው ባደረው ጉዳይ መላው ቤተሰብ ጭንቅ ገባ። ሲነጋ ሆስፒታል ሄዶ ሀኪም አገኘው። ድንገት ያጣደፈው ህመም ውጤቱ ሲጠበቅ የደም ግፊት መሆኑ ታወቀ። በአስቸኳይ መድሃኒቱን ጀመረ። ጊዜያት አለፉ። አባወራው ያዝ ለቀቅ ከሚያደርገው ህመም እየታገለ 12 ዓመታትን አስቆጠረ።

አባወራው በእነዚህ ዓመታት ለሻሌ የማይዝል ብርቱ ክንድ ከመሆን አልታቀበም። ሁለቱም ውጥናቸውን ከዳር ለማድረስ መታገላቸውን ቀጠሉ። በግብርናው፣ በአትክልቱ ምርት ፍሬያማ ለመሆን ታገሉ። ጥንዶቹ ሁሌም ልጆቻቸውን አስተምረው ወግ ማዕረግ ለማድረስ ያቅዳሉ። ይህ ይሆን ዘንድ አባወራው የቤቱ ራስ ነው። ሚስቱ ሻሌ ደግሞ ምሰሶና ማገር።

ባልና ሚስቱ ብዙ አቅደዋል። ሥራቸው ባለበት እንዲቆም አይሹም። ስለነገ ዛሬን ይሮጣሉ። ሩጫቸው ድካም አልባ እረፍት የለሽ ነው። ውሎ አድሮ ግን ይህን ፍጥነት የሚገታ እንቅፋት ተከሰተ። ብርቱው አባወራ አቅም ከጤና ያጣ ጀመር።

አሁንም ከሀኪም ፊት ቀረበ። የህክምናው ውጤት ሁለቱም ኩላሊቶቹ ሥራ ማቆማቸውን አመላከተ። መላው ቤተሰብ ከማይወጣው ጭንቅ ገባ። ስድስተኛ ልጇን ነፍሰጡር የሆነችው ሻሌ ከልብ ከፋት፣ ሆድ ባሳት። ትይዘው ትጨብጠው አጣች። ህመሙን ዋጥ አድርጎ ቤተሰቡን የሚያጽናው አባት አልቻለም። ለተሻለ ህክምና በአዲስ አበባ ሆስፒታሎች ውሎ አደረ።

ተስፋ ያልቆረጠው ቤተሰብ ታማሚውን ከቤቱ መልሶ በዙሪያው ከበበ። አባወራው አሁንም ይስቃል፣ይጫወታል። ሻሌ ገጽታውን ስታይ ደስ ይላታል፣ ትጽናናለች። ከቀናት በአንዱ ግን ታሪክ ተቀየረ። የቤቱ ምሰሶ ደጉ አባወራ በድንገት ክንዱ ዛለ። በቤቱ ድንጋጤ ሆነ። በየነ ብዙ አልቆየም። ህመም ያደከመው አካሉ ለሞት እጁን ሰጠ።

ይህ ጊዜ ወሯ ለገባው ነፍሰጡሯ ሻሌ በእጅጉ የከፋ ሆነ። የልጅነት ባሏን ሞት በነጠቃት ማግስት ቤቷ ቀዘቀዘ። ይህኔ አብሯት የኖረው ብርታት ጥንካሬዋ ሲከዳት ተሰማት። ትዝታው፣ ደግነቱ አይዞሽ ባይነቱ በፊቷ ተመላለሰ። ውስጧ እንደ አገዳ ተሰበረ። በዕንባ የማትወጣው፣ በጭንቀት የማትዘልቀው ኀዘን ዋጣት።

ከቀናት በኋላ ሻሌ በሰላም ሴት ልጅ ወለደች። ይህ ጊዜ በዕንባና ሳቅ፣ በብርሃንና ጨለማ ስሜት የተደበተችበት ነበር። የአራስ ቤቷን ቆይታ በሯን ዘግታ ባሳለፈች ጊዜ የእስከዛሬውን አስታወሳ በትኩስ ዕንባ ታጠበች። አሁን ስትወልድ የሚያርሳት፣ የሚያጎርሳት ባሏ ጎኗ የለም። እሷን የሚጽናኑ ቃላት የጠፉ እስኪመስሉ በብቸኝነት አነባች ... አነባች... አነባች..።

### ሕይወት እንደገና...

እነሆ ! እነዛ ፈታኝ ጊዜያት በአይረሴ ትዝታዎች ተጠቅልለው በሌሎች አዲስ ቀናት ተተኩ። ሻሌ አሁን ልጇን በጀርባዋ ፣ የባሏን ትዝታ በልቧ አኑራ ርምጃ ጀምራለች። ትንሽዬዋ ስጦታ ለእሷ የመጨረሻ መታሰቢያዋ ናት። በእርሷ ጥንካሬን ታያለች፣ ቃልኪዳኗን ታጠብቃለች፣ ርምጃዋን ታፈጥናለች። ሻሌ ህፃኗን ‹‹ሴና›› ስትል ሰይማታለች። ‹‹ሴና›› ያለፈ ታሪክ እንደማለት ነው።

አዎ! አሁን ፈታኙ የታሪክ ጉዞ በፈተናዎች አልፏል። ከዚህ በኋላ ሻሌ በአዲስ መንፈስ በልዩ ጥንካሬ ሕይወትን ልትጀምር ተነስታለች። ዛሬን እንደትናንቱ ‹‹ልሙት፣ ግደለኝ›› ስትል ወደ ፈጣሪዋ አትጮህም። ይህ እንዳይሆን የሟች ባሏ ጅምር ሥራዎች ቃልኪዳኗ ናቸው። ከዚህ በኋላ ከፍጥነቷ፣ የሚመልስ ከሃሳቧ የሚገታት የለም። በየአፍታው እሱን እያስታወሰች ውስጧን ‹‹አይዞኝ›› ትላለች። መለስ ብላም ባሏን በምናብ እያወጋች ‹‹አይዞህ ብቻዬን አይደለሁም›› ትለዋለች። ክንደ ብረቷ ሻሌ ሁሌም ጥንክሬዋ ከእሷ ነው። ውጥኖቿን ልትቋጭ ቆርጣ ተነስታለች። በዚህ ስሜት በአጭር ጊዜ ቪላ ቤቷን ገንብታ ጨርሳለች።

ቀድሞ ሰፊ ጊቢዋ በተከረከሙ የጽድ ዛፎች የተሞላ ነበር። በውበቱ ይማረኩ የነበሩ ብዙዎች ሰርጋቸውን ደግሰውበታል፣ ፎቶግራፍ ተነስተውበታል። ዛሬ ግን ይህ ታሪክ ተቀይሮ ሥፍራው የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻ ሆኗል።

ሻሌ የዕለት ትጋቷ እናትነቷን አላስጣለም። ሁለት ህጻናት ልጆቿን አቅፋ እያዘለች ከሥራዋ ትገኛለች። የሰብል፣ የእርሻ ውጤቷ ፣ የአትክልት ፍራፍሬ ምርቷ፣ የእጅ ጥበቧ ፍሬማ መሆን ይዟል። እነዚህ ተግባራት ዓይነ ግቡ መሆናቸው በርካቶችን እየሳበ ነው። የወይዘሮዋ ብርታት በጠንካራ ሴት አርሶአደሮች ተርታ አሰልፎ ለአድናቆት አድርሷታል፣ ለሽልማት አብቅቷታል።

### የሻካራ እጆች ፍሬ ሽልማት ...

በሻሌ ሳሎን ከባለቤቷ ፎቶ አጠገብ በክብር የተቀመጡ ዋንጫና ሜዳሊያዎች ዓይን ይስባሉ። እነዚህ ሽልማቶች የሻካራ እጆች ውጤት ናቸው። ከሽልማቶቹ ጀርባ የላብና ድካም ወዝ ታትሞባቸዋል። የብርታት፣ ጥንካሬ ዐሻራ ደምቆባቸዋል። ከሜዳሊያዎቹ አንዱ ባለቤቷ በሕይወት እያለ በጤና ኤክስቴንሽን በ2002 ዓ.ም ከኦሮሚያ ክልል የተሸለመችው ነው።

ይህ መነሻ ብርታት ሆኗት ሌሎችን ሜዳሊያዎችና የዋንጫ ሽልማቶችን አክላለች። አንደኛው ዋንጫ ከፌዴራል መንግሥት በ2008 ዓ.ም የተበረከተላት ነው። ‹‹የአፍሪካ ባዮጋዝና ኮንፍረንስ፣ የኦሮሚያ ክልል የባዮ ጋዝ ማብላያ አርአያ›› የሚል ጽሁፍ ታትሞበታል።

ሻሌ ለበርካቶች ብርታት ሆናለች። ማንም ከእርሷ ደርሶ ጥንካሬዋን ቢሻ ፣ልምዷን ቢቀስም ተሞክሮዋን ለማጋራት አትሰስትም። በተለይ ሴቶች እንደእሷ ክንደ ብርቱ ቢሆኑላት ምኞቷ ነው። ትናንትን በትጋትና በፈተናዎች መሀል ያለፈችው ሻሎ ስለ ልጆቿ ነገ በብዙ ታስባለች። እሷ አባታቸው በሕይወት ሳለ ያስብ የነበረውን ዕቅድ ከግብ ለማድረስ እየተጋች ነው።

በጨዋነት ተኮትኩተው ያደጉት ልጆች ታዛዦቿ ናቸው። ከቃሏ ዝንፍ አይሉም። የምትላቸውን ይሰማሉ። በእሷ መንገድ ይጓዛሉ። አሁን ልፋቷ ፍሬ ይዞላታል። ልጆቿ ለቁምነገር ደርሰዋል። የመጀመሪያ ልጇ ከዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን አጠናቆ ሥራ ጀምሯል።

አሁን ላይ ለልጇ የተሻለ ዕውቀት ብታስብ ከመቀነቷ አቅም ከፍላ እያስተማረችው ነው። ሌሎች ልጆቿም በዩኒቨርሲቲ እንዲማሩ የአቅሟን እያደረገች ነው። ትንንሾቹም ከትምህርታቸው እንዳይታጎሉ ሁሌም ከጎናቸው ናት።

### ሻሎ በባለሙያዎች ዓይን ...

ጅብሪል መኮንን በሂጦሳ ወረዳ የግብርና ባለሙያ ነው። በሻቂ ወረዳ ያለፉትን ዓመታት ከሻሌ ጋር የመሥራት አጋጣሚ ነበረው። ባለሙያ ነውና እሷን መሰል አርሶ አደሮች ሊያገኝ ግድ ይለዋል። እሱ ስለ ሻሌ ያለው አመለካከት ግን ከሌሎች ተጠቃሚዎች ሁሉ ይለያል። እሷን የሚገልጻት ጥንካሬና ብርታቷን አስቀድሞ ፣ሥራና ውጤቷን አክብሮ ነው።

ይህች ብርቱ ገበሬ ሁሌም የግብርና ባለሙያዎች የሚነግሯትን ለመተግበር የፈጠነች፣ ሠርታ ለማሳየትም የተጋች ናት። ጅብሪል እንደሚለው ሻሎ በአትክልትና ፍራፍሬ በተለይ በአቦካዶ ምርት የራሷን ጥረት አክላ መሥራቷ ለሌሎች ጭምር አርአያ ያደርጋታል። ወደፊት ይህን ምርት በሰፊው ከያዘች የሚገኘውን ገቢ ወደባንክ በመቀየር ቀጣይ ፕሮጀክችን ማስፋት ይቻላታል።

ሻሎ የወረዳው ሞዴል አርሶ አደር ነች፣ ነገን ከፍ ብላ እንድትወጣ የመንግሥትና የሌሎችም አጋርነትን ትሻለች። ለዚህ ተግባራዊነት እሱን ጨምሮ ሌሎች የግብርና ባለሙያዎች ወደ ኢንቨስትመንቱ እንድትገባ ተጨማሪ ክንዶች ሊሆኗት ዝግጁ ናቸው።

### ስለ ነገ...

ሻሌ ከባለቤቷ የተለየችባቸው ያለፉት ሰባት ዓመታት እንደ ስለት ሞርደዋታል። ከነበረችበት ፈተና በተሻገረች ጊዜ ራሷን ከጥንካሬ ፣ ከብርታት መንገድ አግኝታዋለች። ክንደ ብርቱዋ ሻሌ ዛሬም ዕቅዷ የሰፋ ፣ ሃሳቧ የበዛ ነው። ስለ ሥራ ካሏት እጇን አታጥፍም፣ ፊቷን አታዞርም። የትናንቱን በተሻለ መስመር ተክታ ፍሬያማ መሆንን ትሻለች።

የሻሎ ነገ በምኞት ብቻ አልተከለለም። ሃሳቧ ዕውን እንዲሆን ውጥኖቿን አስፍታለች። ያለችበት ቦታ ለዋናው መንገድ ቅርብ በመሆኑ ሆቴል ብትከፍት ለብዙዎች እንደሚበጅ ታውቃለች። መዝናኛና ሌሎች ተመሳሳይ ፕሮጀክቶችም የወደፊት ዕቅዶቿ ናቸው። ይህ ይሆን ዘንድ የእሷ ጥረት ብቻውን በቂ አይደለም። በሙያ፣ በሃሳብና በገንዘብ ድጋፍ የሚሰጧትን ትሻለች።

እንዲህ ከሆነ እሷ ብቻ ሳትሆን አካባቢ ፣ አገርና ሕዝብ ይጠቀማል። ክንደ ብርቱዋ ሻሎ ዛሬም እንደ ስሟ ስያሜ ሃሳቧ ደማቅ ብርሃን ነው። በዚህ ብርሃን ስንፍናን የማጥፋት፣ ሥራን የማስፋት ዓላማን ሰንቃለች። ሻሎ ፈተና ያልሰበራት፣ ችግር ያልበገራት ልበ ሙሉዋ ፣ እጀ ብረቷ ገበሬ።

ልዩ ዕትም

# “በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት የግንባታ ክሬን ባለሙያ በመሆኔ እኮራለሁ”

ወይዘሮ ማርታ መሰለ
የታወር ክሬን ኦፐሬተር

**መክሊት ወንድወሰን**

የክሬን ኦፐሬት ስራ እጅግ ጥንቃቄን የሚፈልግና የኦፕሬተሩ ሃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት አብዛኛውን የስሜት ህዋሳቶቹን በአንድ ጊዜ በአግባቡ መጠቀም መቻል አለበት። ትንሽ ስህተት ውድ የሆነውን የሰው ልጅ ህይወት ያስከፍላል። ከህይወት በተጨማሪም በርካታ ወጪ የወጣበትን ንብረት እስከማውደም የሚያደርስ ጉዳትንም ያስከትላል። ታዲያ ይህን ግዙፍ ተሽከርካሪ የማንቀሳቀስ ስራ ለወንዶች ብቻ የተፈቀደ እስኪመስል ድረስ እምብዛም ሴቶች ሲደፍሩት አይስተዋልም። የዛሬዋ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የሴቶች ቀን ልዩ እትም እንግዳችንም ሴትነት ይህን ግዙፍ ተሽከረካሪ ከማገላበጥ ያላገዳት ሴት የታወር ክሬን ኦፕሬተር ናት ።

ወይዘሮ ማርታ መሰለ ትባላለች። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የታወር ክሬን ኦፐሬተር ናት። የተወለደችው ሰኔ 13 ቀን 1964 ዓ.ም ቀድሞ ባሌ በሚባለው በአሁኑ የአርሲ ዞን አዳባ ውስጥ ነው። ወላጆቿ ምንም ሳያጓድሉባት በደንብ እንዳሳደጓት ትናገራለች።

የመንግሥት ሠራተኛ የነበሩት አባቷ፤ ብዙ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በአዲስ አበባ ነበር። እንዲያም ሆኖ ለስፖርትም ሆነ ለኪነጥበብ ክበብ ተሳትፎ የሚያስፈልጓትን ነገሮች ከማሟላት ወደ ኋላ ብለው አያውቁም። ትምህርት ላይ አማካይ ተማሪ እንደነበረች ትናገራለች ። ከቀለም ትምህርቷ ጎን ለጎን ቮሊቦል መጫወትና በወጣት የኪነጥበብ ክበብ ውስጥ በተወዛዋዥነት ተሳትፋለች።

“ሰዎች ክሬን ላይ በመሥራቴና ከመሬት 70 ሜ. ከፍታ ላይ ወጥቼ ስሰራ፣ እንዴት እንደማያዞረኝ ተደንቀው ሲያወሩ ስሰማ ደስ ይለኛል። ከቤተሰቤና ከሥራ ባልደረቦቼ እንዲሁም ወደ ክሬን ሙያ እንድገባ እድሉን ካመቻቸልኝ የመጀመርያ አለቃዬ ግሩም ድጋፍ በማግኘቴ እድለኛ ነኝ።” ትላለች


አባቷም ልጆቻቸውን እንዳይፈሩ እና ደፋር እንዲሆኑ እያስተማሩ ነበር ያሳደጓቸው። ማርታ የስምንተኛ ክፍል ትምህርቷን እንዳጠናቀቀች ነበር ወላጅ አባቷን በሞት የጣችው። ክፉኛ በማዘኗም ራሷን አረጋግታ ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ አልቻለችም።

ትምህርቷን አቋርጣ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ስራ የገባችበትን አጋጣሚ እንደዚ ታስታውሳለች “ትምህርቴን ትቼ ሥራ ለመፈለግ ወሰንኩ። ክፋቱ ግን የሚቀጥረኝ አጣሁ። ገና የ15 ዓመት ታዳጊ ስለነበርኩና የሥራ ልምድ ወረቀት ስለሌለኝ በብዙ ተንገላታሁ። በመጨረሻ ግን መልካዋከና የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግንባታ መስክ ውስጥ ለወጣት የኪነጥበብ አባላት የሥራ እድል ይሰጡ ስለነበር ለመቀጠር ቻልኩኝ።” ትላለች።

ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀጠረችበት ሥራ የፕሮጀክቱን ግምጃ ቤት መቆጣጠር ነበር። ውስጧ በነበረው መስክ ላይ የመስራት ፍላጎት ቢሮዋ ቁጭ ብላ መስኩ ላይ የሚከናወነውን ሥራ ስትመለከት ነበር የምትውለው። ፕሮጀክቱ ላይ የሚሠሩት የውጭ ሰዎች አነስተኛ ክሬኖች (እቃዎችን ከቦታ ወደ ቦታ የሚያንቀሳቅሱ ማሽኖች) አስመጥተው ሴቶችን ማሰልጠን እንደሚፈልጉ ስትሰማ እድሉን ለመጠቀም ጥያቄ አቀረበች። በእድሉ ለመጠቀም በጣም ጓጉታ ስለነበር በሁሉም ነገር ሲደግፉት የነበረው አለቃዋ የጓጓችለትን ሥልጠና እንድታገኝ ረዳት።

ከሥልጠናውም በኋላ፣ የተሰጠውን የንድፈ ሃሳብና የተግባር ፈተና አልፋ፣ ወዲያውኑ በክሬን ባለሙያነት መሥራት ጀመረች። ሥልጠናውን ከወሰዱት ስምንት ሴቶች መካከል በሥራው የገፋበት ሁለት ብቻ እንደነበሩ ትናገራለች። ወይዘሮ ማርታ በከባድ ማሽን ላይ መሥራቷን ስትቀጥል በጣም የምታደንቃት ሌላኛዋ አብራት ስትሰለጥን የነበረችው ደግሞ በካቶ ክሬኖች እና በመሠረት ቁፋሮ ማሽን ስራ ላይ እንደገፋችበት ትናገራለች።

> ወጣት ሴቶች ለወንዶች ብቻ የተፈጠረ ሥራ እንደሌለ በማወቅ የፈለጉትን ሁሉ መስራት እንደሚችሉ ማሳሰብ እፈልጋለሁ። ሥራው ምንም ይሁን ምን ተግተው እስከሰሩ ድረስ ስኬታማ የማይሆኑበት አንዳችም ምክንያት የለም። ››



የ17 አመት ታዳጊ እያለች የመልካዋካና ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ፣ ወደ አዲስ አበባ መጥታ ያቋረጠችውን የቀለም ትምህርቷን ለማጠናቀቅ ሽመልስ ሃብቴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገባች። በመቀጠልም በኢትዮጵያ መንገድ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የሞጆ ጣቢያ ተቀጥራ በረዳት አውቶ ኤሌክትሪሽያንነት ስራዋን ጀመረች። ቀደም ሲል በክሬን ላይ መሥራቷን የሰሙ የሥራ ባልደረቦቿ፣ ሳሊኒ ኮንስትራክሽን ለክሬን ባለሙያዎች ላወጣው ክፍት የሥራ ማስታወቂያ እንድታመለክት አበረታተዋት፣ የሥራ ልምዷን ይዛ ወደ ሳሊኒ ቢሮ አመራች።

“መጀመሪያ ላይ ሴት እንዴት ክሬን ላይ ትሰራለች የሚል ጥርጣሬ ገብቷቸው ነበር። የሳሊኒ ማሽን በፊት ከሰራሁበት በእጅጉ የሚበልጥና ትልቅ ፕሮጀክት ቢሆንም መሠረታዊ የኤሌክትሪክ ሲስተሙ ግን ተመሳሳይ ነበር።” ሥራውን ለመቀጠር ፈተና መውሰድ ነበረባትና ፈተናውን እንዳለፈች ወዲያው በግልገል ጊቤ አንድ ፕሮጀክት ላይ ሥራ እንድትጀምር ተነገራት።

በወቅቱ ፕሮጀክቱ የሰው ኃይል እጥረት ስለነበረበት የጤና ምርመራ ውጤት እስኪታመጣ እንኳን አልጠበቁም ነበር። ለሦስት ሳምንት ያህል የቅጥር ውል ሳትፈርም ስለቆየች ከደሞዟ ጋር እንደሚያስፈርሟት ጠብቃ ነበር። ሆኖም ዝም ብለዋት ቆዩ። ጉዳዩ ያሳሰባት ወይዘሮ ማርታም “ቢቸግረኝ እኔው ራሴ ጠየቅኋቸው”ትላለች።

ቆይቶ ግን የአስተዳደር ኃላፊው ሴትን በክሬን ባለሙያነት አምኖ ለመቅጠር ፈቃደኛ እንዳልሆነ ነገራት። “የሰራሁበትን ክፈሉኝና እለቅላችኋለሁ” ብላ ልትወጣ ስታስብም። ሥራዋን ያዩና ኃላፊነቷን በአግባቡ እንደምትወጣ የተማመኑባት የቅርብ አለቆቿ እንድትለቅ ሳይፈቅዱ ቆዩ። የቅርብ አለቆቿም ከአስተዳደር ኃላፊው ጋር “ትቀጠር አትቀጠር” በሚል ሲከራከሩ ቆዩ።

በመጨረሻ የአስተዳደር ኃላፊው በስራ ሰአት እሷ ሳትመለከታቸው ስትሰራ በዓይናቸው በመመልከታቸው እንድትቀጠር ተስማሙ። « ሥራው ከባድ እንደሆነ መካድ አልችልም » ትላለች ማርታ። ሆኖም የወንዶቹን ያህል የመሥራት ብቃት እንዳላት ለማሳየት በትጋት ተወጥታዋለች።

የሳሊኒ ሥራ ሲጠናቀቅ ሳሊኒዎች ክሬኑን ለጀርመኑ ዙብሊን ኮንትራክተሮች ለማስተላለፍ ወሰኑ። በዚህም እሷም ከክሬኑ ጋር እላካለሁ የሚል ተስፋ አድሮባት ነበር። ሆኖም ከቅርብ አለቃዋ ጋር ከሥራ ውጭ በሆነ ጉዳይ ተጋጭተው ስለቆዩ፣ እሷን አባርሮ እሷ ያሰለጠነችውን ረዳቷን ለመላክ መወሰኑን ሰማች። ይህን ፍትሃዊ ያልሆነ ድርጊት በዝምታ ለመቀበል አላስቻላትም። እናም በቀጥታ መብራት ኃይል ቢሮ ሄዳ የደረሰባትን በደል ተናገረች። በደረሰባት ነገር በጣም አዘኑ። በመጨረሻም ከክሬኑ ጋር ወደ ዙብሊን ኮንትራክተርስ እንድትላክ ተወሰነ። በዙብሊን ኮንትራክተርስ ለተወሰነ ጊዜ ከሰራች በኋላ፣ የጤና እክል የነበረባትን ልጇን በቤት ውስጥ ለመንከባከብ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰች።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወንድምና እህቶቿ ወደ ሥራ እንድትመለስ ገፋፏት። በአጋጣሚም ራማ ኮንስትራክሽን ካዛንቺስ አካባቢ ክሬን እየተከለ ስለነበር፣ እዚያ ማመልከቻ አስገባች። የራማ ኮንስትራክሽን ባለቤትን ጨምሮ አመራሩ ሴቶችን ለመቅጠር ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበራቸው በደስታ ለፈተና አስቀመጧት። ፈተናውን አልፋም ወዲያው ሥራ ጀመረች። የሚገርመው ግን ከዚያ በፊት ለውጭ ኮንስትራክሽን ኩባንያ ለማመልከት ሄዳ ኢትዮጵያዊው የሠራተኛ ቅጥር ኃላፊ፤ ማመልከቻዋን እንኳን ለመቀበል ፈቃደኛ እንዳልነበር ትናገራለች።

‹‹ወጣት ሴቶች ለወንዶች ብቻ የተፈጠረ ሥራ እንደሌለ በማወቅ የፈለጉትን ሁሉ መስራት እንደሚችሉ ማሳሰብ እፈልጋለሁ ። ሥራው ምንም ይሁን ምን ተግተው እስከሰሩ ድረስ ስኬታማ የማይሆኑበት አንዳችም ምክንያት የለም። ›› ስትል መልእክቷን ታስተላልፋለች።



ፎቶ - ሀዲስ አብርሃ

# ዳግመኛ የተፃፈ ወርቃማ ታሪክ

**እየሩስ ተስፋዬ**

ውልደቷ እና እድገቷ አዲስ አበባ ነው። ከንግድ ሥራ ኮሌጅ የአካውንቲንግ ምሩቅ ናት። ወደ ትዳር ዓለም ከገባች በኋላ ግን በትምህት መግፋት አልቻለችም። ከባለቤቷ ጋር በመለያየቷ ልጆቿን ብቻዋን ነበር የምታሳድገው። በአካውንታንነት በአንድ ድርጅት ውስጥ ትሠራ የነበረ ሲሆን፤ የሚከፈላት ደመወዝ ከልጆቿ የትምህርት ቤት ክፍያ አያልፍም። የተሻለ ሕይወት ፍለጋ ምርጫዋ ስደት ሆነ። ልጆቿንም ለእህቷ እና ለእናቷ በአደራ ሰጥታ ወደ ደቡብ አፍሪካ አቀናች።

ይሁንና በሄደች በስምንተኛ ወር ልጇ ሻሎም መታመሟ ተነገራት። እናትና እህት ‹‹እኛ እናስታምማታለን አንቺ እዛው ቆዩ›› ቢሏትም  የልጇ ሕመም እየተባባሰ ሄደ። እናት ወደ ሀገሯ መምጣት እንዳለባት ተነገራት። ወደ ሀገሯ በሠላም ብትገባም የልጇ ሕመም ግን ሠላም ነሳት። ልጇ የካንሰር ታማሚ ብትሆንም እንደምትድን በጽኑ ታምን ነበር። ግን  አልሆነላትም። ልጇ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየቻቸው።

በልጇ ሞት ተፈተነች። የሽንፈት ስሜት እየተሰማት ቢሆንም ‹‹አልተሸነፍኩም›› በማለት ራሷን ለማበርታት ሞከረች። በሰው ፊት ጠንካራ መስላ ብትታይም ነገሩ ግን ተቃራኒ ሆነ። እንቅልፍ ከዓይኗ ጠፋ። በድባቴ ተሰቃየች። ለራሷም ‹‹ልጄ አልሞተችም›› በማለት ካለችበት ነገር ለመውጣት ራሷን ማበርታት ጀመረች። በድጋሚ ወደ ደቡብ አፍሪካ ብታቀናም የእርሷ ሕይወት ለብዙ ሴቶች ትምህርት ይሆናል ‹‹እነርሱን መርዳት አለብኝ›› ብላ የምትሠራውን ሥራ በመተው እንዲሁም ያለፈችበትን ህመም ማባከን አልፈለገችምና ዳግም ወደ ሀገሯ ተመለሰች። ይህች ጠንካራ ሴት ፌቨን ጋሻው ትባላለች።

ፌቨን ያለፈችባቸውን የሕይወት ውጣ ውረዶች ለብዙዎች ለማስተማር ‹‹የንጉሱ ሴት ልጅ ወርቃማ መንገዶች›› የተሠኘ መጽሐፍ ለንባብ አበቃች። የመጀመሪያው መጽሐፏ ሰዎችን በግል እና በጋራ ተሰባስበው የምታስተምርበት አጋጣሚ ስታገኝ ያለፈችበትን መንገድ ከመንገር በሻገር ለብዙዎች እንዲደርስ በማሰብ በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅታ እንዲጠቀሙበት እና እንዲማማሩበት አድርጋለች። በመጽሐፉ አብዛኛው ክፍል የራሷን ታሪክ የሚዳስስ ሲሆን፤ እስከ አራተኛ ዕትም ደርሶላት አማዞንን ጨምሮ በበርካታ መደብሮች ላይ ለመገኘት በቅቷል።




በመቀጠልም ‹‹የንጉሱ ሴት ልጆች የልማት፣የማብቃት እና የበጎ አድራጎት ድርጅት መመሥረትም ቻለች። ድርጅቱ ከመመሥረቱ በፊትም ቢሆን ሱሰኛ የሆኑ ወጣቶችን ታስተምር የነበረችው ብርቱዋ ሴት ፤ ድርጅቱ ከተቋቋመ በኋላም በአራት ዘርፎች ሴቶች ስልጠና እንዲያገኙ፣ የማማከር አገልግሎት፣ የበጎ አድራጎት እና የሚዲያ  ሥራ መሥራት ጀመረች።

የመሠረተችው ድርጅት በስልጠና በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጪ በክልል ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች በመሄድ ስልጠና ይሰጣል። በብዙ ውጣ ውረድ የሚያልፉ ሴቶችን ደግሞ የማማከር ሥራ ይሠራል። በበጎ አድራጎት ሥራ ደግሞ ‹‹ልብሴን ለእህቴ›› የሚል ዘመቻ በመክፈት አልባሳትን ከአዲስ አበባ ከሚገኙ ሴቶች በመሰብሰብ ‹‹ማንም ሴት ልጅ በልብሷ ምክንያት ከማሕበራዊ ሕይወቷ አትገለልም›› በማለት ከሁለት ሺ በላይ ሴቶች ድጋፍ እንዲያገኙ አድርጋለች።

ፌቨን በድጋሚ ትዳር መመሥረቷን ተከትሎ ‹‹ጎጆ መውጫ›› በሚል ዘመቻ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ በማረሚያ ቤቶች፣ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላሉ ሴት ተማሪዎች እስከ ሁለት ዓመት የሚያገለግል የንጽህና መጠበቂያዎችን በአዲስ አበባ እና በክልሎች ድጋፍ ተደርጓል። በሚዲያው ዘርፍም ቢሆን በዩቲዩብ እና በማሕበራዊ ትስስር ገጾቿ ላይ ለሴቶች የሚጠቅሙ ሃሳቦች ይንሸራሸርበታል። በቅርቡም በራዲዮ እና በቴሌቪዥን ሴቶችን የሚያበረታታ ርዕሰ ጉዳይ በመቅረጽ ፕሮግራሙን ለመጀመር ዝግጅቷን አጠናቃለች።

አንዳንድ ወላጆች ሴት ልጆቻቸው በሱስ ውስጥ እንዳሉ አያውቁም። ብዙዎቹ ግን በድባቴ እና በሱስ ሕይወት ውስጥ እየተዘፈቁ ይገኛሉ።ራሳቸውን ‹‹ሱሰኛ ነን›› ብለው እንዳያጋልጡ ማሕበረሰቡ ያሸማቅቃቸዋል።ፌቨን በሱስ ሕይወት  ያሳለፈች ሴት እንደመሆኗ በሱሰኝነት እና ድባቴ ላይ እየሠራችም ትገኛለች። ከዚህ ጋር ተያይዞም በዚህ ዓመት ለሴቶች ብቻ የሚሆን ከሱስ ማገገሚያ ቦታ ለማዘጋጀት እቅድ እንዳላት ስትናገር ትደመጣለች።

ፌቨን በአንድ ቀን ውሳኔ ከሱስ ለመውጣት ችላለች። ደግሞም በሂደት ያቆመችባቸው ጊዜያት ነበሩ። በገጠማት ተደራራቢ ፈተናዎች ለመደበቅ እንዲሁም አራዳ ለመባል የገባችበት ሱስ ለመግባቱ እንደቀለላት መውጫው

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## ልዩ ዕትም



ፎቶ - ሀዲስ አብርሃ

# ‹‹ እናቴ አክንባሎ ሸጣ ስላሳደገችኝ ስራ አልንቅም ››

**ወይዘሮ አስናቀች ያደታ**

**አርሶ አደር እና አርብቶ አደር**

**መክሊት ወንድወሰን እና ሰሚራ በርሀ**

ሰዎች በተለያየ መንገድ የሀብት ባለቤት ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ሀብታቸውን ለማስተዳደር እውቀት እና ብልሀት ከሌላቸው ያላቸውን ሀብት እንደያዙ ላይቆዩ ይችላሉ። የሥራ ጥንካሬ ፣ ትጋት እና ህልም በውስጣቸው ያሉ ሰዎች ደግሞ በዙርያቸው ያለውን ትንሽ ነገር ተጠቅመው በማሳደግ እና ያልተገደበ ጥረትን በማድረግ የሀብት ባለቤት ይሆናሉ። ሀብታቸውም በሚታየው ቁሳቁስ ብቻ ሳይሆን ይህንን ለማድረግ የለፉባቸው ዓመታት ውስጥ ያሳለፉት ውጣውረድ የሚመነዘር የሕይወት ልምድም ጭምር ይሆናል።

ብዙዎች የተለየ ሚስጢር እንደያዙ አድርገው ልምዳቸውን ይጠይቋቸዋል። ለሌሎች ሰዎች ተምሳሌትና ፣ ሞራል ይሆናሉ። የዛሬው የሴቶች ቀን ልዩ እትም እንግዳችን ከቤተሰቦቿ ያገኘችውን ጥቂት ሀብት ተጠቅማ የምትሠራዋን አርሶ አደር እና አርብቶ አደር የሥራዋን ጥንካሬ ሰምተን ቤቷ ተገኝተናል። ሰው አክባሪ እና ፈገግታ የማይለያት ናት። ሱሪዋን ታጥቃ ለከብቶቿ የሚሆን ገለባ ትከምራለች።

ሰላምታ ከሰጠችን በኋላ ወደ ቤቷ እንድንገባ ጋበዘችን። ቤቷን ላየ ባንዲት ትንሽዬ ቀበሌ ገበሬ ማህበር የሚገኝ አይመስልም። እጅግ አስውባ ሠርታዋለች። የቤት አያያዟም ታታሪነቷን ያሳብቃል። ማን ትሆን እያላችሁ እንደሆነ አስባለሁ። እንግዲህ እናስተዋውቃችሁ መልካም ንባብ .....

አስናቀች ያደታ ትባላለች። ተወልዳ ያደገችው ከአዲስ አበባ ከተማ በ140 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው በሒጦሳ ወረዳ በኡዳ ጂላ ቀበሌ ውስጥ ነው። ለቤተሰቦቿ የመጨረሻ ልጅ ናት። እናትና አባቷ በልጅነቷ ሲለያዩ ልጆች የማሳደግ ሃላፊነት በብቸኛዋ እናቷ ላይ ይወድቃል። አራት ልጆችን ለብቻ ማሳደግ ቀላል ያልሆነላት እናት ሶስት ልጆቿን አያቶቻቸው ዘንድ ያድጉ ዘንድ ለወላጆቿ ሰጠች። ነገር ግን የመጨረሻ ልጇ የሆነችውን አስናቀችን ደግሞ ከእርሷ ጋር ለማሳደግ ወሰነች። የአስናቀች እናት ለብቻዋ የእንጀራ ምጣድ መክደኛ የሆነውን አክንባሎ እየሸጠች ልጇን ማሳደጉንና ኑሮዋን መግፋቱን ተያያዘችው።

አስናቀች ልክ እንደ እኩዮቿ ወደ ትምህርትቤት ብትገባም እስከ ስድስተኛ ክፍል ከተማረች በኋላ ግን ችግር ትምህርቷን እንድታቋርጥ አደረጋት። ከእናቷ ጋር የምትኖረው አስናቀች ችግርን ለመረዳት የእናቷን ጭንቀት ለማስተዋል ደርሳለች እና እንዲሁ መቀመጡ በጎ ሆኖ አላገኘችውም። ስለዚህም እንደ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ እና ችግርን ለማሸነፍ እንደሚያደርጉት ወደ አረብ ሀገር አቀናች።

አስናቀች ፣ በአረብ ሀገር በመጀመሪያ የገባችበት ቤት ጊዜያዊ ነበር። በአረብ ሀገራት በየሰው ቤት የሚሠሩ ሴቶች ከአሰሪዎቻቸው ብዙ በደል እና ከፍተኛ የሥራ ጫና ይደርስባቸዋል። አስናቀችም በምትሠራበት ቦታ የነበረውን ጊዜም ስታስውስ ‹‹ደመወዜን ይከለክሉኛል፤ ሊደበድቡኝ ይነሳሉ።›› ትላለች። አስናቀች በዚህ ቤት ውስጥ ከአንድ ዓመት ከሶስት ወር በላይ ልትቆይ ባለመቻሏ ከአቅሟ በላይ ሲሆን ጠፍታ ወደ ሌላ አሠሪዎች ቤት ገባች። ከአንዱ ቤት ወደ አንዱ ቤት እየተንከራተተች በአረብ ሀገር ለአምስት ዓመት ያክል ቆየች። በዚህ መሀል ግን እናቷ ታመመች ፤ የናቷን መታመም ሰምታ በሰው ሀገር መቀመጥ አላስችል አላት። ወደ ትውልድ ሀገሯ ተመለሰች። ነገር ግን ከእናቷ ጋር መኖር ከጀመረች ብዙም ሳትቆይ ከአንድ ወር በኋላ እናቷ አረፉ። እናቷ በሕይወታቸው እስኪያልፍ ድረስ ትደግፋቸው የነበረችው አስናቀች ነበረች። አባቷም ያረፉት እናቷ ከማረፋቸው ከጥቂት ወራት ቀደም ብለው ነበር።

አስናቀች ከዚህ በኋላ በእናቷ ቤት ሆና ኑሮዋን ቀጠለች። ‹‹እናቴ አክንባሎ ሸጣ ስላሳደገችኝ ሥራ አልንቅም›› የምትለው አስናቀች ከአባቷ ባገኘችው ውርስ የተሰጣትን አንድ ሄክታር ተኩል መሬት ይዛ ሥራ መሥራት ጀመረች። ከአረብ ሀገር ስትመጣ የነበራትን 60 ሺህ ብር ለእናቷ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ላይ አውጥታ ስለነበር በተረፋት ብር በአቅራቢያዋ ካሉ ሰዎች ትንሽዬ ጊደር እና አንድ በሬ ገዛች፣ የገዛቻት ጊደርም ማደጓ አልቀረም፤ አድጋ ወለደችላት። ከዛም ባለፈ ለመሥራት ከፍተኛ ጉጉት ስለነበራት የነበራትን ሰባት ግራም ወርቅ የአንገት ሀብል ሸጣ ጠምዶ ለማረስ ያስችላት ዘንድ አንድ ተጨማሪ በሬ ገዛች።

አስናቀች ከውርስ ያገኘችውን እና የእናቷን ሀብት ይዛ ሥራዋን እየሠራች ከዚያም ትዳርን መሠረተች። በትዳር በቆየችባቸው ዓመታት አንድ ወንድ ልጅ ልታፈራ ችላለች። ነገር ግን ልጅ ያፈራበት ትዳሯ ሊቆይ ባለመቻሉ ከባለቤቷ ጋር ተለያይታ እንደገና ሕይወቷን መኖር ቀጠለች። ባለቤቷም ከተለያዩ ከሁለት ዓመት በኋላ አረፈ። አስናቀች ችግር ብዙ ቢፈትናትም ካሰበችው እንድትቀር አያደርጋትም ኀዘኗንም ችግሯንም ይዛ ሕይወቷን ለመለወጥ የተለያዩ መንገዶችን ትፈልጋለች ትሞክራለች።

አስናቀች በአሁኑ ሰዓት የምትኖረው ከልጇ እና ከታላቅ ወንድሟ ጋር በሠራችው መኖሪያ ቤት ሲሆን ከወላጆቿ ያገኘችው መሬት ጦሙን ማሳደር የማይታሰብ ነው። ከእናቷ ያገኘችው ሁለት ሄክታር መሬት በዓመት እስከ 70 ኩንታል የስንዴ ምርት ታስገባለች። የምትዘራው እህልም እንደየወቅቱ ይለያያል። አስናቀች ለምታርስባቸው በሬዎች ውጪ ሁለት ወተት የሚሰጡ ላሞች እና አንድ ክበድ ላም አላት። አስናቀች አልባ ያዘጋጀችውን ወተት አንዳንዴም በባጃጅ በብዛት ግን በጋሪ ታደርሳለች። ራሷ ያለበችውን ወተት በቀን ሁለት ጊዜ ጋሪዋን እየነዳች ከምትኖርበት ቀዬ በሰባት ኪሎ ሜትር ርቃ ወተቱን ለሚረከቧት ሰዎች ታደርሳለች። በአንድ ቀንም እስከ 18 ሊትር የሚደርስ ወተት ታቀርባለች። ጋሪዋን እየነዳች ለሚያዩዋት እና እንድታቆም ለሚነግሯት ሰዎች አስናቀች ፍጹም ቦታ የላትም። በትንሹም ለምታቀርበው ወተት በቀን ውስጥ ከ500 እስከ ሁለት ሺህ ብር ገቢ ታገኛለች። አስናቀች በቤቷ ውስጥ እንዲሁ ፈረሶችም አሏት።

ታታሪዋ አስናቀች የስድስት ዓመት ልጇን ታዲዮስ ኦሳን ትምህርት ቤት በትምህርቱ እንዲበረታ መክራ ትልከዋለች። ለብቻዋ በምትሠራው ሥራ እና በምትመራው ሕይወት ደስተኛ መሆኗን ትናገራለች።

‹‹ሥሰራ የሚያዩኝ ወንዶች ጎበዝ ነሽ ይሉኛል፤ ሴቶች ግን ትጎጃለሽ ተይ ይሉኛል። ›› ያለእረፍት ስትሠራ

ወደ ገጽ 29 ዞሯል

# ሴትነት ከውሳኔዋም ከዓላማዋም ዝንፍ ያላደረጋት - ሻምበል

አስቴር ኤልያስ

የኮማንዶና አየር ወለድ ማሰልጠኛ ማዕከል የሴቶች ጉዳይ አመራር ናት - ሻምበል ትቅደም ወርቁ። የተወለደችው በኦሮሚያ ክልል፣ በቡሌሆራ ቡዳ መጋዳ አካባቢ ሲሆን፣ ያደገችው ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጌዴኦ ዞን ዲላ ከተማ ነው። ትምህርቷን የተከታተለችው እዛው ዲላ ውስጥ ነው። ትምህርቷንም እስከ አስረኛ ክፍል ከተማረች በኋላ መከለከያን ተቀላቀለች።

ብዙዎቹ ልክ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ፍላጎታቸው የነበረው የመንግሥት ሥራ ፈልገው መቀጠር ነው የምትለው ሻምበል ትቅደም፣ እኔም ልክ እንደእነርሱ ሁሉ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀጣሪ መሆን የሚያስችለኝን ትምህርት ገፉ አድርጌ እቀጥላለሁ የሚል ነገር ነበረኝ ትላለች። ነገር ግን ይህ በሃሳብ ደረጃ የተያዘ እንጂ ምርጫዬ የነበረው ሀገሬን በውትድርናው ዘርፍ ማገልገል ስለሆነ አስረኛን እንዳጠናቀቅሁ ምርጫዬ ወደሆነው ውትድርና ለመግባት በቃሁ ስትል ትገልጻለች። እኔ ውትድርናን ምርጫዬ አድርጌ የገባሁት ዓላማ ስላለኝ ነው፤ ስገባም ነገሮች ቀላል ይሆናል የሚል እምነት አልነበረኝም›› ትላለች።

ወስኜ ገብቻለሁ፤ ለወሰንኩት ነገርም ዓላማ አለኝ። በርግጥ ነገሮች እንዳሰብኩት ላይሄዱ እንደሚችሉ እረዳለሁ፤ ይሁንና እሱ ግን ከውሳኔዬና ከዓላማዬ ቸል እንድል አላደረገኝም። እንደምወጣው አውቅ ነበር። ምክንያቱም ይታየኝ የነበረው የትልቅ ሀገር ልጅ መሆኔ ነው። ሀገር በእኛ አዕምሮ አይለካም። ስለዚህ ትልቅና ሰፊ የሆነውን ነገር ለመሸከም ትከሻዬ ሰፊ መሆን አለበት። ትከሻዬ ሲሰፋና አዕምሮዬ ሲዳብር እሰራለሁ ብዬ በገባሁት ነገር ላይ በቁርጠኝነት እደርሳለሁ ትላለች።

እኔ ሀገሬን በውትድርና ለማገልገል ስለመረጥኩ እጅግ ደስተኛ ነኝ። ወደዘርፉ የገባሁት ያለምንም ግፊት ራሴ ነኝ። የወሰነልኝ ማንም የለም። ዛሬ የሻምበል ማዕረግ አለኝ፤ ነገ ደግሞ ከፍ ያለው ቦታ ላይ እደርሳለሁ። ለዚህ ደግሞ ጾታዬ አይከለክለኝም፤ ትናንትም አልከለከለኝም ትላለች። በውትድርናው ዓለም 19 ዓመት የቆየች ሻምበል ትቅደም፣

> **ሀገሬ! እምዬ! ታላቅ ደረጃ ላይ ደርሳ ማየት ምኞቴ ነው፤ ምኞት ብቻ ሳይሆን ኃላፊነቴን ለመወጣትና ሌሎች ለሚሰሩ መልካም ሥራዎች እተባበራለሁ። የሀገሬ አፈር ተቆርሶ የሚበላ ነው። የሀገሬ አየር ተቀድቶ የሚጠጣ ነው።**



ፎቶ - ዳኜ አበራ

ውትድርናውን የተቀላቀለችው በ1997 ዓ.ም ነው። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ትዳር መስርታ የሁለት ልጆች እናት መሆን ችላለች።

እርሷ፣ እናትነት በውትድርናው ዘርፍ ተሰማርቶ ሀገርን ከማገልገል አያግድም ትላለች። ሻምበል ትቅደም፣ ለሀገሯ ወታደር፤ ለልጆቿ ደግሞ እናት ናት። ሀገር ትጋቷን፤ ልጆች እናትነቷን ፈልገው አላጡም። እርሷ ለሁሉም ራሷን አልሸሸገችም። ሁሉም በሚፈልጓት ዓይነት ሁኔታ ተገኝታላቸዋለች። ይሁንና በዚህ መካከል አስቸጋሪ ጊዜያት አላለፉም ማለት እንዳልሆነ ትናገራለች። እነዚያን አስቸጋሪ ጊዜያት በብልሃት ማለፍ ችላለች።

በሥልጠና ወቅት ሴትነት ፈተና አይሆንም ብሎ መደምደም አይቻልም የምትለዋ ሻምበል ትቅደም፣ "ፈተናዎች ይኖራሉ። ነገር ግን እነዛ ፈተናዎች ከዓላማዬ አላስቀሩኝም። በተለይ ደግሞ ማዕረግ እየጨመረ፣ ልምድም እየዳበረ በመጣ ቁጥር ፈተናውም የዚያኑ ያህሉ ጠንካራ ይሆናሉ።" ትላለች።

በተለይ ደግሞ የአየር ወለድ ሥልጠና በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ምክንያቱም፤ በምድር ላይ የሚደረጉ ሥራዎችም ሆኑ ሥልጠናዎች በብዙ ላይፈትኑ ይችላሉ። በእንቅስቃሴ ጊዜ እንቅፋት ቢመታን እንኳ የሆነ ነገር ይገጥ አሊያም ታክኬና ተደግፌ እተርፋለሁ ተብሎ ሊታሰብ ይችላል። ተንደርድረን ልንቆምም እንችላለን። እንተርፋለን ብለንም ልናስብ እንችላለን ስትል የምታስረዳው ሻምበል ትቅደም፣ የአየር ወለድ ሥልጠናው ግን እንደእሱ ዓይነት ነገር አይታሰብም፤ ተንደርድሬ እቆማለሁ ማለት አይቻልም። የሆነ ነገር ይገጥ እተርፋለሁ ይሉት ምኞት አይሰራም። ከአየር ላይ በገመድ መወርወር ነው። ይህ በራሱ አንድ ፈተና ነው። ይሁንና ያም ቢሆን ሴት አትችልም የሚል ነገር የለም፤ ሴትም እሱን ታደርገዋለች፤ አድርገዋለችም። እኔም ተወጥቼዋለሁ። አምስት ጊዜ በመዝለሌም ዊንጉን አግኝቻለሁ። ከዛ በላይ ግን ገፍቼ አልሔድኩም። ዊንግ ለማሻሻል የሚዘለለውን ሌላውን ዝላይ አልገፋሁበትም።" በማለት ትናገራለች።

እርሷ፣ ለሴቶች አንድ ምክር አለኝ ትላለች፤ ሴቶች አንድ ብሂል አላቸው፤ ከወንድ አላንስም የሚል። እሱ ነገር በፍጹም ሊኖር አይገባም ባይ ነኝ። እኔ የምለካው በእሱ አይደለም። እኔ የምለካው በእኔነቴ ነው። እኔ የምለካው በአቋሜ፣ በዓላማዬ እና በሥራዬ ነው። ስለዚህ 'እሷ እኮ ከወንድ እኩል ናት። ከወንድ አታንስም' የሚሉት ነገር ሴቶችን የሚገልጽ ነው ብዬ አላምንም። ሴት ሴት ለመሆን ፈልጋ አልተፈጠረችም፤ ወንድም እንዲሁ። ርግጥ ነው ሴቶች ላይ ተጽዕኖች የሉም ማለት አይደለም። አንዳንዴ የቱንም ያህል እውቀት ቢኖራትም ለዚህ ቦታ አትመጥንም የሚለው አካል ይበዛል። ይህ በራሱ ፈተና ነው። እንዲያም ቢሆን እኛን ሴቶች ምንም ዓይነት አባባል እንዲገድብን ዕድል አንስጠው። የምንሰራው ሥራ በፉክክር ዓይነት አካሄድ ሳይሆን በዓላማ ይሁን።" ትላለች።

### ሀገርሽ የት እንድትደርስ ትፈልጊያለሽ

ሀገሬ! እምዬ! ታላቅ ደረጃ ላይ ደርሳ ማየት ምኞቴ ነው፤ ምኞት ብቻ ሳይሆን ኃላፊነቴን ለመወጣትና ሌሎች ለሚሰሩ መልካም ሥራዎች እተባበራለሁ። የሀገሬ አፈር ተቆርሶ የሚበላ ነው። የሀገሬ አየር ተቀድቶ የሚጠጣ ነው። ትርፍ ሀገር የለኝም፤ እንዲኖረኝም አልሻም። በፊት ልጅ እያለሁ ሰዎች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዘው ሲያለቅሱ የሚያስመስሉ እንጂ እውነት አይመስለኝም ነበር። አሁን አሁን ላይ የሀገሬ አፈር ጠረኑ ራሱ ለእኔ መድኃኒቴ እንደሆነ ተረድቻለሁ። ያለኝ አንድ ሀገር ነው። ሌላ የትም መሄጃ የለኝምና ሀገሬን አከብራለሁ ስትል ትናገራለች።

እንደ እርሷ አባባል፤ እኛ የሚያምርብን ስንዋደድ እንጂ ስንጋደል አይደለም። አንዳችን ለሌላችን እናስፈልጋለን፡፤ የሚያምርብን መስማማት ነው፤ ፍቅር ነው። ስለዚህ ተባብረንና ተግባብተን ሀገራችንን ትልቅ ደረጃ ላይ እናድርስ፤ ሀገራችን ትልቅ ደረጃ ላይ ደረሰች ማለት እኛም ትልቅ ደረጃ ላይ መድረስ እንችላለን ማለት ነው።

## ‹‹ እናቴ አክንባሎ ሽጣ ስላሳደገችኝ...

ከገጽ 28 የዞረ

ከሚያዩዋት ሰዎች የሚደርሳት አስተያየት መሆኑን ትናገራለች። ልጆቻቸውን ለብቻቸው ለሚያሳድጉ እናቶችም ማንኛውንም ሥራ አትናቁ ምክሯ ነው።

በሀገራችን አሁንም ድረስ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ሴቶች ወደ አረብ ሀገር ያልፍልኛል ብለው ይሰደዳሉ። ‹‹ አረብ ሀገር ብዙ ፈተና አለ። በሰው ሀገር መሞትም ማጣትም አለ ሰው ሀገር ሄደው መንከራተትም አለ፤ ሴቶች የሚያገኙትን ገንዘብ ብቻ አይተው አይሂዱ።›› የምትለው አስናቀች በሰው ሀገር እየሠሩ ጉልበታቸውን ከሚፈጁ እና የሰው ሀገር ከሚያሳድጉ በሀገራቸው ከትንሽ በመጀመር መለወጥ ይችላሉ ትላለች። ‹‹ ሀገራችን ለሚያውቃት ሰው ወርቅ ናት። ለማያውቅ ሰው ደግሞ ይከብዳል።›› ይህ የአስናቀች ምልከታ ነው።

አስናቀች ከብቶች ትልቅ ሀብት በመሆናቸው እንደ አንዲት አርብቶ አደር እና አርሶ አደር አስፈላጊውን እንክብካቤ ሳትሰለች ታደርጋለች። የምታገኘውንም ገቢ በአግባቡ ታስተዳድራለች። አሁን የምትኖርበት ባለ56 ሉክ ቆርቆሮ ቤት የሠራችው ራሷ ናት። አሁን ያላት ባላት ሀብትም ሆነ ንብረት በቃኝ አላለችም። በዚሁ ሥራዋ ከዚህ የተሻለ ደረጃ ላይ ለመድረስ እና በከተማ ቤት እና መኪና በመግዛት ከዚህ የተሻለ ትልቅ ደረጃ መድረስ በእቅዷ ውስጥ አለ።



> **ሀገራችን ለሚያውቃት ሰው ወርቅ ናት። ለማያውቅ ሰው ደግሞ ይከብዳል።››**

ከአረብ ሀገር ይዛ በመጣችው ገንዘብ የገዛቻቸው ጊደር እና ወይፈን አድገው ፣ መሬቷም እየታረሰ ምርቷን እየሰበሰበች ፣ ላሞቿም እየታለቡ ዛሬ ላይ ወደ ዘጠኝ የሚጠጉ ከብቶች ፣ ሁለት ፈረስ ፣ ሶስት አህያዎች ፣ የምታረባቸው ዶሮዎች እንዲሁ አሏት። ይህ እንዲሁ ሳይሆን በሥራ እና በትጋት ስለመሆኑ አስናቀች ማሳያ ናት ። ‹‹ አንድ ዶሮ ነው ያለችኝ ተብሎ ያቺን ዶሮ እንዲንቁ አልፈልግም። ምክንያቱም ያቺ ዶሮ እንቁላል ትጥላለች፣ እንቁላሏን ይሸጧታል። ከዚያ ደግሞ እቁብ ይገባሉ ፤ ሌሎች ዶሮዎች ይጨምራሉ እያደገ ይሄዳል። ›› ይህ ሲታይ የሚሆን የሚሳካ አልያም ቀላል ነገር ቢመስልም ማረጋገጫው ግን አስናቀች ናት። ‹‹ በመጀመርያ በአራት ሺህ 500 ብር የገዛኋት ላም ስትወልድ እሷን በ34 ሺህ ብር ሸጬ ለከብቶች የሚያገለግል ማደሪያ ሰራሁላቸው።" ትላለች። የነበርኩበትን እና አሁን ያለሁበትን ሰዎች ያውቃሉ የምትለው አስናቀች ‹‹ እናቴ አክንባሎ ሽጣ ስላሳደገችኝ ሥራ አልንቅም ›› መርኋ ነው።

# የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሞተር

ብርሃን ፈይሳ

በዓለም ላይ ከሚዘጋጁ የጎዳና ላይ ውድድሮች በአስደሳችነቱ ከቀዳሚዎቹ መካከል አንዱ፣ በአፍሪካ ደግሞ በግዝፈቱ ቀዳሚው ሩጫ፤ ኢትዮጵያዊው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ነው። ከተለያዩ የዓለም ሃገራት ተሳታፊዎችን የሚስበው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ እስከ 50ሺ የሚደርሱ ተሳታፊዎችን በማስሮጥ በአውሮፓና አሜሪካ ከሚደረጉት ታላላቅ የሩጫ ውድድሮች ተርታ ይሰለፋል። የኢትዮጵያዊያን ኩራት የሆነው ይህ ተቋም በርካቶችን በሩጫ ከማሳተፍ ባለፈ የ10 ኪሎ ሜትር ሩጫው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ (የዓለም የጎዳና ላይ ሩጫዎች ማህበር አባል) በመሆኑ ታዋቂና ጀማሪ አትሌቶችንም በማፎካከር የገቡበትን ሰዓት ያስመዘግባል።

‹‹የሯጮቹ ምድር›› የሚል ቅጽል ያተረፈችው ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ስፖርት መልካም ገጽታዋን የገነባች እንደመሆኑ በዚህ ሩጫ ላይ መሳተፍ ከዓለም የአትሌቲክስ ከዋክብት ጋር መሮጥ በመሆኑም የተለየ ትርጉም ያሰጠዋል። እጅግ ደማቅ፣ በአስደሳች ድምጽ የታጀበ እና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን በቅርበት ለማወቅ ምቹ እንደሆነ ስለሚነገርለትም የውጪ ዜጎችን ይስባል። ይህም በስፖርት ቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦን ያበረክታል። ከሚያገኘው ገቢ ላይ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብን ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች በየዓመቱ በማበርከት ማህበራዊ ኃላፊነቱን የሚወጣው ተቋሙ፣ ሴቶችን፣ ህጻናትን፣ ተፈጥሮን፣ ጤናን፣... የሚመለከቱ መልዕክቶችን በማስተላለፍም ይታወቃል። በዛሬው ዕለት የሚከበረውን የሴቶች ቀንን (ማርች8) ተከትሎም የ5 ኪሎ ሜትር ሩጫ በማከናወን ሴቶችን የማነሳሳትና የማነቃቃት ስራ ያከናውናል።

ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስተዋወቀው ተቋም የሩጫውን የደስታ መንፈስ እንደጠበቀ ቆይቷል። ኢትዮጵያን ተሻግሮም በተለያዩ የአፍሪካ ሃገራት ጭምር የሩጫ ውድድርን ለማዘጋጀትም ችሏል። በስራ ባህሉ ለበርካቶች ተምሳሌት ሲሆን፤ በሃገር አቀፍ ደረጃ ግዙፍ ውድድሮችን በማስተናገድ የሚስተካከለው የለም። ከዚህም በላይ ሊባልለት የሚገባውን ይህንን ተቋም የምታንቀሳቅሰው ሞተር ደግሞ ሴት ናት። የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ስራ አስኪያጅ ወይዘሪት ዳግማዊት አማረ ልምዷ ለብዙዎች አርዓያ ሊሆንና ተነሳሽነትን ሊፈጥር ይችላል በሚል የዛሬው ልዩ እትም እንግዳ ሆናለች።

> ከሴቶች ጋር በተያያዘ የተለመደው ነገር እኩልነት የሚለው ነው፤ የመማር፣ የመስራት፣...። ነገር ግን አሁንም ጎታች የሆኑና ሊቀየሩ የሚገባቸው አስተሳሰቦች አሉ። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው የሴቶች ቀንን (ማርች 8) አስመልክቶ የሚደረገው ሩጫ ሲሆን፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ሴቶችን ያሳትፋል።"



የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ስራ አስኪያጅ ወይዘሪት ዳግማዊት አማረ

**አዲስ ዘመን፡- ታላቁ ሩጫ በዓመት ውስጥ ምን ያህል ውድድሮችን ያዘጋጃል?**

**ወይዘሪት ዳግማዊት፡-** በየዓመቱ በአማካይ ከ6 እስከ 8 የሚደርሱ ሩጫዎችን ያካሂዳል። በዋናነት 10 ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው ታላቁ ሩጫ፣ የሴቶች 5 ኪሎ ሜትር፣ የሃዋሳ ሃይቅ ግማሽ ማራቶን፣ የዱላ ቅብብል፣ የህጻናት እንዲሁም ሌሎች ተጨማሪ ሩጫዎችም ይደረጋሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ይህንን ሁሉ ውድድር ማዘጋጀት እና መምራትስ ምን ያህል አቅም ይጠይቃል?**

**ወይዘሪት ዳግማዊት፡-** ውድድር ማዘጋጀት የሩጫ ቲሸርት መሸጥ ብቻ የሚመስላቸው በርካቶች ናቸው። ነገር ግን በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የሚዘጋጁ አብዛኛዎቹ ሩጫዎች እንደሃገር የሚደረጉ በመሆናቸው፤ ከአትሌቶችና ተሳታፊ (የውጪ ዜጎችን ጨምሮ) ባለፈ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት፣ ከአጋር ድርጅቶች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ የመገናኛ ብዙሃን፣... ጋር መስራት የግድ ይላል። ሁሉም ሩጫዎች የየራሳቸው ባህሪ ያላቸው ከመሆኑም ባለፈ ሁሌም አዲስ ነገርን ለመፍጠር እንጥራለን። ይኸውም ከፍተኛ ስራ የሚጠይቅ ሲሆን፤ አንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ አቅምንና ማንነትን የሚፈታተኑ ይሆናሉ። በእርግጥ ራስን መለካት የሚቻለው በተጓዘበት ርቀት ልክ ነው። በተለይ ውድድሮች ሲቃረቡ ከፍተኛ ጭንቀት ስለሚኖር ጠንካራ ስራ እና ተነሳሽነትን ይጠይቃል።

እንደ ሴት ደግሞ ሁሉም ነገር የተስተካከለ እንዲሆን መጠንቀቅን ጨምሮ ስሜታዊ (የሚያስደስት፣ የሚያስለቅስ፣...) ሊያደርግ ይችላል። የምንሰራው ሰው ላይ በመሆኑ ከእኔ ውጪ ያሉ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሰራተኞች የሩጫውን ተሳታፊ በሙሉ ለማስደሰት ከፍተኛ ጥረት እናደርጋለን። ከስራ ባልደረቦቼ ጋር ኃላፊነትን በእኩል በመጋራት ጫናውን ለማቅለልም እንሞክራለን። ከሩጫው አስቀድሞ ያለውን ውጥረት በሩጫው ዕለት የህዝቡን ደስታ ስንመለከት ወደ ሃሴት ተቀይሮ ስለሚቀጥለው ሩጫ ማሰብም እንጀምራለን። ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ እንደሃገር ትልቁ ሩጫ በመሆኑ በዚህ ተቋም ውስጥ ህዝብን ማገልገል ኩራት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በእርግጥም ስራው ትከሻ የሚጠይቅ ነው፤ ታዲያ አንቺ ይህንን ስፖርታዊ ተቋም የመምራት ችሎታ እንዴት ልታዳብሪ ቻልሽ?**

**ወይዘሪት ዳግማዊት፡-** አሁን ያለሁበት የደረስኩት በሂደት ነው፤ ከእንግዳ ተቀባይነት አንስቶ ሌሎች ስራዎችን በመስራት ለዓመታት በዚህ ተቋም ልምዴን ማዳበር ችያለሁ። እያንዳንዱ እርምጃ አዲስ ነገር ይጨምራል፤ የማይታለፉ የሚመስሉ ሁኔታዎች ጭምር አስተምረውን የሚያልፉት ነገር አለ። ሁሌም ራስን ለትምህርት ማዘጋጀትም አስፈላጊ ነው፤ ስራው የብዙዎች እንደመሆኑ የሌሎች ሰዎችን አስተያየትና ምክርን መውሰድም ይለውጣል። ከእኔ በፊት ከነበሩት የታላቁ ሩጫ መሪዎች እንዲሁም በአውሮፓ ሃገራት ካሉ የውድድር አዘጋጅ ድርጅቶችም በርካታ ዕውቀት አግኝቻለሁ። በእርግጥ ማንነትም የራሱ ሚና አለው፤ ባህሪዬ ተፎካካሪ የሚባል ነው፤ ከልጅነቴ አንስቶ አሸናፊ ለመሆን፣ አዲስ ነገር ለመፍጠር እና ችግሮችን በቶሎ ለማለፍ የነበረኝ ነገር አድጎ አሁንም በስራ ላይ እየተገበርኩት ነው። በስራዬ ቀጥተኛና እውነተኛ ያደረገኝን ባህሪ ያዳበርኩት ደግሞ ከአባቴ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በሴሳው ዓለምም የሩጫ ውድድሮችን የሚያዘጋጁ በርካታ ተቋማት አሉ፤ ካለሽ ልምድ በሴቶች የሚመራ ውድድር ይኖር ይሆን?**

**ወይዘሪት ዳግማዊት፡-** ከዚህ ቀደም የነበረችው የኒውዮርክ ማራቶን ዳይሬክተር ሴት እንደነበረች አውቃለሁ። የዓለም ጎዳና ላይ ውድድሮች ማህበር (AIMS) ጨምሮ በርካታ የጎዳና የውድድር የሚያዘጋጁ ድርጅቶች ውስጥ ያሉት ሴቶችን የሚመለከት ካልሆነ በቀር በመሪነት ደረጃ የሉም።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ትልቅ ስኬት ነው፤ ለበርካቶችም መነሳሳትን ይፈጥራል።**

**ወይዘሪት ዳግማዊት፡-** ልክ ነው፤ ነገር ግን ዋናው ነገር ቦታውን መያዝ ብቻ ሳይሆን እንደሃገር የሚያኮራና ሁሉንም የሚያስደስት ስራ ማከናወን ነው። በዚህ ውስጥ የሚመለከቱን ይኖራሉ ስለዚህም እኔ ብቻ ሳልሆን እንደተቋም ካለንበት ሽርተት ማለት የለብንም ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ስራ ላይ ባሳለፍሻቸው ዓመታት ሴቶችን በሚመለከት ምን ታዝበሻል?**

**ወይዘሪት ዳግማዊት፡-** ከሴቶች ጋር በተያያዘ የተለመደው ነገር እኩልነት የሚለው ነው፤ የመማር፣ የመስራት፣...። ነገር ግን አሁንም ጎታች የሆኑና ሊቀየሩ የሚገባቸው አስተሳሰቦች አሉ። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው የሴቶች ቀንን (ማርች 8) አስመልክቶ የሚደረገው ሩጫ ሲሆን፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ሴቶችን ያሳትፋል። ስፖርት ውስጥ ነጻነት አለ፤ ሩጫው ላይ በብዙዎች ዘንድ የሚታየውም ይኸው ነው፣ በብዙ ምክንያቶች ያጧቸውን ደስታ ያጣጥማሉ። ከብዙዎች ጋር የመገናኘት እድልና በህይወታቸው ውስጥ ካለው ችግር አረፍ የሚሉበት የምንጊዜም ትውስታ ሊሆንም ይችላል።

ምናልባት የሴቶች ችግር በዚህ ላይቀረፍ ይችል ይሆናል። ነገር ግን በሩጫው ላይ የሚተላለፈው መልዕክት፣ ተምሳሌት ሴቶችን መመልከት፣... የማነቃቃት ኃይል አለው። የሴቶች ሩጫ ከተጀመረ ዘንድሮ 21ኛ ዓመቱ ነው፤ ይህ እድሜ በአብዛኞቻችን ህይወት ትምህርት ጨርሰን ወደ ስራ የምንገባበት ነው። ከትምህርት ቤት ባለፈ በርካታ ትምህርት የምናገኝበትና በህይወታችንም ለውጥ የምናመጣበት ወቅት ነው። በመሆኑም እርስ በእርስ በመተጋገዝ ወደ አዲስ ነገርና የተሻለ ነገር ማደግ እንዳለብን አስባለሁ።

በስፖርት ታሪክ የሴቶች ተሳትፎ 50 ዓመት ቢሆነው ነው፤ ይህም ብዙ ተከልክለን እንደቆየን የሚያሳይ በመሆኑ አነሳሽ ምክንያት ይሆናል። ለውጦች ቢኖሩም አሁንም ግን ጠንክረን መስራት እንደሚገባን ያሳየናል። በተለይ በአትሌቲክስ ስፖርት በሚካሄዱ ውድድሮች ሴቶች ውጤታማ ቢሆኑም አሁንም ግን በቁጥር ረገድ ከፍተኛ ልዩነት አለ።

በሌላ በኩል በስፖርቱ አመራርነትም ተጨማሪ እድል ለሴቶች ሊሰጥ ይገባል። ዕድል ሲያገኙ ደግሞ መቻላቸውን ከመጠራጠር ይልቅ ድጋፍ ቢሆኑ፣ ባይሳካላቸውም ደግሞ እንደማንኛውም ሰው የመመልከት እንጂ ሴት ስለሆነች በሚል አለመመዘን ተገቢ ነው። ይህ ማለት ግን ዕድሉን የሚያገኙ ሴቶችም ራሳቸውን ማብቃትና በጥንካሬ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል። ለምሳሌ እኔ የምሰራው ታላቁ ሩጫን ለማኩራት ነው፤ ይህ ሲሆን ኢትዮጵያን ማኩራት እንደሆነ አውቃለሁ። እኔ ካልቻልኩ ታላቁ ሩጫ እንዲሁም ኢትዮጵያ አትችልም እደሚያሰኝ እረዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ቆይታሽ የማትረሻቸው አጋጣሚዎች ይኖሩ ይሆን?**

**ወይዘሪት ዳግማዊት፡-** ከአስደሳቹ ስነሳ እ.አ.አ በ2015 ጀግናው አትሌትና የዚህ ውድድር መስራች የሆነው ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ የመጨረሻውን ተሳትፎ ባደረገበት ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ቀዳሚው ነው። በወቅቱ ስሜታዊ ያደርግ የነበረው የአትሌቱ ስንብት መቼም የሚረሳ አይደለም። የፈተነኝ ደግሞ በ2014 ዓ.ም የሰሜኑን ጦርነት ተከትሎ ውድድሩን ለማዘጋጀት አስጨናቂ ሁኔታዎችን ማለፍ ነበረብን። በወቅቱ አዕምሯዊም አካላዊም ፈተናዎችን እስተናግጃለሁ። በእርግጥ ከ40ሺ በላይ ሰዎችን አሳትፈን ሩጫውን አካሂደናል፤ ነገር ግን የሩጫው መዳረሻ ሊረሳ የማይችል ከባድ ሁኔታን አልፈናል። ‹የማይገልህ ነገር ያጠነክርሃል› እንደሚባለው ሆኖ ከባልደረቦቼ ጋር ሆነን የነበረውን ሁኔታ ልናልፈው ችለናል።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻም የምታስተላልፊው መልዕክት ካለ?**

**ወይዘሪት ዳግማዊት፡-** በአንድ ጫካ እሳት ይነሳና አንዲት ትንሽ ወፍ በትንሹ መንቁሯ ውሃ በማመላለስ ለማጥፋት ጥረት ስታደርግ የተመለከቷት ምን አቅም አላት ብለው አሾፉባት። በዚህ ጊዜ ዋናው ነገር የአቅምን ማድረግ እንጂ መጠኑ አይደለም ስትል መለሰችላቸው። እኛም ባለንበት የትኛውም ቦታ የአቅማችንን ያህል አስተዋጽኦ ማድረግ አለብን እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**ወይዘሪት ዳግማዊት፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ልዩ ዕትም

# ‹‹የእግርኳስ ዳኝነት የሙያ እና የአቅም ጉዳይ ነው››

- ሊዲያ ታፈሰ ዓለም አቀፍ የእግር ኳስ ዳኛ

ሰሚራ በርሀ



በሀገራችን እግር ኳስ ስፖርት ውስጥ ስማቸው በጉልህ ከሚነሱ ሴቶች ውስጥ ናት ። እሱም ደግሞ በዳኝነት የሙያ ዘርፍ በብዛት የወንዶችን የእግር ኳስ ጨዋታ የዳኘች ሴት ዳኛ በመሆኗም በቀዳሚነት ትነሳለች ። ለብዙ ሴቶችም ኩራትና ተምሳሌት መሆን የቻለችውን ዓለምአቀፍ የእግርኳስ ዳኛ ሊዲያ ታፈሰ የዛሬው የአዲስ ዘመን ልዩ እትም እንግዳችን አድርገናታል ።

ተወልዳ ያደገችው በጅማ ከተማ ነው ። ለቤተሰቦቿም የመጨረሻ ልጅ ናት። አብዛኛውን የልጅነት ጊዜዋን በመንፈሳዊው ውስጥ በማገልገል እንዳሳለፈችው ትናገራለች ። የስፖርት እና የእርሷ ግንኙነትም የሚጀምረው ከትምህርት ቤት ነው። በተማሪነት ጊዜዋ የቅርጫት ኳስ ትጫወት ነበር። በስፖርት ውስጥ በንቃት መሳተፍ የጀመረችው ከልጅነቷ ቢሆንም በዚህ ሥራዋም ሆነ በምታደርገው እንቅስቃሴ የተቃወማት የቤተሰብ አካል አልነበረም ። በትምህርት ቤት ውስጥ ሳለች የቅርጫት ኳስን ጅማ ከተማን ወክላ ትጫወት ነበር። ታዲያ በአንድ ወቅት ወደ ጅማ የመጣው ኢንስትራክተር ሽፈራው፣ ለአራት ሴቶች የእግር ኳስ ዳኝነት ሥልጠናን ለመስጠት እድልን ፈጠረ። ታዲያ ሊዲያም ከአራት ሴቶች ውስጥ አንዷ ሆና ሥልጠናውን ከሌሎች ወንዶች ጋር በጋራ ለመውሰድ ቻሉ ። ይህ አጋጣሚም ለሊዲያ የዳኝነት ሕይወትን ‹‹ሀ›› ብላ እንድትጀምር አድርጓታል። ሥልጠናውን ከወሰደች በኋላም ከ17 ዓመት በታች ያለን ጨዋታ ለመጀመሪያ ጊዜ የመዳኘት እድሉን አግኝታለች። ትምህርቷን ያጠናቀቀችው በፋርማሲ ቢሆንም ልቧ ግን በአብዛኛው ወደ ዳኝነቱ አድልቶ በትምህርትቤት በአጋጣሚ የወሰደችው ሥልጠና ከ15 ዓመት በላይ ያገለገለችበት ሙያ ለመሆን ችሏል። ሊዲያ የዳኝነት ሥልጠናዋን ካጠናቀቀች በኋላ ለሙያው ያላትን መረዳት እያሳደገች የተለያዩ ጨዋታዎች በረዳት ዳኝነት ከዚያም ደግሞ በመሀል ዳኝነት ማጫወቷን ቀጠለች።

የእግር ኳስ ዳኝነት እንኳን ለሴት ለወንዶችም ቢሆን ከባድ እንደሆነ የምትናገረው ሊዲያ ለዚህ እንደምክንያትነት የሚነሳው ደግሞ በሜዳው ውስጥ ያሉ ተጫዋቾችም ሆኑ ደጋፊዎች ዓላማቸው ማሸነፍ ነውና አንዳንዴም ከእውቀት ማነስ አንዳንዴም ደግሞ ለማሸነፍ ከመፈለግ ሜዳ ውስጥ ግጭት አለመግባባት ዳኞች ላይ ጉዳት የማድረስ ነገር ይኖራል ። ‹‹በሜዳ ውስጥ እንዲህ ነው የምለው በጣም የተጋነነ ጉዳት አልደረሰብኝም ›› ትላለች ።

ሊዲያ የዳኝነት ሥልጠናዋን ካጠናቀቀች በኋላ የተለያዩ ጨዋታዎችን የዳኘች ሲሆን፣ ዓለምአቀፍ ሥራዋን የጀመረችው በ (ኦል አፍሪካን ጌም) ከዚያም የሀገር ውስጥ ሥልጠናዎችን እና ፊፋ የሚያዘጋጃቸውን ሥልጠናዎች በመውሰድ ዓለምአቀፍ ጨዋታዎችን በተደጋጋሚ የመዳኘት እድሉንም አገኘች።

ሁለት ጨዋታዎችን በኦል አፍሪካን ጌም፣ አምስት የአፍሪካ ዋንጫዎችን ፣ በአውሮፓ ፊፋ በሚያዘጋጃቸው አንዳንድ ውድድሮች ላይ ፣ በዓለም ዋንጫ ላይ አንድ ከ20 ዓመት በታች እና ሁለት ከ17 ዓመት በታች እንዲሁም የዓለም ዋንጫ ላይ በዳኝነት ተሳትፋለች። በአፍሪካ ደረጃ የወንዶችን የቻን ውድድር ያጫወተች የመጀመሪያዋ ሴት ዳኛ ናት የቻምፒዮንስ ሊግ ውድድር የመጨረሻ ጨዋታውን ጭምር ዳኝታለች።

‹‹ወንድም ሆነ ሴት ዳኝነት የሚፈልገው ሜዳ ውስጥ የጥንካሬ እና የአቅም ጉዳይ ነው ። ›› የምትለው ሊዲያ በጾታ ልዩነት ሳይሆን ሙያው የሚጠይቀውን እውቀት ፣ ክህሎት እና ጥንካሬ መያዝ እና መወዳደር የምታምንበት ሃሳብ ነው ። በሌላው ዓለም ልክ እንደ ኢትዮጵያ ብዙም ፈተና ላይኖረው ይችላል። በሀገራችን ዳኝነት ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎች በዓለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን እና ለመሳተፍ እድሉን ሲያገኙ የሚታይባቸውን የቋንቋ ችግር ፣ ከሰዎች ጋር የመግባባት ክህሎታቸውን መጨመር እና በአሁኑ ሰዓት በዘርፉ ላይ እየተዋወቁ ያሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መላመድና ቴክኖሊጂዎችን ለመጠቀም ራሳቸውን ማብቃት ይጠበቅባቸዋል በማለት ትገልጻለች። ከዚህም ባሻገር አንድ ዳኛ ራሱን በአካል ብቃት ማዘጋጀት እና ብቁ መሆን እንዳለበት በተደጋጋሚ የምታነሳው ጉዳይ ነው ።

ሊዲያ ሥራዋን በጀመረችበት ወቅት በእግርኳስ ዳኝነት ውስጥ ብቸኛ ሴት እስከመባል ድረስ ጎልታ የምትታይ ባለሙያ ነበረች። በሥራ ቆይታዋም ለሌሎች ሴት ዳኞች መምጣት ምሳሌ ሆና በተለያየ ጊዜ ልምዷን ታካፍላለች። ነገር ግን አሁን ሊዲያ ይህንን የዳኝነት ሥራዋን በቃኝ ያለችበት ሰዓት ላይ ትገኛለች ። ታዲያ በሥራ በቆየችባቸው ዓመታትም ብዙዎች ራስሽን ሳትተኪ ነው የወጣሽው ይሏታል ። እሷ ደግሞ ‹‹ በአሁኑ ሰዓት አራት ዓለምአቀፍ ሴት የመሀል ዳኞች አራት ረዳት ዳኞች ያሉ ሲሆን ሌሎች ሴት ዳኞችም እድሉን እያገኙ እየወጡ ይገኛሉ።›› በማለት ትገልጻለች።

ሊዲያ ያሳለፈችው እና በሙያው ላይ የነበራት የሥራ ቆይታም እንደ ጥሩ ተሞክሮ ሊሆናቸው እንደሚችል ታስባለች ። ‹‹በሙያው ላይ እያለውም ጀምሮ ከሴት ዳኞች ጋር ልምድ የመለዋወጥ ፣ እነሱን የማስተማር ፣ ጨዋታዎችን የመገምገም እድሉን ስላገኘሁ እነዚህ ስራዎች ይጠቅማቸዋል ብዬ አስባለሁ።›› በማለት ትገልጻለች።

በሀገራችን ካሉ የሙያ ዘርፎች የስፖርት ዘርፍ ሴቶች እንደ እንግዳ የሚታዩበት የሙያ ዘርፍ ይመስላል ምንም እንኳን አሁን ላይ ይህ አመለካከት እየቀነሰ መጥቶ ሴቶች በዳኝነትም ሆነ በተጫዋችነት ሀገራቸውን ወክለው እየተሳተፉ ቢገኝም ቀድሞ የነበረው አመለካከት ቢኖርም። ታዲያ በዳኝነት ሙያ ላይ ያሉ ሴቶች በብዛት የሴቶችን ጨዋታ ብቻ የሚዳኙ ተደርጎ ይወሰዳል ። የወንዶችን ጨዋታ መዳኘት ለሴቶች የሚያስፈራ ነገር ይመስላል ። ‹‹ዳኝነት የሙያ ጉዳይ በመሆኑ ያስፈራል የሚል እምነት የለኝም ዳኝነት በባህሪው ለሴት ለወንድም የሚከብድ ነው ። ነገር ግን ጠንካራ መሆን እና የአዕምሮ ዝግጁነት ፣ ምንም ነገር አያቅተኝም የሚለውን ሃሳብ በውስጥ መያዝን ይጠይቃል።››

ሊዲያ የተለያዩ ጨዋታዎችን ዳኝታለች በሁሉም ጨዋታዎቿ ላይ የምታሳየው ኮስተር ያለ ባህሪም ተጫዋቾችም ሆኑ ደጋፊዎች በሜዳ ውስጥ በምትዳኝበት ጊዜ እንዲያከብሯት አድርጓል ። ከተጫዋቾች ጋርም ባላት መልካም ግንኙነት ከዳኝነት ባለፈ ለምትሰጣቸው ምክርም ‹‹ዳኛ ነች ወይስ አሠልጣኝ ›› ይባልላታል። ከሴቶች እና ከወንዶች ጨዋታ ምርጫ ቢሰጣትም‹‹ የወንዶችን ጨዋታ በምዳኝበት ወቅት ጠንካራ ሆናለሁ ፣ ኮስታራ ሆናለሁ እና ለኔ የወንዶችን ጨዋታ መዳኘት ይቀለኛል።›› በማለት ትገልጻዋለች።

ዳኛ መሆን ማለት በሜዳው መሀል ላይ ሆነው ለአሸናፊነት የሚፋለሙት የሁለት እግርኳ ቡድኖችን በእኩል አይን ሕጉን ተከትሎ መዳኘት ነው ። ሁለቱም ቡድኖች መጨረሻ ላይ አሸናፊ መሆን ህልማቸው ነው። ዳኛ ደግሞ ጨዋታውን ሕጉን በተከተለ መልኩ ማስኬድ ፤ ታዲያ በዚ መሀል ሕግ ቢኖር ፣ ሃላፊነት ቢኖር ሰው ናቸው እና ልባቸው ለማን ያደላ ይሆን ? የትኛው ጨዋታ ይማርካቸው ይሆን ? ፤ ይህ ቡድን ባሸነፈ የሚሉት የላቸውም ይሆን ? የሚለው ጥያቄ በተለይ በሜዳው ውስጥ ታድመው ባሉ ደጋፊዎች ላይ የሚመላለስ ጥያቄ ነው። ‹‹ዳኛ ብሆንም ጨዋታውን መመልከቴ ስለማይቀር የምደግፈው ቡድን ይኖራል ። ነገር ግን ይህን ቡድን ነው የምደግፈው ብሎ በይፋ መናገር በተለይ በእኛ ሀገር ነገሮች በተለየ አቅጣጫ የሚታዩ በመሆናቸው ከባድ ነው ። ›› የምትለው ሊዲያ ‹‹እንደ እግር ኳስ ተመልካች ግን የምደግፈው ቢኖርም በዳኝነት ሕይወቴ ግን የሚቆጨኝንና ህሊናዬን የሚጸጽተኝን ነገር አላደረኩም።›› ባይ ነች። በዚህም የሙያ ጓደኞቿም ሆኑ ተጫዋቾች የሚመሰክሩላት ነው ።

ሆኖም ሊዲያ ከኢትዮጵያ ውጪ የማንቼስተር ደጋፊ ስትሆን ልክ እንደሌሎች ደጋፊዎች ሲያሸንፍ በደስታ ሲሸነፍ ደግሞ በጣም በንዴት ስሜት የምትደግፈው ቡድን ነው ። በትርፍ ሰዓቷን ልምዷን ከማካፈል ባለፈ የተለያዩ ጨዋታዎችን በማየት ታሳልፋለች።

‹‹በዳኝነት ሙያ ቆይታዬ ይህ ቀረኝ የምለው የለም ብዙ ሥራዎች ብዙ ስኬቶችን አግኝቻለሁ›› የምትለው ሊዲያ በቆይታዋ በአፍሪካ የወንዶችን የቻን ውድድር የመራች ፣የዳኘች ፣ ያጫወተች የመጀመሪያዋ ሴት ዳኛ ናት። ከሷ በመቀጠልም ሌሎች ሴት ዳኞች በአፍሪካ ይህንን እድል አግኝተዋል ሊዲያም ለዚህ በር ከፋች በመሆኗ ደስተኛ እና ትልቅ እድል እንደሆነ ትናገራለች። በእግርኳሱ ዓለም በነበራት ቆይታም የተለያዩ እውቅናዎች እና ሽልማቶችን ያገኘች ሲሆን ራሷን ከዳኝነት ባገለለችበት ወቅትም ምስጋና እውቅና ተሰጥቷታል ።

ሊዲያ ታፈሰ ዳኝነት በሜዳ ውስጥ እንኳን ጉዳት ደርሶባቸው ተመልሰው ግን ጨዋታ ለመዳኘት የሚመጡበትና ለመተው ቀላል ያልሆነ ሙያ መሆኑን ትገልጻለች። ሊዲያ ከ15 ዓመት በላይ ቆይታ በኋላ ይህንን ሥራዋን ጨርሳ ወጥታለች። ዳኝነትን ከመተዋም በፊት እና አሁንም ከሴትም ወንዶች ዳኞች ጋር በመሆን ጨዋታዎችን ትገመግማለች ታስተምራለች። ዳኞችም የተሰጣቸውን ሥልጠና ተቀብለው የመተግበር ራሳቸውን የማብቃት እና የሚያገኙትን እድል በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባቸው ትገልጻለች።

ሊዲያ ከዚህ ሁሉ ዓመት የሥራ ቆይታ በኋላ ሥራዋን የመተው ሃሳብ በውስጧ የነበረ ሲሆን ነገር ግን ፊፋ በአዘጋጀው ሥልጠና ላይ እንድትጋበዝ ጥሪ ሲቀርብላት ሥልጠናውን የወሰድኩ እንደሆን በሥራው ላይ ልቀጥልበት ይገባል በማለት የተሰጣትን እድል አመስግና ሥራዋን በዚሁ ልታቆም ችላለች። ሊዲያ ከሥራዋ ባሻገር ትዳር የመሰረተች ሲሆን የአንድ ሴት ልጅ እናትም ነች ። በሀገራችን የተለያየ ዘርፍ ላይ በርካታ አስተዋጽኦ ያደረጉ ባለሙያዎች ታሪካቸውን የመጻፍ እና ለሌሎች እንዲቀመጥ የማድረግ ልምድ የላቸውም። ሊዲያ በተለያዩ መድረኮች ላይ ልምዷን ያካፈለች ሲሆን ይህንን ታሪኳን እና የሕይወት ልምዷን በአንድ የመሰነድ ሃሳብም አላት።